ኢትዮጵያውያን የወንጌል መልእክተኞች

በዲክ ማክሌላን

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሚስዮናውያን
በኦሞ ወንዝ ሸለቆዎች ውስጥ
ወንጌልን ያደረሱ ሰዎች

‹‹በኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ ላለች . . .
እናንተ ፈጣኖች መልእክተኞች ሆይ፣ ወደ ረጅምና ወደ ለስላሳ
ሕዝብ፣ ከመጀመሪያው አስደንጋጭ ወደ ሆነ ወገን፣ ወደሚሰፍርና
ወደሚረግጥ፣ ወንዞችም ምድራቸውን ወደሚከፍሉት ሕዝብ ሂዱ።››
ኢሳይያስ 18፡1፣2

BIBLE BASED BOOKS
BIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት
የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ

ኢትዮጵያውያን የወንጌል መልእክተኞች
በዲክ ማክሌላን

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሚስዮናውያን -
በአሞ ወንዝ ሸለቆዎች ውስጥ ወንጌልን ያደረሱ ሰዎች

Copyright© 2010 Richard J McLellan
በመጀመሪያ በፌብሩዋሪ 2010 በዲክ ማክሌላን ታተመ

ትርጉም፡- ተካልኝ ዱጉማ
እርማት፡- ኃይሌ ጀናይ እና
ዳንኤል ተሾመ
ዋና አርታዒ፡- ዘነበ ገብረሐና
የኮምፒዩተር ጽሑፍና የገጽ አቀማመጥ፡- ጥሩወርቅ በቀለ
የአማርኛው ትርጉም አሳታሚ፡- የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ
የፖ. ሣ. ቁ. 127፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ ቁጥር- 011-349-3069/ 011-551-2973
ኢሜይል – simethiopia.publication@gmail.com
(or) simmedia@ethionet.et

ሕጋዊ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ የዚህ ጎትመት የትኛውም ክፍል
ያለ አሳታሚው ፈቃድ በኤሌክትሮኒክስ፣ በመካኒካል፣ በፎቶ ኮፒ፣ በስካኒንግ፣
ወይም በማንኛውም መንገድ ተባዝቶ ለሌላ አካል ማስተላለፍ አይፈቀድም፡፡
የፊት ሽፋን ፎቶ፡-
በኢትዮጵያ ውስጥ በቦረና ያለች
ልዩ የሆነች የወንጌል መልእክተኛ ሴት ናት፡፡
ፎቶ አንሺዎች፡- ዲክ ማክሌላን እና ጆን ማክሌላን ናቸው፡፡

በኤስ ኣይ ኤም ማተሚያ ቤት ኢትዮጵያ ውስጥ ታተመ

ማውጫ

መታሰቢያና ምሥጋና 5

ካርታ 8

መቅድም 9

መግቢያ 12

1. ሊድጇይ አዲስ ግንኙነት 15
2. ዛቡ መጽሐፉን መፈለግ 25
3. ዱባሌ ማዕከላዊ ምሰሶ 31
4. ጅግሬ ትንቢቱ ተፈጸመ 37
5. ባሎቲ እስከ መጨረሻ የሚጸና ጓደኝነት 45
6. ማሄ ከሞት ጋር የተደረገ ቀጠሮ 55
7. ሃሚ በመመልከቻ መስታወት ውስጥ 61
8. ጌናሚ በውኃዎች ውስጥ 67
9. ጌንቦ ዝናብ በዝምታ ሲቆም 74
10. ገብሬ ከዓርበኛ ተዋጊነት ወደ ቅዱስነት 82
11. ጴጥሮስ በሸክላ ውስጥ ያለ መዝገብ 106
12. ጌርሾ የበና ጎሳ ዳግም የተወለደው ሰው 113
13. ዳኖ ከዲያብሎስ ጨለማ 121
14. ናና ጸላዩ እስረኛ 129
15. ሻንካ ብርሃኑ ይብራ 134
16. ተስፋዬ በሩን መክፈት 139
17. ለማ የነገሩ ርዝመትና እጥረት 145
18. ሳዎል በጨለማ ውስጥ ያለ ብርሃን 153
19. ዓለሙ ለኢየሱስ መዘመር 164
20. ኳየሩ አባልነት 167
21. ዴልጋ የጠንቋዩ ልጅ 169
22. ፈንቶ የጌታ እስረኛ 174

23.	አልዳቦ	በሶሪ ውስጥ ያለ ምሥጢር	183
24.	ካሮታ	ግራ እጅ	189
25.	ዋንዳሮ	የወጎኒ ቤቱን ደጃፍ ከፈተ	195
26.	ኢያሱ	ዛሬ እነርሱ የት ናቸው?	200
27.	ጀሬናይ	የተበላሸ ሸክላ-አዲስ ዕቃ	209
28.	ባሳ	በጌታ መዳሰስ	216
29.	ዳንኤል	ሐቀኝነትና ፍትሕ	225
30.	የቀብር ሥነ ሥርዓት	የመሪው ስንብት	231
31.	ቦዲ	የቦዲዎች ጭካኔ	236
32.	በላታ	ሁሉንም ነገር ማጣት	240
33.	ጎፖሎ	ሕይወትን ለማትረፍ ሩጫ	243
34.	እንድርያስ	በሁሉም ውስጥ ኢየሱስ	245
35.	ሀብታሙ	የወንድሜ ጠባቂ	249
36.	ኮንታ ዛሬ ላይ	እግዚአብሔር እንዲሆን ያደረገው ነገር	254
37.	ቦዲ ዛሬ ላይ	ያልተጠናቀቀ ሥራ	256
38.	ተካ	ትክክለኛ ቃል	259
		የክርስቶስ መልእክተኞች	266

የዚህ መጽሐፍ መታሰቢያነቱ

እጅግ ብዙ መሥዋዕትነት ለከፈሉ እና የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በታማኝነት በማካፈል ላገለገሉ ነርሶች፣ መምህራን፣ ተርጓሚዎች፣ ጸሐፊዎች እና ሁሉንም ዓይነት እገዛ ላደረጉ በጣም ብዙ ሠራዊት ለሆኑት ያላገቡ ሴቶች ይሁን፡፡ ሴልማን፣ ፊዮናን፣ ኔልዳን፣ ቤቲን፣ ዴይሲን፣ ፍሬዳን፣ ቤቨርሌይን፣ ሜርሌን፣ ጁኔን፣ ሩትን፣ ጆይ፣ ዶሪስን፣ ፐአርልን፣ ኬይን ስማቸውን ለመጥቀስ እጅጅግ የሚበዙትን እናስታውሳቸዋለን፡፡

እንዲሁም

‹‹እግዚአብሔር ቃሉን ሰጠ፣ የሚያወሩት ብዙ ሠራዊት ናቸው።››

መዝ. 68፡11

ኢትዮጵያ በሶሻሊስት አብዮት አገዛዝ ሥር በነበረችበት ወቅት፣ ከ1967-1983 ዓ.ም፣ ግፍ ለተፈጸመባቸው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት ለታሰሩት፣ ለተገረፉት ደግሞም ለአንዳንድ ‹‹በቀይ ሽብር›› ለተገደሉት ክርስቲያን ኢትዮጵያዊያን እኅቶች፣ ለእነ ሩት፣ ጣቢታ፣ ራሔል፣ ሙሉነሽ እና ለሌሎች በጣም ብዙ ወጣቶች ለከብራቸው መታሰቢያ ይሁን፡፡

ምስጋና

ጓደኛዬና አጋር ሚስዮናዊ ለሆነው፣ በተጨማሪም በምዕራፍ 11 እና 12 ውስጥ ያለውን ታሪክ ከእኔ ጋር ለተጋራው፣ የዚህን መጽሐፍ መቅድም ለጻፈው ለዶ/ር ማልከልም ሀንተር ታላቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በዓለማችን ዙሪያ ላሉት አርብቶ አደር ሕዝቦች ያለው ራእይ እና ሸክም ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር የፍቅር ስጦታ የሆነው፣ ኢየሱስ ክርስቶስን መስማት ይችሉ ዘንድ ብዙዎቻችንን እንድንጸልይ እና እንድንሄድ አነሣሥቶናል፡፡

በተጨማሪም

የዚህን ጽሑፍ ረቂቅ ላነበቡ፣ አርትዖታዊ ሥራ ለሠሩ እና ለአስተካከሉ ለቪዳ፣

ለማርጋሬት እና ለጆን፤ ፎቶግራፎቹን ላቀናጀልኝ ለጆን፣ የኢትዮጵያውያንን የፖስታ መልእክት ለሣለችልኝ ለኤሚ እና ‹‹ኢትዮጵያውያን የወንጌል ጀግኖች›› የተሰኘውንም መጽሐፍ ካነበቡ በኋላ ሌሎች ብዙ ታሪኮችን እንድጽፍ ላበረታቱኝ፣ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ በዚህ ዓመት በነበረኝ በአስቸጋሪ ጊዜ|ያት ስታገል በጸሎት የረዱኝን ሰዎች ሰዎች ሁሉ አመሰግናለሁ።።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች

በግልጽ ካልተጠቀሱ በስተቀር፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በ1954 ዓ.ም ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የተወሰዱ ሲሆን፣ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ከኪንግ ጀምስ ቨርዥን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጋር ተመሳሳይ ነው።።



ካርታ ፣

ኢትዮጵያ እና አጎራባች አገሮች



ካርታ 2

የአሞ ወንዝ ሸለቆ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ

መቅድም

የዲክ ማክሌላን ሁለተኛ መጽሐፍ ጠቃሚ እና በዲክ እንዲሁም በቪዳ ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር የሠራውን ሥራ የሚያወሳው ‹‹ሊትዮጵያውያን የወንጌል ጀግኖች›› የሚለው መጽሐፉ ትክክለኛ ተከታይ ነው፡፡ በዚህኛው መጽሐፍ ውስጥ ጦረኞች፣ ሰዎችን በመግደል እንዴት ከብቶችን ይዘርፉ እንደ ነበሩና የሰላም ወንጌል መልእክተኞች ደግሞ ወንጌልን እንዴት ይሰብኩ እንደ ነበሩ ያሳያል፡፡ ዲክ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት በጎሳዎች አማካይነት በኡሞ ሸለቆዎች ውስጥ፣ ያደርግ በነበረው ጥረት ውስጥ ከእርሱ በኋላ ለ15 ዓመታት ያህል ጉዳዩን የመከታተል ዕድል ገጥሞኛል፡፡ በአንድ ጊዜ የተለያዩ የብሔረሰብ ባላቸው ቡድኖች መካከል በስፋት መሥራት መቻል የተለመደ የወንጌል መልእክተኞች አሠራር አይደለም፡፡ ነገር ግን፣ የዚህ ስኬት ምሥጢር፣ በብሔራቸው ውስጥ በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን አማካይነት በብዛት አርብቶ-አደር ለሆኑ ቡድኖች ወንጌልን ይዘው እንዲሄዱ የተላኩት አገር በቀል ወንጌላውያን ነበሩ፡፡ ይህ መጽሐፍ ከዚህ በፊት እንደ ተጻፈው መጽሐፍ ሁሉ ወደ ተለያዩ ጎሳዎች ወንጌል ይዘው በመሄድ በዚያ የኖሩ፣ ቋንቋቸውን እና ባህላቸውን የተማሩ እንዲሁም እግዚአብሔር የሚፈልገውን ዓይነት ለውጥ ለማምጣት መሣሪያ የሆኑ የእምነት አርበኞች/ጀግኖች ታሪክ ነው፡፡ በጣም ጥቂት የወንጌል መልእክተኞች በወንጌል ማዳረስ መስክ ላይ ተሰማርተዋል፣ ነገር ግን ዲክ የጀመረውን ዓይነት ሕይወት ለመኖር ፈቃደኛ የሆኑ የወንጌል መልእክተኞች ብዙ አይደሉም፡፡

በዓመታዊ ጉባኤያቸው ላይ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት የሚመጡ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አማኞችን ተናግሮ ለማሳመን እግዚአብሔር ተጠቅሞብናል፡፡ ወንጌል ወዳልደረሳቸው ጎሳዎች ወንጌልን ለመስበክ ከእኛ ጋር ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችን ስንጠይቅ፣ በጣም ብዙ ሰዎች ምላሽ ይሰጡ ነበር፡፡ ሕዝባቸውን በደንብ ጠንቅቀው የሚያውቁት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስጦታው ያላቸውን እና ሊታመኑ የሚችሉ ሰዎችን ይመርጡና ከቤተሰባቸው ጋር ይልኳቸዋል- በዚህ ስፍራ የአጭር ጊዜ የሚስዮን ጉብኝት የሚባል ነገር የለም፡፡ የአገሬውን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን አክብሮት ያገኘ የውጭ ሀገር ሚስዮናዊ፣ ‹‹ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰምተው ወደማያውቁት ሰዎች አብረን እንሂድ፣›› ከሚል ንግግር በላይ የሚያነሣሣቸው ነገር የለም፡፡

እንዲሁም እንደ ዲክ በአገሬው መሪዎች ዘንድ ከበሬታን ያገኘ እና እግዚአብሔር የተጠቀመበት አንድም ሰው የለም፡፡ ለሌሎች ሰዎች እንዲሄዱ የሚገፋፉ በጣም ታላላቅ የሆኑ ሰባኪዎች አሉ፣ ነገር ግን ወንጌላዊ ዲክ እንዳደረገው፣ እነዚህ ሰዎች እራሳቸው አይሄዱም፣ አስቸጋሪ ነገር አይገጥማቸውም፣ እንዲሁም ‹በረጅም ጉዞ› አይሠቃዩም፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ዲክ ስለ ደረሱበት ፈተናዎች እና ችግሮች በአጽንዖት አልጻፈም፣ ነገር ግን ጽሑፎቹን አስተውላችሁ ካነበባችሁ፣ እርሱ እና ቪዳ ለወንጌል ሲሉ የተቀበሉትን መከራ መመልከት ትችላላችሁ፡፡

በሁለቱም መጻሕፍት ውስጥ በሐዋርያዊ አገልግሎት ስማቸው የተጠቀሰው አስገራሚ ወንጌላዊ፣ አቶ ማሄ ናቸው፡፡ ዲክ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረውን የረጅም ጊዜ አገልግሎቱን ከተወ በኋላ፣ የማሄ ሹፌር በመሆን ለብዙ ጊዜ ከእርሱ ጋር የማውራት ዕድል አግኝቻለሁ፡፡ ማሄ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ታሪኮቻቸውን በምታነብቧቸው በአብዛኛዎቹ የብሔር ቡድኖች ውስጥ እንቅስቃሴን ለመጀመር እግዚአብሔር የተጠቀመበት ሰው ነው፡፡ በእያንዳንዱ ጎሳ ውስጥ በጣም ጥቂት ወንዶችን እና ሴቶችን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እና በጽኑ ጸሎት አማካይነት ክርስቶስን ወደ ማወቅ ይመራቸዋል፡፡ እነዚህ አዳዲስ አማኞችን ያስተምሩ ዘንድ የተሻለ እውቀት ያላቸው ሰዎች እንዲያስተምራቸው ይጠራል፤ ከዚያም በአቅራቢያቸው ወደሚገኙ ሌሎች ጎሳዎች ከእርሱ ጋር ወንጌል ይዘው እንዲሄዱ ከእነዚያ መካከል ጥቂቶቹን ይቀሰቅሳቸዋል፡፡ ብዙ ጊዜ እነዚህ ጎሳዎች እርስ በርሳቸው ጠላቶች ነበሩ፣ ስለዚህም የጎሳን ድንበር መሻገር አደገኛነቱ እሙን ነበር፡፡ ይህ እንግዲህ እኛ ከሌላ አገር የመጣን ሚስዮናውያን ከዘመናዊ ሕክምና፣ ትምህርት እና ባደገ ቴክኖሎጂ አማካይነት ከአገር በቀል ወንጌላውያን ጋር ያገለገልንበት ስፍራ ነው፡፡

‹‹ብዙ ጊዜ፣ ወንጌልን ሰምተው ወደማያውቁት ወደሚቀጥለው ጎሳ እንድንሄድ እግዚአብሔር ተናግሮኛል›› የሚለው ማሄ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ወዴት አቅጣጫ እየተጓዘ እንደ ሆነ ማሄ የሚረዳ መሆኑን ስንገነዘብ፤ ይህ የተቀባ የእግዚአብሔር መልእክተኛ የሚለውን ነገር መስማት ጀመርን፡፡ ወደ ስፍራውም ስንሄድ ወንጌልን ለመቀበል እና ለማመን የተዘጋጁ ሰዎችን እናገኛለን፡፡

‹‹በቦረና ጎሳዎች መካከል የተናቀው የዋቶ ዋንዶ ጎሳ የሆነ አንድ ሰው ማሄ ከዕለታት አንድ ቀን በአንዲት ትንሽ የገበያ ስፍራ ሲሰብክ ሰምቶት ‘መልእክቱን

አድምጫለሁ እንዲሁም መልካም መስሎ ታይቶኛል፡፡ ኢየሱስን እንደ አዳኜ አድርጌ እኔም መቀበል እችላለሁን?’ ሲል ጠየቀው፡፡ ማሄ ሰውዬውን በማግኘቱ በደስታ ተዋጠ፣ እንዲሁም በፍጥነት ወደ ሰውዬው መኖሪያ መንደር ተከትሎት ሄደ፡፡ የዚህ ሰው መኖሪያ ቤት በቀጭጥቋጦ ውስጥ የአምስት ሰዓት መንገድ ያህል ሩቅ ነበር፡፡ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ማሄ እግዚአብሔር ሲሠራ ተመለከተው፣ እንዲሁም አብዛኛዎቹ የማኅበረሰቡ አባላት ወደ አንድ ሺህ የሚጠጉ ሰዎች ኢየሱስን ለመከተል ዝግጁ መሆናቸውን ገለጹ፡፡ እንዲህ ያለው ነገር በአብዛኛዎቹ ዝቅተኛ እና የተናቁ ሰዎች ዘንድ እንደ ሌሎች ሰዎች ሁሉ እነርሱም በእግዚአብሔር ዓይን እንደሚወደዱ እና ተቀባይነት እንዳላቸው ሲረዱ ብዙ ጊዜ የሚሆን ነገር ነው፡፡

‹‹ይህ አቶ ማሄ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሰፊ በሆነው የቦረና ሕዝብ ዘንድ ለማስፋፋት ካደረጋቸው ጥረቶች መካከል በቅርብ ጊዜ የተከናወነ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ወደ ሦስት ሚሊዮን አካባቢ ሲሆኑ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢ የተሰበጣጠሩ እና በሰሜን ኬንያ ውስጥ የሚገኙ ሕዝቦች ናቸው፡፡ ማሄ የዘጠና ዓመት ሰው በመሆኑ ምክንያት በአሁን ሰዓት የመሪነት ስፍራውን በመያዝ ብዙ እንቅስቃሴ አያደርግም፣ ነገር ግን ለተከላቸው አብያተ ክርስቲያናት ለረጅም ጊዜ በጽናት ይጸልያል፡፡ በምዕራብ ቦረና አካባቢ ከመንደር ራቅ ብለው በሚገኙት የግጦሽ መሬቶች ውስጥ የመለመላቸው አገር በቀል ወንጌላውያን ወደሚያገለግሉበት ስፍራ አደጋን ሁሉ እየተጋፈጠ ይሄዳል፡፡ እንዲህ ያለ ጉዞ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ካደረገ በኋላ በሦስተኛው ቀን በመንገድ ላይ ራሱን ስቶ የተገኘው በዚህ ዓመት ውስጥ ነው፡፡ ማሄ በዚህ ምክንያት ለሞት ተቃርቦ ነበር፣ ነገር ግን ለብዙ ሳምንታት በሆስፒታል ሕክምና ሲከታተል ከቆየ በኋላ ወደ ቤቱ ሊመለስ ችሏል፡፡

‹‹በቅርብ ጊዜም ማክሌላን ወይም ዶ/ር ሀንተር መጥተው ከእነርሱ ጋር ወንጌላውያንን ለመጐብኘት ዝግጁ መሆኑን በመጥቀስ መልእክት ልኮባቸዋል፡፡ እኔ እና ዲክ ሁለታችንም እንደገና፣ በአንድ ታላቅ ቅዱስ ሰው፣ እና ምናልባትም በጣም በማከብረው ረጂ-አሠልጣኜ አገልግሎት ማገባደጃ ላይ አብረን የምንሆንበት ጊዜ እንደሚመጣ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ እግዚአብሔር ሁለቱንም ይባርክ!››

ማልከልም ሀንተር

ኦክቶበር 2009

መግቢያ

ወጣ ገባ በበዛበት ትልቅ የተራራ አናት ላይ ስደርስ ለማረፍ የበቅሎዬን ልጓም ያዝ አደረግሁኝ፣ ልጓሙን በጣም ስቤው ኖሮ ከኮርቻው ላይ ለጥቂት ወድቄ ነበር። ዕረፍት ፈልጌያለሁ፣ እንዲሁም ረጅሙን ተራራ ከወጣን በኋላ በመቆማችን በቅሎዋም ደስተኛ ነበረች። በአንድ የጥድ ዛፍ ጥላ ሥር ተቀምጬ እያለሁ በቅሎዋ በመንገዱ ዳር የበቀሉትን ሣሮች መጋጥ ጀመረች። ከዚያም በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ *ኢትዮጵያዊውን መልእክተኛ የመልእክቱን ኤድራሻ* ተመለከትሁኝ። መልእክተኛው በምድሪቱ ውስጥ አሁን ያለው የፖስታ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት፣ ልዩ መልእክተኛ ነበር።

ያየሁት ገና ከሩቁ፣ በዚያኛው ተራራ ላይ ሆኖ ነበር፣ በመካከላችን ጥልቅ ገደል ነበር። በእግሮቹ ከተራራው ወደ ታች እየሮጠ ከመጣበት ስፍራ በዚያ ስፍራ ለሚኖሩ ሰዎች መልእክት እንዳለው በታላቅ ድምፅ እየጮኸ ይናገር ነበር። በዚያች መንደር እንኳ አልቆመም፣ ነገር ግን ጉዞውን ቀጥሏል፤ እየሮጠም መልእክቱን ይናገራል። አንድ ትንሽ ጅረት በምትወርድበት ስፍራ ላይ ሲደርስ ቆም ብሎ ትንሽ ውኃ ለመጎንጨት እና ተራራውን ከመውጣቱ በፊት ፊቱን ለመታጠብ ዐረፍ አለ። እኔ ደግሞ ወደ ታች እየወረድሁ ነበር።

እየቀረበኝ ሲመጣ በጎኑ ሻጥ ያደረጋት የቆዳ ቦርሳ እንዳለች ተመለከትሁኝ፣ ምናልባት በጉዞው ላይ የሚመገበው የተቆላ በቆሎ ወይም ባቄላ ሊሆን ይችላል። ከፊቱ ላይ፣ እንደሚቸኩል ያስታውቅበታል። እየቀረበኝ መጣ፣ እንደ ልጅ ወዲያ እና ወዲህ ካማተረ በኋላ፣ በፍጥነት ሰላምታ ሰጥቶኝ ተራራውን መውጣቱን ቀጠለ። የዚህ መልእክተኛ ጥንካሬ በጣም አስገራሚ ነበር።

መልእክተኛው ሁልጊዜ የሚይዛት አንድ አጭር በትር አለችው። ይህች በትር የሚሄድበትን አቅጣጫ እና በሥራ ላይ እያለ ያለውን ጎላፊነት የምታመለክት ነበረች። ይህች በትር ጫፏ ላይ ለሁለት የተሰነጠቀች ስትሆን፣ በስንጥቅጅም መካከል ብዙ ደብዳቤዎችን ይዛለች። ከቀጣና ጎላፊዎች ለአካባቢ አስተዳዳሪዎች የሚላኩ መልእክቶችን ተሸክማለች። እንዲህ ካለው ልዩ መልእክተኛ ጋር የተገናኘሁት በሌላ አንድ ጊዜ ብቻ ነበር። የምንኖርበት ዘመን በፍጥነት የሚያልፍ ዘመን ነው።

በእኔ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛ ቆሮንቶስ 5፡20 ላይ እኛ ወንጌልን የምናውጅ ‹‹የክርስቶስ መልእክተኞች›› ተብለን ተጠርተናል፡፡ የጠፉ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር የምናስታርቅ ነን፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ታሪኮች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን ለመናገር የእርሱ ልዩ መልእክተኞች አድርጎ የላካቸው ተራ የሆኑ ኢትዮጵያውያንን ታሪክ ታገኛላችሁ፡፡ የተሰጣቸውን መልእክት በማስተላለፍ ሂደት ውስጥ ለአዳኛቸው ያላቸውን መሰጠት በመመልከት ተባረኩበት፣ እንዲሁም መነሣሣትን ይፍጠርባችሁ፡፡

ዲክ ማክሌላን

የአየር መልዕክት
AIR LETTER
AEROGRAM

፩

ኪድጀይ

አዲስ ግንኙነት

ዮጌታውን ጥሪ የሰማው ትንሹ ልጅ እየሮጠ በሩን አልፎ ወደ ውስጥ ዘለቀ፡፡ ዕርቃኑን የሆነ፣ የሚያብለጨልጭ ጥቁር፣ ወደ ስድስት ዓመት ገደማ የሚሆነው ልጅ ነበር፡፡ ነገር ግን፣ ወደ ክፍሉ ገብቶ የተመለከተው ነገር ከዚያ በፊት አይቶት የማያውቀው ነገር ነበር - ይህም በጣም አስፈርቶታል! በድንጋጤ ደርቆ ቀረ፣ ጠጉሮቹ በራሱ ላይ ቀጥ ብለው ቆሙ! ዓይኖቹ ፈጠጡ! በምድር ላይ ወደቀ፣ ወደ ኋላ ተንከባለለ፣ ከዚያም በመጣበት አቅጣጫ ወጥቶ መሮጥ ጀመረ- ፍጥነቱ ግን በፊት ሲመጣ ከነበረው ፍጥነት በጣም ይበልጥ ነበር!

ይህንን ልጅ በጣም ያስፈራውና አስደንብሮ እንዲህ ያስሮጠው ነገር በበርጩማ ላይ በቤት ውስጥ የተቀመጠው ነገር ነበር፡፡ ሰው ነበር - ነጭ ሰው! ይህ ልጅ የወሬ ወሬ ስለ ነጭ ሰው ሰምቷል፣ ነጭ ስለሆኑ ሰዎች፣ አስፈሪ ወሬ ሰምቷል፣ ነገር ግን የሰማቸው ነገሮች በወቅቱ እውነት አልመሰሉትም፡፡ እነዚህንም ወሬዎች ማታ ማታ በእሳት ዙሪያ እንደሚነገሩ ታሪኮች አድርጎ ይመለከታቸው ነበር፡፡

አንድ ጊዜ ጌታው፣ ባለ ርስቱ የሆኑት ሰውዬ፣ በኮንታ ከአንድ ነጭ ሰው ጋር መገናኘታቸውንና ከሰዬው ጋር ማውራታቸውን ሰማ፡፡ ጌታውም ሰውዬውን ቀዩ ሰውዬ እያሉ ነበር የሚጠሩት፡፡ ይህ ሰው ቀይ ነበር! ቀይ ጠጉር ነበረው፣ በፀሐይ የተቃጠለ ቀይ ፊት እና እጅ ነበረው፡፡ በጣም ግዙፍ ይመስላል፡፡ ይበላው ይሆንን? ልጁ በፍራቻ ተዋጠና መሮጡን ቀጠለ!

ᚐᚅ

በዋካ ከሚገኘው የሚስዮን ጣቢያ ወደ ኮንታ ኮይሻ የተጓዝነው በሚሽን

አቪዬሽን ፌሎውሺፕ (ኤም.ኤ.ኤፍ) አውሮፕላን ነበር፡፡ ተራራማ በሆነው አገር ይህ ቦታ በበቅሎ የአምስት ቀን መንገድ ነበር፡፡ ነገር ግን፣ በዚያች ትንሽ አውሮፕላን የሠላሳ ደቂቃ ጉዞ ነበር፡፡ የሚቻል ሲሆን የላይኛውን መንገድ እንመርጣለን - ማለት የሰማዩን መንገድ እንመርጣለን! በየወሩ ለአምስት ወይም ስድስት ቀናት አገልግሎት ወደ ኮንታ እንጓዛለን፡፡

አውሮፕላኑ እንዳረፈ፣ አብራሪው በቀጠሮው ቀን ተመልሶ እንደሚመጣ ቃል ገባልን፣ እኛም በፍጥነት ድንኳናችንን ተከልን፡፡ ጥቂት ንብረቶቻችንን ውስጥ በማስቀመጥ፣ መኝታ እና የምግብ ክምችቶቻችን እንዲሁም መድኃኒቶችን በድንኳናችን ውስጥ አኖርናቸው፡፡ የአውሮፕላኗ ድምፅ በረጅም ርቀት ላይ ያሉትን ሰዎች ተመልሰን መምጣታችንን አስታወቃቸው፡፡

እንደ ተለመደው፣ ሰዎች የሕክምና እርዳታ ለማግኘት እኛ ወዳለንበት ስፍራ መምጣት ጀምረዋል፡፡ ሰዎቹም ሁሉ ወባ ወይም የሳንባ ነቀርሳ ወይም ሁለቱም በሽታዎች ያሉባቸው ይመስላሉ፡፡ ሴሰኝነት የሞላበት የአኗኗር ዘይቤን ስለሚከተሉ፣ በቂጥኝ እና በጨበጥ በሽታ የተጠቁ ብዙ ሰዎች ነበሩ፡፡ እንዲሁም የቆላ ቍስል፣ ተስቦ፣ የሳይን በሽታ እና ሌሎች ብዙ በሽታዎች ነበሩባቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ከዚህ በፊት ምንም ዓይነት መከላከያ (አንቲባዮቲክ) መድኃኒት ወስደው ስለማያውቁ ቪዳ ኃይለኛ ሐኪም፣ ዶክተር ያሰኛትን ጥሩ ውጤቶች አግኝታለች፡፡ በምትሃት የሚያምኑት ሰዎችን ስትነካ እና ስትጸልይላቸው በእጆቿ ላይ የሆነ ትንግርታዊ ኃይል እንዳለ ያስባሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ኃይሉ ሁሉ ያለው በምትሰጠው መርፌ ውስጥ መሆኑን ይናገራሉ!

ቪዳ የሕክምና አገልግሎቱን በመስጠት ላይ እያለች ከወላይታ የመጣው ወንጌላዊ ለሕክምና ተራቸውን በመጠባበቅ ላይ ላሉት ሰዎች የክርስቶስን ወንጌል ያካፍላቸዋል፡፡ እኔ ደግሞ ከሌሎች ወንጌላውያን ጋር በመሆን በመንደሩ ውስጥ እና አውሮፕላኑ ቆሞበት በነበረበት ስፍራ ወንጌል ለማካፈል እንሄድ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከወንጌላውያን ጋር ወይም በቅርብ ጊዜ ከተተከሉ አብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎች ጋር ስብሰባ አደርጋለሁ፡፡

ᚕᚔᚖ

አንድ ቀን ከሌላ አካባቢ የመጣ፣ ሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆኑ ጎሳዎች የሆነ ሰው ወደ ክሊኒክ መጣ፡፡ የለበሰው ከዛፍ ቅርፊት እንደ ነገሩ የተሠራ እራፊ ነገር

ነበር፡፡ በአካባቢው በሚገኝ አስተርጓሚ ከየት አካባቢ እንደ መጣ ጠየቅሁት፡፡ በአገጩ ወደ ደቡብ አቅጣጫ እያመለከተ ከተራራማው አገር መሆኑን እያሳየኝ ‹‹ከጻራ›› ነው አለኝ፡፡

‹‹እሩቅ ነው እንዴ?›› ስል ሰውዬውን ጠየቅሁት፡፡

‹‹ኧረ ቅርብ ነው፣›› ሲል በአገጩ ቅርብ መሆኑን አሳየኝ፡፡ ‹‹በጣም ቅርብ ነው፡፡ እዚያ ጋ ነው፡፡ እነዚህ ተራራዎች ጋ፣›› አለኝ፡፡

‹‹ወደዚያ ልትመራኝ ትችላለህ?›› ስል ጠየቅሁት፤ ሰውዬውም ‹‹እወስድሃለሁ›› አለኝ፡፡ ከወር በኋላ ስንመጣ ከሰውዬው ጋር ለመገናኘት እና ወደ ጻራ አብረነው ለመሄድ ቀጠሮ ያዝን፡፡

ᚕᚖ

እኔ ‹‹በጣም ቅርብ ነው፡፡ እዚያ ጋ ነው፡፡ እነዚህ ተራራዎች ጋ›› ተብሎ በጻራው ሰውዬ ግምት የተነገረውን ርቀት አላመንሁም፡፡ ስለዚህም በሚቀጥለው ጉብኝታችን የኤም. ኤ. ኤፍ አውሮፕላን ይዛን በምትበርበት ወቅት፣ ሁለት ወጣቶች በቅሎዎቻችንን ይዘው ከዋካ ወደ ኮንታ ኮይሻ እንዲሄዱ ላክኋቸው፡፡ ግምቴ ልክ ነበር! የጻራው ሰውዬ እኛን ለመገናኘት በዚያ ነበር፣ እንዲሁም የላኳቸው ሰዎች እስከነ በቅሎዎቻቸው እዚያ ደርሰው ነበር፡፡ ከጥቂት ወንጌላውያን ጋር በመሆን ያንን ትንሽ ሰውዬ ተከትለን መጓዝ ጀመርን፡፡

ይህ ሰው በሸለቆ ውስጥ አድርጎ ወደ ተራራው መራን፣ ተራራውን ወጥተን፣ በዚያኛው የተራራው ክፍል የሚገኘውን ጅረት ተሻግረን፣ በረጃጅም ሣሮች ውስጥ ተጉዘን እንደገና ሌላ ተራራ ወጥተን ወደ ማዶ ተሻገርን፡፡ ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ ተጉዘን በመጨረሻ ለ48 ሰዓታት ያህል ከተጓዝን በኋላ፣ ወደ ጻራ አካባቢ ደረስን!

በሦስቱ ጎኖቹ ጥቅጥቅ ባለ ደን የተከበበ አንድ ሰፊ ንጹሕ ስፍራ ነበር፡፡ ከዚህ ንጹሕ ስፍራ በደቡብ በኩል የሚፈስሰው የኦሞ ወንዝ ነው፡፡ በጫካዎቹ ጥግ ጥግ ላይ ሦስት ትናንሽ መንደሮች ሲኖሩ፣ በእያንዳንዳቸው ውስጥ በግምት ሙቶ ሰው ያህል ይኖርባቸዋል፡፡ ከሣር የተሠሩ በእጅ እና በጉልበት እየሄዱ የሚገቡባቸው ትናንሽ ጎጆዎች የማኅበረሰቡ ዝቅተኛ ሰዎች ሲኖሯቸው፣ ነገር

ግን በትንሽ ኮረብታማ ቦታ ላይ አካባቢውን ሁሉ በደንብ ለመቃኘት በሚመች ስፍራ ላይ ትልቅ፣ በንብ ቀፎ ቅርጽ የተሠራ፣ ሙሉ ለሙሉ ሣር የለበሰ የባለ ርስት ቤት ይታያል። ይህ ቤት ከወለሉ የሰባት ጫማ (2.1 ሜትር) ከፍታ ሲኖረው፣ ለዚያ የተገለለ ስፍራ ግሩም ቤት ነበር።

በዚያ ቤት ውስጥ ከቤተሰቡ ጋር የሚኖረው ሰው የተፈጠረው ምድር ሁሉ፣ ጫካው ሁሉ፣ እንስሳት ሁሉ እና ሰዎች ሁሉ የእርሱ እንደ ሆኑ ይናገራል። ሁሉም ነገር! ሁሉም ነገር የእርሱ ነበር! በኢትዮጵያ ውስጥ ሕጋዊ የሆነ የባርያ አሳዳሪ ሥርዓት አልነበረም። ነገር ግን፣ ይህ ሰው ባሮች የነበሩት ሰው ነው! ምክንያቱም በአንድ ወቅት ምድሩን ለመገዛበኘት ሄጃለሁ፤ እንዲሁም ሰላም ለእርሱ ልለው ወደ መኖሪያ ቤቱ ተጠግቼ ነበር።

‹‹ደግ፣ ቅንነት ያለው አምባገነን›› ዓይነት ነበር። በሳምንት ውስጥ ሦስት ቀን መሥራት ለሚችሉ ቤተሰቦች ካመረቱት ግማሹን የሚሰጡት ከሆነ፣ ትናንሽ መሬቶች ይሰጣቸዋል። በተቀሩት ሦስት ቀናት እያንዳንዱ ሰው በዚህ በጌታቸው ማሳ ውስጥ ይሠራል - ማሳውን ይመነጥራል፣ ይቄፍራል፣ ያርሳል፣ ይተክላል፣ ያርማል፤ በአጠቃላይ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ያደርጋል። ለሥራቸው ግን ምንም ነገር አይከፈላቸውም፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ስኳር ድንች፣ ቡና፣ ሙዝ ወይም በአካባቢው የሚመረተው ቅመማ ቅመም ምንም አይሰጣቸውም። ሰዎቹ ወደ ሰውዬው ቤት የማገዶ እንጨት ተሸክመው ይወስዳሉ፣ ላሉት ብዙ ከብቶች ሣር ያጭዳሉ፣ እንዲሁም ከምንጭ ውኃ ይቀዳሉ። ከዱር አራዊት እርሱን ለመጠበቅ ሰዎች ዘበኞች ይሆኑታል እንዲሁም ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀስ ሰዎች ዕቃውን ይሸከሙለታል።

ባለ ርስቱ ለእኔ ሞቅ ያለ አቀባበል ካደረገልኝ በኋላ፣ ወደ መኖሪያ ቤቱ ጋበዘኝ። እየመራ ያመጣኝ ሰው ለምን ‹‹ከእንግዳ ሰው›› ጋር እንደ መጣ ዜናውን በሕዝቡ ዘንድ እያሰራጨ ሄዶ ሳለ፣ ባለ ርስቱ ከሚስቱ እና ከሁለት ትላልቅ ልጆቹ ጋር አስተዋወቀኝ። በተለመደው የኢትዮጵያውያን የእንግዳ አቀባበል ባህል፣ በበርጩማ ላይ እንድቀመጥ ካደረገ በኋላ ጤንነቴ እንዴት እንደ ሆነ፣ ስለ ጉዞው ሁኔታ፣ በመጨረሻም ለምን ወደዚያ በጣም ሩቅ ወደ ሆነ ስፍራ እንደ መጣሁ ጠየቀኝ። ባለቤቱ በጓዳ ነበረች፣ ነገር ግን ንግግራችንን ታደምጥ ነበር፤ ከዚያም ‹‹ለአገልጋዮቹ›› እሳት አቀጣጥለው ቡና እንዲያፈሉና

ቆሎ እንዲቆሉ ትእዛዝ ሰጠ።።

ለትንሽ ጊዜ በዓለማችን ውስጥ ምን እየሆነ እንዳለ፣ ከኤርትራ ጋር ስለ ነበረው ጦርነት እንዲሁም ስለ ሱማሌ የጎሳዎች ጦርነት አወራን።። እንዲሁም ስለ እህል እና የማር ዋጋ ነገረን።። ከጫካም ሰዎች የዱር እንስሳት ቆዳ እና ማር ይዘው መጡ።። ጻራ ባላት የማር ጥራት ትታወቃለች፤ ይህ ደግሞ ለባለ ርስቱ ዋና የገቢ ምንጭ ነበር።።

የተለያዩ ነገሮችን እያወጋን፣ በድንገት ሰውዬው ሦስት ጊዜ ያህል አጨበጨበ።። ምንም ነገር አልተፈጠረም።። ከትንሽ ቆይታ በኋላ እንደገና አጨበጨበ-ሦስት ከባድ ደማቅ ጭብጨባዎች።። አሁንም ምንም አልተፈጠረም።። ትንሽ ደቂቃዎች ቆይቶ እንደገና አጨበጨበና ‹‹ባሬ›› ብሎ ተጣራ።። *ባሬ* ማለት፣ *ባርያ* ማለት ነው፣ ነገር ግን የመጨረሻውን ቃል በመተው *ባሬ* ብሎ ነው ሰውዬው የተጣራው።። ነገር ግን፣ ትርጓሜው ተመሳሳይ ነው!

በድንገት አንድ ትንሽ፣ ጥቁር ዕርቃኑን የሆነ ልጅ በተከፈተው በር በኩል ዘው ብሎ እየሮጠ ገባ።። ከመንደር ውስጥ ወይም ከጫካው ውስጥ በሩጫ ከመምጣቱ የተነሣ ሊሆን ይችላል፣ ትንፋሹ ይቁራረጥ ነበር።። በእርግጠኝነት እኔ በዚያ ስለ መኖሬ የሚያውቀው ነገር አልነበረም! ወደ ቤቱ በሩጫ እንደ ገባ እኔን አየኝና ፊቱ ከፈገግታ ወደ መገረም፣ ከዚያም ወደ ድንጋጤ በመጨረሻም ፍጹም ወደ ሆነ ፍራቻ ተለወጠ! በሞቃታማው አየር ውስጥ ፈዝዞ ቀረ፣ ዓይኖቹ ፈጠጡ እና አፉ በጣም ተከፈተ! ወደ ኋላ በመንገዳገድ በመጣበት አኳኋን ለመመለስ ፊቱን አዞረ! ፍራቻው እንደ ወፍ መብረር አስችሎታል!

ልጁ ዞሮ እግሬ አውጪኝ ከማለቱ ገና የበሩ መውጫ ጋ ሳይደርስ አለቃው እንደ ገና ጠራው።። ቆም ብሎ የበሩን መቃን በእጆቹ ያዘ፤ ዓይኖቹ ግን አሁንም በእኔ ላይ እንዳፈጠጡ ነበሩ! ነጭ፣ ቀይ ሰዎች የሚለው ታሪክ እውነት ነው! በሕይወቴ እኔን ማንም ሰው እንዲህ በጣም ፈርቶኝ አያውቅም።። ሳቅሁበት፣ ነገር ግን ጥርሶቼ ፍራቻውን አባባሱበት! ዓይኖቹ ይበልጥ ፈጠጡ፤ ወደ ነበሩበት ሊመልሳቸው ፈጽሞ አልቻለም።።

አለቃው እንደገና ጠራው፣ ልጁም እያንገራገረ የበሩን መቃን በመልቀቅ ቀስ

ብሎ ጥግ ጥጉን በማድረግ፣ ከእኔ በተቻለው መጠን ለመራቅ እየሞከረ ወደ አለቃው ሄደ። በሰውዬው እና በሴቲቱ መካከል ቆሞ ነበር፣ አሁንም ዓይኖቹ በእኔ ላይ እንዳነጣጠሩ ነበር። አለቃው ትእዛዝ ሲሰጠው እንኳ የአለቃውን አንዳች ቃል አልሰማም። እጅግ በጣም ፈርቷል! የተነገረውን ነገር ማስተዋል የቻለው አለቃው ጆሮ ግንዱን በጥፊ ባለው ጊዜ ነበር። ከዚያም ልጁ በገባበት መንገድ ወጥቶ እየሮጠ ሄደ።

ከአሥር ደቂቃዎች በኋላ ያ ወጣት፣ አጭር፣ ጠንካራ፣ የሚያብለጨልጭ ልጅ፣ የተፈለጠ ከእንጨት የተሠራ ማስታጠቢያ የሚመስል ጐድጓዳ ሳሕን እንዳቀፈ ተመልሶ መጣ። ይህንን መታጠቢያ እንዳቀፈ በጣም ቀስ ብሎ ወደ እኔ ተጠጋ። ይበልጥ ወደ እኔ በተጠጋ ቁጥር፣ እነዚያ አጫጭር እጆቹ ይበልጥ እያጠሩ በተቻለው መጠን በእኔ እና በእርሱ መካከል ያለውን ክፍተት ለማስፋት ይሞክራል። ምን ላደርገው እንደምችል አላወቀም። እይዘው ይሆንን? እበላው ይሆን? ማስታጠቢያውን ከእግሬ አጠገብ አስቀምጦ ሁለት ቁራጭ እንጨቶች ብቻ ለማምጣት እንደገና እየሮጠ ሄደ።

ቀዝቃዛ ውኃ ያለበት ቅል ይዞ የመጣው በሦስተኛው ጉዞ ላይ ነበር። በመሬት ላይ ካስቀመጠው በኋላ፣ መሬት ላይ ከፊቴ ተንበረከከ፣ ነገር ግን አሁን በተቻለው መጠን የፈራች ጥንቸል ተነሥታ ለመሮጥ እንደምትዘጋጅ፣ ሁሉ እርሱም ከእኔ ለመራቅ እየሞከረ ነበር። እንደምታውቁት፣ በእርግጥ፣ ልጁ እግሬን እንዲያጥብ ተነግሮታል። ይህ ደግሞ የባሮች ሥራ ነበር። ይህ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል ውስጥ ተወዳጅ የሆነ ባህል ነው። የእንግዶችን እግር ማጠብ የመልካም አቀባበል ምልክት ነው።

በተለይ ክርስቲያኖች የቀጣናቸውን የኅብረት ስብሰባ ለመካፈል ረጅም ጉዞ ተጉዘው የሚመጡትን ሰዎች እግር ማጠብ ይወድዳሉ። እንዲህ ዓይነቱ ጉባኤ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በወር አንድ ጊዜ ይካሄዳል። ይህ ተግባር ጌታቸው ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርትን እግር የማጠቡን ሁኔታ ያስታውሳቸዋል። ልማዳቸውን አከብራለሁ፣ እንዲሁም ሰዎች እግሬን ለማጠብ ሲሉ እፈቅድላቸዋለሁ እንዲሁም አክብሮቴን ለማሳየት እና ኅብረት ለማድረግ ስል እኔ የሌሎችን እግር አጥባለሁ።

ይህን በፍራቻ የተዋጠ ልጅ ስመለከተው ከፍራቻ የተነሣ ይንቀጠቀጣል፣

ላቡ በጀርባው ላይ ይንቆረቆራል፤ በጣም አዘንሁለት፣ የጫማዬን ማሰሪያ ፈትቼ እግሮቼን ከካልሲዬ ውስጥ አወጣኋቸውና እንደ ልማዴ ሱሪዬን ወደ ጉልበቴ ሰበሰብኋቸው፡፡ ልጁ ነጭ በሆነው ቆዳዬ ላይ አፍጥጦ ቀረ፡፡ የእግሮቼን ጣቶች ተመልክቶ ከእርሱ የእግር ጣቶች ጋር ተመሳሳይ ቁጥር እንዳላቸው በመመልከት መገረሙ ከዓይኖቹ ላይ ይነበባል፡፡

በቀስታ የቀኝ እግሬን በማንሣት፣ በማስታጠቢያው ውስጥ አስቀምጦ ትንሽ ቀዝቃዛ ውኃ ደፋባቸው፡፡ ሳሙና ወይም ፎጣ የለውም፣ ነገር ግን እግሬ ለቀናት አግኝቶ የማያውቀውን እጥበት ለመስጠት በፊቴ ተቀምጧል፡፡ ይመስለኛል የልጁ ትግል ነጭ የሆነው ነገር በማስለቀቅ ቆዳዬ ወደ ትክክለኛው መልኩ እንዲመለስ ጥረት በማድረግ ላይ ነበር፡፡ አንዱን እግሬን በንጹሕ ውኃ ካለቀለቀ በኋላ፣ የግራውን እግሬን እንስኪያጥብ ድረስ በንጹሕ እንጨት ላይ እንዲደርቅ አስቀመጠው፡፡

ከጨረሰ በኋላ ወደ አለቃው ዞሮ ተመልከተ፤ አለቃውም አንገታቸውን ወደ ላይ ወደ ታች በመነቅነቅ ማረጋገጫ ሰጡት፡፡ እግሮቼ በደረቁ አየር አማካይነት እየደረቁ ሳለ በማስታጠቢያው ውስጥ ያለውን ቆሻሻ ውኃ ይዞ ወጣ፡፡ ከአለቃው ጋር እያወራን ሳለ፣ የውኃ መቅጃ ቅሉን ለመውሰድ ተመልሶ መጣ፡፡ አሳቤ እንዳይበታተን ሰውዬውን በማስተዋል በማድመጥ ላይ ስለ ነበርሁ ልጁ ተመልሶ መምጣቱን አላስተዋልኩም ነበር፡፡ ከዚህ በፊት ተንበርክኮ በነበረበት ቦታ ላይ እንደገና ተንበርክኮ፤ ወደ ፊት ፊቱን አስግጎ እኔ ከማወቄ በፊት፤ የቀኝ እግሬን አውራ ጣት ሳመው!

በኢትዮጵያ በቆየሁባቸው ዓመታት ሁሉ ውስጥ ማንም ሰው እግሮቼን እንዲስም ፈቅጄ አላውቅም፣ እንዲያውም እንዲሞክረውም አላደርግም! ወይም በአንዳንድ አካባቢዎች ሰዎች እንደሚያደርጉት ጉልበቴን እንዲስሙ አላደርግም፡፡ ሰዎች እነርሱ ከእኔ በታች ወይም እኔ ከእነርሱ በላይ እንደ ሆንሁ አድርገው እንዲያስቡ ማድረግ አስጸያፊ ነገር መስሎ ነበር የሚታየኝ፡፡ ነገር ግን ይህ ነገር ሆነ! ልጁ የእግሬን ጣት ሳመ! በጣም ደነገጥሁኝ፤ በፍጥነት ምላሽ በመስጠት ልጁን ያዝሁት! ከዚህ በፊት ፈርቶ ከሆነ፣ አሁን ደግሞ በጣም ፈርቷል! ልጁ ወደ ኋላው ዘለለ፡፡ በእጆቼ ትከሻውን መያዝ አልቻልኩም፣ ነገር ግን በቀኝ እጄ ክንዶቹን ያዝሁ! አጥብቄ በመያዝ ልጁን ከመሬት ላይ አነሣሁት- ዓይን ለዓይን ተያየን! ያ ጥቁር ልጅ፣ ነጭ ሆነ! ወደ ራሴ ማስጠጋት ጀመርሁ!

ልጁ ይበልጥ እየገረጣ ሄደ! በጣም ፈርቷል! በእግሮቹ ተወራጨ! ለማምለጥ የሚችለውን ሁሉ ሙከራ አደረገ፡፡ ነገር ግን፣ አጥብቄ በመያዝ ወደ እኔ አቀረብሁት፡፡ ይበልጥ ወደ እኔ እየሳብኩት በሄድሁ ቁጥር፣ ቡናማ የሆኑት ዓይኖቹ ይበልጥ እየፈጠጡ ሄዱ፡፡

ልጁ ምን እንደማደርገው ግራ ገብቶታል! ምን እያሰበ ይሆን? እንደምበላው? እንደምገድለው? ከዚያም አንድ ቃል ተናገርሁ፣ ‹‹ሊድጂይ - ልጄ›› ብዬ ጠራሁት እና ጉንጩን በሁለቱም በኩል ሳምሁት፡፡ ከዚያም እንዲሄድ ለቀቅሁት፡፡ እርሱ ግን አልሮጠም፡፡ እዚያው ቆሞ ቀረ፡፡ የእፎይታ ስሜት ተሰማው፡፡ በሆነ መልኩ ምን እንዳደረግኩ ገብቶታል፡፡ ከባርነት አንሥቼ ልጄ አድርጌዋለሁ! ከእስራት አዲስ ወደ ሆነ ግንኙነት! የባሪያ እና የጌታ ሳይሆን፣ የልጅ እና የአባት! እርሱ ይህንን ስጦታ ተቀብሏል፡፡ ከእንግዲህ መፍራት አያስፈልገውም፡፡ መሮጥም አያሻውም፡፡ አሁን ከአባቱ ጋር እንዳለ ልጅ ነው! በዚህ ጊዜ ልጁ ለጥቂት ጊዜ ትንፋሹን ያዝ ያደረገ መሰለ፡፡ እንዲህ ሲል በለሆሳስ ተናገረ *‹‹አባ፣ አባዬ››!*

ከዚያን ጊዜ አንሥቶ ምድሪቷ ከእርሱ ፊት ልትሸሸገኝ አልቻለችም፡፡ ወደምሄድበት ሁሉ ይሄዳል፤ ብዙ ጊዜ ትንሸዋን ጣቴን ይዞ ከእኔ ጋር ይጓዛል፡፡ እኔ ስቀመጥ ይቀመጣል፣ እኔ ምግብ ስበላ ይበላል፡፡ ቤት ውስጥ በሙቀት ምክንያት መተኛት ስለማይችል፣ በሣር ውስጥ እኔ ስተኛ እርሱም ይተኛል፡፡ ወደ መንደሮች ሄጄ ጥላ ሥር ቁጭ ብዬ ለሰዎች ኢየሱስ ያደረገውን እና የተናገረውን ታሪክ ሳወራላቸው፣ እርሱም በዚያ ስፍራ ይገኛል፡፡

ልጁ የሆነውን ነገር የተመለከተችው የጌታው ሚስትም እኔ ወደ ሄድሁበት ስፍራ ሁሉ ተከትላ ትመጣለች፡፡ ይበልጥ ለማወቅ ትፈልጋለች፡፡ ወንጌልን ይበልጥ ሳብራራላቸው እና የድነትን መንገድ ስገልጥላቸው በጥንቃቄ ያደምጡኝ ነበር፣ እንዲሁም የተረዱ ይመስሉ ነበር፡፡ እነርሱ እና ሌሎች ጥቂት ሰዎች አመኑ እንዲሁም ኢየሱስን ለመከተል ወሰኑ፡፡

ꕥ

ከዓመታት በኋላ፣ በ‹‹ቀይ ሽብር›› ወቅት የኮምዩኒስት ወታደሮች ወደ ጻራ ደረሱ፡፡ ባለ ርስቱም ሀብቱን ለመከላከል ተዋግቶ ነበር፣ ነገር ግን ከልጆቹ ጋር

በጥይት ተመትቶ ሞተ፡፡ ሚስቱ ወደ ግዞት ተወሰደች፡፡ ይህ ውስጣዊ ግዞት ሲሆን፣ የተወሰደችውም በኮንታ ውስጥ ወደምትገኝ አንዲት ከተማ ነበር፡፡ ይህች ከተማ ወደ ሰሜን የአራት ቀን ጉዞ ያህል ትርቃለች፡፡ በጻራ ወደ ነበረው ቤቷ መመለስ አልተፈቀደላትም፡፡ ጻራን ለቅቃ በሄደችበት ወቅት ያ ልጅ ዕቃዎቿን በፈቃደኝነት ተሸክሞላት ነበር፡፡ ከእርሷ ጋር ቆየ፣ እንዲሁም አትክልቶችን በመትከል፣ እንጨት በመልቀም እና ከምንጭ ውኃ በመቅዳት ያግዛት ነበር፡፡ እርሷም እንደ ባሪያ ወይም አገልጋይ ሳይሆን፣ እንደ ቤተሰቧ አካል ትንከባከበው ነበር፡፡

በኋላ ላይ፣ በከተማዋ ውስጥ ትምህርት ቤት ሲከፈት እንዲማር ወደ ትምህርት ቤት ላኩት፡፡ በጎረቤታቸው የሚኖር ሰው ከባለ ሥልጣናት ደብቆ ካስቀመጠው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ የወንጌላት መጻሕፍትን ታሪክ ወዲያው ማንበብ ቻለ፡፡ ጎረቤቶቻቸው ቡና እንዲጠጡ ወደ ቤታቸው ይጋብዟቸዋል፤ ከዚያም ታሪኮቹን ያካፍላቸዋል፡፡ ጥቂት ሰዎች እያመኑ ሲመጡ ትንሽዬ የጸሎት ቤት ገነቡ፤ ሊድጂይ እና ሌሎች ወጣቶች በሳምንቱ የዕረፍት ቀናት ወንጌልን በመስበካቸው ምክንያት በከተማዋ አካባቢ ወዳሉ መንደሮች ሁሉ ወንጌል ተሰራጨ፡፡

ꕥ

የኮምዩኒስት መንግሥት ውድቀትን ተከትሎ እንደገና ወንጌላውያን ወደ ኮንታ ለመምጣት በር ተከፈተላቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት በኮንታ ወደ ሰባ የሚጠጉ አብያተ ክርስቲያናት ሲኖሩ፣ በጻራ ውስጥ ደግሞ ስድስት ቤተ ክርስቲያናት አሉ፡፡ ከጠጠር የተሠራ አዲስ መንገድ በኮንታ ውስጥ አልፎ ወደ ተራራው በመውጣት ወደ ጻራ ይደርሳል፡፡ ሊድጂይ እና ሌሎች ወንጌላውያን ለረጅም ጊዜ ተዘንግቶ የቆየውን አካባቢ መንገድ እንዲያገኝ በማድረግ የክርስቶስን ወንጌል ለመስበክ የሚያመች መንገድን እግዚአብሔር እንደ ሰጣቸው ይናገራሉ፡፡

ከዚያ መንገድ ማብቂያ በኋላ ደኅንነት የሚያስፈልጋቸው ገና ብዙ መንደሮች አሉ፡፡ ለክርስቶስ ያልተገዙ በጣም ብዙ ተራሮች አሉ፡፡ እነዚህ በመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ ላሉ ነሳዎች ወንጌልን ለማድረስ በመጀመሪያ ረድፍ ላይ በመሆን ሕይወታቸውን አደጋ ውስጥ እየከተቱ የሚሰብኩ፣ በቅርቡ ከኢየሱስ

ክርስቶስ ጋር አዲስ ግንኙነት የመሠረቱት በሊድጂይ እና ሌሎች ወንጌላውያን አማካይነት ወንጌል ይሰበካል።

ከመገናኘታችን በፊት የሊድጂይ ስም ማን እንደ ነበረ አልነግራችሁም። በጣም የሚያስገርም ሰይጣናዊ ስም ነበረው፤ እኔም ይህንን ስሙን ለመርሳት ቁርጠኞያለሁ። በመሠረታት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጋቢ ሆኖ ሲሾም ወንጌላውያን የሰጡትን አዲሱን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስሙንም አልነግራችሁም። በእርግጥ ይህ እጅግ በጣም ጥሩ ስም ነው! ነገር ግን እኔ ሁልጊዜ ‹‹ልጄ›› ብዬ ነው የምጠራው፣ እንዲሁም እርሱ አቶ ማክሌላን ብሎ መጥራትን አልለመደም። ሁልጊዜ እኔን የሚጠራኝ ‹‹አባቴ›› በማለት ነው።

ይህ አንድ ነገር ብቻ ያስቀርልኛል፤ ይኸውም ‹‹በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ባለ እምነት ከእግዚአብሔር ጋር በአዲስ ግንኙነት ውስጥ ናችሁን?›› የሚል ጥያቄ ነው። እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ‹ክርስቲያን› የሚል ስያሜን አግኝታችኋል ወይ? ጌታን ‹ሰማያዊ አባቴ› ብላችሁ መጥራት ትችላላችሁ ወይ? እንዲሁም ስለ ፍቅሩ እና ጸጋው ለሌሎች ሰዎች ትናገራላችሁ ወይ?

> *‹‹ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ፥ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ። ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም፤ ልጅም ከሆንህ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ።››*
>
> ገላትያ 4፡4-7

2

ዛቡ

መጽሐፉን መፈለግ

ምንም እንኳ ፀሐይ ትዕንግርታዊ ጎብረ ቀለማት ያለው ጨረሯን በሰማይ ላይ ብትዘረጋም፣ ዛቡ ግን የዚህን ነገር ውበት ልብም አላለውም፡፡ ወደ ሰማይ ተመልከቶ አያውቅም ደግሞም በጣም ተረብሿል፡፡ በዙሪያው ስላሉት መንፈሳዊ አካላት በደንብ ተገንዝቧል፤ በሕልም፣ በራእይ እና በገጽ ምልክቶች አማካይነት ብዙ ጠቃሚ ነገሮችን ተመልክቷል፡፡ ጠንቋዩ እና ሚስቱ ወደ ‹‹ሰይጣን ቤት›› ሄደው ነበር፡፡ ይህ ቤት ትንሽ፣ በዋርካ ዛፎች በተሞላ ደን ውስጥ በጭቃ እና በሣር የተሠራ ክብ ቤት ነበር፡፡ ሚስቱ ዕጣን እና ሽታ ያላቸውን ነገሮች ለማጨስ በሸክላ ፍም ይዛ ሄዳለች፡፡ ከጎጆው ውጭ ዕጅብ ብለው የበቀሉት ሸምበቆዎች ለመንፈሱ መሥዋዕት የሚቀርብበት ቦታ ይህ መሆኑን ያሳያሉ፡፡

በዚህ ቤት አቅራቢያ በሚገኝ አንድ ዛፍ ሥር ባለ የድንጋይ መሠዊያ ላይ የተጠራቀመ ደም እና ከዚህ በፊት በቀረቡት መሥዋዕቶች ምክንያት እዚያ እና እዚህ የተበታተኑ አጥንቶች ይታያሉ፡፡ የዛፎቹ ቅርፊቶች ቅቤ ተቀብተዋል፣ እንዲሁም በዛፎቹ ቅርንጫፎች ላይ ጥጥ ተንጠልጥሎባቸዋል፡፡ በሸምበቆ አጥር ተከብቦ ያለውን ጎጆ ማንም እንግዳ የሆነ ሰው ለመቅረብ አይደፍርም፡፡ ክፉውን መንፈስ እና ያንን አካባቢ ለቅቀው እንዳልሄዱ፣ ነገር ግን በዛፎች እና በድንጋዮች ላይ ይኖራሉ ብለው የሚያምኑትን የአያት ቅድመ-አያቶቻቸውን መናፍስት ይፈራሉ፡፡

ለበሽታቸው ባህላዊ መድኃኒትን እየጠበቁ የነበሩት ሰዎች የዛቡን ልብ የሞላውን ኀዘን እና ፍርሃት መገመት አልቻሉም ነበር፡፡ ሕልም አልሟል-

ሕልሙም ያልተለመደ እና ሕይወቱን የሚለውጠው ዓይነት ነበር፡፡ በሕልሙም ያየው፣ ዲያብሎስ የደም መሥዋዕትን ከእርሱ ሲፈልግ ሳይሆን፣ አንድ ሰውን ነበረ-ምን ዓይነት ሰው ነበር! ሰውን አፍቃሪ እና መልካም ነው፡፡ ይህ ሰው ለዛቡ መጽሐፍ አውጥቶ ሰጥቶት እንዲህ አለው፣ ‹‹ይህ መጽሐፍ የዘላለም ሕይወት ቃል አለው፡፡ መጽሐፉን ፈልግ ሰላምንና ሕይወትን ታገኛለህ›› አለው፡፡ በዚያ ከዓለም ተገልላ በምትገኝ መንደር ውስጥ ስለ ኖረ፣ ዛቡ በሕይወቱ መጽሐፍ አይቶ አያውቅም፣ ነገር ግን ይህንን መጽሐፍ በሰውዬው እጅ ላይ በግልጽ አይቶታል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ ጠንቋዩ መጽሐፉን ይፈልግ ጀመረ- ያም ቢሆን ፈልጎ ካገኘው ብቻ ነበር!

ከእርሱ በፊት እንደ ነበረው አባቱ፣ ዛቡ ለብዙ ዓመታት በክፉ መንፈስ ተይዞ ነበር፤ ስለዚህም እነዚህን ክፉ መናፍስት ለማስደሰት የእንስሳት ደምን በመሥዋዕትነት ለብዙ ጊዜ ያቀርብ ነበር፡፡ ከእጅ ጠባብ እና ከነብር ቆዳ ከተሠራ ልብስ በስተቀር በጣም ትንሽ ልብስ ብቻ ነበር የሚለብሰው፡፡ በትከሻው ላይ የሚያንጠለጥላት ትንሽ ከጦጣ ቆዳ የተሠራች ቦርሳ የነበረችው ሲሆን፣ በውስጧም የራሱን መድኃኒት፣ አንዳንድ መርዞችን እና ማጌጫዎችን ይይዛል፡፡

ከአባቱ ሞት በኋላ የአካባቢውን የጥንቁላ ሥራ የተረከበ በመሆኑ፣ ጠጉሩን ተቈርጦት አያውቅም፣ ነገር ግን ወደ ኋላ ያስይዘዋል፡፡ በሳል ቅቤ እና ትኩስ የከብት እበት ጠጉሩን ይቀባል፡፡ የዛቡ ጥፍሮች ተቈርጠው አያውቁም፣ እንዲሁም ለብዙ ዓመታት ገላውን ታጥቦ አያውቅም፡፡ ዛቡ ቆሻሻ፣ መጥፎ ጠረን ያለው ሰው ነበር-ያም በጣዖት አምልኮ እስራት ውስጥ መሆኑን የሳያል፡፡

በጎጆዋ ውስጥ ይሰማ የነበረው የዶሮ ጩኸት ከታች ባለው መሠዊያ ላይ ደም መፍሰስ ሲጀምር አቆመ፡፡ በሣር በተሠራው ጣሪያ ውስጥ የዕጣን ጭስ መትመም ጀመረ፡፡ ከዚያ እንዲህ ሆነ! ዛቡ እርስ በርሳቸው የሚጨቃጨቁ እና የሚጯጯኹ፣ እንዲሁም የሚደባደቡ በሚመስሉ በብዙ አጋንንት ቊጥጥር ሥር ሆነ፡፡ ሚስቱም እጅግ በጣም ከመፍራቷ የተነሣ ከቀርከሃ በተሠራው በር ሥር ተደበቀች፡፡ ከዚያም ብዙ ክፉ መናፍስት ዛቡን ‹‹የእነርሱን መንገድ በመተው ወደ እግዚአብሔር እየተመለሰ መሆኑን›› በመናገር ከሰሱት፡፡

ዛቡ እንደ ገለጸው እነዚያ ክፉ መናፍስት ብዙ ጊዜ ወደ ሰማይ ወርውረው

መሬት ላይ ፈጥፍጠውታል፣ ቀኑስል በቀኑስል እስኪሆን ድረስ ደብደበውታል። ከዚያም ስብራት፣ ቅጥቅጥ እና ቀኑስል በቀኑስል ይሆን ነበር!

በእርግጥ የሆነው ነገር ባለቤቱ እንደ ተናገረችው ከሆነ፣ ዛቡ በድንገት ቀጥ ብሎ ደርቆ ቆመ፤ እጆቹና እና እግሮቹ መንቀሳቀስ አቆሙ። ለረጅም ጊዜ ያህል መንቀሳቀስ አይችልም ነበር፣ ፍዝዝ ብሎ ነበር። መጽሐፉን መፈለግ የሚል ነገርን ብቻ እየተናገረ ይቃዥ ነበር፤ ከዚያ ወደቀ። ባለቤቱ ጎትታ ወደ ውጭ ባወጣችው ጊዜ ሁሉም ሰዎች ክፉ መናፍስቶቹ ሲጮኹ እና ሲናገሩ ሰምተው መሸሻቸውን ተገነዘበች።

ዛቡ ከሁኔታው አገገመ፤ ለዘመናት ባሪያ አድርገውት የነበሩት ክፉ መናፍስት ከዚያ በኋላ ግን አላስቸገሩትም። በሚቀጥለው ቀን፣ ስንቁን በአንድ እጁ ጦሩን ደግሞ በሌላኛው እጁ አድርጎ መጽሐፉን መፈለግ ጀመረ። በሸለቆው ውስጥ ባሉት መንደሮች ውስጥ፣ ከዚያም በተራራማዎቹ ላይ ባሉት መንደሮች ፈለገ፤ ያገኘውን ሰው ሁሉ ስለ መጽሐፉ ይጠይቅ ነበር፣ ነገር ግን ማንም ሰው ሊረዳው አልቻለም። ‹‹የሞት ቀጣና›› ተብሎ ወደሚጠራው የጠላት መንድር እንኳ አልፎ በመሻገር መጽሐፉን ፈልጓል፣ ነገር ግን ሊያገኘው አልቻለም።

ሳምንታት እና ወራት አለፉ። አልፎ አልፎ ብቻ ወደ መኖሪያ ቤቱ ዕረፍት እና ተጨማሪ ምግብ ለማግኘት ይመለስ ነበር፣ ነገር ግን ወዲያው ወጥቶ መጽሐፉን መፈለጉን ይቀጥላል። የመንግሥት ባለ ሥልጣናትን፣ ጠንቋዮችን፣ ብቸኛ ገበሬዎችን እና አዳኞችን ስለ መጽሐፉ ጠየቃቸው፤ እነርሱ ግን የዘላለም ሕይወት ያለበትን መጽሐፍ እንደማያውቁ ነገሩት። አንድ አዳዲስ ቦታዎችን የሚጐበኝ ነጭ ሰው እንኳ ሳይቀር እንዲህ የሚባል መጽሐፍ አለመኖሩን ነግሮታል። ነገር ግን፣ ልቡ ይህንን መጽሐፍ በመፈለግ ረገድ በጽኑ መሻት ትቃጠል ነበር።

ሁለት ረጃጅም የፍለጋ ዓመታት አልፈዋል ማለት ይቻላል፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን ተጉዟል- ሁልጊዜም በተሳሳተ አቅጣጫ ተጉዞ ይገኛል-ደግሞም ዘላለማዊ ሕይወት የሚሰጠውን መጽሐፍ ከቶ የማያገኘው ይመስል ነበር። መጽሐፉ ይገኝ ይሆን በሚል በአሳብ እየባዘነ ተመልሶ ወደ ቤቱ እያቀና ነበር። በጠባብ መንገድ ላይ በሚያቃጥል ፀሐይ ውስጥ እየተጓዘ

ሳለ፣ በመንገዱ ላይ ጥላውን ያጠላ ጥላማ ዛፍን ከርቀት ተመለከተ ደግሞም እዚያ ለማረፍ ወሰነ፡፡ እየቀረበ ሲመጣ፣ ሁለት ወንዶች ሰዎች ቀድሞውኑ በጥላው ውስጥ ተቀምጠው ተመለከተ፡፡

ከዚያም ያንን መጽሐፍ አየው! መጽሐፉን! እነዚህ ሰዎች በሕልሙ ያየውን ዓይነት መጽሐፍ ይዘው አያቸው! ዛቡ ወደ እነርሱ ሲሮጥ አዩ፣ እነዚያም ሰዎች ተገረሙ፣ በመሬት ላይ ራሱን ጥሎ እንዲህ ሲል ለመናቸው፡- ‹‹ይህ መጽሐፍ ምን እንደሚል እባካችሁ ንገሩኝ፡፡ እባካችሁ መጽሐፉ የሚለውን ንገሩኝ፡፡ ዘላለማዊ ሕይወትን እንዴት ላገኝ እችላለሁ?›› የዛቡ የረጅም ጊዜ ፍለጋ ተጠናቀቀ- መጽሐፉን አገኘው!

ከጎፋ የመጡት ሁለቱ ወንጌላውያን የድነትን መንገድ ለመንገር ፈቃደኞች ነበሩ፡፡ ስለ ቅዱሱ እግዚአብሔር፣ ስለ ኃጢአተኛው የሰው ልጅ፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለ እግዚአብሔር ልጅ፣ ስለ የምትከነት ሞቱ፣ ስለ መዋጀት እና ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝ እና ጌታ በመቀበል ስለሚገኘው ዘላለማዊ ሕይወት ሲናገሩ ሰዓታት አለፉ፡፡ በዚያ ምሽት ዛቡ ሰይጣንን ካደ፣ እንዲሁም ‹‹ሁለት እጆቹን›› ወደ ላይ አንሥቶ ራሱን አሳልፎ በመስጠት ክርስቶስን ሲቀበል ሕይወቱ ፈጽሞ ተለወጠ፡፡

ዛቡ እነዚያን ወንጌላውያን ወደ ቤቱ ይዞዋቸው ሄደ፤ በሳምንት ጊዜ ውስጥ በአካባቢው ረጅም ርቀት ላይ ያሉት እንኳ ሳይቀሩ እንደ ተለወጠ አወቁ፡፡ ንጹሕ ለበሰ ደግሞም ቆሻሻው ሁሉ ተወገደለት፡፡ ሁሉም የዲያብሎስ ጥቃቅን ዕቃዎች እና የሰይጣን ቤትም ተቃጠሉ፡፡ ነገር ግን፣ ትልቁ ለውጥ፣ ሰላምን እና ከኃጢአት የመዳኑን ማረጋገጫ ማግኘቱ ነበር፡፡ ወንጌላውያኑ ከመሄዳቸው በፊት፣ የዛቡ ባለቤት እና ሌሎች ጥቂት ሰዎችም በኢየሱስ አመኑና ጌታን የሚያመልኩበት ትንሽ ጸሎት ቤት ሠሩ፡፡

የመንደሩ ሰዎች ግራ የመጋባት ጉዳይ በመጨረሻ ወደ ግልጽ ጥላቻ በመለወጡ፣ የዛቡ ከብቶች መጥፋት ጀመሩ፡፡ በሸለቆ ውስጥ የሚገኘው ማሳውን የሚያጠጣበት የመስኖ ውኃው ቦዩ ከወንዙ በመቋረጡ ምክንያት ሰብሎቹ ክፉኛ ተጐዱ፡፡ ለሁለት ቀናት ያህል ከአዳዲስ ክርስቲያኖች ጋር ጸሎት አደረገ፤ ብዙ ጊዜ ዝናብ በማይገኝበት ወራት ውስጥ ብዙ ዝናብ በመዝነቡ መሬቱን አረሰረሰው፡፡ የዘነበው ዝናብም እጅግ በጣም ብዙ ከመሆኑ የተነሣ

የአንዳንድ ጠላቶቹ ሰብሎች ተጠራርገው ተወሰዱ፤ የዛቡ ሰብል ግን ከዚያ በፊት ሆኖ ከሚያውቀው በላይ በጣም ጥሩ ሆኖ ነበር። ዛቡም ምርቱን ለእነርሱም በማካፈል፤ የክርስቶስን ፍቅር ያሳያቸው ነበር።

የዛቡ ተወዳጅ የሆነ ወንድ ልጅ ድንገት በሞተ ጊዜ፣ እነዚያ እምነት-አልባ የሆኑ ሰዎች ይህ የሰይጣን እና የክፉ መናፍስት ቀጣ እንደ ሆነ በመናገር ወቀሳውን በእርሱ ላይ አደረጉ። በእርሱ ቤት ውስጥ ለማልቀስ እና ለመጨፈር ጦራቸውን፣ ጋሻቸውን እና ጎራዴዎቻቸውን አነሡ። ወደ ቤቱ ሲሄዱ ዛቡን ያገኙት ብዙ ጊዜ ያደርግ እንደ ነበረው ማልቀስ እና ገላውን እየቁራረጠ በዝምታ አዝኖ ቆሞ ሳይሆን፣ ነገር ግን በሁሉም ጊዜ በሚያጽናናው በእግዚአብሔር ሐሤት እያደረገ ነበር።

ዛቡ ለመጀመሪያ ጊዜ ስብከት የሰበከው በዚያን ዕለት ነበር፤ ብዙ ሰዎችም በማመን ኢየሱስን ተቀበሉ። ነገር ግን፣ ያመኑት ጥሩ ስብከት ስለ ሰበከ ሳይሆን፣ በሕይወቱ በታየው አስገራሚ ለውጥ አማካይነት ነበር። ከዚህ በፊት አይተውት በማያውቁት መልኩ ሕይወቱ ተለውጧል፣ ስለዚህም እነዚህ ኢ-አማኒያን የሆኑት የጎረቤቱ ሰዎች ለዚህ ሰው አዲስ ስም አወጡለት። ዛሬ ‹‹ዛቡ ጠንቋዩ›› እያሉ አያወሩም፣ ነገር ግን እርሱን ‹‹እንደ እግዚአብሔር የሆነው›› ክርስቲያኑ ብለው ይጠሩታል።

በአሁኑ ጊዜ ከዓለም ተገልላ ባለች በዚያች ሸለቆ ውስጥ በጣም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። ትልቁ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው በዛቡ መሬት ላይ ነው፤ እንዲሁም በአቅራቢያው ነዋሪዎቿ ሁሉ ክርስቲያኖች የሆኑበት አንድ መንደር አለ። በሳምንት ሁለት ጊዜ ክርስቲያኖች በአንድነት ያመልካሉ። ዛቡ ‹‹እንደ እግዚአብሔር የሆነው›› ብለው የሚጠሩት ሰውዬ አሁን የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ሽማግሌ ነው።

በሌላ ሳምንት፣ ዛቡ እና አንዳንድ ወዳጆቹ ሆነው፣ ከዚህ ብቸኛ ከሆነ ሸለቋማ መንደራቸው በመውጣት፣ ኮንሼንሽን (መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኮንፍራንስ) ለመካፈል ወደ ተራራው ለሁለት ቀናት ያህል ተጓዙ። አንድ ቀን፣ ዛቡ ዝማሬውን እንዲመራ ተጠየቀ፤ ለመዘመር የመረጠው መዝሙርም ‹‹እርሱ በቂ ነው። አዳኛችን ኢየሱስ ለሁሉም በቂ ነው›› የሚል ነበር። ከእርሱ ጋር ከመጡት ሰዎች መካከል አንዱ በዚህ ስብሰባ ላይ ኢየሱስን ለመቀበል

በመወሰኑ በጣም ተደስቶ ነበር።።

ዛሬ ወዳጃችን የሆነውን ዛቡን ስናስብ፣ ሁለት ጥያቄዎች ወደ አእምሮአችን ይመጣሉ፣ እነርሱም፤ የማያምኑ ሰዎች በሕይወታችን የሚታየውን ፍቅር፣ ሰላም እና የክርስቶስን ጸጋ ተመልከተው ‹‹እንደ እግዚአብሔር›› ናቸው ብለው ስለ እኛ ያስቡ ይሆን? እንዲሁም መጽሐፉን ለማግኘት ሲል፣ ዛቡ መጽሐፉን ለምን ለሁለት ዓመት ያህል ፈለገ? የሚሉ ናቸው።። ምናልባት እኔም፣ ለክርስቶስ የሚገባውን ያህል ለአዳኜ ራሴን አልሰጠሁም ይሆን? እንዲሁም የመጨረሻ ትእዛዙ የሆነውን ሄጀ ደቀ መዝሙር የማፍራቱን ጉዳይ አልታዘዝሁም ይሆንን? በማለት ስለ ራሳችንም እንጠይቅ ይሆናል።።

‹‹የሕጉን መጽሐፍ በእግዚአብሔር ቤት አግኝቻለሁ።።››

2ኛ ነገሥት 22፡8

‹‹በዚያም ቀን ደንቆሮች የመጽሐፍን ቃል ይሰማሉ፣ የዕውሮችም ዓይኖች ከጭጋግና ከጨለማ ተለይተው ያያሉ።።››

ኢሳይያስ 29፡18

፫

ጴጥሮስ

ማዕከላዊ ምስሶ

ከስከ አሁን ድረስ አልፎ ወደ ኪንዶ የሄደ አንድም የወንጌል መልእክተኛ (ሚስዮናዊ) የለም፡፡ ሁሉም ያቆሙት አፋ ላይ ሲሆን፣ ወደ ተራራው ወደ እኛ አካባቢ ግን መጥተው አያውቁም፡፡ ‹‹አቶ ማክሌላን፣ እርስዎ ወደ ኪንዶ የመጡ የመጀመሪያው ሚስዮናዊ ነዎት፡፡ እባክዎትን፣ ወደ ስብሰባችን መጥተው የእግዚአብሔርን ቃል ያክፍሉን›› በማለት ሁለት ሰዎች ተማጠኑኝ፡፡ እነዚህ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የነበሩ ሲሆን፣ አንደኛው የአንዲት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ፣ ልላኛው ደግሞ ዋና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ነበሩ፡፡ ቀጣናቸው የሆነችው ኪንዶ በአሞ ወንዝ አካባቢ የምትገኝ በጣም ገጠራማ አካባቢ ነች፤ ወደዚያ ተራራማ እና ድንጋያማ መንደር መድረስ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ምንም መንገድ ካለመኖሩ የተነሣ፣ አብዛኛው ጉዞ የሚካሄደው በእግር ወይም በበቅሎ ነበር፡፡

ይህ በዓመት ውስጥ በጣም የሥራ ጫና ያለበት ጊዜ ስለ ነበር፣ ግብዣቸውን ለመቀበል በጣም አቅማማሁ፡፡ በወላይታ ቀጣና ውስጥ በሚገኙ አሥራ አራት ቀጣናዎች ውስጥ በተደረጉ ተከታታይ ስብሰባዎች ላይ በሳምንት አንድ ቀን የእግዚአብሔርን ቃል አካፍል ነበር፡፡ በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ ጌታ በብዙ ባርኮናል፤ የማያምኑ ሰዎች አምነዋል፣ ከእምነታቸው ያፈገፈጉ ሰዎች በንስሓ ተመልሰዋል፣ እንዲሁም ወጣቶች ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አንዳንዶቹ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ ከአካባቢያቸው ውጭ ለመሄድ ራሳቸውን ሰጥተዋል፤ በተጨማሪም፣ ወንጌልን ወደ ተለያዩ ስፍራዎች ለማዳረስ በደስታ ድጋፍ የመስጠት ጊዜ ነበረን፡፡

ከብዙ ጉዞ እና ስብከት የተነሣ ደክሞኝ ነበር፣ ግን ወደ ኪንዶ ለመሄድ

የመጀመሪያ ሚስዮናዊ የመሆን ነገር ደግሞ ሞግቶ ያዘኝ። ከአንድ ሳምንት በኋላ ባለው ቀን ላይ ተስማማን። እስከ መንገድ መጨረሻ ድረስ መኪናዬን እየነዳሁ እሄድና መኪናዬን በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ እተዋታለሁ። እነርሱ እዚያ በቅሎ፣ መሪ እና ዕቃ ተሸካሚ ሰው አዘጋጅተው ይጠብቁኛል። ወደ ተራራው እንወጣና ከኪንዶ ግማሽ መንገድ ርቀት ላይ በሚገኝ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እናድራለን። በሚቀጥለው ቀን ረጅሙን ጉዞአችን በመቀጠል ስብሰባው ይደረጋል ወደ ተባለው ስፍራ እንደርሳለን።

ኪንዶ ስንደርስ፣ በኮርቻ ላይ ብዙ ከመቀመጣችን የተነሣ ብዙ ደክሞናል፣ ግን ደግሞ እዚያ በሰላም ደርሰናል፣ በዚያም ክርስቲያኖች በደስታ ተቀበሉን። ከብዙ ሰዎች ጋር ከተጨባበጥን በኋላ፣ እኔ እና ከእኔ ጋር የመጣው ወንጌላዊ ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ እንድንገባ ግብዣ ቀረበልን። ወንበርም ተዘጋጀልን፤ በቤተ ክርስቲያኒቱ ማዕከል ላይ በሚገኘው ምሰሶ በጀርባዬ መደገፍ ስለ ቻልኩ በጣም ደስ ብሎኝ ነበር። ያለ ምንም ምስማር፣ ቤቱ በጠቅላላ፣ ግድግዳው እና ጣራው እርስ በርሱ በሐረግ ተሳስሯል። ይህ ማዕከላዊ ምሰሶ የቤቱን ሙሉ መዋቅር ይደግፋል።

ከእኛ መምጣት የተነሣ በደስታ ያወሩ የነበሩት ክርስቲያኖች ወሬአቸው በአንድ ሽማግሌ ወደ ጸሎት ቤቱ መምጣት ተቋረጠ። እኚህ ሰው አቶ ዱባለ ናቸው። ሁሉም ሰው ከመቀመጫው በአክብሮት ተነሥቶ እኔን ይገናኙ ዘንድ መንገድ ለቀቁላቸው። እኔም ከመቀመጫዬ በመነሣት ምሰሶውን እንደ ተደገፍሁ ቆሜ ሰውዬውን በመጨበጥ እና በማቀፍ ሰላም አልኋቸው። በእኔ ስፍራ እንዲቀመጡ ጋበዝኋቸው፣ ነገር ግን ግብዣዬን ሳይቀበሉ ከጎኔ ተቀመጡ።

ይህን የመሰለ ክብና ትልቅ ቤተ ክርስቲያን የተገነባበትን ምሰሶ ጉድጓድን ቁፍሮ ለመትከል ብዙ ጠንካራ ሰዎችን ይጠይቃል። የቤተ ክርስቲያኒቱ ቅጥር በቂ በሆነ ሁኔታ ሰፊ እንዲሆን፣ ክርስቲያኖች የተራራውን ግርጌ በመቁፈር በድንጋይ እና በአፈር ደልድለውታል። ለቤተ ክርስቲያኒቱ ማዕከላዊ ምሰሶነት ዛፍ በመቍረጥ አቁመዋል። ይህንን ዛፍ ቤተ ክርስቲያኒቱ ቅጥር ድረስ ጎትቶ ለማምጣት ወደ አርባ የሚሆኑ ሰዎች ተሳትፈዋል። ከዚያም በረጅም ገመድ እና በእንጨቶች በመታገዝ በተቈፈረው ጉድጓድ ውስጥ አቆሙት። በጣም

ከባድ ልፋት ነበር፤ እኔንም ሥራቸውን እንዳደንቅ አስገድዶኛል። በተመሳሳይ መልኩ ደግሞ፣ በአቅራቢያቸው ለጥ ያለ ሜዳ፣ ቀለል ያለ ቦታ እያለ ለምን ይህንን ስፍራ መረጡ ብዬ አስቤያለሁ። በቤተ ክርስቲያኒቱ ዙሪያ የተሠራውን መንገድ እንደገና መሥራት ነበረባቸው።

አቶ ዱባለ ወደ ረጅም ከዘራቸው ወደ ፊት ዘንበል በማለት፣ አንድ ጊዜ ሕዝቡን ቃኘት አደረጉ። ሽማግሌ ሲናገር ሕዝቡ በጸጥታ ያዳምጣል። ‹‹የጆን አባት፣ ነገሩ እንደዚያ አይደለም!›› አሉኝ። (በወላይታ ባህል በትልቁ ልጅ ስም መጠራት የተለመደ ነው።) ‹‹ይቅርታ አድርግልኝ፣ አንተ ወደዚህ ስፍራ ለመምጣት የመጀመሪያው ሚስዮናዊ አይደለህም። አንተ ሁለተኛው ነህ። የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች ወደ ኪንዶ ለመምጣት የመጀመሪያ ሚስዮናዊ እንደ ሆንህ እና ሕዝቡም በደስታ እንደ ተቀበለህ ሰምቻለሁ።››

አርባ እና ሃምሳ ዓመት የሞላቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ሰዎች እየተመለከቱ፣ ‹‹እነዚህ ምንም አያውቁም። ገና ወጣቶች ናቸው። ነገር ግን፣ ከረጅም ጊዜ በፊት ቢያንስ ከሠላሳ ዓመት በፊት ሌውዝ የተባለ ሰው ወደዚህ ስፍራ መጥቶ ነበር። እርሱ በመጣ ጊዜ የነበረውን ሁኔታ አስታውሳለሁ። ነጭ ፈረስ ነበረው። አንተ እና በቅሎህ ዛሬ እንደ መጣችሁት፣ ወደዚህ ተራራ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጣው ሌውዝ የተባለ ሚስዮናዊ ነበር። ሌውዝ በዚህ ስፍራ የቆየው ለአንድ ቀን ብቻ ነበር፤ ከዚያ አካባቢውን የሚያስተዳድረው ጠንቋይ የሆነው አባቴ ከዚህ ስፍራ አባረረው›› ማለታቸውን ቀጠሉ።

አቶ ዱባለ በእጃቸው እጆቼን ይዘው፣ ‹‹የጆን አባት፣›› ብለው ጠሩኝ። ‹‹በእውነት ከሠላሳ አምስት ወይም ከአርባ ዓመታት በፊት ሌውዝ የሚባል ሰው እዚህ መጥቶ ነበር። ያን ጊዜ እኔ በጣም ትንሽ ልጅ ነበርሁ፣ ነገር ግን ሁሉንም ነገር በሚገባ አስታውሰዋለሁ። ሌውዝ ቋንቋችንን በደንብ ተምሮ ነበር፣ እንዲሁም ስለ ኢየሱስ ይነግረን ነበር። ስለ እግዚአብሔር እና ኃጢአት እንዲሁም ስለ ፍርድ ይነግረን ነበር፣ ግን ሊሰሙት የወደዱት በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ነበሩ ። ሁላችንም ፈርተን ነበር። ከዚያ ቀን በፊት ነጭ ሰው ተመልክተን አናውቅም። ጠንቋይ የሆነው አባቴ ሌውዝን እንዳንሰማው ከልክሎናል። ጠንቋዮች ሁሉ ክፉ መናፍስትን በመፍራት ሌውዝን አስፈራርተው አገሩን ለቅቆ እንዲሄድ ነግረውት ነበር፣ ነገር ግን ሌውዝ እየሳቀ

ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን ስለ መስጠቱ ለእነርሱ መናገሩን ቀጠለ፡፡›› ኧርል ሌዊስ (አቶ ዱባለ ሌውዝ ብለው የሚጠሩት) እና ዋልተር ኦህማን በወላይታ አካባቢ የወንጌልን ሥራ ለመሠራት የተሰጡ ከኤስ ኣይ ኤም ጋር ይሠሩ የነበሩ አሜሪካውያን የሆኑ ሚስዮናውያን ነበሩ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በሶዶ ውስጥ አማኞችን ያጠመቁት በ1933 ዓ.ም ነበር፡፡ ስለ ሚስተር ሌዊስ የወላይታ ሕዝብን ይወድድ እንደ ነበረ፣ በወላይታ አካባቢዎች ሁሉ እየተዘዋወረ የክርስቶስን ወንጌል ይሰብክ እንደ ነበር መስማቴን ለአቶ ዱባለ ነገርኧቸው፡፡

አቶ ዱባለም እንዲህ ሲሉ መለሱልኝ፣ ‹‹አዎ፣ የጆን አባት፣ ጠንቋዩ ሌውዝን ቢያስፈራራውም፣ ሌውዝ ግን መሳቁን ቀጥሎ ነበር፡፡ ጠንቋዩም እጅግ በጣም ተናደደ፤ ብዙ ዊስኪም ጠጥቶ ነበር፡፡ እንዲሁም ለረጅም ዓመት በሕዝቡ ላይ ያለውን ሥልጣን ይህ አዲስ ትምህርት ያበላሽብኛል ብሎ ፈርቶ ነበር፡፡ አንዳንድ ሰዎች ከዚህ በፊት ያደርግ እንደ ነበረው ሌውዝን ይገድለዋል ብለው ፈርተው ነበር›› አሉኝ፡፡

እንዲህ ሲሉም ትረካውን ቀጠሉ፡- ‹‹አቶ ሌውዝ ግን አልፈራውም ነበር፡፡ ፈገግታ እያሳየ ዝም ብሎ ይቆም ነበር፡፡ ይህን ጊዜ ጠንቋዩ ይበልጥ እየተናደደ መጣ፡፡ ከዚያም ጠንቋዩ እጁን ዘርግቶ ሌውዝን ፊቱ ላይ መታው፡፡ ሁላችንም በጣም ደነገጥን - ድርጊቱ በጣም አሳፋሪ ነበር- እንግዳን፣ ለአገሩ እንግዳ የሆነን ሰው መምታት የማይታሰብ ነገር ነበር፤ ይህ ነገር ከባህላችን ጋር ፈጽሞ ሊሄድ የማይችል ነገር ነበር፡፡ እርሱ ባደረገው ነገር እኛ በጣም ደንግጠናል አፍረንማል›› አሉ፡፡

‹‹ከዚያም ሚስተር ሌውዝ በአፍንጫው እና በአፉ ያልተጠበቀ ደም ይፈስሰው ጀመር፡፡ የሰውዬው ቡጢ ያልጠበቀው መሆኑና በቡጢው ጥንካሬ ተገርሟል፤ ለመውደቅ ወደ ኋላ ተንገዳግዶ ነበር፤ እንደገና ተስተካክሎ ለመቆም ጥረት አደረገ፡፡ ደም ከአፍንጫው እና ከተሰነጠቀው ከንፈሩ ውስጥ እንደ ጉድ ይፈስስ ነበር፡፡ በእጆቹ እና በጉልበቱ በመሬት ላይ ተንበረከኮ ደሙ አቧራ በሞላው መንገድ ላይ እየተንጠባጠበ ክብ ክብ ቅርጽ ይሠራ ነበር፡፡

እዚያው ተንበርክኮ እያለ፣ ትንሽ ራሱን ለማረጋጋት ሙከራ ካደረገ በኋላ ሌውዝ እንዲህ ሲል በወላይትኛ ቋንቋ ጸለየ፡- ‘ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ዛሬ ስለ አንተ

መከራን መቀበል በመቻሌ ደስተኛ ነኝ። ምን እንደሚያደርጉ አያውቁምና ይቅር በላቸው። ጌታ ሆይ፣ ዛሬ ይህንን ስፍራ፣ ደሜ የፈሰሰበትን ይህንን ቦታ በእምነት ለአንተ አውጀለሁ' አለ። ከዚያም አቶ ሌውዝ ፈረሱ ላይ መውጣት እንዲችል ሰዎች አገዙት። ይህንንም ስፍራም ለቅቆ ወጣ፤ እንደገና ያንን አካባቢ ተመልሶ መጐብኘት አልቻለም።

አቶ ዱባለ እጃቸውን በትከሻዬ ላይ አድርገው እንዲህ ብለው በድጋሚ ተናገሩ፣ ‹‹የጆን አባት፣ እዚህ ሁለተኛው የወንጌል መልእክተኛ ሆነው እንኳን ደህና መጡ። ብዙ ዘመናት መጠበቅ ነበረብን፣ ነገር ግን ከዓመታት በኋላ የሆኑ ሰዎች ወንጌሉን ይዘው በተራራው ላይ መጡ፣ እኛም ደግሞ በኢየሱስ አመንን። እነዚያ ሰዎች ስለ ጌታ፣ ኃጢአት፣ ንስሐ እና ደኅንነት ሌውዝ ሊነግሩን የሞከሩትን ዓይነት ተመሳሳይ መልእክት ይዘው መምጣታቸውን አስታውሳለሁ። ለዚያም ነው ይህንን የመጀመሪያ የጸሎት ቤት እዚህ ቦታ ላይ የሠራነው። ይህ መካከለኛው ምሰሶ እዚህ ጋ የተተከለው ሌውዝ ደማቸውን ያፈሰሱበትና ስፍራውን ለኢየሱስ እንዲሆን ያወጁበት ስፍራ ስለሆነ ነው።››

‹‹እኔ በአድናቆት ስጮኽ ይህች ቤተ ክርስቲያን ለምን በመንገድ መሀል ላይ እንደ ተሠራች የማያውቁት ከእኔ ጋር የመጡት ሰዎች፣ ለእግዚአብሔር ምስጋናን በታላቅ ጭብጨባ መስጠት ጀመሩ። እግዚአብሔር ስላደረገው ታላቅ ነገር ተንበርክከን ምስጋናን ሰጠን። የኧርል ሌዊስ ጸሎት ምላሽን አግኝቷል!›› አሉ አቶ ዱባለ።

ወንጌላውያን ወንጌልን ወደ ስፍራው ይዘው ሲመጡ፣ የጠንቋዮቹ ኃይል እንደ ተሰበረና አብዛኞቹም የኦሞን ወንዝ ተሻገረው እንደ ሸሹ አቶ ዱባለ ነገሩን። ወንጌልን ለመቀበል አቶ ዱባለ የመጀመሪያው ሰው ሲሆኑ፣ አካባቢውንም በማሳየት ወንጌላውያኑን ማገዛቸውን ወዲያው ነበር የጀመሩት። በአቶ ዱባለ ሕይወት የታየው ለውጥ፣ ብዙ ሰዎች ምስክርነታቸውን እንዲሰሙና እርሳቸውን ያዳነውን ጌታ ለመቀበል ፈቃደኞች እንዲሆኑ አድርጓል።

ෛ

በሦስቱ ቀናት ስብሰባ ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ለሰዓታት የእግዚአብሔር ቃል ያደምጡና ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና መልካምነት ይዘምሩ

ነበር፡፡ በዚህም ስብሳባ ላይ በጣም ብዙ ሰዎች ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው እና ጌታቸው አድርገው ተቀበሉት፤ ሦስቱም ቀናት የደስታ ቀናት ነበሩ፡፡ አዲስ በተከፈተው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው ለመማር ብዙ ወጣቶች ቃል ገቡ፡፡

በአሁን ሰዓት በአካባቢው ሠላሳ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ፤ ቁጥሩም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው፡፡ ትምህርት ቤቶች ተገንብተዋል፤ ብዙ ሰዎችም ወደ ክርስቶስ ተመልሰዋል፡፡ ጳውሎስ የሚባለው የአቶ ዱባለ ወንድ ልጅ እጅግ በጣም ጎበዝ ተማሪ የነበረ ሲሆን፣ በሶዶ ሆስፒታል እና በአዲስ አበባ ተምሯል፡፡ ጳውሎስ ወደ ኢትዮጵያ ጌታን ለማገልገል ከመምጣቱ በፊት በሃዋይ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ነፃ የትምህርት ዕድል አግኝቶ የዶክትሬት ዲግሪውን አግኝቷል፡፡

በእግዚአብሔር ምሪት መሠረት፣ ወንጌላውያኑ ሩቅ ወደ ሆኑት አካባቢዎች ይሄዳሉ ወይም በአንዲት አጥቢያ ውስጥ መጋቢ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ መንገድ፣ ትምህርት ቤት እና ክሊኒኮች እየተገነቡ ሲሄዱ የኪንዶ ኤኮኖሚ ፈጽሞ ተለወጠ፤ ብዙ ሰዎችም ማንበብ እና መጻፍ ጀመሩ፡፡ ክብር ለጌታ ይሁን!

ለጌታ ልዩ መልእክተኞች ስለ ሆኑት ስለ ሚስዮናዊው ኧርል ሌዊስ እና የበጐ ፈቃድ አገልጋይ የሆኑት ስለ አቶ ዱባለ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፡፡ እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች በመጠቀም መንፈሳዊ ጨለማ ሰፍኖበት በነበረው አካባቢ ላይ የወንጌልን ብርሃን እንዲበራ አድርጓል፡፡ ይህ ጨለማ ለብዙ ዘመናት በወላይታ ምዕራብ አካባቢ በሚገኙ ቦታዎች ላይ ሰፍኖ የኖረ ነበር፡፡

‹‹አሕዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በሥራ፣ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል፣ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእኔ አድርጎ ከሠራው በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም፤ ስለዚህ ከኢየሩሳሌም ጀምሬ እስከ እልዋሪቆን ድረስ እየዞርሁ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ፤ ሰብኬአለሁ፡፡ እንዲሁም በሌላው ሰው መሠረት ላይ እንዳልሠራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ሰፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ. . .››

ሮሜ 15፡18-20

፬

ጅግሬ

ትንቢቱ ተፈጸመ

ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ምግባችንን ተመግበን ከጨረስን በኋላ፣ ጅግሬ ከጎጆ ቤቱ ይዞኝ በመውጣት ከቤተ ክርስቲያኑ ፊት ለፊት ወደሚገኘው ሜዳ ወሰደኝ። ቀድሞውኑ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በዚያ ተሰብስበው ነበር። ከሁሉም አቅጣጫ ደግሞ ብዙ ሰዎች ወደ ስፍራው በመትመም ላይ ነበሩ። በጥቂት ጊዜ ውስጥም ያ ሜዳ በደስታ በተሞሉ፣ በሚያዜሙና እርስ በርሳቸው በሚያወሩ ሰዎች ተሞላ። ብዙዎች ጓደኞቻቸውን እና ጎረቤቶቻቸውን የወንጌል መልእክት መስማት ይችሉ ዘንድ ወደዚህ ልዩ ጉባኤ ይዘው መጥተዋል። ለረጅም ዓመታት ከኖሩበት መንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ ጓደኞቻቸው እና ዘመዶቻቸው እንዲወጡ ክርስቲያኖች ስላላቸው ፍላጎትና ጽኑ መሻት እግዚአብሔርን አመሰገንሁ።

ጅግሬ እጄን ይዞ እየጎተተ ወደ አንድ ያረጀ፣ በጣም ትልቅ የሆነ የባሕር ዛፍ ወሰደኝ። ‹‹ይህ መጽሐፍ ቅዱስን ይዞ የተቀመጠበትና ድንኳኑን የተከለበት ስፍራ ነበር›› አለኝ፣ በአገጩ በሦስት ዛፎች መካከል ያለውን ትንሽ ቦታ እያሳየኝ። ‹‹አስበው እስቲ›› አለኝ። ‹‹ይህ ስፍራ ሰይጣንን የምናመልክበትና ለእርሱ የምንደንስበት ቦታ ነበር፤ ክፉ የሆኑ መናፍስቶችንና የአያት ቅድመ-አያቶቻችን መንፈስ ለማስደሰት መሥዋዕት የምናቀርብበት ቦታ ነበር። ይህ አያቴ ለወደፊት ስለሚሆነው ነገር ትንቢት የተናገረበት ስፍራ ነው። አሁን ግን እግዚአብሔር ይመስገን፣ ጌታችንን ለማምለክና ከኃጢአት ዋጅቶ ከጨለማ ላወጣን ለክርስቶስ የምስጋናን መሥዋዕት ለማቅረብ ተሰብስበናል።

ነጩ ሰው ወደ መንደሩ ሲደርስ ለዓይን ያዝ ማድረግ ጀምሮ ነበር። የፈረሱን ልጓም ያዘ አድርጎ ካቆመው በኋላ ኮርቻውን ማውረድ ጀመረ። እንደ ምን አመሻችሁ ብሉ ሰላምታ ሰጠ፣ ነገር ግን ማንም መልስ አልሰጠውም። ለረጅም ሰዓታት ፈረስ በመጋለቡ ምክንያት ሰውነቱ ጓጉሏል፤ ስለዚህም እየተንጠራራ ሰውነቱን እያፍታታ ተበታትነው ያሉትን ጎጆ ቤቶች በዓይኑ ቃኛቸው። ከዚያም የእርሱ ሠራተኛ ዕቃ የጫነች በቅሎ ይዞ መጣ፤ ሁለቱም ሰላም ተባባሉ። የመንደሩ ሰዎች ሁሉ ፈርተው ስለ ነበር ማንም ሰው ምላሽ አልሰጣቸውም፤ ሁሉም በየመኖሪያ ጎጆዋቸው ውስጥ ተደብቀው ነበር። ከዚህ በፊት ነጭ ሰው አይተው አያውቁም። በቤቱ ግድግዳ ውስጥ በሚገኙት ቀዳዳዎች እንግዳውን ሰው አሾልቀው እየተመለከቱ ሴቶቹ ልጆቻቸውን በጸጥታ እንዲቀመጡ ያደርጉ ነበር። ነጩ ሰውዬ እንደገና ‹‹ሰሮ፣ ሰሮ›› (ሰላም፣ ሰላም) ሲል እንደ ገና ተጣራ፤ ከዚያም ከፈረሱ ላይ ኮርቻውን አወረደ። ፈረሱ ከሸክሙ ነፃ በመሆኑ ተደሰቶ በመሬት ላይ መንከባለል ጀመረ።

የመንደሩ ነዋሪዎች መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ሆነው አዲሱን፣ ነጩን ሰውዬ በቀዳዳ በአንከሮ ይመለከቱታል። በባህላቸው መሠረት አዲስ ሰው ሲመጣ ማስተናገድ የተለመደ ነበር። ብዙ ጊዜ፣ ማታ ማታ በእሳት ዙሪያ ሆነው ሲጫወቱ፣ በሌላ ስፍራ ስላሉ ሰዎች እና በዚያ ምን እንደሚደረግ የሚያወሱ ብዙ ታሪኮች አሏዋቸው። ይኼኛው ግን የተለየ ነበር። ሰውዬው ነጭ ነው! ወደ ሶዶ ነጫጭ ሰዎች መጥተው እንደ ነበር ከዚህ በፊት የወሬ ወሬ ሰምተዋል፣ ነገር ግን ከእነርሱ ጋር ተገናኝቶ የሚያውቅ ማንም ሰው የለም። ሶዶ ከተራራው በኩል የምትገኝ ከተማ ናት። ይህ ተራራ የዳሞት ተራራ የሚባል ሲሆን፣ 10,00 ጫማ (3048 ሜትር) ከፍታ ሲኖረው፣ በወላይታ አውራጃ መሀል ላይ ይገኛል፣ ዋና ዋና የሚባሉት የገጠር ከተሞች ከዚህ ተራራ በሃምሳ ኪሎ ሜትር ክልል ውስጥ ርቀው ይገኛሉ። እንግዶቹ ዕቃቸውን ከጫኑባት በቅሎ ማውረዳቸውን ሲመለከቱ፣ በዚህ መንደር ማደር እንደ ፈለጉ ተረዱ።

በመጨረሻም አንድ ሰው በድፍረት እንግዶቹን ለማነጋገር ወደ እርሱ መጣ። ጅግሬ ፈርቶ ስለ ነበር ከእነርሱ ትንሽ ርቀት ላይ ቆመ፣ ነገር ግን *‹‹ሰላም፣ ሰላም››* አላቸው። ነጩ ሰውዬ በእርጋታ፣ በቀላሉ የወላይታን ቋንቋ ሲናገር በመስማቱ እጅግ በጣም ተደነቀ። በመንደሩ ውስጥ ማደር ይቻል እንደ

ሆነ ጠየቀው፡፡ ጅግሬ እንግዶቹን ተቀበላቸው፡፡ ‹‹አዎ›› ለማለትና ሁልጊዜ ለተጓጉች መስተንግዶን እንደሚያደርገው (ይህ ባህል ነው) እንግዶችን ወደ ቤቱ ለመውሰድ ፈልጎ ነበር፤ ነገር ግን ቤቱ ንጹሕ አልነበረም፣ እንዲሁም መኖሪያ ቤቱ በቤተሰቡ አባላት እና በከብቶቻቸው ተጣብቦ ነበር፡፡ መኖሪያ ቤቱ ከውጭ አገር ለመጣ እንግዳ የማይስማማ መሆኑን በደመነፍስ ያወቀ ይመስላል፡፡ ጅግሬ በውስጡ ተሸበረ፡፡ ነጭ ሰው በነጭ ፈረስ ላይ! ይህ በጣም ያሳሰበው ነገር ነበር፡፡ የሚያስገርም ነው! ይህ የተባለው ነገር ይሆንን? ሚስዮናዊው ጥቁር ፈረስ ለመግዛት ተስማምቶ ገንዘቡን ለመክፈል ሲሄድ ጌታ ነጭ ፈረስ እንዲገዛ እንደ ነገረው ጅግሬ የሚያውቀው ነገር አልነበረም፡፡

ሚስዮናዊው የጅግሬን ስጋት ተረድቶ እንዲህ አለው፡- ‹‹የማድርበትን ቤት ይገፎ መጥቻለሁ፡፡›› ይህን ያለበት ምክንያት በእነርሱ አገር ቋንቋ ድንኳን ምን እንደሚባል ባለማወቁ ነበር፡፡ ‹‹በእነዚህ ዛፎች መካከል አቆመዋለሁ›› አለ፡፡ ሦስት ትላልቅ ዛፎች በሦስትዮሽ ጎን ቆመዋል፡፡ ጅግሬ የሚናገረው ነገር ጠፋው! ሚስዮናዊው እና ረዳቱ ድንኳናቸውን በፍጥነት ሲተክሉ፣ የምግብ ሣጥናቸውን እና መኝታቸውን ወደ ውስጥ ሲያስገቡ፣ ጭንቅላቱን ከፍ እና ዝቅ አድርጎ መነቅነቅ፣ መመልከት እና መደነቅ ብቻ ነበር ጅግሬ ማድረግ የቻለው፡፡ በዚህ ጊዜ ብዙ ሰዎች ይህንን አዲስ ነገር ለመመልከት ወደ ጅግሬና ወደ አዳዲሶቹ ሰዎች መጡ፡፡ የመንደሩ ሰዎች እርስ በርሳቸው እየተነጋገሩ ወደ እንግዶቹ ይበልጥ እየቀረቡ መጡ፡፡

ከመንደሩ ነዋሪዎች አንዳንዶቹ እንደ ሰዎቹ ሁሉ የፈረሱ መልክም ትኩረታቸውን ሳባቸው፡፡ እንዲህ ያለ ቀለም ያለው ፈረስ በወላይታ የማይታወቅ ቢሆንም፣ በብዛት የሚታይ አይደለም፡፡ ሚስዮናዊው፣ ታጣፊ አልጋውን ከዘረጋ በኋላ፣ ውኃ ይሰጡት እንደ ሆነ ጠየቃቸው፡፡ ጅግሬ በፍጥነት በሸክላ ሳሕን ንጹሕ ውኃ አመጣለት፡፡ በዚህ ጊዜ እየጨለመ በመሆኑ ጅግሬ የሚስዮናዊውን ረዳት እና ፈረሱን ወደ መኖሪያ ቤቱ ይዟቸው ሄደ፡፡ ምሽት ላይ የሚስዮናዊው ረዳት፣ ገብሬ ስለ ነጩ ሰውዬ ብዙ ጥያቄ ተጠየቀ፤ እርሱም በሶዶ ውስጥ ነጮች ሰዎች በሠሩት መኖሪያ ቤቶች እና ሆስፒታሎች በከተማዋ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ እየተደነቁ መሆኑን ነገራቸው፡፡

በሚቀጥለው ቀን ማለዳ ላይ፣ ሚስዮናዊው ታጣፊ መቀመጫውን ይዞ

ፀሐይ ለመሞቅና የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሱን ለማንበብ ወደ ድንኳኑ ደጃፍ ወጣ። ዓይኖቹንም ከፍቶ ሲመለከት፣ እርሱን ለማየት የመጣ የከተማውን ሕዝብ ብዛት ሲያይ እጅግ በጣም ተገረመ፤ ከዚያም ሰላም ብሎአቸው መጽሐፍ ቅዱሱን ከፍቶ ማንበብ ጀመረ። ከዚህ በፊት መጽሐፍ፣ እንደዚህ ብዙ ገጾች ያሉት የሚገለጥ ነገር መሆኑን አይተው በማያውቁ ሰዎች መካከል ትልቅ መነጋገሪያ ርእስ ሆነ። የነገሩን ምንነት ቀርበው ለመመልከት ይበልጥ እየቀረቡ መጡ፤ ከዚያም ጅግሬ ለእንግዳው በቂ ስፍራ ይሰጡ ዘንድ ወደ ኋላ እንዲያፈገፍጉ አደረጋቸው።

ሚስዮናዊው መጽሐፍ ቅዱስ በወላይታ ቋንቋ ተተርጕሞ እስኪደርሳቸው ድረስ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ እያሰበ ኢየሱስ ሕመምተኛውን ሰውዬ እንዴት እንደ ፈወሰ አንብቦላቸው ወደ ወላይታ ቋንቋ ተረጕመላቸው። ጅግሬ ከዚህ በፊት ስለ ኢየሱስ ሰምቶ ባለማወቁ፣ ይህ ሰው ማን ይሆን ሲል ጠየቀ። ሁሉም የሚሉትን ነገር አጥተው ሳለ፣ ጅግሬ ይበልጥ ለመስማት እንደሚፈልግ ተናገረ። በዚህ ወቅት የሚስዮናዊው ረዳት ፈረሱን ሌሊቱን በሙሉ ብዙ ገብስ ሲበላ ካደረበት ቦታ ይዞት መጣ። የጅግሬ ሚስት ለእንግዶቹ ቍርስ የሚሆን የተፈላ የጀበና ቡናና ቆሎ ይዛ መጣች። እንደገና እንግዶቹ ምግብ ከመብላታቸው በፊት አንገታቸውን አቀርቅረው ዓይናቸውን ሲጨፍኑ በመመልከታቸው ተደነቁ። ይህም ለእነርሱ አዲስ ነገር ነበር!

ሚስዮናዊው በተራራው አካባቢ ቅኝት ለማድረግ ዐቅዶ ስለ ነበር በዕቅዱ መሠረት ለመሄድ ፍላጎት አደረበት፤ ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን የሰው ቍጥር እና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ለመስማት ያላቸውን ጕጉት በመመልከቱ፣ አሳቡን በመለወጥ የጥዋቱን ጊዜ ከእነርሱ ጋር ለማሳለፍ ወሰነ። ስለ እግዚአብሔር ቅድስናና፣ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ስለ ማመፃቸው፣ ኃጢአት እግዚአብሔርንና ሰውን እንዳለያየ፣ የጠፉትን የሰው ልጆችን ከራሱ ጋር ለማስታረቅ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እንደ ላከ፣ ኢየሱስ በመስቀል ላይ የመሥዋዕትነት ሞት ሞቶ እዳችንን እንደ ከፈለ፣ ኢየሱስ ከሞት በመነሣቱ እንዲሁም ወደ ሰማይ በማረጉ ሰይጣንን እና ሞትን እንዳሸነፈ፣ እንዲሁም ለሚያምኑት ሁሉ እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር እንደሚል ነገራቸው።

ሁሉም ነገር ለእነርሱ አዲስ በመሆኑና ቋንቋ በደንብ ባለመቻላቸው ምክንያት በጣም ብዙ ነገሮች ለመረዳት አስቸጋሪ ሆኖባቸው ነበር። ነገር ግን፣

የጅግሬ ልብ ይበልጥ ለማወቅ በመጓጓቱ ከፍተኛ ፍላጎት አደረበት፡፡ ወደ ሶዶ ለመሄድ እና ይበልጥ ለማወቅ ወሰነ፡፡ ሚስዮናዊው ከሰዓት በኋላ ከሄደ ከረጅም ጊዜ በኋላ የመንደሩ ሰዎች ሰውዬው ስለ ነገራቸው ነገር በሰፊው እርስ በርሳቸው እየተነጋገሩ፣ ‹‹ነገሩ እውነት ይሆንን?›› እያሉ እርስ በርሳቸው ተጠያየቁ፡፡

ጅግሬ ይህ ሚስዮናዊ ኧርል ሌዊስ እንደ ሆነ እርግጠኛ ሲሆን፣ ነገር ግን የእርሱ ወንድም ደግሞ ዋልተር ኦህማን ወይም ዶ/ር ሆፐር ነው ይላል፡፡ የሁሉም መልክ የሚመሳሰል አይደለምን? በማለትም ተነጋገሩ፡፡ የወንጌል መልእክተኛው (ሚስዮናዊው) ማን መሆኑ ይህንን ያህል ጠቃሚ አልነበረም፡፡ ዋናው ነገር እግዚአብሔር ይህንን ሰው ወደዚህ ስፍራ መምራቱና እንደ ታማኝ መልእክተኛ የወንጌልን መልእክት ማስተላለፉ ነበር፡፡

ይህ

ታይለኛ ጠንቋይ የነበረው የጅግሬ አያት ሊሞት በተቃረበበት ሰዓት ለቤተሰቡ ስለ አንድ ራእይ (ሕልም) እንዲህ ሲል ነግሯቸው ነበር ፡- ‹‹አንድ ቀን፣›› በማለት ትንቢት ተናገረ፡፡ ‹‹በነጭ ፈረስ ላይ ሆኖ ነጭ ሰው ይመጣል፡፡ በሦስቱ ዛፎች መካከል ድንኳኑን ይተክላል፤ በሚቀጥለው ቀን ድንኳኑን ያፈርሳል፡፡ በእጆቹም የሕይወት መጽሐፍ ይይዛል፡፡ ይህ ሊከተሉት የሚገባ እውነተኛ መንገድ ነው፡፡››

ጅግሬ መልሶ አያቱ አስቀድመው ስለ ተናገሩት ነገር አሰላሰለ፣ ይህንን ዘላለማዊ ሕይወት ይኖረው ዘንድም በጣም ፈለገ፡፡ ጅግሬ ወንድሙ ከእርሱ ጋር ወደ ሶዶ እንዲሄድ አሳመነው፡፡ በጠዋት ተነሥተው፣ ጦሮቻቸውን፣ የአደን ጩቤዎቻቸውን እና ያለ እርሾ የተጋገረውን ዳቦ የሚይዙበትን ቦርሳ በመያዝ ጉዞ ጀመሩ፡፡ ጅግሬ ጠንቋይ የነበሩት አያቱ ‹‹ከከፉ ዓይን›› ይሠውረው ዘንድ የሰጡትን የተጠቀለለ ቅጠል በቦርሳው ውስጥ ይዟል፡፡ በነጮች ሰዎች ዘንድ ምን ዓይነት አደጋ ሊደርሰበት እንደሚችል ምንም የሚያውቀው የለም፡፡

ወደ ሶዶ ከተማ አቅራቢያ፣ አቶና ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ ቀኑልቀኑለት ላይ የተለያዩ ሥራዎች ሲሠሩ ተመለከቱ፤ ወዲያውም ደግሞ ሚስዮናውያንን አገኙ፡፡ ለራሳቸው በሣር የተሠራ መኖሪያ ቤት ገንብተዋል፡፡

እንዲሁም የታመሙ ሰዎች መጥተው የሚታከሙበትን ክሊኒክ እና ሆስፒታል በመገንባት ሥራ ተጠምደዋል። ለጥቂት ቀናት ያህል ጅግሬ እና ወንድሙ እንዲሁም በአካባቢው ካሉ ሰዎች ጋር በቅርብ ርቀት ሆነው ሚስዮናውያኑ እንጨት ሲቈርጡ ወይም ለግንባታው አፈር ሲያቦኩ እየተመለከቱ ቆዩ። በእያንዳንዱ ዕለት ማለዳ ላይ ሚስዮናዊው ሰውዬ ለሠራተኞች የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ሲነግራቸው አደመጡ። ሁሉም ነገር ያልተለመደ እና ልዩ ሆኖ አገኙት- እውነት ከሆነ፣ ጥሩ ነው ብለው አሰቡ። ጅግሬ እና ወንድሙ የሰሙትን ነገር አመኑ፣ ግን ወዲያው ወደ ቀያቸው ተመለሱ። ማንም ሰው ስለ ምንም ነገር ሳያስተምራቸው እንደ ቀድሞው መኖር ቀጠሉ። ዳሩ ግን መንፈሳዊ ጥማታቸው መርካት አለበት።

ꕥ

ሁሉም ሚስዮናውያን በጣልያን ወረራ ጊዜ አገሪቱን ለቅቀው እንዲወጡ በተደረገበት ወቅት በሶዶ ውስጥ ቆጥራቸው በጣም ትንሽ የሆኑ አማኞች ተጠምቀው ነበር። እግዚአብሔር እነዚህን አዳዲስ አማኞችን ሌሎችን በወንጌል ለመድረስ ተጠቀመባቸው። ደኅንነት የሚገኝበትን ወንጌል በወላይታ አካባቢ ባሉ መንደሮች ሁሉ እየተዘዋወሩ አዳረሱ። እነዚህ ወንጌላውያን እነ ጅግሬ መንደር ሲደርሱ፣ ጅግሬ እና ሌሎች ብዙ ሰዎች ሰይጣንን በመካድ በደስታ አዳኛቸው ኢየሱስ ክርስቶስን ተቀበሉ። ከዚያም በአካባቢው የመጀመሪያ የጸሎት ቤት ተመሠረተ።

ምንም እንኳ ተቃውሞው እና ስደቱ እጅግ በጣም የጸና ቢሆንም፣ አማኞች በእምነታቸው እያደጉ ሄዱ፤ በትምህርትም እየጠነከሩ ሲሄዱ፣ አጎራባች ወደ ሆኑ መንደሮች በመሄድ ወንጌልን መናገር ጀመሩ። ጅግሬ መሪያቸው እንዲሆን ተመረጠ። ባለው የወንጌላዊነት ቅንዓት ወደ ሁሉም ስፍራዎች እየሄደ ወንጌልን እየሰበከ ለክርስቶስ ነፍሳትን ይማርክ ነበር። በፍጥነትም በአካባቢው ባሉ መንደሮች ውስጥ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ጸሎት ቤቶች ተከፈቱ። ጅግሬ ለብዙ ሰዎች እንዴት አምልኮን መምራት እንደሚችሉ ሥልጠና ይሰጥ ነበር። ጅግሬ በጣሊያናውያን እንዲሁም በኦርቶዶክስ መሪዎች ተደብድቧል፣ ደግሞም ለእስር ተዳርጓል፣ ግን ጠላት ይበልጥ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ጥረት ሲያደረግ፣ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ይበልጥ ማበብ ጀመረች። ጅግሬ በዚያ

አካባቢ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ዓመታት በታማኝነት ሲመራ ቆይቷል።

ෛ

በሺህዎች የሚቈጠሩ የሰዎችን ስብስብ እየተመለከትን ሳለ፣ ጅግሬ ወደ ስኳር ድንች እና በቆሎ ማሳ እያሳየ እንዲህ አለኝ፡- ‹‹አያቴ እንዲህ ብሎኝ ነበር፡- ‘ነጩ ሰውዬ በነጭ ፈረስ ከመጣ በኋላ በዚህ ማሳ ውስጥ ትልቅ ቤት ይሠራል፤ ብዙ ወጣት ወንዶች እና ሴቶች ወደዚህ ቤት ይገባሉ እንዲሁም ይወጣሉ’ ነገር ግን ይህ አልተፈጸመም። ስለዚህ ማሳውን ለመሸጥ ፈቃደኛ አልሆነም።››

በሕዝቡ ፊት ለመሆን ወደ መድረኩ እያመራን ሳለን፣ ሕዝቡን ስመለከተው በታላቅ ድምፅ ‹‹ኢየሱስን እንከተላለን›› እያለ ያዜማል። ጅግሬን እንዲህ አልሁት፡- ‹‹እግዚአብሔርን ልናምነው ይገባል፣ እንዲሁም መጸለያችንን መቀጠል አለብን። ምናልባት በሚቀጥለው ዓመት ወይም ከዚህ በኋላ ይህ ነገር ይከሰት ይሆናል›› አልሁት።

ያ ቀን ምንኛ አስደሳች ቀን ነበር! የእግዚአብሔር ቃል ተሰበከ፣ በኋላም በጣም ብዙ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን ለመቀበል እጃቸውን አነሡ። በሰዎች ሁሉ ፊት ሆነው ሰይጣንን እና ሥራዎቹን ሁሉ ካዱ። ‹‹ሁለት እጃቸውን እንደ ተማረከ ሰው ወደ ላይ ከፍ በማድረግ›› አዳኛቸውን ጌታቸው አድርገው ተቀበሉት። የእግዚአብሔር ስም የከበረበት አስደናቂ ቀን ነበረ። እኛም እንዴት እርሱን ማመስገን ይገባን ይሆን!

ෛ

ከጥቂት ዓመታት በኋላ፣ ጅግሬ በዓመታዊ ጉባኤያቸው ላይ እንድሰብክ ጋበዘኝ። ‹‹መጥተህ ማየት የሚገባህ ነገር አለ፣›› በማለት ጮተጮተኝ። ወደ ስፍራው እንደ ደረስሁም፣ በደስታ ተሞልቶ በቍጥቋጦ ውስጥ እየመራኝ እየተስተካከለ ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ አዲስ መሬት ወሰደኝ። ‹‹ያንን ስፍራ ተመልከተው›› አለኝ።

ቀድሞ የስኳር ድንችና የበቆሎ ማሳ የነበረበት ቦታ አሁን ትልቅ ባለ ቆርቆሮ ቤት ተሠርቶበታል። አራት በሮች እና ስድስት መስኮቶች ያሉት ረጅም ቤት

ነው፡፡ ቤቱ የተሠራው አዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለመጀመር ነበር፡፡ ወጣት ወንዶች እና ሴቶች በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታቸውን ይከታተላሉ፡፡ ጅግሬ በደስታ ጨፈረ!

ከጥቂት ወራት በፊት ጅግሬ እንዲህ ሲል ነገረኝ፡- ‹‹የዚህ ማሳ ባለቤት በድንገት ሞተ፡፡ ይህ ሰው ብዙ ዕዳ ነበረበትና ልጆቹ ዕዳውን ለመክፈል መሬቱን መሸጥ ፈለጉ፡፡ በእኛ ባህል መሠረት አንድ ሰው ዕዳውን ሳይከፍል መሞቱ ነውር ነው፣ ስለዚህም እኛ እንደ ቤተ ክርስቲያን መሬቱን ከእርሱ በመግዛት ሰዎቹን ልንረዳቸው ደስተኞች ሆንን፡፡ አሁን የዚህ ቤተሰብ ወጣት ልጆች በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ይማራሉ›› አለኝ፡፡

ጅግሬ በጣም እንደ ተደሰተ ምንም ጥርጥር አልነበረውም፡፡ የተነገረው ትንቢት ተፈጽሟል፡፡ በአካባቢው ላይ ያለው የሰይጣን ቀንበር ተሰብሯል፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ከብሯል! በእግዚአብሔር መልካምነት ሐሤት እናደርጋለን፣ እንዲሁም ጌታችንን ደጋግመን እናመሰግነዋለን! እናንተም ምስጋናችሁን ጨምሩለት!

> *‹‹ነገር ግን ተነሣና በእግርህ ቁም፤ ስለዚህ እኔን ባየህበት ነገር ለአንተም በምታይበት ነገር አገልጋይና ምስክር ትሆን ዘንድ ልሾምህ ታይቼልሃለሁና። የኃጢአትንም ስርየት በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ፣ ከሕዝቡና ወደ እነርሱ ከምልክህ ከአሕዛብ አድንሃለሁ።››*
>
> የሐዋ. 26፡16-18

5

ጣልያኖች

እስከ መጨረሻ የሚጸና ጓደኝነት

ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት ዋንዳሮ፣ ዳና መጃ የተባለውን ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ እንዲያምን ሲያደረግ ይህ ነገር ምን ዓይነት አስገራሚ ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል ማንም ሰው አልገመተም ነበር። ይህ ውጤት ዛሬም ድረስ ቀጣይነት ያለው ነው። የመሪያቸው ሕይወት መለወጡ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሕይወት ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ፈጥሯል። ዳና መጃ ከዚህ በፊት የሸጣቸውን እና የገዛቸውን ባሪያዎቹን አስታወሰ። በእርሱ መሬት ላይ የሚገኙ ‹‹አሽከሮች›› ሁሉ የራሳቸውን ንብረት እንዲወስዱ ተደርገዋል። ወጣቶችም ሁሉ ማንበብ እና መጻፍ እንዲችሉ አበረታቷል፣ እንዲሁም አንድ ወጣት ልጅ በእርሱ መሬት ላይ ትንሽ ትምህርት ቤት እንዲከፍት ፈቅዶለታል።

ባሎቲ ማንበብ እና መጻፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የቻለች የወላይታ ሴት ናት። የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ እና ታሪኮቹን ለሌሎች ማካፈል ትወድዳለች። ኦሞቼ የተባለው ልጅ በአነር የተጠቃው ከብቶችን በሚጠብቅበት ወቅት ነበር። ከደረሰበት ጉዳት መትረፍ ቢችልም፣ ይህ ጉዳት በቀኝ ዓይኑ አካበቢ ትልቅ ጠባሳ ትቶበት አልፏል። እርሱም ማንበብ እና መጻፍ ተምሯል፣ እንዲሁም ለሌሎች ሰዎች እምነቱን ማካፈል ይወድዳል።

ቆንጆ፣ ፈጣን፣ ፎልፋላ የሆነችው ባሎቲ፤ ዝምተኛ፣ ቀጭበ፣ እንዲሁም ትልቅ ጠባሳ ያለበትን ኦሞቼን ለማግባት ስትስማማ ብዙዎች በሁኔታው በጣም ተገርመዋል። ኦሞቼ በቀጣናዎች እየተዘዋወረ የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰብክ፣ ባሎቲ ደግሞ ትላልቅ ሴቶችን እና ልጃገረዶችን በክፍል ውስጥ ታስተምራለች።

ልጃቸው ፔርሲስ ስትወለድ ባሎቲ ወደምታስተምርበት ክፍል ሁሉ ልጇን ይዛት ትሄድ ነበር።

ትንሽዋ ልጅ፣ ገና የሦስት ዓመት ልጅ ሳለች በትኩሳት፣ ምናልባትም በወባ በሽታ ክፉኛ ታመመች። አሞቼ ለአገልግሎት በመሄዱ ምክንያትና ባሎቲ ሁለተኛ ልጇን በማንኛውም ሰዓት ለመውለድ በመጠባበቅ ላይ ስለ ነበረች፣ ጓደኞቻቸው ፔርሲስን በሶዶ ከተማ ውስጥ ወደሚገኘው የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮን ሆስፒታል ወሰዷት፣ ነገር ግን ልትተርፍ አልቻለችም። ከዚያም ጓደኞችዋ ሬሳዋን ተሸክመው በድንጋጤ ልቧ ወደ ቆመው ባሎቲ ወሰዱ። አሞቼም ከሄደበት ለልጁ ቀብር መጣ።

ለባሎቲ ይህ በጣም አስቸጋሪ ፈተና ነበር፣ ነገር ግን ጓደኞቿ እና ጎረቤቶቿ ለማስተዛዘን ወደ እርሷ ሲመጡ ባሎቲ እንዲህ ስትል ተናግራ ነበር፡- ‹‹እግዚአብሔር መልካም አይደለምን? ትንሽዋ ልጄ ከጌታ ጋር ናት። በጣም የሚያማምሩ ትናንሽ ሴት ልጆች እያሉ እግዚአብሔር የእኔን ትንሽዋን ልጅ መምረጡ አያስገርምም? ባሎቲ እና አሞቼ በእግዚአብሔር ጸጋ እና ማጽናናት ላይ በመደገፍ ልጃቸው ከእነርሱ በመለየቷ የደረሰባቸውን ጎዘን ማሸነፍ ችለዋል። ልጃቸው ደስታ ሲወለድ ምን ያህል ተደስተው ይሆን?

ባሎቲ እና ባለቤቷ ብዙ ጊዜ ለጠፉት፣ ወንጌል ላልደረሳቸው፣ በመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ ላሉ ብዙ ሰዎች ሁልጊዜ ይጸልያሉ። ከዚህ በተጨማሪ በጣም ሩቅ ላሉ ጎሳዎች ወንጌልን ለማድረስ ስለሚሄዱ ወንጌላውያንም ይጸልያሉ። ‹‹ወላይታን ለቅቃችሁ ወደ ሌላ ስፍራ ሂዱ›› የሚል ጥሪ ከእግዚአብሔር ሲመጣላቸው፣ ለባሎቲ ሌላ የእምነት ፈተና ነበር። ይህም ያሏትን ጓደኞች ሁሉ፣ የለመደችውን መኖሪያ አካባቢ ትታ ወደማታውቀው፣ ማንንም ወደማታውቅበት ስፍራ መሄድ ለእርሷ እምነትዋ የሚፈተንበት ሌላ መንገድ ነበር የሆነባት። አሞቾ ማሎ ወደሚባል አካባቢ በደቡብ ምዕራብ ትንሽ ጎጆ መሥሪያ መሬት ለመከራየት ቀድሟት ሄደ፤ ከዚያም ወደ ባሎቲ እና ደስታ ከመመለሱ በፊት መኖሪያ ቤቱን በመሥራት፣ የጓሮ አትክልት በዙሪያው ተከለ።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ባረኳቸው ደግሞም ትንሽ ስጦታ ሰጧቸው፣ እንዲሁም እንደሚጸልዩላቸው ቃል ገቡላቸው። ከተሾኙም በኋላ፣ ሁሉንም ንብረታውን የያዘችውን ትንሽዋን አህያ እየነዱ ጉዞ ጀመሩ። ባሎቲ ልጇን

በጀርባዋ ተሸክማለች፡፡ በአንድ እጇ ደግሞ በገንቦ ወተት እና የስንዴ ዱቄት ይዛለች፡፡ ይህ ለመንገዳቸው ስንቅ ነበር፡፡ ወደ አዲሱ ቤታቸው ለመድረስ በቀስታ ለአሥር ቀናት ተጉዘዋል፡፡ እንደ ደረሱም ባሎቲ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ጓደኞችን እና ጎረቤቶች አፍርታ ሴቶቹን ቡና እንዲጠጡ በመጥራት የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል መመስከር ጀመረች፡፡

ማሎ ከሌሎች አካባቢዎች የራቀ መሆኑ፣ የሕክምና እርዳታ ከሚገኝበት አካባቢ የቀናት ጉዞ ርቀት ላይ መገኘቱ እና ከገበያ አካባቢ የሰዓታት ጉዞ ርቆ መገኘቱ ባሎቲን የገጠማት ሌላኛው ችግር ነበር፡፡ በጣም አስቸጋሪ፣ ከዚህ በፊት በወላይታ ከለመደችው ሕይወት ፈጽሞ የተለየ ሕይወት ነበር፣ ነገር ግን ከባለቤቷ ጋር በጉዳዩ ላይ እየጸለዩበት ከአዲሱ አካባቢ ጋር እየተላመደች መጣች፣ እንዲሁም የመጀመሪያዎቹን ጥቂት ለወንጌል ምላሽ የሰጡ ሰዎችን ለመመልከት ቻሉ፡፡ ኦሞቼም ለወንዶቹ አሳቡን ካካፈላቸው በኋላ፣ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው የሚገናኙበት እና ጌታቸውን የሚያመልኩበት ትንሽ የጸሎት ቤት ገነቡ፡፡

አንድ መልእክተኛ ከሶዶ መጥቶ ኦሞቼን እኔ ጋ ያስቀመጥኽው ልጅህ ጠፍቶብኛል እና አፈላልገኝ የሚል መልእክት ላከበት፡፡ በአንድ ወር ውስጥ እመለሳለሁ በማለት ኦሞቼ ብቻውን በፍጥነት እየተጓዘ ሶዶ በአምስት ቀን ውስጥ ደረሰ፤ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥም ልጁን አገኘው፡፡ ባሎቲ ከትንሹ ልጇ ጋር ለብቻዋ ነበረች፡፡ ጎረቤቶቿ እንደ ጓደኞቿ ስለሆኑ ብቻዋን በመሆኗ አልፈራችም ነበር፡፡ ከልጃገረዶች እና ከሴቶች ጋር የጀመረችውን የቀን ትምህርት መስጠትም ቀጥላ ነበር፡፡

ꕥ

አንድ ምሽት አንድ የሰማችው ድምፅ ባሎቲን ከእንቅልፏ የሆነ ነገር ቀሰቀሳት፡፡ ሕልም ነበር ወይስ ራእይ? ማንንም አላየችም፣ ነገር ግን ድምፅ ሰማች፡፡ ድምፁም፡- ‹‹ባሎቲ፣ ባልሽ ሳይመለስ ቢቀር ምን ታደርጊያለሽ?›› የሚል ጥያቄ ቀረበላት፡፡

ባሎቲ እንዲህ ስትል መልስ ሰጠች፡- ‹‹በእርግጥ ይመለሳል፡፡ ጌታ ሆይ፣ አንተ ከሆንህ፣ ጌታ ሆይ፣ በዚህ ስፍራ እንድናገለግል ያመጣኸን አንተ ነህ፤ አሁንም በጣም ብዙ የሚሠራ ነገር አለ፡፡ በእርግጥ ይመለሳል፡፡›› አለች፡፡

ባሎቲ ተመልሳ መተኛት ፈለገች፣ ግን በተመሳሳይ ድምፅ እንደገና ከእንቅልፏ ነቃች። ‹‹ጌታ ሆይ፣ የምትናገረው አንተ ከሆንህ፣ እርሱ ያንተ ነው። እኔም የአንተ ነኝ። በእኛ ላይ እንደ ፈቃድህ አድርግ›› አለችው። ባሎቲ እንደገና ተጋደመች፣ ነገር ግን መተኛት አልቻለችም፣ ሌሊቱን ሁሉ ዓይኗን አፍጥጣ ይህ ምን ሊሆን ይችላል? ስትል ስታሰላስል አነጋች።

የአሞቼ መመለሻ ጊዜ አለፈ። ብዙ ቀናት አለፉ፣ ነገር ግን ስለ እርሱ ምንም ቃል አልተሰማም። አንድ፣ ሁለት . . . ሳምንታት አለፉ። አሁንም ምንም የለም። ከዚያም፣ አንድ ቀን ከወላይታ አንድ ጓደኛቸው መጣ፣ ይህ ሰው በቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተላከ መልእክተኛ ነው። ባሎቲ በታላቅ ድምፅ ጮኻ ‹‹ተመልሶ አይመጣምን?›› ስትል ጠየቀችው።

መልክተኛውም፣ ‹‹አዎ፣ አይመጣም›› ብሎ መለሰላት። ወደ ቤት ከገቡ በኋላም አሞቼ እና ልጁ በአሰቃቂ ሁኔታ በሽፍታዎች፣ በወላይታ ምሥራቅ ድንበር ላይ መገደላቸውን ነገራት።

በመኖሪያ ቤቷ ውስጥ ሆና ባሎቲ እግዚአብሔር ጥንካሬን እና ጽናትን እንዲሁም ጥበብን እንዲሰጣት በጉልበትዋ ተንበርክካ ጸለየች። ብዙ የጎረቤት ሰዎች እንደ ባህሉ ለማልቀስ ከመሰብሰባቸው በፊት ለማሰብ በቂ ጊዜ አልነበራትም። እንደ ባህላቸው ወደ ሰማይ እየዘለሉ እና ወደ ምድር ራሳቸውን እየጣሉ ማልቀስ ጀመሩ።

ባሎቲ ልታስቆማቸው ሞከረች። ‹‹ለምን ታለቅሳላችሁ? እንዲሁም ራሳችሁን ለምን እንዲህ ትጐዳላችሁ?›› ብላ ጠየቀቻቸው። በጣም ብዙ ቡድኖች አሁንም ሲመጡ ይህንን ጥያቄ ደጋግማ ጠየቀቻቸው።

‹‹ምክንያቱም ጓደኞችን፣ ባልሽ፣ በመገደሉ ነው። እርሱ ተመልሶ ወደ እኛ ስለማይመጣ ነው የምናለቅሰው። ለእርሱ ማልቀስ አለብን›› በማለት መለሱላት።

ባሎቲ በታላቅ ድምፅ እየጮኸች፣ ‹‹ስለ እናንተ ሲል የሞትን ጽዋ ስለ ጠጣው ስለ ኢየሱስ ነግረናችኋል። እናንተን ለማዳን ስለ ሞተው ስለ እርሱ አላለቀሳችሁም። ታዲያ ለምን ስለ ባሌ ታለቅሳላችሁ? እርሱ ስለ እናንተ

አልሞተም! ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ስለ እናንተ ሞቷል›› አለቻቸው። ከዚያም ኢየሱስ እንዴት እነርሱ ከኃጢአት እንዲድኑ የደኅንነት መንገድን እንዳዘጋጀ ነገረቻቸው። ባሎቲ የባሏን ቦታ በመውሰድ ደጋግማ አስረዳቻቸው። አንዳንዶች የክርስቶስን የመስቀል ላይ የስርየት ሥራ በተረዱ ጊዜ ምላሽ ሰጡ።



በወላይታ ያሉ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አሁን ባሎቲ ወደ ቤቷ መመለስ እንደምትችል መልእክተኛ ሲልኩ እንዲህ በማለት እንቢ አለች፡-‹‹እግዚአብሔር ባሌን እና እኔን ወደ ማሎ መጥተን ወንጌልን እንድንሰብክ ጠርቶናል። እግዚአብሔር ከዚህ ስፍራ ሂጂ እስኪለኝ ድረስ አልሄድም። በዚህ እቆያለሁ። በዚህ ስፍራ በጣም ብዙ የሚሠራ ሥራ አለ፣ ሕዝቡም አዳኝ ለማግኘት ተጠምቷልና ተጨማሪ ሌላ ቤተሰብ ወደዚህ ላኩ›› አለቻቸው።

ባሎቲ የተለመደውን የኅዘን ሥርዓት ለመፈጸም ወደ ወላይታ ለመሄድ ስትነሣ፣ የማሎ ሰዎች ወደ እነርሱ የማትመለስና የማታስተምራቸው መስሎዋቸው በጣም ፈሩ። ይህ እውነተኛ ፍራቻ ነበር። እርግጥ ነው፣ የባሎቲ ባል እንዲሁም ሴት ልጇ የተቀበሩት በወላይታ ነበር፣ እንዲሁም ጓደኞቿ ያሉት እዚያ ነበር። ስለሆነም፣ በእርግጠኝነት አትመለስም ብለው አሰቡ። ስለዚህም እርሷን አንለቅቅም አሉ። እነርሱን ማሳመን ለባሎቲ አስቸጋር ነገር ሆኖ አገኘችው።

ግራ የተጋባችው ባሎቲ፣ ጌታ ይረዳት እና አቅጣጫ ይጠቁማት ዘንድ እርዳታውን ፈለገች። በመጨረሻ ባሎቲ ትንሹ ልጇን ደስታን ከማታውቃቸው ሰዎች ጋር እንደ መያዣያ አድርጋ ትታ ለመሄድ ወሰነች። ይህ ለጌታ የሚከፈል ምንኛ ከባድ የሆነ መሥዋዕትነት ነው! ለእርሷ ብቸኛ ቤተሰብ የሆነው ልጇን መተው፣ የእርሷ ብቸኛ የሥጋ ዘመድን ከማታውቃቸው እንዲሁም አብዛኞቹ የማያምኑ ሰዎች ከሆኑ ጋር መተው በጣም አስቸጋሪ ነበር። ነገር ግን እርሷ ይህን አደረገች! ባሎቲ ለሁለት ወራት ከእርሱ ርቃ ስትቆይ፣ ልጇ በሰላም እንደሚጠበቅ እግዚአብሔርን አመነች።

ከጓደኞቿ እና ከአሞቼ ወላጆች ጋር ሆነ በቆየችባቸው ጊዜያት፣ ወደ ጌታ በጸሎት በመቅረቧ ምክንያት እንዴት እንደ ተጽናናች ግልጽ የሆነ ምስክርነት ሰጠች። የእግዚአብሔር መንፈስ ስለ ሰጣት ታማኝነት እና ማጽናናት እንዲሁም

ሰላም፣ ተቀባይነት እና ሐሤት መሰከረች።።

ባሎቲ በጸሎት ታማኝ እንደ ነበረች ሁሉ፣ በገንዘብም ታማኝ ነበረች፤ ከምታገኘው ነገር ሁሉ ላይ አሥራት ታወጣለች፣ እንዲሁም ሴቶቹ ይህኑን እንዲያደርጉ ታስተምራለች።። ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ሌሎች ወንጌላውያንን ለመርዳት ኦሞቼ የገባውን ቃል ለመጠበቅ ብዙ ብር ትሰጣለች።።

ጠንካራ እና ጽኑ የሆነ ጓደኝነት የሚወለደው በችግር ውስጥ ነው! ወንጌላዊ ማሄንም ያገኘሁት በዚህ ወቅት ነበር።። ምግባችንን፣ መድኃኒቶችን፣ ገንዘብ እና የግንባታ ቀሳቀሶችን የጫነችው መኪና በተራራ አጠገብ ተገለበጠች።። ይህንን የጠፋውን ነገር በዓመት ውስጥ እንኳ በምንም መንገድ መመለስ አይቻልም።። ወደ ከተማ እየተጓዝሁ ሳለ ወንጌል በመስበኩ ምክንያት ታስሮ፣ ቄሳስሎ እና ሰውነቱ እየደማ ሳለ፣ ከማሄ ጋር መንገድ ላይ ተገናኘን።። ዓይኖቻችን ተገጣጠሙ፤ ከዚያ ጊዜ አንሥቶ መንፈሳችን እርስ በርስ ተቈራኘ፤ እንዲሁም ከሃምሳ አምስት ዓመታት በላይ በኅብረት እና በአገልግሎት በአንድነት አለን።።

በተመሳሳይ መልኩም፣ ከአሥራ አምስት ወራት በኋላ ቪዳ እና ባሎቲም የተገናኙት በመከራ ጊዜ ነበር።። በቅርብ ጊዜ ጋብቻችንን ፈጽመን፣ በአንድ አሮጌ የጣልያን መኪና ለዓመት የሚበቃንን ስንቅ፣ መድኃኒት እና የግንባታ ቀሳቀሶ ይዘን እየተጓዝን ነበር።። ከሶዶ ወደ ቡልቂ በተበላሸው መንገድ ላይ 90 ማይል (144 ኪሎ ሜትር) ያህል ያ የጨቀየ መኪና ይዞን እንዲሄድ ለሳምንት መቆየት ነበረብን።። ከዚያ የኦሞ ወንዝን ወደ ታች እየተመለከትን ወደ ባኮ ለመሄድ የአራት ቀናት የበቅሎ ጉዞ ያስፈልገናል።።

በመኪና ውስጥ ባሎቲ እንዲሁም አማንታ፣ ታንጋ እና ሻንካ የተባሉ ሦስት ወንጌላውያን ከእኛ ጋር ነበሩ።። ያለ ጊዜው የመጣ ዝናብ ጉዞአችንን በጣም አስቸጋሪ አደረገው፤ ብዙ ጊዜ በአንድ ቀን የጀመርነውን ጉዞአችንን ለማጠናቀቅ አሥር ቀናት ፈጀብን።። ከሹፌሩ እና ከሠራተኞቹ ጋር በመሆን ጭቃውን በመቈፈር፣ እንጨት እና ድንጋይ በመሸከም በጎማው ሥር በማስቀመጥ መኪናው ትንሽ እንዲጓዝ እንጥራለን።። ጕርፉ እና ጭቃው ጥረታችንን ሁሉ መና ያደርገዋል።። አንድ ቀን፣ መኪናው ሃያ ጫማ (ስድስት ሜትር) ያህል ይሄዳል፤ በሚቀጥለው ቀን ደግሞ ስድስት ኢንች (አሥራ አምስት ሴንቲ

ሜትር) ያህል ይንሷቀቃል፡፡ ሙቀቱ፣ ድካሙ እና የምግብ እጥረት ሁላችንንም ፈትኖናል፤ ከዚህ በተጨማሪ የበረሃ ዝንብ እና የወባ ትንኝ አሠቃይተውን ነበር፡፡ ባሎቲ እንዲህ ስትል ተናገረች፡- ‹‹ጭስ ወደ ላይ መውጣቱን እንደማይተው ሁሉ እኛም ለመከራ ተወልደናል፣ ስለዚህ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም ወታደር መከራን መቋቋም አለብን፡፡››

ከዚያ ወደ ቡልቂ ተራራ ስንቃረብ፣ ጥቂት ወንዶች አንድ ወጣት ልጅ በቃሬዛ ይዘው ወደ እኛ መጡ፡፡ ሹፌራችንንም የልጁን እግር የሰበርኸው አንተ ነህ በማለት በውሸት ከሰሱት፡፡ ምናልባት ይህ ልጅ ከዛፍ ላይ ወድቆ ይሆናል፡፡ በጣም የተናደደው ሹፌር ከእነርሱ ጋር ለመስማማት ለብዙ ቀን መደራደር አስፈልጎታል፣ እንዲሁም ከዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ለመውጣት ብዙ ገንዘብ ከፍሏል፡፡ ያን ጊዜ ያደረግነው የጉዞው ትዝታ አሁንም ገና ከአምሮአችን አልጠፋም፤ እንዲሁም በባሎቲ እና በቪዳ መካከል ያለው ዘመናት ያስቈጠረ ፍቅር፣ ጓደኝነት እና አገልግሎት ያስተሳሰረ ነበር፡፡ ቪዳ ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ በመስጠት አውስትራሊያ ውስጥ ከሚገኘው የምቾት ቀጣናዋ በመውጣት፣ ምንም የመገናኛ አውታር ወይም የሕክምና እርዳታ ወደማይገኝበት ከነገሮች ሁሉ ተገልሎ ወዳለ ወደ ኦሞ ወንዝ ሸለቆ ጉዞዋን አድርጋለች፡፡ ባሎቲ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ወላይታ ስትጓዝ ልጇን ደስታን በደንብ በማታውቃቸው ሰዎች እጅ ወደ ተወችበት፣ በኦሞ ሸለቆ ውስጥ ወደሚገኘው ገለልተኛ ወደ ሆነው የማሎ መንደር በመመለስ ላይ ነበረች፡፡

በቅሎ እስክንከራይና ዕቃዎቻችንን ወደ ተራራዎቹ የሚሸከሙልን ጥቂት ሰዎችን እያፈላለግን ቡልቂ ውስጥ ሳለን፣ ባሎቲ በማሎ ወደሚገኘው ወደ ደስታ በፍጥነት ጉዞዋን አደረገች፡፡ ሁሉም ነገር ሰላም ነበር፤ ሕዝቡ በሙሉ በነቂስ ከቤቱ ወጥቶ እንደገና ሞቅ ያለ አቀባበል አደረገላት፡፡ ይህችን ትንሽ ሴት አደነቋት፣ መልእክቷንም አዳመጡ፡፡ ባሎቲም ሌላ ቤተሰብ ከእርሷ ጋር ለመሆን የክረምት ወራት ሲያበቃ- በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ከባዱ ዝናብ ሲያበቃ-እንደሚመጡ አረጋገጠችላቸው፡፡

ሕፃናት ከብቶች ለማሰማራት ከመሄዳቸው በፊት ማለዳ ወደ ባሎቲ ይመጡና ማንበብ እና መጻፍ ይማራሉ፡፡ ረፋድ ላይ ደግሞ የቤት ሥራቸውን ከጨረሱ በኋላ፣ ሴቶች ለመማርና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮችን ለመስማት ወደ

ባሎቲ ይመጣሉ፡፡ ባሎቲ ስለ ነገሮች ሁሉ እንዲጸልዩና በእግዚአብሔር እንዲታመኑ ታስተምራቸዋለች፡፡ ወጣት ወንዶች እና አዋቂዎች አመሻሽ ላይ ከሥራ በኋላ ይመጣሉ፡፡ ይህም ጊዜ አመርቂ ውጤት የታየበትና ብዙ ሰዎች ወደ ክርስቶስ የተመለሱበት ነበር፡፡

ᚕᚖᚗ

አዲሱ ወንጌላዊ ከሚስቱ እና ከቤተሰቡ ጋር ወደ ማሎ ሲመጣ ባሎቲ አሞቹ ለእርሷ የሠራውን ቤት ለቀቀችላቸው፡፡ ከዚያን ጊዜ አንሥቶ፣ ባሎቲ የራሴ የምትለው ቤት ኖሯት አያውቅም፡፡ እግዚአብሔር ሲጠራት በመስማት ለማስተማር ሩቅ ወደ ሆኑት መንደሮች በመሄድ መቆየት በምትችልበት ቦታ ትቆያለች፡፡ የሌላኛው ወንጌላዊ ሚስት ለአንድ ወይም ለሁለት ሳምንት ሴቶችን እና ኮረዶችን እንድታስተምር ትጠራታለች፡- ደስታ አድጎ በእግሩ መሄድ እስኪችል ድረስ ባሎቲ ከቦታ ቦታ ስትንቀሳቀስ በጀርባዋ አዝላው ትጓዛለች፡፡

በጣም ብዙ ወንዶች ለዚህች ባል የሞተባት ወጣት ሴት የጋብቻ ጥያቄ አቅርበውላት ነበር፣ ነገር ግን እርሷ ሁሉም ላቀረቡላት ጥያቄ አዎንታዊ መልስ አልመለሰችላቸውም፤ ለእነርሱ የምትሰጠው መልስም፡- ‹‹አሁንም አሞቼን እወድደዋለሁ›› የሚል ነበር፡፡ በእርግጥ የፈለገችው ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀች የማገልገል ነፃነቷን ነበር፡፡

አብያተ ክርስቲያናት በይበልጥ እየተተከሉ ሲሄዱና የክርስቲያኖችም ቍጥር እየጨመረ ሲሄድ፣ ወንጌላውያኑ፣ ለረጅም ጊዜ ከእነርሱ ጋር እንድትቆይ ባሎቲን ይጠይቋታል፡፡ በአንድ ጊዜ ጉብኝት ለሁለት ወራት ከእነርሱ ጋር እንድትቆይ በመጠየቅ ለእርሷ እና ለልጇ ለደስታ፣ የሚሆን የሣር ቤት ይሠሩላታል፡፡ ባሎቲ ለወንጌላውያኑ ሚስቶች ልዩ የሆነ አገልግሎት አላት- ከእርሷ ጋር ሲጸልዩ እና ጎብረት ሲያደርጉ ይበልጥ ይበረታታሉ እንዲሁም በእምነታቸው ይጠነክራሉ፡፡ ወንዶቹ ብዙ ጊዜ በአቅራቢያቸው ያለ ሌላ ወንጌላዊ ለመጐብኘት እና ከእርሱ ጋር ጎብረት ለማድረግ ይሄዳሉ፡፡ ስለዚህም ሴቶቹ ብዙ ጊዜ ብቻቸውን ይሆናሉ፤ ባሎቲ ስትመጣ ግን በወላይታ ትተውት የመጡት ተመሳሳይ ቋንቋ፣ ባህል እና ትውስታ ይኖራቸዋል፡፡

ᚕᚖᚗ

በቡልቂ የሚስዮን ሥራ ለመጀመር ከባኮ ተጉዘናል፡፡ ባሎቲም ከአንድ ቀጣና ወደ ሌላኛው ቀጣና ስትዘዋወር ብዙ ጊዜ ትጐበኝናለች፡፡ ከባድ ስደት በነበረበት ወቅት ወንጌላውያን በታሰሩና የጸሎት ቤቶች ሁሉ በተቃጠሉበት ወቅት፣ ባሎቲ ለታሳሪዎቹ ምግብን በማሰባሰብ ታቀብላቸው ነበር፣ ከክርስቲያኖችም ጋር በመኖሪያ ቤታቸው ለጸሎትና ኅብረት ትገናኝ ነበር፡፡ ቪዳ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ማንበብ፣ ልብስ መስፋት እና ጌጣ-ጌጥ መሥራትን ለልጃገረዶች ማስተማር ስትጀምር፣ ባሎቲ በጣም ደስ አላት፡፡ ቪዳ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነውን የሴቶች ጉባኤ (ኮንቬሽን) ስታዘጋጅ ባሎቲ ከተናጋሪዎቹ መካከል አንዷ ነበረች፤ ሴቶቹም ለዚህ ጉባኤ ጥሩ የሆነ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ባሎቲን፣ የጎፋ አካባቢን የሚያጠቃልል ሰፊ መሬት ሴቶችን የማስተማርና ሌሎችን ሴቶች እንዴት እንደሚያሠለጥኑ የማስተማር አገልግሎት እንዲኖራት በመጠየቃቸው ምክንያት ደስታ በኤስ ኣይ ኤም ትምህርት ቤት ውስጥ ለመማር ወደ ተመዘገበበት ወደ ቡልቂ ሄደች፡፡ ባሎቲ እና ቪዳ አገልግሎታቸውን ይበልጥ በጋራ እያከናወኑ በሄዱ ቍጥር አገልግሎቱ ሥር እየሰደደና እየጠነከረ ሄደ፡፡

የጎፋ ቤተ ክርስቲያን የራሷን የወንጌል ስርጭትና ሥልጠናን ማድረግ ስትጀመር እኛ ወደ ወላይታ ተመለሰን፣ ወንጌላውያኑ ተጠሩ እንደገናም ድልደላ ተደረገ፡፡ ባሎቲም ወደ ሶዶ ተመለሰች፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትንሽ ጎጆ ቤት ሰጧት፤ በዚያም ሆና ሌሎችን ማስተማሯን ቀጠለች፡፡ ቪዳ በተለያዩ ቀጣናዎች ውስጥ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ሴቶች የእግዚአብሔርን ቃል ለመማር በሚሰበሰቡበት ጊዜ የሴቶች ኮንፈራንሶችን ማዘጋጀት ጀምራ ነበር፡፡ በዚህ አገልግሎት ዘርፍ ቪዳን ያግዟት ከነበሩ ሰዎች መካከል አንዷ ባሎቲ ነበረች፡፡

በኮምዩኒስት መንግሥት ዘመን (ከ1966 – 1983 ዓ.ም) በወላይታ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ተዘግተው ነበር፡፡ የእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ብዛት 700 ያህል ነበር፡፡ በጣም ብዙ ሰዎች ተገድለዋል ወይም ታስረዋል፡፡ ባሎቲ አሥር ወይም ከዚያ በላይ ሴቶችን በመኖሪያ ቤታችን ወይም በራሷ ትንሽ ጎጆ ውስጥ ለጸሎት ትሰበስብ ነበር፡፡ የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ከአራት ሰዎች በላይ እንዳይሰበሰቡ በከለከሉበት ጊዜ ሴቶቹን በሦስት ወይም አራት ትናንሽ የጸሎት ቡድኖች አብዝታ አደራጅታ ነበር፡፡ እነዚህ የጸሎት ቡድኖች በእነዚያ የጨለማ ዘመናት ምን ያህል ክርስቲያኖች ይባረኩና ይበረታቱ እንደ ነበር

የሚያውቀው ጌታ ብቻ ነው።።

እስከ ዛሬ ድረስ የዘለቀው የባሎቲ ዋና አገልግሎት የነበረው፣ ጸሎት እና ለሴቶች የምክር አገልግሎት መስጠት ነው።። በእግዚአብሔር መልእክተኛ አማካይነት እርሱን ማወቅ እና ማገልገል እንዲቻል ያደረገውን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን።።

> ‹‹ከትያጥሮን ከተማም የመጣች ቀይ ሐር ሻጭ እግዚአብሔርን የምታመልክ ልድያ የሚሉአት አንዲት ሴት ትሰማ ነበረች፤ ጳውሎስም የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልብዋን ከፈተላት።።››
>
> የሐዋ. 16፡14

፮

ማሄ

ከሞት ጋር የተደረገ ቀጠሮ

ኽጅግ አልፎብኛል፣ ለእኔ ጊዜው እጅግ አልፎብኛል›› በማለት ሰውዬው ጮኸ፡፡ ‹‹እርግጥ ነው፣ ይህ እውነተኛና መልካም ዜና ነው፣ ነገር ግን እኔ የምሞት ሰው ነኝ፡፡ እኔ ዓርብ ዕለት የምሞት ሰው ነኝ›› አለ፡፡

ወንጌላዊ ማሄ እና ባለቤቱ በላይነሽ በትንሽ ሣር ቤት ውስጥ ቆሻሻ በሆነ ወለል ላይ ለጸሎት ተንበርክከዋል፡፡ በተራሮች አናት ላይ የምትገኘውን ትንሽዋን ቤታቸውን ልታሞቅ ፀሐይዋ ገና መውጣት መጀመሯ ነበር፡፡ በጣም ሞቃታማ በሆነ ሸለቆ ውስጥ ከኖሩ በኋላ፣ አሁን ቀዝቃዛ ቦታ ማግኘታቸው ፈታኝ ነበር፡፡ ይህ ስፍራ እግዚአብሔር ለእነርሱ እንዲሆን የጠራቸው ካልሆነ በቀር፣ በሩቅ በተራራማ አገር ወደሚኖሩ ሕዝቦች ለመሄድ ፈቃደኛ ነበሩ፡፡

ጋቢያቸውን ወደ ትከሻቸው ከፍ እያደረጉ፣ የአካባቢው ቅዝቃዜ ብቻ ሳይሆን፣ በእነርሱ ዙሪያ የጨለማው ክፉ ኃይል ማንጣበቡ ተሰማቸው፡፡ ይህ ኃይል፣ ሰዎች ሁልጊዜ በፍርሃት ውስጥ እንዲሆኑ የሚያደረግ ኃይል ነበር፣ ፍርሃቱም የመናፈስት እና የሞት ፍርሃት ነበር፡፡ ወንጌላዊው እና ሚስቱ ወደዚህ ስፍራ የመጡበት ምክንያት የኢየሱስ ክርስቶስን የወንጌል ብርሃን ወደዚህ ጨለማ ወደ ሞላበት ስፍራ ለማምጣት ነበር፡፡ ትንሽ የአየሩ ቅዝቃዜ ወይም ምቾት ማጣት የመጡበትን ዓላማ ከመፈጸም አያስቆማቸውም፡፡ የዲያብሎስን ጨለማ ሲጋፈጡ፣ በጣም የሚያስፈልጋቸው ነገር የመንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ የጦር ዕቃ ነበር፡፡

የሰይጣን ኃይል እንዲደቅቅ፣ በኃይለኛው ጠንቋይ አማካይነት በሕዝቡ ላይ ያለው ተጽዕኖ እንዲሰበርና አንድ ሰው ዲያብሎስን በመካድ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን መዳን ይችል ዘንድ በአንድነት ሆነው ጸለዩ። የሰዎቹን ሕይወት ፍርሃት ተቆጣጥሮታል። ሕዝቡ የአሰቃቂ ክፉ መናፍስት እና የሞቱ ዘመዶቻቸው የሙታን መናፍስት ፍርሃት ነበረባቸው።

የተቆላ ቦቆሎ እና ብዙ ቡና ከጠጣ በኋላ፣ ማሄ ራቅ ብሎ በተራራው አጠገብ ባለ መንደር ወንጌልን ለመስበክ ከቤቱ ወጥቶ ሄደ። ባለፈው ወር፣ በጣም ብዙ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ ብዙ ለቅሶ እና ዋይታ በመንደሩ ውስጥ ነበር። ማሄ6 በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ምንም ዓይነት ተስፋ እንደ ሌላቸው ያውቅ ነበር። የሚያደርጉትን አያውቁም፣ እንዲሁም ፍላጎታቸውን ሊያሟላ የሚችል መፍትሔ ያለው በእርሱ ዘንድ ብቻ ነበር።

ማሄ ወደ መንደሩ እንደ ደረሰ፣ በብዙ መኖሪያ ጎጆዎች የተከበበ ስፍራን ተመለከተ። ጥቂት ወንዶች በዱር የበለስ ዛፍ ሥር ሆነው ጋያ ያጨሱ ነበር። ወንጌላዊው ሰዎቹን ሰላም ካላቸው በኋላ፣ የሰው ልጆችን ሁሉ ከፈጠረው ፈጣሪ ዘንድ መልእክት እንዳለው ነገራቸው። ከእግዚአብሔር ቃል የሆነው መልእክት ልታዳምጡ ትወዳላችሁን? በማለት ጠየቃቸው። ሰዎቹ አዎንታዊ ምላሻቸውን ሲሰጡትም፣ ማሄ የወንጌልን መልእክት ማካፈሉን ቀጠለ። የእርሱ የራሱ ሕይወት ምን ያህል በክፋት እና በፍርሃት የተሞላ እንደ ነበረ ነገራቸው፤ በሞት እና የወደፊቱን ባለማወቅ ፍርሃት ውስጥ እኖር ነበር በማለት አስረዳቸው። የቀደመውን መንገድ በመተውና በኢየሱስ በማመን ያገኘውን ሰላም እና ሐሤት መሰከረላቸው። ማሄ ለብቻው ተነጥሎ የተቀመጠ፣ በጣም ጎዘን የገባው የሚመስል የእርሱን ንግግር በአንክሮ የሚሰማው ሰው እንዳለ አስተዋለ።

ማሄ ለአንድ ሰዓት ያህል ስለ እግዚአብሔር ቅድስና፣ ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት፣ ስለ ኃጢአታችን ዋጋ ለመክፈል ኢየሱስን በመላክ ስለ ተገለጸው ስለ ጌታ ጸጋ እና ፍቅር ስለ ክርስቶስ ሞት እና ትንሣኤ ሲናገር ሳለ በጣም ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ። ከሮሜ 6፡23 እንዲህ የሚለውን ጥቅስ አነበበላቸው፡- *‹‹የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።››*

‹‹ይህ መልካም ዜና አይደለምን? ይህንን ስጦታ ልትቀበሉት የሚገባ መልካም ዜና አይደለምን? በእርግጥ ይህ እስከ መጨረሻው የሚጸና ስጦታ ነው፡፡ ዛሬ የእግዚአብሔርን ስጦታ ልትቀበሉ ትወዳላችሁን?›› በማለት ተናገረ፡፡

በአገጩም፣ ለብቻው ወደ ተቀመጠው ሰውዬ እያመለከተ፣ ‹‹አንተ ወንድም፣ ይህ በእርግጥ መልካም ዜና ይመስልሃልን? ለሁሉም ሰው የሚሆን መልካም ዜና እንዲሁም ለአንተም የሚሆን መልካም ዜና ይመስልሃልን?›› አለው፡፡

ሰውዬውም፣ ‹‹እውነት ነው፣ ይህ መልካም ዜና ነው፡፡ በእርግጥ መልካም ዜና ነው፡፡ ለእነርሱ መልካም ዜና ነው፤ ለእኔ ግን ጊዜው እጅግ አልፏል›› ሲል መለሰ፡፡

‹‹ጊዜው አልፏል? ጊዜው አልፏል? በጭራሽ፣ ጊዜው አላለፈም፡፡ የእግዚአብሔርን ስጦታ ዛሬ መቀበል ትችላለህ! ለምን ‘ጊዜው እጅግ አልፏል’ አልህ?›› በማለት ወንጌላዊው ጠየቀ፡፡

ሰውዬውም፣ ‹‹ምክንያቱም እኔ ሟች ሰው ነኝ! በሚቀጥለው ዓርብ ቀን እሞታለሁ!›› በማለት መለሰለት፡፡ ‹‹የሚቀጥለው ዓርብ እሞታለሁ፡፡ ስለዚህ ለእኔ ጊዜው አልፏል›› አለ፡፡

ማሄ በሁኔታው ግራ ተጋባ፡፡ የመሞቻ ቀኑን የሚያውቅ ወይም የተቀጠረለት ሰው ከዚህ በፊት ገጥሞት አያውቅም፡፡ ስለዚህም ሰውዬውን እንዲህ ሲል ጠየቀው፣ ‹‹‹እንዴት የምትሞትበትን ቀን ልታውቅ ቻልህ?››

‹‹ጠንቋዩ ነገረኝ፡፡ አምስታችንንም በክፉ እርግማን ረገመንና አምስታችንም መቼ መቼ እንደምንሞት ነገረን፡፡ አራቱ ሰዎች ልክ እርሱ እንዳለው ሞተዋል፡፡ አሁን እኔ ብቻ ቀርቻለሁ፤ እኔ ደግሞ በሚቀጥለው ዓርብ ቀን እሞታለሁ›› በማለት መልስ ሰጠ፡፡

‹‹ዝናብ ያለ ጊዜው ቶሎ በማቆሙና ሰብሎች ቶሎ የመድረቃቸው ምክንያት እኛ አምስታችን መሆናችንን ጠንቋዩ ከተናገረ በኋላ፣ እያንዳንዳችን የእርሻ

በሬዎቻችንን ለእርሱ እንድንሰጥ ጠየቀን፡፡ ንፉግ የሆነው ጠንቋይም ከበሬዎቹ መካከል አንዱን ለሰይጣን መሥዋዕት በማድረግ እንደገና ዝናብ እንደሚያዘንብ ተናገረ፡፡

ለእነርሱ አስፈላጊ የሆኑትን እንስሳት ገበሬዎቹ ለመስጠት ፈቃደኞች ሳይሆኑ ሲቀሩ፣ ጠንቋዩ በጣም ተናድዶ ረገማቸው፡፡ እንስሳቱን ለእርሱ ቢሰጡት እነርሱ በምን ያርሳሉ? ስለዚህ ለእያንዳንዳቸው መቼ እንደሚሞቱ ቀን ቁረጠላቸው፡፡ ለአንደኛው በሦስት ቀናት ውስጥ፣ ለሌላኛው በሚቀጥለው ሳምንት ረቡዕ፣ ለሦስተኛው ከአሥር ቀን በኋላ ሐሙስ ቀን፣ ለአራተኛው ሰው በቀጣዩ ሐሙስ ደግሞም ለእኔ ከአራተኛው ሰው በኋላ ባለው በስምንተኛው ቀን ነው ብሎ ነግሮኛል፤ አሁን ገባህ?›› አለ አይኬ፡፡ አይኬ የዚያ የመሞቻ ቀኑን ይጠባበቅ የነበረ ወጣት ልጅ ስም ነበር፡፡ አራቱ ጓደኞቹ ጠንቋዩ ባለው መሠረት ሞተዋል፤ ግን የገደላቸው ፍርሃት ወይስ ተመርዘው ይሆን? ይህን የሚያውቅ ሰው የለም፡፡ አሁን የቀረው አይኬ ብቻ ነበር፡፡ ዓርብ ቀን እንደሚሞት እርግጠኛ ነበር!

ማሄ ለአይኬ መልስ እየሰጠ ወደ እግዚአብሔር ይጮኽ ነበር፤ ‹‹በኢየሱስ ካመንህ ዓርብ ቀን አትሞትም፡፡ ያ የሰይጣን ጉልበት ነው፤ ኢየሱስ ደግሞ ከሰይጣን በላይ ኃያል ነው፡፡ በመስቀል ላይ ሞቶ ከሞት በመነሣትና ለዘላለም በመኖር ሰይጣንን እና ሞትን አሸንፏል፡፡ አንተም በኢየሱስ ካመንህ ዓርብ ቀን አትሞትም›› አለው፡፡

አይኬም እንዲህ አለ ‹‹እንዴት? እንዴት ማመን እችላለሁ?››

ማሄም እንዲህ ሲል መለሰለት፣ ‹‹ሰይጣንን እና ክፉ መናፍስትን ካድ፤ ሁሉም የዲያብሎስ የሆኑትን ነገሮች ካድና ኢየሱስን እንደ አዳኝህ እና ጌታህ በሁለት እጆችህ እና በሙሉ ልብህ ተቀበል፡፡ አሁኑኑ አድርግ፤ አንተም በሕይወት ትኖራለህ፡፡››

ማሄ ለሰውዬው እየነገረው እና በጸጥታ እየጸለየ ሳለ፣ ሰውዬው ነገሩን ለመረዳት ሲቸገር አየው፡፡ ነገር ግን፣ ቀስ በቀስ እውነቱ ወደ ውስጡ እየዘለቀ መጣ፡፡ ጭላንጭል የሚሆን መረዳትን አግኝቷል፡፡ በጨለማ ውስጥ ያለ ብርሃን፡፡ ተስፋ? ሕይወት? ሰላም? እርግጥ ነው ምንም የሚያጣው ነገር

አልነበረም።።

አይኬ በድንገት ከመቀመጫው ተነሥቶ፣ ‹‹እንግዲያውስ ይህን አደርጋለሁ!›› በማለት ጮኸ።። ቀኝ እጁን ወደ ላይ በማንሣት፣ ሰይጣንንና መንገዱን ካደ።። ኃጢአቱን ሁሉ በወንጌላዊው በመታገዝ እንዲህ ሲል ተናዘዘ፣ ‹‹ሰይጣንን በመቃወም፣ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ አምናለሁ፣ እንዲሁም ኢየሱስን አዳኜና ጌታዬ አድርጌ ሁለት እጆቼን ዘርግቼ እቀበላለሁ›› አለ።።

ማሄ በከፍተኛ ድምፅ እንዲህ ሲል ጸለየ፣ ‹‹ሁሉን ቻይ የሆንክ አምላካችን ሆይ፣ አይኬ አሁን የአንተ ልጅ ነው።። ከሰይጣን እስራት ነፃ ነው።። ጌታ ሆይ፣ ሕይወቱን ጠብቅ።። መግባት መውጣቱን አንተ ተቈጣጠር።።››

ወንጌላዊው ሌሎች ሲያደምጡ የነበሩትን ሰዎችም ኃጢአታቸውን እንዲናዘዙና ኢየሱስን እንዲቀበሉ ጐተጐታቸው፣ ነገር ግን ብዙዎቹ የጠንቋዩን ኃይል በጣም ፈሩ።። ጥቂት ሰዎች አይኬ ዓርብ ቀን ሳይሞት ከቀረ እንደሚያምኑ ተናገሩ! ማሄ ኢየሱስ በሰይጣን እና በዲያብሎስ ላይ ያለውን ጒልበት የሚያሳዩ ብዙ ታሪኮችን ለብዙ ሰዓታት ለአይኬ ሲነግረው ቆየ እንዲሁም በየቀኑ እየመጣ ይበልጥ እንደሚያስተምረው ቃል ገባለት።።

ለዚህም አዲስ ክርስቲያን እንዴት በሰማይ ወደ አለው አባቱ እንደሚጸልይ አስተማረው፣ እንዲሁም ለቤተሰቦቹ እና ለጓደኞቹ ያደረገውን ነገር እንዲናገር ነገረው።። ማሄ ለአይኬ የሰጠው የመጨረሻ መመሪያ፣ ‹‹ከጠንቋዩ አጥር ግቢ የሚመጣ ማንኛውንም ነገር እንዳይበላና ሐሙስ እና ዓርብ ማታ ዘመዶቹ እና ጓደኞቹ እንዲጠብቁት›› አዘዘው።።

አይኬ ሳይሞት ቀረ! ታሪኩም ብዙ ርቆ በስፋት ተሰማ! ከሰይጣን እና ከክፉ መናፍስት የሚበልጥ ጒልበት ያለው ሌላ አለ! አይኬ ትዳር ያለው እና ትልቅ ቤተሰብ ያለው ሰው ነበር።። ሁሉም የክርስቶስ ተከታዮች ሆኑ።። አይኬ ስለ እምነቱ መከራን ተቀበለ፣ ተደበደበ እንዲሁም ታሠረ፣ ነገር ግን ለጌታ ታማኝ ሆኖ ኖሯል።። ልጁም ተደብድቧል፣ ነገር ግን በተራራው ሰንሰለት ላይ ሦስት ቤተ ክርስቲያናትን ለመትከል ትልቅ መሣሪያ ሆኖ አገልግሏል።። ከሴት ልጆቹ መካከል አንደኛዋ አንድ ወንጌላዊ በማግባት ሩቅ በሆነ ስፍራ ጌታን በማገልገል ላይ ትገኛለች።።

ጠንቋዩስ ምን ሆነ? እርሱ ደግሞ ምን ሆነ? ኃይሉ ተሰበረበት እንዲሁም ሕዝቡን የመቈጣጠር ሥልጣኑ ጠፋበት። ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ሞተ። ከልጆቹ መካከል ጥቂቶቹ በክርስቶስ ኢየሱስ አመኑ። ከእርሱ ልጆች መካከል አንደኛው በዚህ ሰንሰለታማ ተራራ አገር ከረጅም ጊዜ በፊት በጀመርነው መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ አሁን መምህር ሆኖ ያገለግላል። ሌሎቹ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪዎች ናቸው።

እግዚአብሔር የሠራው ምንኛ አስገራሚ ነገር ነው! በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት በመንፈሳዊ ጨለማ ላይ ብርሃን ለመፈንጠቅ የክርስቶስ መስቀል ታማኝ መልእክተኞች ስለ ሆኑት ሰዎች እግዚአብሔርን አመስግኑ።

> *‹‹ዳሩ ግን ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበረ ሕያው ሰለ ሆነ ጠፍቶም ነበር ሰለ ተገኘ ደስ እንዲለን ፍሥሐም እንድናደርግ ይገባናል አለው።››*
>
> ሉቃስ 15፡32

> *‹‹በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ . . . ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ሰለ ሆነ፣ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፣ በጸጋ ድናችኋልና፣››*
>
> ኤፌሶን 2፡1፣ 4፣ 5

፯

ሃመሜ

በመመልከቻ መስታወት ውስጥ

እናቱ በድንገት በታላቅ ድምፅ እየጮኸች ወደ ጫካው በፍጥነት እየሮጠች ስትሄድ የተመለከተው ልጅ እጅግ በጣም ፈርቶ ነበር። እናቱ ምን እንደ ገጠማት አስጨንቆት ነበር። በታላቅ ድምፅ ማልቀስም ጀመረ። ይህ ነጭ እንግዳ ሰው እናቴን ምን አደረጋት? ብዙ ሰዎች የተፈጠረው ነገር ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ከየመኖሪያ ቤታቸው መጥተው ነበር። አንዳንድ ሰዎች እናቱን ተከትለው የሮጡ ሲሆን፣ ሃሚ ግን በዚያም ወቅት እናቱ ስትጮኽ በርቀት ላይ ሆኖ ይሰማት ነበር። እጅግ በጣም በመፍራት ድምፁን ከፍ አድርጎ አልቅሷል።

ፈቃ

ደብረ ፀሐይ አቅራቢያ ወደሚገኘው የአሪ መንደር ቦሺ የተባለ መንገድ መሪዬ እና እኔ የደረስነው አመሻሽ ላይ ነበር። በተራራው ላይ ቀዝቃዛ እና ነፋሻማ የነበረ ሲሆን፣ እኛም ማደሪያ የሚሆን ስፍራ እየፈለግን ነበር። በመንደሩ መሃል ላይ ቆም አልንና እኔ ከበቅሎዋ ላይ ወርድሁኝ፣ በበቅሎ ብዙ ከመጓዜ የተነሣ በጭኖቼ መካከል ከተፈጠረው መላላጥ በማረፌ ደስ አለኝ። ከቀርከሃ ከተሠሩት ቤቶች ቀዳዳዎች ውስጥ ሆነው በጣም የብዙ ሰዎች ዓይኖች አሾልከው እኛን ያዩናል። ሴቶች እና እናቶች ሁሉ እንግዶቹን ፈርተዋል፤ ምክንያቱም ከዚህ በፊት ነጭ ሰው አይተው አያውቁም።

ጥቂት ወንዶች በቡድን ተቀምጠው ጋያ ያጨሳሉ። እያንዳንዱ ሳንባው እስኪሞላ ድረስ ጭሱን ወደ ውስጥ ይስባል፣ ከዚያም ወደሚቀጥለው ሰው ያስተላልፋል። ሌሎች የወንዶች ቡድን ደግሞ ክብ ሠርተው በመቀመጥ ከትልቅ እንስራ ውስጥ ጠላ እየቀዱ ይጠጣሉ። ሰዎች ሁሉ ጠላውን የሚጠጡበት መቃ አላቸው።

ሰዎቹን በአሪ ቋንቋ ሰላምታ ስናቀርብላቸው፣ ጥሩ ምላሽ ሰጡን፡፡ ምንም እንኳ ከእነርሱ ራቅ ካለ ስፍራ የመጣን ቢሆንም፣ ቦሺን ከወገኖቻቸው አንዱ እንደ ሆነ ተገነዘቡ፡፡ እነዚህ ሰዎች በጣም ተጠራጣሪዎች ናቸው፡፡ ስለ ነጭ ሰው ሰምተዋል፣ ነገር ግን አይተው አያውቁም፡፡ ከእነርሱ መካከል ጥቂቶቹ ወደ እኔ ቀርበው በነጭ ቆዳዬና ሉጫ በሆነው ጠጉሬ ላይ አፈጠጡ፡፡ ቁመቴ፣ ጫማዬና ልብሴ ምላሳቸው እንዲንቀጠቀጥ አድርጓል፡፡

ከጎጆ ውስጥም አንድ እራፊ ጨርቅ እና የአነር ቆዳ በትከሻው ላይ ብቻ የለበሰ ሰው ወጣ፡፡ የእርሱን መምጣት የተመለከቱ ሰዎች በፍርሃት መንገድ ለቀቁለት፡፡ አቲጋ የአካባቢው ጠንቋይ ሲሆን፣ ሁሉም የእርሱን ኃይል ይፈራሉ፡፡ ከትልቅ ቀርከሃ ጫካ ጀርባ በሚገኘው የእርሱ የሰይጣን ቤት ሰዎች በጣም አጣዳፊ ጉዳይ ከሌላቸው አይቀርቡም፡፡ በሥሩ መሠዊያ ያለው የተቀደሰ ዛፍ፣ አድባር ይባላል፡፡ በዚህ ዛፍ ሥር ሰዎች አቲጋ ለሚያናግራቸው ለቅድመ አያቶቻቸው መንፈስ እና ለክፉ መናፈስት መሥዋዕታቸውን ያቀርባሉ፡፡

ጠንቋዩ በቤቱ እንድንቆይ ጋበዘን፣ ደግሞም እኛ ፍርሃት ቢኖረብንም፣ ከእርሱ ጋር ቆየን፡፡ ስድስት ሚስቶች ነበሩት፣ እያንዳንዳቸውም የራሳቸው ጎጆዎች የነበራቸው ቢሆንም፣ እርሱ ግን በዋናው መኖሪያ ቤት ውስጥ ነበር የሚኖረው፡፡ ይኸውም ከሌሎቹ ጎጆዎች ሁሉ ትልቁ ነበር፡፡ በዚያ ቆሻሻ በሆነው፣ እንዲሁም በብዙ ሰዎች በተጨናነቀ ቤት ውስጥ ለሦስት ቀናት ቆየን፡፡ እነዚህ ሰዎች ስለ ኢየሱስ በጭራሽ ሰምተው አያውቁም፣ ስለዚህም እንግዶች አድርገው ለተቀበሉን ለእርሱ ቤተሰብና እንግዶች በመሆናችን ምክንያት እኛን ለማየት በየቀኑ ለሚሰበሰቡ የመንደሯ ነዋሪዎች ደጋግሜ የወንጌል ታሪክ ነገርኳቸው፡፡ በመጀመሪያ ልጆች ነጭ በማየታቸው ፈርተው ነበር፣ ነገር ግን ቀስ በቀስ ወደ እኔ እየተጠጉ መጡ፡፡ በቀላል አማርኛ የኢየሱስን ታሪክ ነገርኳቸው፣ ቦሺ ደግሞ ወደ አሪ ቋንቋ ተረጐመላቸው፡፡

ወደ መንደሩ ከገባን በሦስተኛው ቀን፣ ጥዋት ላይ የማለዳ ፀሐይ እየሞቅን ሳለ፣ ጢሜን መላጨት እንዳለብኝ ተሰማኝ፡፡ ቦሺ አንዷን ሴት፣ ውኃ እንድታመጣ ጠየቃት፡፡ ይህች ሴት የጠንቋዩ ሦስተኛ ሚስቱ ናት፣ ውኃ በገንቦ አድርጋ ይዛ መጣች፡፡ እኔም ጢሜን ስላጭ ተመልከታ ትገረም ነበር፡፡ በእጇ የያዝሁት ትንሽ የፊት መስታወት ግራ አጋብቷታል፤ ስለዚህም ምን እንደ ሆነ ለመመልከት እንዲያስችላት ወደ ፊት ይበልጥ ቀረብ አለች፡፡

በመጨረሻም፣ በእጇ የያዝሁት ነገር ምን እንደ ሆነ ጠየቀች፣ ቀርባም ተመለከተችው፡፡ እኔም ይህ ፊቴን መመልከት የሚያስችለኝ መስታወት ነው አልኋት፡፡ ከዚህ በፊት ብርጭቆ ወይም መስታወት ተመልክታ ስለማታውቅ ንግግሬን መረዳት አልቻለችም፡፡ ስለዚህም ይህ ነገር ምን እንደ ሆነ መረዳት እንድትችል ማድረግ እጅግ በጣም አስቸገረኝ፡፡ ከዚያም እርሷ ‹‹አየዋለሁ›› አለች፡፡ ምናልባት ትርጓሜው ‹‹አንድ ጊዜ በእጇ ልያዘውና ሁለተኛ አታገኘውም›› የሚል ሊሆን ይችላል፡፡

እኔም እንዲህ ስል ምላሽ ሰጠኋት፣ ‹‹እኔ በእጇ እንደ ያዝሁ መመልከት ትችያለሽ፡፡›› እርሷም በመልሴ የረካች ትመስላለች፤ ስለዚህም መስታወቱን ወደ ፊቷ አቀረብሁት፤ እርሷም ወደ መስታወቱ ማፍጠጥ ጀመረች፡፡ ቀስ በቀስ ዓይኖቿ በመስታወቱ ላይ ወዳለው ወደ እርሷ ፊት ማተኮር ጀመሩ፣ በጠጉሯ ላይ የተቀባችው ቅቤ፣ በጆሮዎቿ ላይ ያደረገቻቸው ጉትቻዎች፣ በፊቷ ላይ ያለው ጠባሳ፣ የአንገቷ ንቅሳት እና የጎሳ መለያ ምልክቷን ተመለከተች፡፡ ለጥቂት ጊዜ ያህል በመስታወቱ ውስጥ እየተመለከተች ያለችው ነገር ምን እንደ ሆነ አላወቀችም ነበር፡፡

በድንገት ሴትዮዋ በታላቅ ድምፅ ጮኸች! በጣምም አስደነገጠችኝ! መስታወቱን ከእጇ ቀምታ በተቻላት መጠን አርቃ ወደ ጫካው መሀል ወረወረችው፡፡ በታላቅ ድምፅም እየጮኸች ወደ ጫካው እየሮጠች ሄደች፡፡

ቦሺ በታላቅ ድምፅ መሳቅ ጀመረ፣ ነገር ግን የመንደሩ አብዛኛው ሰዎች በፍራቻ ሲከታተሏት፤ ጥቂት ሴቶች ግን ከእርሷ ኋላ ተከትለው ወደ ጫካው ሮጡ፡፡ ‹‹ምን እያለች ነው? ለምን ትጮኸለች?›› ብዬ ቦሺ እንዲነግረኝ ግድ አልሁት፡፡ ቦሺ እንባው እስኪፈስስ ድረስ በጣም ሳቀ፡፡

ሁለቱንም ጐኖቹን ይዞ እየሳቀም እንዲህ አለ፡- ‹‹ዲያብሎስን አየሁት! ዲያብሎስን አየሁት! ነው ያለችው፡፡››

❧

መጽሐፍ ቅዱሴን ወደ ሰማይ አንሥቼ፣ ተሰብስበው ላሉት ወንጌላውያን ‹‹ይህ መጽሐፍ፣ የእግዚአብሔር ቃል፣ እንደ መስታወት ነው፡፡ ይህ በጣም ልዩ የሆነ መስታወት ነው፡፡ ወደዚህ ስመለከት ራሴን አያለሁ፡፡ ኃጢአቴን፣ ዕዳዬን፣ ፍርሃቴን፣ ድክመቴን፣ አለማመኔን እና ዓመፃዬን እመለከታለሁ፡፡ ነገር ግን፣ ጌታ

ይመስገን፣ ወደዚህ መጽሐፍ ስመለከት የማየው ራሴን ብቻ ሳይሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኜንና ጌታዬንም አያለሁ፡፡ የእርሱን ፍቅርና ጸጋ፣ የእርሱን ርኅራኄና ኃይል አያለሁ፡፡ ድምፁ ሲያስተምረኝ፣ ሲመራኝና የተሳሳተ ነገር ሳደረግ ሲወቅሰኝ እሰማዋለሁ፡፡ በቃሉ ውስጥ አስፈላጊ ሲሆን ጸጋውን እና እንክብካቤውን ያሳየኛል፡፡››

በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ውስጥ የሚያገለግሉ ሁሉም ወንጌላውያን ቱርሚ በሚባል ስፍራ ላይ ተሰብስበው ነበር፡፡ ወደ ሰማንያ የሚጠጉ ወንጌላውያን ባህል-ዘለል በሆነ መንገድ ብዙ ጎሳዎችን በወንጌል ለመድረስ ጥረት በማድረግ ላይ ነበሩ፡፡ በዚህ ስፍራ የመገኘታቸው ምሥጢር የአራት ቀን ጸሎት እና ጎብረት በማድረግ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለመማርና ልምዳቸውን ለማካፈል ነበር፡፡

ለእነዚህ ወንጌላውያን በአሪ የምትገኘው የጠንቋዩ ሚስት በእኔ ትንሽ የፊት መስታወት ውስጥ የራሷን ምስል በመመልከቷ ምን ያህል እንደ ፈራች እና እንደ ደነገጠች፣ መስታወቱንም ወርውራ እየጮኸች ወደ ጫካ እንዴት እንደ ሮጠች ለወንጌላውያኑ ነገርኳቸው፡፡ በታሪኬም ወንጌላውያኑ ከልባቸው ሳቁ፡፡ አብዛኛዎቹ ከዚያ ጎሳ የመጡ ነበሩ፡፡

የትምህርቱ ክፍለ ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በምናውቀው ቋንቋ ስለ ተሰጠን እግዚአብሔርን በጸሎት በማመስገን ተጠናቀቀ፡፡ በጣም ጥቂት ሰዎች የወላይታ መጽሐፍ ቅዱስ ሲኖራቸው፣ አብዛኛዎቹ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነበር ያላቸው፣ ወይም ከአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሳቸው ጋር የሚያነጻጽሩት የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ነበራቸው፡፡

ስብሰባውም እንደ ተጠናቀቀ፣ ወንጌላውያኑ በትናንሽ ቡድኖች በመሆን ስለ መልእክቱ ተወያዩ፣ እንዲሁም ገጠመኞቻቸውን እርስ በርሳቸው ተከፋፈሉ፡፡ ከአሪ የመጡት ወንጌላውያን በሙሉ ወደ እኔ መጡ፡፡ ስሙ ሃሚ የተባለው አጭር ጥቁር ሰውዬ በታሪኬ ውስጥ እንደ ጠቀስሁት በደብረ ፀሐይ እንደ ተወለደ ነገረኝ፡፡

ሃሚ እንዲህ አለ፣ ‹‹በዚያን ጊዜ እኔ በጣም ትንሽ ልጅ ነበርሁ፡፡ አባቴ ጠንቋይ ነበር፡፡ ሰይጣናዊ ኃይል የነበረው ሲሆን፣ ሁላችንም እንፈራው ነበር፡፡ እናቴ ከነበሩት ስድስት ሚስቶች መካከል ሦስተኛዋ ናት፡፡ መስታወትህን ወደ ጫካው የወረወረችው እርሷ እናቴ ናት፡፡ ይህንን ያደረገችበት ምክንያትም

ሰይጣንን በመስታወቱ ውስጥ የተመለከተች ስለ መሰላት ነበር!›› አለኝ፡፡ በዚህ ንግግሩ በጣም ተገርሜ ሃሚን አቀፍሁት፡፡ ያንን አካባቢ ለአጭር ጊዜ ብቻ ጐብኝተን ከተመለስን በኋላ፣ በአካባቢው ምን ምን ነገሮች እንደ ተከሰቱ እንዲነግረኝ ጠየቅሁት፡፡

ትንሹ ሰውዬ እንዲህ አለኝ፣ ‹‹ለብዙ ጊዜ በነበርነበት ሁኔታ ከቆየን በኋላ፣ እኔ ወጣት ሳለሁ፣ አንድ ወንጌላዊ ከጎፋ ወደ እኛ መጣ፡፡ መኖሪያ ቤት ሠርቶ በመካከላችን ኖረ፡፡ እርሱም ስለ ኢየሱስ ታሪክ ነገረን፡፡ እኔም በመልእክቱ በማመን ሰይጣንን እና የሰይጣንን የጨለማ ሥራ ሁሉ ካድሁኝ፡፡ በእምነትም ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ ተቀበልሁ፡፡››

ሃሚ በመቀጠል፣ ‹‹አባቴ ግን አላመነም፡፡ እኔ የቀድሞውን መንገድ በመተዌ እጅግ በጣም ተቈጣ፡፡ እኔም እንደ እርሱ ጠንቋይ እንድሆን ይፈልግ ነበር፡፡ አባቴ የእርሱን መንገድ እንድከተል በበትሩ ይመታኝና ያስፈራራኝ ነበር፡፡ ደም በደም ሆኜ መራመድ ተሣነኝና ከመኖሪያ ቤቱ አውጥቶ ወደ ውጭ ጣለኝና ተመልሼ ወደ ቤቱ እንዳልመጣ አስጠነቀቀኝ፡፡ እናቴ ከዚህ ሁሉ ታደገችኝ፡፡ ደኅና እስክሆን ድረስ ደብቃ ተንከባከበችኝ፡፡ ከዚያ ግን መንደሩን ለቅቄ መሄድ ግድ ሆነብኝ፡፡››

‹‹ጠንቋዩ አባቴ የክርስቶስን ወንጌል ለመስማት አልወደደም፤ በወንጌልም አላመነም፤ በጨለማ ውስጥ እንዳለ ነበር የሞተው፡፡ እናቴ ግን ክርስቲያን ሆነች፣ እንዲሁም የአባቴ ሌሎች ሚስቶች ሁሉ፣ ወንድምና እኅቶቼ ሁሉ ወደ አዳኙ መጥተዋል፡፡››

ሃሚ በመቀጠል እንዲህ አለ፣ ‹‹ዛሬ በደብረ ፀሐይ አካባቢ ብዙ ቤተ ክርስቲያናት አሉ፡፡ ብዙ ሰዎች በኢየሱስ አምነዋል፡፡ ጌታ ኢየሱስን ይከተላሉ፣ እንዲሁም በአካባቢው ውስጥ የቀረ አንድም ጠንቋይ የለም፡፡››

‹‹ጎፋ ወደሚገኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገባሁኝ፤ እግዚአብሔር በአሞ ሸለቆ ውስጥ ወደሚገኙት ዳሳነች ሕዝቦች ላከኝ፡፡ በተለይ በደርግ ጊዜ (17 ዓመት የኮምዩኒስቶች ዘመን) እጅግ በጣም ፈታኝ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ቤተሰባችንን ስለ ጠበቀና ስለ ተንከባከበ እናመሰግነዋለን፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን እኔ እና ልጄ ሳሙኤል በአሞ ወንዝ ዳር ዳሩን ይዘን እየተጓዝን ሳለ፣ የዳሳነች ጦረኛ ከጫካ ውስጥ ሆኖ ይተኵሰብናል፡፡ ጌታ

በእርግጥም ይጠበቀናል! በኋላ ላይ፣ ጀግናው ተኵሶ ከመካከላችን አንድ አዲስ ክርስቲያን ገደለ፡፡ የደርግ ፖሊስ ገዳዩን ያዙትና ረሸኑት፡፡››

‹‹በበና ሕዝቦች መካከል ወደ ተለያዩ ስፍራዎች ተዘዋውረናል፡፡ ማንበብ እንዲችሉ ሕፃናትንና ወጣቶችን እያስተማርንና የክርስቶስን ወንጌል እየሰበክን ስንሄድ ጥቂት ሰዎች አምነው ተጠመቁ፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያናት ተመሠረቱ፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው፤ እኛ ለእርሱ ምስጋናን እናቀርባለን፡፡››

በእግዚአብሔር ጸጋና በደብረ ፀሐይ አካባቢ ባሉ በአሪ ሕዝቦች መካከል በሚሠራውን ሥራ እና ከሃሚ ጋር ሐሜት እያደረግሁ ሳለ፣ ስለ ገዛ ቤተሰቡ ሃሚን ጠየቅሁት፡፡ የእርሱ የመጀመሪያ ልጅ የሆነው ሳሙኤል ትምህርት በጨርሰ ጊዜ፣ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ እንዲሠራ ተመረጠ፡፡ ይህ ጥሩ የሥራ ቦታ ከጥሩ ደመወዝ ጋር እንደ ሆነ ይቈጠራል፣ የማደግ ተስፋም ነበረው፡፡ ነገር ግን፣ ሳሙኤል እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል የሚሰብክ ወንጌላዊ እንዲሆን እንደሚፈልግ ስለሚያምን፣ ያንን ሥራውን ትቶ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገባ፡፡ የሃሚ ሌሎች ልጆች ሁሉ ጌታን ይከተላሉ፣ እንዲሁም ትምህርታቸውን በሚከታተሉባቸው የተለያዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ጥሩ መስካሪዎች ናቸው በማለት ነገረኝ፡፡

ሰማያዊ አባታችን ሰዎችን ወደ ራሱ ለመሳብ ያልተለመዱ መንገዶችንና ትናንሽ ነገሮችን የድነትን መልካም ዜና ለጠፉት ሰዎች የማድረስን ዘዴ በመጠቀም ሁልጊዜ ያስደንቀናል፡፡ እነዚህ ትናንሽ ነገሮች መስታወት፣ ድራማ፣ ራእይ፣ የተቀዱ መልእክቶች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ምስሎች፣ የተለወጡ ሰዎች ምስክርነት ወይም ነፃ የወጡ ምላሶች ናቸው፡፡ ክብርና ምስጋና ለእርሱ ይሁን፡፡

> *‹‹ነገር ግን ወንጌልን ሊደራ ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር የታመንን ሆነን እንዳገኘን መጠን፣ እንዲሁ እንናገራለን፣ ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ደስ እንደምናሰኝ ሊይደለምና፡፡››*
>
> 1ኛ ተሰሎንቄ 2፡4

፰

ጌናሚ

በውኃዎች ውስጥ

ወላጆቿ ጌንቦ የሚባል በኡቾሎ ውስጥ የሚገኝ የአንድ ጠንቋይ ልጅን እንደምታገባ ሲነግሯት፣ ጌናሚ ገና በአሥራዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ዕድሜ ላይ የምትገኝ ልጅ ነበረች። የተባለውን ልጅ አግኝታው አታውቅም፣ ነገር ግን አንድ ጊዜ ከርቀት አይታዋለች። እርሱም በደንብ አይቷት ኖሯል ለካ!

ᚕᚖᚗ

እንደ ጎሳቸው ወግ እና ልማድ፣ የጌንቦ ወላጆች ለወንድ ልጃቸው ሚስት መፈለግ ነበረባቸው። በአካባቢያቸው ስላሉ ቆነጃጅት ማጠያየቅ ጀመሩ፤ እንዲሁም ለጌንቦ ጥሩ ሚስት መሆን የምትችለዋን መፈለግ ጀመሩ። ከዚያም ዝርዝር ጉዳዩን ከጌናሚ ወላጆች ጋር ተወያዩ። ‹‹ትንሽ ጥሎሽ›› ለመስጠትም ተስማሙ። ትንሽ ጥሎሽ የሆነበት ምክንያት፣ ኃይለኛ የሆነው የጠንቋዩ ዘር ውስጥ መግባት በራሱ መታደል መሆኑ ስለ ታመነበት ነበር። ጌናሚን ማንም ሰው አላማከራትም-እንዲህ ባሉ ጉዳዮች ላይ ያላት አማራጭ በጣም ጥቂት ነበር።

ወላጆቿዋ ነገሩን ለሴት ልጃቸው በመንገር ቀኑን እና ዝርዝር ጉዳዩን አስታወቋት። ለእርሷ ወላጆች ስጦታ፣ ለጌናሚ አዲስ ልብስ እንዲሁም ለእርሷና ለጓደኞቿ ድግስ ተዘጋጀ። ከዚያም ጌንቦ ከጓደኞቹ ጋር አመሻሽ ላይ መጥቶ ከቤቷ ጠልፎ ወሰዳት። ጌንቦ ከወላጆቹ ቤት አጠገብ ወደ ሠራው አዲስ ቤት ይዞአት ሄደ። በዚያም ሌላ ድግስ ተደግሶ ነበር፤ ከዚያ በኋላ የዚህ ቤተሰብ አባል ሆነች።

ᚕᚖᚗ

ጌናሚ እንዴት ባሏን ማስደሰት እንደምትችል ቶሎ ተማረች፤ ቢያንስ ቢያንስ እንዴት እርሱ እንዳይናደድ ማድረግ እንደምትችል አወቀች! የጌንቦን ፍላጐቶች ሁሉ በማሟላትና መኖሪያ ቤታቸውን ሥርዓት ባለው ሁኔታ በማስተካከል ታስደስተው ነበር፡፡ ከንጋት ጀምሮ እስከ ዕኩለ ሌሊት ድረስ በትልቅ እንስራ ውኃ ከምንጭ በመቅዳት፣ ከጫካ እንጨት በመልቀም፣ ከብቶችን በመንከባከብ፣ ላሞችን በማለብና የተለያዩ ምግቦችን በማብሰል ታገለግለው ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የጌንቦ እናት የምትጠይቃትን ሁሉ በማድረግና ሁሉም የቤተሰቡ አባላት እጅግ በጣም የሚወድዱትን ትኩስ ቡና በቅቤ እና በቅመም በማፍላት ታስደስታቸው ነበር፡፡

እንደ የጎሳዎቿ ሰዎች ሁሉ፣ ጌናሚ ሕይወቷን ሁሉ ያሳለፈችው ለልማድ፣ ለተለያዩ እምነቶች በፍርሃት በመገዛት፣ ክፉ መናፍስትን በመፍራት፣ የአያቶቿን መንፈስ - የጨለማውን ሥልጣን፣ የማይታዩ ኃይላትን፣ የማይታወቁ የሙት መናፈስትን በመፍራት ነበር፡፡ ነገር ግን፣ ከዕለታት አንድ ቀን ሁለት እንግዶች ወደ መንደራቸው መጡና በመኖሪያ ቤታቸው ደጃፍ ላይ ከሚገኝ አንድ ዛፍ ጥላ ሥር አረፉ፡፡ ጌንቦ በተለመደው የኢትዮጵያዊያን ትሕትና ጎንበስ ብሎ ሰላምታ ሰጣቸውና ቡና ይጠጡ ዘንድ ጋበዛቸው፡፡

ጌናሚ በፍጥነት ከሰሉን በማቀጣጠል የቡና ጀበናውን ጣደችበት፤ ቡና እና የቡና ቀሩርስ የሚሆን ጥሬ መቀሉላት ጀመረች፡፡ እንግዶቹ ለጌንቦ ኢየሱስ ስለ ተባለ ሰው ሲነግሩት ታዳምጥ ነበር፡፡ በሕይወቷ ከሰማቻቸው ታሪኮች ሁሉ ይህ የተለየ ታሪክ ነበር፡፡ ጌንቦ በትኩረት ሲያዳምጥና ጥያቄዎችን ሲጠይቃቸው ተመለከተች፡፡

ሰዎቹ ይበልጥ እየተናገሩ ሲሄዱ፣ ጌናሚ በሚናገሩዋቸው ታሪኮች እጅግ እየተመሰጠች ሄደች፡፡ ታሪኩን ሙሉ በሙሉ ለመስማት ከመጓጓቷ የተነሣ፣ ቡናውን አሳርራው ነበር! ይህ ኢየሱስ የሚባለው ሰው ከዚህ በፊት ከምታውቃቸው ሰዎች ሁሉ የተለየ ነበር፡፡ በሽተኞችን ይፈውሳል፣ ለምጻሞችን ያነጻል፣ እንዲሁም የዓይነ ሥውራንን ዐይን ያበራል፡፡ የተራቡ በሺህ የሚቈጠሩ ሰዎችን ይመግባል፣ በውኃ ላይ ይራመዳል፣ እንዲሁም የሞቱትን ከሞት ያስነሣል! ይህ ሁሉ ልዩ የሆነና እንግዳ ነገር ነበር፡፡ ኢየሱስ ሴቶችን ያከብራል፤ ኃጢአትንም ይቅር ይላል! ይህ እውነት ሊሆን ይችላልን? ኢየሱስ ሰው ነውን? ኢትዮጵያዊ ይሆንን? አሁን ያለው የት ነው?

ከዚያም ከቀጣዩ አውራጃ፣ ከወላይታ፣ የመጡት ሁለቱ ወንጌላውያን ኢየሱስ የታላቁ የፈጣሪ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ነው አሉ። በሰማይ ካለው ከአባቱ ዘንድ መምጣቱን፣ ልጅ ሆኖ መወለዱን እና ማደጉን ተናገሩ። በኃጢአተኛው ሰውና በእግዚአብሔር መካከል እውነተኛ አስታራቂ እርሱ ነው ሲሉ ተናገሩ። ይህ ሁሉ አዲስ ነገር ነበር። ጌንቦ እና ጌናሚ ሊቀበሉት አልቻሉም! በይበልጥ መስማት ይፈልጋሉ!

ብዙ ሰዓታት አለፉ፤ ፀሐይዋም መጥለቅ ጀመረች፣ ወዲያውም ጨለማ ይሆን ነበር። ጌናሚ ከብቶቹን ወደ ቤት ለማምጣት በፍጥነት ወጣች፤ በግድግዳው ላይ ባሉ ግንዶች ላይ አሰረቻቸው። የሚነዱ እንጨቶችን ወደ ቤት ካስገባች በኋላ፣ እንስራዋን ይዛ ከምንጭ ውኃ ለመቅዳት በፍጥነት ሄደች። ከታሪኩ ውስጥ ምንም ነገር እንዲያመልጣት አልፈለገችም፤ ሰዎቹን ሌሊቱን ሁሉ ከእነርሱ ጋር እንዲያሳልፉ ጌንቦ እንደሚጋብዛቸው እርግጠኛ ነበረች።

ከወላይታ የመጡት ሰዎች እነርሱ ራሳቸው እንደዚህ ካለ ጨለማ ውስጥ ስለ ወጡ ጌንቦ እና ጌናሚ አሁን ያሉበትን ግራ መጋባት ተረድተዋል። ከዚህ በፊት እነርሱ ራሳቸው ዛፍና ድንጋይን ከሚያመልኩ ሰዎች መካከል ነበሩ። የአያቶቻቸውን መንፈስ የሚፈሩና ስለ ክርስትና ምንም ነገር ሰምተው የማያውቁ ሰዎች ነበሩ፣ ነገር ግን የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ እንደ ሆኑ ተቁጥረው ለካህናቱ በየጊዜው እንዲገብሩ ይደረግ ነበር።

ከወላይታ የመጡት ‹‹ገበሬ-ወንጌላውያን›› ደመወዝ የሚከፈላቸው ቅጥረኞች አልነበሩም፣ ነገር ግን እነርሱ ራሳቸው በቅርብ ጊዜ ጌታን ያገኙ በደስታ እና በክርስቶስ ባገኙት ነፃነት የተነሣሡ ሰዎች ነበሩ። ሰዎች ከሰይጣን ፍርሃት እና ኃይል ነፃ መውጣት የሚችሉበትን መንገድ የሚያሳይ መልእክት አምጥተዋል። እነርሱ እየተናገሩት የነበረው ሰዎች ቢሞቱ እንኳ ስለ ማያበቃው አዲሱ ሕይወት ነበር። ይህ ሕይወት ዘላለማዊ ነው። ጌናሚ እና ጌንቦ ወንጌላውያኑ ባመጡት መልእክት እጅግ በጣም ተገርመዋል። በጣም ሩቅ ስፍራ የሚኖረው ታላቁ ፈጣሪ- በእርግጥ ይወድድዳቸዋል፣ እንዲሁም ልጁን ኢየሱስን እንደ ሰው እንዲኖርና ለእነርሱ ሲል እንዲሞት ሕፃን ልጅ አድርጎ ላከው። ይህ እጅግ የሚያስገርም ነገር ነበር። ይህ ምንኛ የሚያስደንቅ ዜና ነው! በዚህ ተስፋ፣ ሰላም እና ነፃነት አለ!

እንግዶቹ ከጌናሚ እና ከጌንቦ ጋር እስከ ዕኩለ ሌሊት፣ ምግብ እስከ ቀረበበት ሰዓት ድረስ ይነጋገሩ ነበር። ጌናሚ እራቱን ለማዘጋጀት ከተለመደው ጊዜ በላይ ወሰደባት። የሰዎቹን እያንዳንዷን ቃል መስማት ከመፈለጓ የተነሣ ሰዎቹ ሲናገሩ ለማዳመጥ ደጋግማ ታቆም ነበር። እነዚህ ሰዎች ስለ ምግቡ እግዚአብሔርን ማመስገን ይችሉ እንደ ሆነ ፈቃድ ጠየቁ እንዲሁም ጌንቦ እና ጌናሚ የወንጌልን መልእክት ሰምተው ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው ለመቀበል ይችሉ ዘንድ ልቦናቸው እንዲያበራ ጸለዩ። ከምግብ በኋላም፣ እስከ ምሽት ድረስ አራቱ ሰዎች ሲያወሩ አመሹ። ጌናሚ ወደ ጌንቦ ጆሮ ጠጋ ብላ እንዲህ አለች፣ ‹‹ይህ ነገር እውነት መሆን አለበት፣ ምክንያቱም ልቤ እውነት እንደ ሆነ ነግሮኛል አለችው።›› ይህንን ነገር ጌንቦም እንዲያምን ትፈልጋለች።

ጠዋት ላይ፣ እነዚህ ጥንዶች ውሳኔያቸውን አስታወቁ- ይህንን አዲሱን ሕይወት ይፈልጉታል! ሰይጣንን በአደባባይ በካዱ እና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው በተቀበሉ ጊዜ የመንደርዋ ሰዎች ሁሉ እጅግ በጣም ተገረሙ። ወዲያውም ሌሎች ጥቂት ወጣቶች እና ብዙ አዋቂ ሰዎች አመኑ። ብዙ ሌሎች ሰዎችም የእነርሱን ፈለግ ተከተሉ፤ ትንሽ የጸሎት ቤትም ሠሩ። ከወላይታ የመጡት ወንጌላውያንም ለሳምንታት ከእነርሱ ጋር በመቆየት፣ እነዚህ አዳዲስ አማኞችን እንዴት መኖር እንዳለባቸው እና እንዴት መጸለይና ማምለክ እንዳለባቸው አስተማሯቸው።

ብዙ ሰዎች የቀድሞ መንገዳቸውን በመተው የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች እየሆኑ ሲመጡ፣ ዜናው እስከ ጨንቻ ከተማ ድረስ ተሰማ። መጀመሪያ ሰሞን አዳዲስ አማኞች ‹‹ንጹሕ ያልሆኑ ገበሬዎች የኢየሱስ ሰዎች ሆኑ!›› ተብለው ይሳቅባቸውና ይቀለድባቸው ነበር። ከዚያ በኋላ ግን ይህ ቀልድ ቀስ በቀስ ወደ ቁጣ ተለወጠ፤ ከዚያም እነዚህ የተናቁ ሰዎች ለባለ ርስቶች የካህናቱን ግብር አንከፍልም አሉ። እርግጥ ነው፣ ለባለ ርስቶቹ የመሬት ግብር ይከፍሉ ነበር፤ ነገር ግን ከዚያ ጊዜ ጀምረው እንደ ባሪያ ወይም አገልጋዮቻቸው አልሆኑላቸውም።

ይህ የሚያበቃው የት ነበር? ይህ ‹‹ዓመፅ›› መቆም ነበረበት! የመንግሥት ባለ ሥልጣናት፣ ፖሊስ፣ ባለ ርስቶች፣ ካህናት እና ጠንቋዮች ጎበረት በማድረግ የኢየሱስን ሰዎች ማሳደድ ጀመሩ። እነዚህ ሰዎች እንዲገዙላቸው ወታደሮችን

በመላክ እንዲደበደቡ አደረጉ፡፡ ሕዝቡም በመነሣት የክርስቲያኖችን ቤቶች ዘረፈ፡፡ መኖሪያ ቤቶች ተቃጠሉ፣ ከብቶቻቸውና ንብረቶቻቸው ሁሉ ተሰረቁ፤ ክርስቲያኖች ከቀዬያቸውና ከመንደራቸው እንዲሰደዱ ተደረጉ፡፡ ለዓመታት ስደተኞች ሆነው ቆዩ፡፡ የእንቅስቃሴው መሪዎች ታሠሩ፣ ተደበደቡ እንዲሁም ወደ ወኅኒ ተጣሉ፡፡ ብዙ እናቶች ከትናንሽ ልጆቻቸው ጋር ደኅንነት ወደሚያገኙበት ስፍራ ሸሹ፡፡ ብዙ ቤተሰቦች ተበታተኑ፡፡

ጌንቦና ብዙዎቹ መሪዎች በእስር ቤቶች ውስጥ መከራ ገጠማቸው፡፡ ተደበደቡ፣ በረሃብ ተቀጡ፣ እንዲሁም አግባብነት የሌለው ሥቃይ ደረሰባቸው፣ ነገር ግን ክርስቶስን ለመካድ እንቢ አሉ፤ ወደ ቀድሞው የአባቶቻቸው መንገድም ለመመለስ አሻፈረኝ አሉ፡፡ ከሌሎች ሴቶች ጋር በመሆን ጌናሚ ለጌንቦ እና ለሌሎች ታሳሪዎች ምግብ ታደርስ ነበር፡፡ ጌንቦ እና ሁለት ሌሎች ሰዎች በለጠና ሃሼቦ መንግሥትን በመቃወም ንግግር አድርጋችኋል ተብለው በውሸት ተከሰሱ፡፡ ሦስት ዓመትም አዲስ አበባ በሚገኘው ቆሻሻ እስር ቤት ውስጥ እንዲቆዩ ተደረገ፡፡ ነገር ግን እነርሱ አሁን አዲስ ሕይወት፣ ሰላም እና ሐሤት ስላላቸው፣ ለሌሎች እስረኞች እና የእስር ቤቱ ጠባቂዎች ወንጌልን ያካፍሉ ነበር፡፡ በአገራቸው ያሉ ክርስቲያኖች ስለ እነርሱ በጸለዩና ወደ እግዚአብሔር በጮኹ ቍጥር የሚደርስባቸው መከራ ይበልጥ እያጠነከራቸው ሄደ፡፡

ጌንቦ በአዲስ አበባ በሚገኘው ወኅኒ ቤት ውስጥ እያለ፣ ሠላሳ የሚያክሉ ሰዎች መኖሪያ ቤቱን ለማቃጠል በአንድ ምሽት ወደ መኖሪያ ቤቱ መጡ፡፡ ንብረቱን ሁሉ ዘረፉና ጌናሚ ቤቱን ለቅቃ እንድትሄድ አዘዟት፡፡ ወደዚህ ስፍራ ከተመለሰች እንደሚገድሏት አስጠነቀቋት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የእርሷን እና የልጇን፣ የሳሙኤልን፣ ልብስ ከላያቸው ላይ ገፍፈው በመውሰድ ራቍታቸውን ሰደዷቸው፡፡ ምንኛ አሰቃቂ ነገር ነበር! እንዲህ ያለ ነገር ተሰምቶ ታይቶም አይታወቅም! የማይታመን ነገር ነበር! እንዲሁም በጣም የሚያስፈራ ነገር ነበር!

ሰዎቹ መንገዱን ተከትለው መሄድ ሲጀምሩ፣ ጌናሚ፣ የምታደረገውን በቅጡ ሳታውቅ፣ ልጇን እንደ ተሸከመች ተከትላቸው በመሄድ የእርሷንና የልጇን ልብስ ይተዉላት ዘንድ ለመነቻቸው! ሰዎቹ ግን እየሳቁ ትተዋት ሄዱ፡፡ በመጨረሻ፣ እየጮኸችንና እየለመነች ስላስቸገረቻቸው፣ ከመካከላቸው አንድ ሰው ወደ ኋላ ዘወር ብሎ ስስ ልብስ ወረወረላት፡፡

ምን ማድረግ እንዳለባት ሳታውቅ፣ ብቸኛ ሆናና ተስፋ ቁርጣ ከልጇ ጋር ቀረች። የተቃጠለው መኖሪያ ቤቷን ትታ፣ ወላጆቿ ወደሚኖሩበት ሩቅ ወደ ሆነው መንደር በጨለማ ውስጥ መጓዝ ጀመረች። አዳላጭ በሆነ መንገድ ለመጓዝ አስቸጋሪ ሆነባት፣ እንዲሁም ልጇን ሳሙኤልን በጫካ ውስጥ ካለው ቁንጥር ለመከላከል ከፍተኛ ጥረት ታደርግ ነበር። ወደ ትውልድ ቀዬዋ ለመድረስ አንድ ትልቅ ወንዝን መሻገር እንዳለባት ረስታው ነበር። ቆሻሻ የሆነውን እና ሞልቶ የሚፈስሰውን ወንዝ ስታይ ደነገጠችና ፈራች። ወንዙ ሞልቶ ስለ ነበረ ልትሻገር የምትችልበት ምንም ዓይነት መንገድ አልነበረም። በጥንት ጊዜ እንደ ነበሩት እስራኤላውያን መሄጃ አልነበራትም፤ ጠላቶቿ ከኋላ ስላሉ ልትሄድ የምትችልበት ስፍራ አልነበራትም።

በመራራ ስሜት፣ ጌናሚ ወደ ጌታዋ ጮኸች። እርሷን ሊረዳት የሚችል እርሱ ብቻ ነበር!፡ በዚያ ወንዝ በሌሊት ደኅና ሆኖ ማለፍ አይቻልም። ከዚያ ወደ ልቧ ትልቅ ጸጥታና ሰላም መጣ፤ ጌታዋ ስለ እርሷ እና ስለ ልጇ ግድ እንደሚለው እርግጠኛ ሆነች። እንዴት እንደ ሆነ እስከ አሁን በማታውቀው መንገድ፣ ራሷን በድንገት ከወንዙ ማዶ፣ ምንም ውኃ ሳይነካት፣ ልጇን በክንዷ ላይ ይዛ ተገኘች! ጌታ እርሷን እና ልጇን ተሸክሞ እንዳሻገራቸው ታምናለች! ምስጋናንና ውዳሴን እያቀረበች፣ እንክብካቤና ጥበቃ ሊደረግላት ወደሚቻልበት የወላጆቿ ቤት በፍጥነት ሄደች።

ከባሏ ተለይታ የምትቆይባቸው ብዙ የመከራ ወራትና ዓመታት ቢጠብቋትም፣ ጌናሚ ግን በእምነቷ እንደ ዳነችና ለአዳኝዋ ያላት ፍቅር እያደገ ሄደ። ለበላይ ባለ ሥልጣናት ብዙ አቤቱታ ቀርቦ፣ ከዚህም በላይ ለንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ይግባኝ ብላ ብዙ ሰዎች ቀንና ሌሊት አማላጅነት ከተላኩ በኋላ ነበር የተለቀቁት። ለብዙ ጊዜ ጌናሚ ልጇ ሳሙኤልን ያሳደገችው ለብቻዋ ነበር። ጌንቦ ከብዙ ዓመታት የእስር ቤት ቆይታ በኋላ ሲፈታ ታላቅ ደስታ ሆነ!

ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ ጌናሚን በብዙ ኃፍረት ውስጥ የጣሏት እነዚያ ክፉ ሰዎች ስለ ሠሩት ክፉ ወንጀል ዋጋቸውን መከፈላቸው ገሀድ ሆነ። ከእነርሱ መካከል ከአንዱ በስተቀር ሁሉም ልጅ ሳይወልዱ ሞተዋል፣ ስማቸውን የሚያስጠራ ሰው ሳይተዉ ሞተዋል። ከእነርሱ መካከል የተለየ ዕጣ ፈንታ ያገኘው ሰው በዚያ ሌሊት ለጌናሚ እና ለልጇ ትንሽ ርኅራኄ በማሳየት ልብሳቸውን የወረወረው ሰው ነው። በጋሞ ባህል፣ ትዳር አለመመሥረትና ልጅ

አለመውለድ፣ እንደ ሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ሁሉ፣ ያልተለመደ ነገር ነው። ልጅ-አልባ መሆን ልብን የሚያስጨንቅ እንዲያውም ክፉ መርገምና ከአምላክ ዘንድ የሆነ ቅጣት እንደ ሆነ ተደርጎ ይታሰባል።

ሌሎች ሰዎች በኡቾሎ እና ጋሞ ውስጥ በክርስቲያኖች ላይ ስለ ደረሰው መከራ ጽፈዋል። በአማኞች ላይ ለዓመታት እጅግ በጣም ጽኑ ስደት እና ተቃውሞ ቢደርስባቸውም፣ ቤተ ክርስቲያን ግን እድገቷን ቀጥላለች። በአሥሮችና በሃያዎች፣ በብዙ መቶና፣ በሺህ የሚቈጠሩ ጣዖት አምላኪዎች የነበሩ ሰዎች ክርስቲያን ሆነዋል። ቤተ ክርስቲያናት በዝተዋል፣ የቀለም ትምህርት ቤቶች ተመሥርተዋል፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ተከፍተዋል እንዲሁም በኋላ ላይ ጥቂት የሕክምና መስጫ ክሊኒኮች ተከፍተዋል። እግዚአብሔር የወንጌልን ስብከት በመባረኩ በሺህዎች የሚቈጠሩ ሰዎች ሕይወት ተለውጧል፣ ቤታቸው ተለውጧል እንዲሁም ማኅበረሰባቸው አድጓል።

ትንሹ ሳሙኤልስ ምን ሆነ? ለእርሱ እግዚአብሔር ልዩ የሆነ ነገር አድርጎለታል። ይህም ልጽፈው የሚገባ ሌላ ታሪክ ነው!

> *‹‹የማይመረመረውን ታላቅ ነገርና የማይቈጠረውን ተአምራት ያደርጋል። በምድር ላይ ዝናብን ይሰጣል፥ በእርሻም ላይ ውኃ ይልካል። የተዋረዱትን ወደ ላይ ያወጣል፥ ኀዘንተኞችንም ለደኅንነት ከፍ ከፍ ያደርጋቸዋል።››*
>
> ኢዮብ 5፡ 9-11

፱

ጌጌበ

ዝናብ በዝምታ ሲቆም

ሰማዩ ጠቁሯል፣ የነጐድጓድ ድምፅ ይሰማል፤ ከተራራ ላይ እንደሚፈስስ ማዕበል መብረቁ ደጋግሞ አስፈሪ ድምፁን ያሰማል። ከባድ ዝናብ በአካባቢው እየዘነበ ነበር፤ በፍጥነትም እነርሱ ወዳሉበት አቅራቢያ እየገሰገሰ ነበር። በዚያ ስፍራ የነበሩት ሰዎች ሁሉ፣ በሺህ የሚቈጠሩ ነበሩ፣ ለመሮጥም በመዘጋጀት ቆሙ፣ ከዚያም፣ እንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያት፣ ጌንቦ ለመሄድ ባኮበኮቡት ሰዎች ፊት በመቆም እጆቹን ዘርግቶ እንዲህ በማለት ጮኸ።

‹‹አትፍሩ! ተቀመጡ! ማንም ሰው እንዳይሄድ! ሁሉም ሰው ይቀመጥ! በእኛ ላይ አይዘንብም! ተረጋጉና የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ! እግዚአብሔር አምላካችን ሁሉን ቻይ ነው! ዝናብን በእጆቹ ይዟል። እግዚአብሔር ኃይሉን ዛሬ እንዲያሳየን እንመነው።››› በሚያስደንቅ ሁኔታ፣ ሰው ሁሉ መልሶ መሬት ላይ ተቀመጠ።

ከዚያም፣ እጆቹን ወደ ላይ ዘርግቶ መዳፉን እንደ ትራፊክ ፖሊስ ወደ ፊት አድርጎ በመቆም፣ ሁላችንንም አስገረመን። በታላቅ ድምፅ፣ ‹‹ዝናብ ሆይ! ዝናብ ሆይ! አጥሩ ጋ ቁም! እዚያ ቆይ! ወደዚህ አትምጣ!›› በማለት ትእዛዝ ሰጠ።

ᚕᚖᚗ

ከወላይታ ጎሳ የሆኑት ሁለት ወንጌላውያን ወደዚህ ስፍራ ወንጌል ይዘው ከመምጣታቸው ብዙ ቀደም ብሎ፣ ጌንቦ በጋሞ ጎሳ ውስጥ የባህላዊ እምነት መንገድን የተማረ ሰው ነበር። የታወቀው ጠንቋይ ልጅ የሆነው ጌንቦ የጨለማው መንፈሳዊ ኃይል ምን እንደ ሆነ ያውቃል። በቀድሞው ሕይወቱ አባቱ ያስተማሩትን ቃለ መሐላዎች፣ መሥዋዕቶችና ስጦታዎችን ተመልክቷል።

ከጫካ ውስጥ የትኞችን ሐረጎች፣ ቅጠሎችና ሣሮች እንዲሁም ሥራ ሥሮች ና ፍሬዎች ለታመሙት ሰዎች መድኃኒት ለማበጀት መጠቀም እንዳለበት ተምሯል። እንዲሁም እንዴት ሁሉንም ዓይነት መርዞችንና እርግማንን መሥራት እንደሚቻል ተምሯል። ሰዎች ሁሉ ‹‹ቡዳን›› እጅግ አብዝተው እንዲፈሩና ጠንቋይንም እንዲገዙ የሚያደረግ ነገር ይጠቀም ነበር!።

ጌንቦ የቅድመ-አያቶቹን ስም እስከ አሥራ ሰባተኛ ትውልድ ድረስ በቃሉ ያውቃል፣ እንዲሁም የእነርሱን የሰይጣን ኃይል በሚማርክ መንገድ ሥራ ላይ ያውለው ነበር። አባቱ እንዴት አሥራ ሰባት ነጫጭ ልዩ ድንጋዮችን በመመልከት ወይም ለጨለማው ገዥ በመሥዋዕትነት የቀረቡ እንስሳትን ሞራ በመመልከት የወደፊቱን ነገር መጠንቁል እንደሚችል አስተምረውታል።

ጌንቦ ማስወገድ ያልቻለው ነገር ቢኖር ፍርሃትን ነበር-ሞትን በጣም ይፈራ ነበር። በኦቾሎ አካባቢ እንደሚኖሩ ሰዎች ሁሉ፣ ጌንቦ ጨለማን ይፈራ ነበር። በእርግጠኝነት ይሞታል፤ ከዚያም በእርግጠኝነት የማያውቀውን የወደ ፊቱን ነገር ለብቻው ይጋፈጣል። ማንም ሰው፣ በጣም ኃይለኛ የሆነው ጠንቋዩም ቢሆን፣ ለዚህ ፍርሃት መልስ የለውም፤ አስፈሪ ስለ ሆነው ሞት መልስ የለውም። ጌንቦ የሚረዳው የሌለው መሆኑ ተሰማው፤ ተስፋ ቁረጠ። ሰዎች ኑሮዋቸውን ሁሉ ሞት ተቆጣጥሮታል። ኑሮ ከባድ ነበር። ብዙዎች ሰዎች እስከ እርጅና የሚቆዩ ቢሆንም፣ ብዙዎቹ ግን በወጣትነታቸው ይሞታሉ። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሕፃናት ይሞታሉ። የኮሌራ ወረርሽኝ፣ ታይፎይድ ወይም የማጅራት ገትር በሽታ በመቶዎች የሚቈጠሩ ሰዎችን በአንድ ጊዜ ይፈጇቸዋል። ሁሌም ሞት ያሸንፍ ነበር!

ወንጌላውያን ወደ ኦቾሎ አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ የክርስቶስን ወንጌል ይዘው ሲመጡ፣ መንፈሳዊ ጨለማነትና ሕዝቡ ያለበትን እስራት ተረድተዋል። የክፉ መናፈስትና የቅድመ-አያት መንፈስ ፍርሃት እንዳለ ተረድተዋል። እነርሱ ራሳቸው እንዲህ ካለው እስራት የተፈቱ አይደሉምን? ምንም እንኳ ሁሉም ዛፍንና ድንጋይን የሚያመልኩ ሰዎች ቢሆኑም፣ የቅድመ-አያቶቻቸውን መንፈስ የሚፈሩና ስለ ክርስትና ምንም ነገር ሰምተው የማያውቁ ሰዎች ነበሩ። የኦቾሎ ሰዎች በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አርቶዶክሳውያን እንደ ሆኑ ስለሚታሰብ፣ በየዓመቱ ግብር ለቤተ ክርስቲያኒቱ እንዲከፍሉ ይገደዳሉ። በጨንቻ ከተማ

ውስጥ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል፤ ይህ ከተማ ከኦቾሎ መንደር የብዙ ሰዓት ጉዞ ይርቃል፣ ነገር ግን ማንም ሰው ሕዝቡን ለማስተማር ወደ ኦቾሎ መጥቶ አያውቅም::

ወንጌላውያኑ ይዘውት የመጡት መልእክት ከሰይጣን ፍርሃትና ኃይል ነፃ መውጣትን፣ ብርሃንን እና ተስፋን የሚሰጥ ነበር:: ይህ አካል ሲሞት፣ ስለማያበቃ አዲስ ሕይወት ይናገራል:: በመጀመሪያ፣ ሰዎቹ ወንጌላውያኑ ይዘውት በመጡት መልእክት ደንግጠዋል፣ ተገርመዋል፣ እንዲያውም ተጠራጥረዋል:: እጅግ ርቆ የሚኖረው ታላቁ ፈጣሪ በእርግጥ እነርሱን መውደዱንና ልጁን ኢየሱስን ሰው ሆኖ እንዲኖርና ለእነርሱ እንዲሞት ሕፃን ልጅ አድርጎ መላኩ የሚያስደንቅ ዜና ነበር! ይህ ጥሩ ተስፋ ሰጭ ነገር ነው-ግን እውነት ይሆን?

ወዲያውም በአስገራሚ ሁኔታ ጥቂት ወንዶች፣ ጥቂት ወጣቶችና ሁለት ቤተሰቦች ለዚህ ለወንጌሉ መልእክት ምላሻቸውን ሰጡ! ጌንቦ እና ሚስቱ ሰይጣንን በአደባባይ ሲክዱ እና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው ሲቀበሉ የተመለከቱ የመንደሩ ነዋሪዎች ሁሉ እጅግ በጣም ተገረሙ:: ብዙ ሌሎች ሰዎችም የእነርሱን ፈለግ ተከተሉ፤ ትንሽ የጸሎት ቤትም ሠሩ:: ብዙ ሰዎች የቀድሞ መንገዳቸውን በመተው የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች እየሆኑ ሲመጡ፣ ዜናውም በጨንቻ ከተማ ያሉ የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ዘንድ ተሰማ::

አዲሶቹ አማኞች በመጀመሪያ ተሳቀባቸው እንዲሁም ተሳለቁባቸው፣ ምክንያቱም ‹‹ምንም አያውቁም የተባሉት ገበሬዎች›› የ‹‹ኢየሱስ ተከታዮች›› ለመሆን ታላቅ ድፍረት አገኙ:: ይህም ምንኛ የሚያስገርም ነገር ነበር! ቀስ በቀስ መሳለቁ ወደ ቀጣ መቀየር ጀመረ:: ወዲያውም በከተማው ውስጥ ታላቅ ነውጥ ሆነ-የተናቁት ሰዎች የቀሳውስትን ቀረጥ ለመክፈል አሻፈረኝ አሉ! የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች አይደሉ-ሆነውም አያውቁም:: አሁን ግን ለአዲሱ ጌታቸው ስጦታን ለመስጠት ፍላጎት አደረባቸው:: በእርግጥ፣ ለሀብታሞቹ የመሬት ከበርቴዎቹ የመሬት ግብራቸውን መክፈላቸውን ቀጥለዋል፤ ከዚያን ጊዜ ወዲያ ለጌቶቻቸው ስጦታን እንደሚሰጡ ባሪያዎች ወይም አገልጋዮች ግን አይደሉም::

ይህ ነገር የሚያበቃው የት ይሆን? እነዚህ ‹‹ዐማፅያን›› ሊያስቆሟቸው

ይገባል! ባለ ርስቶች፣ ቀሳውስት፣ የመንግሥት ባለ ሥልጣናት፣ ፖሊስ እና ጠንቋዮች አንድ ላይ በመተባበር የኢየሱስ ሰዎችን ማሳደድ ጀመሩ። መሣሪያ የታጠቁ ሰዎች እነዚህን ሰዎች ይደበድቡና መኖሪያ ቤታቸውን ይዘርፉ ዘንድ ተላኩ። መኖሪያ ቤታቸው ተቃጠለ፣ እንስሶቻቸውና ያላቸው ንብረት ሁሉ ተዘረፈ እንዲሁም መሬታቸው ተወረሰ። የንቅናቄው መሪዎች ታሠሩ፣ ተገረፉ እንዲሁም በወኅኒ ተጣሉ። ሕፃናትን ያዘሉ ሴቶች እስከነ ልጆቻቸው በጨለማ ተሰደዱ። አጠቃላይ ቤተሰባቸው ተበታተነ። በመቶዎች የሚቈጠሩ ሰዎች ከመኖሪያ ቤታቸው ተሰደዱ እንዲሁም በሌላ ስፍራ ስደተኞች ሆነው መኖር ጀመሩ።

ጌንቦ እና ሌሎች መሪዎች በጣም አስቀያሚ በሆነ እስር ቤት ውስጥ ታስረው በድብደባ፣ በረሃብ እና በተለያዩ መንገዶች እንግልት ይደርስባቸው ነበር፣ ነገር ግን በክርስቶስ ላይ ያላቸውን እምነት በመካድ ወደ አባቶቻቸው እምነት እንዲመለሱ ለቀረበላቸው ጥያቄ አሻፈረኝ አሉ። ጌንቦ እና ሁለት ሌሎች መሪዎች ብላቴ እና ሃሼቦ ‹‹መንግሥትን›› ተቃውማችኋል›› የሚል የሐሰት ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ወደ አዲስ አበባ ለቅጣት ተላኩ፣ በዚያም ሦስት ዓመት በእስር ቤት አሳለፉ። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች አዲስ ሕይወት፣ ሰላም እና ደስታን አገኙ። እግዚአብሔር ከደረሰባቸው መከራ እንዲታደጋቸው ሲሉ ያደረጉት ጸሎት እና ጩኸት ጠንካሮች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

ብላቴ በእስር ቤት ውስጥ ታሞ ሞተ። ጌንቦ እና ጓደኞቹ አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው እስር ቤት ለሦስት ዓመት በቆዩባቸው ጊዜያት እነርሱን በሐሰት የከሰሷቸው ሰዎች ሁሉ ሞቱ!

በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ክርስቲያኖች አማካይነት ብዙ ጸሎትና ለበላይ ባለ ሥልጣናት አቤቱታ ይቀርብ ነበር፤ ይህም አቤቱታ ለንጉሠ ነገሥቱ ለኃይለ ሥላሴ እንኳ ሳይቀር ይቀርብ ነበር፤ በመጨረሻም ፍትሕ ተገኘ። የሃይማኖት ነፃነት ታወጀ። የአካባቢው ባለ ሥልጣናት የተሰረቁትን ንብረቶች እንዲመልሱ፣ እንዲሁም የተወረሰባቸው መሬት እንዲመለስና ክርስቲያኖችን ቤት በመሥራት እንዲያግዟቸው ትእዛዝ ተሰጠ። ሁሉም ክርስቲያኖች ተሰድደው የፈራረሰባቸው መንደር ድርቅን፣ የሰብል መበላሸትንና ራብን ተመልክታለች።

ክርስቲያኖች ጠላታቸውን ይቅር ሲሉና ለጠፋባቸው ንብረት ምንም ካሳ ሳይጠይቁ በመቅረታቸው ከሳሾቻቸው እጅግ በጣም ተገርመዋል። ይህ ብዙ

ሰዎች እውነቱን እንዲፈልጉ፣ እንዲያውም የጌታችን ኢየሱስ ተከታዮች እንዲሆኑ አድርጓል። ከዕርቅ ሥነ ሥርዓት በኋላም፣ በአካባቢው ላይ ዝናብ እንደገና መጣል ጀመረ።

❧

አማኞች ለዓመታት እጅግ በጣም ጽኑ ስደት እና ተቃውሞ ቢደርስባቸውም፣ ቤተ ክርስቲያን ግን እድገቷን ቀጥላለች። እግዚአብሔር የወንጌልን ስብከት በመባረኩ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሕይወት ተለውጧል፣ ቤታቸው ተለውጧል እንዲሁም ማኅበረሰባቸው አድጓል። በጣም በብዙ መቶ፣ በሺህ የሚቆጠሩ ጣዖት አምላኪዎች የነበሩ ሰዎች ክርስቲያን ሆነዋል። አብያተ ክርስቲያናት በዝተዋል፣ የቀለም ትምህርት ቤቶች ተጀምረዋል፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ተጀምረዋል እንዲሁም በኋላ ላይ የሕክምና መስጫ ክሊኒኮች እየተከፈቱ ተበራክተዋል።

በቀድሞ ዘመናት የጋሞ ክርስቲያኖች በጨንቻ በሚገኘው የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮን ጣቢያ ለመጽሐፍ ቅዱስ ኮንፍራንስ ይገናኙ ነበር። ይህም ኮንፍራንስ ለብዙ ቀናት የሚቆይ የኅብረት፣ የአምልኮ፣ የጸሎት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ስብሰባ ነበር። በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ ስፍራው ይመጣሉ። እነዚህ በዓመቱ እግዚአብሔርን በአንድነት የማመስገኛና በአካባቢው የወንጌልን ሥራ ለሚሠሩ ሰዎች እርዳታ ማሰባሰቢያ ትላልቅ ቀናት ነበሩ። በዚያ አካባቢ ብዙ የሰላም፣ የቤተ ክርስቲያን ቍጥር እድገትና የክርስቲያኖች እድገት የታዩባቸውን ብዙ ዘመናትን ተመልክተዋል።

ከዚያ በትላልቅ ከተሞች ውስጥ ግን ብጥብጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተነሣ መሆኑ ይሰማ ጀመር። በሁሉም ስፍራዎች የተለያዩ ሰላማዊ ሰልፎች ይደረጉ ነበር። አገሪቱን በጠቅላላ ያጥለቀለቀው የኢ-አማኒያን ለውጥ ማንም ያልጠበቀው ነበር። ይህ ለውጥ ደግሞ በብዙ የእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ትልቅ ተቃውሞን፣ ስደትን፣ መከራን እና ሞትን አስከትሏል። በኢትዮጵያ ውስጥ የኮምዩኒስት መንግሥት ለአሥራ ሰባት ዓመታት በገዛበት ወቅት የወንጌልን ብርሃን ለማጥፋት በመጣር ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተዘግተዋል፣ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ተቃጥለዋል፣ ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተገድለዋል ወይም ታስረዋል።

እግዚአብሔር እነዚህ መከራዎች ለምን እንዲከሰቱ ፈቀደ? ቤተ ክርስቲያኑን

ለማጥራት ይሆንን? ይህ ስደት ክርስቲያኖች በመኖሪያ ቤታቸው ወይም በጫካ ውስጥ እንዲሰበሰቡ አስገድዷቸው ነበር። የአማኞች ቁጥር ከዕጥፍ በላይ ያደገው ግን በዚህ የአሥራ ሰባቱ ዓመት የስደት ወቅት ነበር፤ ከዚያም እንደገና በዕጥፍ አደገ!

የኮምዩኒስት ገዥዎች ‹‹ቀይ ሽብር›› ብለው በሚጠሯዋቸው በጣም አሰቃቂ ዓመታት፣ ከዚህ በፊት ስናገለግል ወደ ነበርንበት አካባቢ ተመልሼ ነበር። ምሥጢራዊ በሆኑ የምሽት ተከታታይ ስብሰባዎች መጋቢዎችን፣ ወንጌላውያንን እና ሽማግሌዎችን ለማበረታታት ጥሬያለሁ። ስለ ጌታ ኃይልና ታማኝነት ከእግዚአብሔር ቃል እየተከፋፈልን በአንድነት ስንጸልይ፣ በኩባ፣ ቻይና እና ሩሲያ ውስጥ ያሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ‹‹የቤት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን›› እንዴት እንደ ጀመሩና ያንንም የጸሎት፣ የአምልኮ እና ጎብረት ማድረጊያ ቦታ እንዳደረጉት ነገርኋቸው።

ኢትዮጵያውያን አማኞችም ተመሳሳይ ነገርን አደረጉ። ወዲያውም በመቶዎች የሚቆጠሩ ጠንካራ የቤት ውስጥ አብያተ ክርስቲያናት ተጀመሩ። እነዚህ የቤት ውስጥ አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት እና እርስ በርስ ለመበረታታት ብቻ ሳይሆን፣ ‹‹የርኅራኄ የወንጌል ስርጭት›› ለማድረግና አዳዲስ አማኞችን ለማስተማር ይጠቀሙበት ነበር። የጥምቀት ሥርዓት ከአሥር ወይም ከሃያ ላልበለጡ ሰዎች በምሽት ይደረግ ነበር። ምንም እንኳ ብዙ ሰዎች መከራ ቢቀበሉም፣ የጌታ ሥራ ግን ቀጥሏል። በእርግጥ፣ በሚያሳዝን ሁኔታ፣ በጣም ጥቂት ሰዎች መከራው ወይም ግርፋቱ ሲበረታባቸው ወደ ኋላ ተመልሰው ጌታን ክደዋል። ጥቂቶች የኮምዩኒስቶች ካድሬ በመሆን ክርስትናን ክደዋል። እንዲያውም አንዳንዶቹ የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አሳዳጆችና ጨቋኞች ሆነዋል።

አሁን ደግሞ ከፍ ባሉት በጋሞ ተራሮች ላይ ዓመታዊ ስብሰባ እንደገና እየተካሄደ ነበር። 9000 ጫማ (2800 ሜትር) ከፍታ በላይ በሆነ ስፍራ ላይ ነን፤ የጨንቻ ከተማ ማታ ማታ ሁልጊዜ ትቀዘቅዛለች፣ ነገር ግን ቀን፣ በደመናው ውስጥ ፀሐይ ብርሃኗን ስትፈነጥቅ ትሞቃለች። ከዝቅተኛ ስፍራ የመጡ ጉበኝዎች ይህች ከተማ ቀዝቃዛ እና ጭጋጋማ መሆኗን አማርረው ይናገራሉ።

በጨንቻ የሚገኘው የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮን ጣቢያ የአባያ እና የጫሞ ሐይቆችን ለማየት ጥሩ ቦታ እንደ ሆነ ይነገርለታል። እነዚህ ሐይቆች በራሳቸው በዓሣ ምርታቸው እና በውስጣቸው ባሉት አዞዎች ይታወቃሉ። በሁለቱ ሐይቆች መካከል የሚገኘው ቀጭን መሬት ዛሬም ድረስ ‹‹የእግዜር ድልድይ›› ተብሎ ይጠራል። በሁሉም አቅጣጫ በአቅራቢያው ከሚገኙ ተራሮች ላይ የሚፈስሱ ወንዞች ሁሉ በትንሹ የጫሞ ሐይቅ ውስጥ ይጠራቀሙና በዝናብ ወራት ሞልተው ወደ አባያ ሐይቅ ይፈሳሉ።

ነገር ግን፣ የዚያ ዓመት የዝናብ ወራት በተለመደው ሁኔታ በመስከረም መጨረሻ ላይ አልተጠናቀቀም። ከዚያ በኋላ ለወራት ያህል አልፎ አልፎ ከባድ ዝናብ ይጥላል፣ እንዲሁም ከፍተኛ ዐውሎ ንፋስ ይነፍሳል! ይህ ዓይነቱ ልዩ ስብሰባ ብዙ ጊዜ የሚዘጋጅበት ወራት የበጋ ወራት ነበሩ። በእርግጥ፣ ለጥቂት ወራት ያህል ጥሩ፣ ፀሐያማ እና ሞቃት ጊዜያት ነበሩ፤ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎችም ተሰብስበው ነበር። አንዳንዶች በጥላ፣ በሣር እና ቅጠል ሥር በመቀመጥ ከፀሐይ ሐሩር ራሳቸውን ይከላከሉ የነበሩ ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ ፀሐዩን ይፈልጉት ነበር።

ያ ቀን የስብሰባው ማጠቃለያ ቀን ነበር። በጣም ከባድ ደመና ተሰብስቦ ሰማዩ አጥቁሮት ስለ ነበር በጣም ያስፈራ ነበር። ያን ቀን ከሰዓት በኋላ መብረቁ በአጥሩ ምዕራብ በኩል በሚገኙ ተራሮቹ ላይ መባረቅ ሲጀምር፣ እኔ ገና የመልእክቱ አጋማሽ ላይ ነበርሁ። ወዲያው በጣም የሚያስፈራ መብረቅ በሁሉም አቅጣጫ ይታይ ጀመር። ሰማዩ ጠቁሯል፣ መብረቁ ምድርን ያናውጣት ጀመር። በዐውሎ ንፋስ እየታገዘ የዝናብ ዶፍ ወደ እኛ ይገሰግስ ጀመር።

ዝናቡ፣ እንደ ጥቁር የውኃ ግድግዳ የሚስዮን ጣቢያው ቅጥር ሊደርስ ትንሽ ሲቀረው ሰው ሁሉ መጠለያ ፍለጋ ከመቀመጫው ተነሣ። ከዚያ ጌንቦ ከመቀመጫው በመነሣት ዝናቡ ባለበት እንዲቆም አዘዘው! እርሱም ቆመ! እዚያው ከቀርከሃ በተሠራው አጥር አጠገብ፣ ወፍራም የውኃ ግድግዳ ሆኖ ቆሞ ቀረ! በዚያ አካባቢ ባሉ ስፍራዎች ውስጥ ሁሉ በከባድ ሁኔታ እየዘነበ ነበር፤ ነገር ግን እኛ በምንገኝበት አጥር ግቢ ውስጥ ደረቅ መሬት ነበር። ጨለማው አስፈሪ ነበር፣ ግን ደረቅ ነበር! ባየነው ነገርም እጅግ በጣም

ተገረምን።።

ከዚያ ጌንቦ ስብከቴን እንድቀጥልና መልእክቴን እንድጨርስ ነገረኝ።። ለሚቀጥሉት ሃያ ወይም ሠላሳ ደቂቃዎች፣ የክርስቶስን ወንጌል ሰበክሁኝ፤ ሰዎችም ለስብከቴ ምላሽ ሰጡኝ።። በጣም ጥቂቶች ሰዎች አልፎ አልፎ ከአጥሩ ውጭ ወዳለው ዝናብ ይመለከቱ ነበር፤ ነገር ግን አብዛኛዎቹ በጸጥታ ተቀምጠው የእግዚአብሔርን ቃል ያደምጡ ነበር።። የንስሐ ጥሪ ከተደረገ በኋላ፣ ለጥሪው ምላሽ ለሰጡና አብረዋቸው ለጸለዩ ሰዎች መሪዎች ንግግር አደረጉ።። ከዚያ አሁን ስለ ተመለከትነው ስለ እግዚአብሔር ኃይልና ታማኝነት ዝማሬ ዘመርን!

ጌንቦ የመዝጊያውን ጸሎት በመጸለይ ስብሰባው ተጠናቀቀ።። ከዚያም ጌንቦ ለሕዝቡ በፍጥነት መጠለያ እንዲፈልጉና በተለያየ አቅጣጫ ወደ መኖሪያ ቤቶች፣ መማሪያ ክፍሎችና ማደሪያ ቤቶች እንዲሄዱ ነገራቸው።። ከትንሽ ደቂቃ በኋላም ዝናቡ ግቢውን ሙሉ አጥለቀለቀው።። ቦይዎች ሞልተው ፈሰሱ፣ ቆሻሻ ውኃ አራት ኢንች (አሥር ሴንቲ ሜትር) ከፍታ ያህል ሆኖ ግቢውን ሞላው።።

በዚያ ከሰዓት በኋላ የሰበክሁት ስብከት ምን እንደ ሆነ ከመቆየቱ የተነሣ አላስታውሰውም (ሕዝቡም እንዲሁ ስብከቱን እንደማያስታውሱት እርግጠኛ ነኝ)፣ ነገር ግን ጌንቦ እግዚአብሔርን በማመን ዝናቡን ማስቆሙን አስታውሳለሁ!

> *‹‹የማይመረመረውን ታላቅ ነገርና የማይቈጠረውን ተአምራት ያደርጋል። በምድር ላይ ዝናብን ይሰጣል፣ በእርሻም ላይ ውኃ ይልካል።››*
>
> *ኢዮብ 5፡9-10*
>
> *‹‹ለነፋሱ ሚዛንን ባደረገለት ጊዜ፣ ውኆችንም በሰፍር በሰፈረ ጊዜ፣ ለዝናብም ሥርዓትን፣ ለነጐድጓድ መብረቅም መንገድን ባደረገ ጊዜ፣››*
>
> *ኢዮብ 28፡ 25-26*
>
> *‹‹ . . . ለፈሳሹ ውኃ መንዶልዶያውን፣ ወይስ ለሚያንጐደጕድ መብረቅ መንገድን ያበጀ ማን ነው?››*
>
> *ኢዮብ 38፡25*

10

ገብሬ

ከዓርበኛ ተዋጊነት ወደ ቅዱስነት

በቁጥጥር ውስጥ የዋሉ ቀኣጣ፣ ቀዝቃዛ ስሜትና ያውጠነጠነው ዕቅዱ የሰውዬውን ልብ ሞልተውት ነበር። ለዚህ ቀን ዝግጅት ሲያደረግ የእያንዳንዱ እንቅስቃሴ መነሻ ጥላቻ ነበር። ትናንሽ ድንጋዮችን ሲሰበስብ፣ ቡና ሲፈለፍል እና ብረት ሲቀጠቅጥ፣ አንዳንድ ትላልቅ የብር የማሪያ ቴሬዛን ገንዘብ እና ትናንሽ ሳንቲሞችን ሲቀጠቅጥ ገብሬ ሁልጊዜ የሚያሰላስለው ስለ አንድ ነገር ብቻ ነበር። ሁሉንም በመቀላቀል ከፍየል ቆዳ በተሠራ ቦርሳው ውስጥ አስቀመጣቸው። ሳንቲሞቹ እንዲያቃጭሉ በቂ ስፍራ ተወላቸውና የቦርሳውን አፍ ከቆዳ በተሠራ ጠፍር አሰረው። ማንም ሰው እንዳይፈታቸው አድርጎ በማሰር፣ ምልክት አደረገባቸው።

ከዚያ ገብሬ ጩቤ ወስዶ በአፎቱ ውስጥ አስገባና በእግሩ ላይ አሰረው። በደንብ ከሰውነቱ ጋር ያልተጣበቀውና የተቀዳደደው ቀኣምጣው የያዘውን መሣሪያ ደብቆለታል። የቆሸሸ ነጠላውን ከወዲሁ ጣል ስላደረገው፣ የተሸከመውን የቆዳ ቦርሳ ሸፍኖታል። ገብሬ ለዓመታት ይህችን ቀን ሲጠብቃት ቆይቷል። ሁለንተናውም በጥላቻ እና በበቀል አሳብ ተሞልቶ ኖሯል። ዛሬ የአባቱን ገዳይ ይበቀላል። ይህንን ለማድረግ የከብር ግዴታ አለበት። ዛሬ አልቴን ይገድለዋል።

ሠ

የገብሬ አባት፣ አቶ ዜማ፣ በማሎ ወረዳ የሚኖሩ ሀብታም ሰው ነበሩ። በማደግ ላይ ባለው ቤተሰብ ውስጥ በቆሎ፣ ማሽላ እና ገብስ ይዘራል፤ ከዚህ በተጨማሪ ስኳር ድንች እና የሸንኮራ አገዳ ተክለዋል። በአሥራዎቹ ውስጥ

ከሚገኘው ልጃቸው ከገብሬ ጋር በመሆን የቡና ፍሬና ቅመማ ቅመም በመልቀም ከነበቅሎዋቸው ለሚመጡ ነጋዴዎች ይሸጣሉ።

በጣም ዐቀበታማ፣ እና እንደ ምሰሶ ከቆሙ ተራራዎቿ፣ እንዲሁም ጥልቅ ሸለቆዎቿ ጋር ማሎ ወባ ያለባት፣ ‹‹ጉልበት ላለው ትከክል›› ፍትሐዊ ሕግ ያላት፣ ለደካሞች ግን ምንም ርኅራኄ የሌላት አገር ነበረች። ትልቁ የአሞ ወንዝ በማሎ ሰሜናዊና ምዕራባዊ ድንበርን ታከኮ ያልፋል። ከባድ የሆነ ወራጅ ውኃ እና ብዙ አዞዎች በመኖራቸው ምክንያት፣ ብዙ ሰዎች ይህንን አካባቢ እንዲሸሹ አድርጓቸዋል። መንገድ፣ መጓጓዣ እና መገናኛ አለመኖርና የመንግሥት አውታሮች አለመኖራቸው ነገሩን አባብሶታል። ሰዎች ለአካባቢው የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ቀረጥ ይከፍላሉ፤ የተወሰነውም ቢሆን ለተገቢው አካል ወደ ቡልቂ ይላካል። ነገር ግን፣ ያ ስፍራ የሦስት ቀን የእግር ጉዞ ነበር። በጣም ጥቂት ሰዎች አብዛኛውን መሬት ተቈጣጥረውታል፤ ስለዚህም አብዛኛው ሕዝብ ለእነዚህ ባለ ርስቶች አገልጋይ ነበር።

የማሎ ሰዎች የሚኖሩት በፍርሃት ነበር። ከእነርሱ በፊት እንደ ኖሩት አባቶቻቸው ሁሉ፣ እነርሱም ባህላዊ እምነት ነበራቸው፤ ፈጣሪ በጣም እሩቅና ሊደረስበት የማይቻል እንደ ሆነ ያምናሉ። አካባቢያቸው በሙሉ በመናፍስት የተሞላ ነበር። ክፉ መናፍስትንና የቅድመ-አያቶቻቸውን የሙታን መንፈስ ያመልካሉ፤ የሰብል፣ የቡና ወይም የቅቤ መሥዋዕቶች እንዲሁም በሕመም ጊዜ የዶሮ፣ የፍየል ወይም የበግ ደም መሥዋዕት ያቀርባሉ። በጣም ከፍ ያለ ሁኔታ ከሆነ ደግሞ፣ ጠንቋዩ በሬ እንዲያርዱ ሊጠይቅ ይችላል። ይህ ግዴታ በቤተሰቡ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖን ይፈጥራል፣ ብድር ውስጥ እንዲገቡ ያደረጋል፣ በዚህም ድህነታቸውን ያባብሳል። በዚህ ሁሉ ፍርሃት ነበር፤ የድንቍርና ፍርሃት፣ ሰዎቹን በጨለማ መንፈስ ውስጥ እንዲቀመጡ ያደረገ የሞት ፍርሃት ነበር።

አልቴ በማሎ ውስጥ የሚገኝ እጅግ በጣም ሀብታምና ኃይለኛ የሆነ ባለ ርስት ነበር፣ እጅግ በጣም ክፉና ጨካኝ ሰውም ነበር። ማንም ሰው በመንገዱ ላይ እንዲቆም አይፈቅድም፤ የፈለገውን ነገር ሁሉ ይወስዳል። በዚሁ መሠረት፣ አልቴ የዜማን ለም የእርሻ መሬት ፈለገ። ጥያቄውን ሲያቀርብም ለዘመናት ሲሠራበት የነበረውን ማስፈራሪያ ተጠቀመ፣ ነገር ግን አሁን አልሠራለትም፣ ስለዚህ ዜማን በጭካኔ ገደለው። አልቴ ግድያውን የፈጸምሁት ራሴን

ለመከላከል ነው በማለት ብዙ ምስክሮችን በማቅረቡ ምክንያት ምንም እርምጃ አልተወሰደበትም። ዜማ ምንም መሣሪያ ባልያዘበት ሁኔታ ራስን መከላከል! ምን ይባላል! ገብሬ ይህ ነገር ሲሆን እየተመለከተ ነበር፤ የአባቱንም ደም ለመበቀል ማለ። በማሎ ውስጥ ነገሮች የሚሠሩት እንዲህ ባለ ሁኔታ በመዝረፍ፣ በመበቀል ነበር።

የፋሽስት ጨካኝ መሪ የነበረው ሙሶሎኒ ኢትዮጵያን እንዲወርሩ ጣልያናውያን ወታደሮቹን ሲልክ፣ በአገሪቱ ውስጥ የነበሩ ወንዶች ሁሉ የመጣባቸውን ወረራ ለመመከት በበጎ ፈቃደኝነት ዘምተዋል። ብዙ ወንዶች ከማሎ ወደ ሰሜን ግንባር ተጉዘዋል። እነርሱም ዘመናዊ የጦር መሣሪያ፣ ቦምብ እና የጦር ጀቶችን እንዲሁም መርዛማ ጢስ በደንብ በታጠቁ ጣልያናውያን ተለቅቆባቸዋል። ከዚያ የተረፉት ብዙዎቹ ተመልሰው ገበሬ ቢሆኑም፣ ያው ተመልሰው የአዲሱ ጌታቸው አገልጋይ ነበር የሆኑት። አንዳንዶች እንደ አልቴ ከፋሽስቶቹ ወገን በመሆን ጎረቤቶቻቸውን በመክዳት እና በመሰለል ፋሽስቶቹን ያገለግሉ ነበር።

ወጣቱ ገብሬ ሚስቱን እና ልጆቹን በመተውና ጥቂት ጀግኖችን በመሰብሰብ ወደ ጫካ ገባ። በፍጥነት የደፈጣ ውጊያ ስልትን ተማሩ። ብዙ ጊዜ የሚያደርጉት ነገር ጠመንጃ መቀማት፣ የጣልያን ወታደሮችን መደብደብ፣ የስንቅ መሥመራቸውን እንዲቋረጥ ማድረግ እና ጣልያናውያንን የሚያግዝ ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ መቃወም ነበር። ብዙ ጊዜ ጣልያናውያን በማሎ ያለውን የጀግኖች ግንባር ለማከሰም የተለያዩ መንገዶችን ተጠቅመዋል። ገብሬ እና ጓደኞቹ ግን ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሱ ነበር፤ በአሞ ወንዝ ሸለቆ ውስጥ ወደ ተለያዩ ስፍራዎች ይንቀሳቀሳሉ፣ በአንድ ስፍራ ለረጅም ጊዜ አይቆዩም። መምታትና መሮጥ፣ መምታትና መሮጥ የውጊያ ስልታቸው ነበር። መትቶ መሮጥ፣ ቦታ መቀየር እና በጫካው ውስጥ ወይም በድንጋያማው ተራራ በማለፍ በስንጥቅ ዓለቶች መካከል መደበቅ እነዚህ ሁሉ ስልቶቻቸው ነበሩ።

የገብሬ ቡድን በአጭር ጊዜ ውስጥ ታማኝ ዓርበኞች የሚል ስያሜን አገኘ። ፋሽስቶች ዓርበኞቹን ይዞም ሆነ ገድሎ ላቀረበ ሰው ጥሩ ወሮታ እንደሚከፍሉ ተናገሩ። ብዙ ጊዜ አልቴ የታጠቁ የራሱን ሰዎችና ጥቂት የጣልያን ወታደሮችን

በመምራት ሽፍታዎች ብለው የሚጠሯቸውን ገብሬን እና ጓደኞቹን ለመያዝም ለመግደልም ሞክሯል። ምንም ያህል ሙከራ ቢያደርጉም፣ ገብሬን እና ጓደኞቹን ግን ማግኘት አልቻሉም። ገብሬ እና የእርሱ ሰዎች አደጋ ያለበትን ስፍራ ለቅቀው እንዲሄዱ ስንቅ የሚያቀብሏቸው ጓደኞቻቸው ማስጠንቀቂያ ይሰጧቸው ነበር።

ይህ በየጊዜው የሚያደርጉት ውጊያ፣ ሩጫ፣ መደበቅ፣ የእንቅልፍ ማጣትና የምግብ እጥረት በገብሬ ሰዎች አካል ላይ በጣም ከባድ ጉዳት አደረሰ። በኋላ ላይ የጣልያን ጦር ተሸነፈና ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ከእንግሊዝ አገር ወደ አገራቸው ተመለሱ። የእርሳቸው ጥበብ የተሞላበት መንግሥት እና አገዛዝ ተመልሶ በመምጣቱ ትልቅ ደስታ ነበር የሆነው። እንደነ ገብሬ ያሉትን ጀግኖች ሽልማት ሲሰጧቸው ለጣልያን ጦር ኢጋዥ ለነበሩት ደግሞ ምሕረት አድርገውላቸዋል።

ገብሬና ጓደኞቹ ወደ ማሎ ሲመለሱ አልቴ ራሱን ጠላትን ሲቃወሙ ከነበሩ ሰዎች ጋር እንደ ነበረ አድርጐ በማቅረብ በአካባቢው ትንሽ ባለ ሥልጣን ሆኖ አገኙት። አልቴ ‹‹የደኅንነት ኃይላት›› የሚል ስያሜ የሰጣቸውን ሰዎች በመጠቀም የብዙዎችን ሀብት ዘርፏል፣ እንዲሁም ገበሬዎችን ጢሰኛ በማድረግ ትልቅ ቀንበር ጭኖባቸዋል። አልቴ በዚህ በጣም ሀብታም ሲሆን፣ ሰዎች ለእርሱ ያላቸው ጥላቻ እጅግ በጣም እያደገ መጣ። እነርሱ ምንም ነገር ማድረግ አልቻሉም፣ አልቴ የበለጠ ግብር ሲጠይቃቸው፣ በጣም ስለሚፈሩት ምንም ማድረግ አይችሉም ነበር። በአልቴ ያልተገባ ሥራ የተነሣ የሰዎች ብስጭት እና ቊጣ እያየለ ከመምጣቱም በላይ፣ ክፉ የሆነ ኢ-ፍትሐዊነት በመላው የማሎ አውራጃ ውስጥ ነገሠ።

ገብሬ እንደ ሌሎቹ ሰዎች ሁሉ ውስጡ በቊጣ ነደደ፤ ብቀላውንም በደንብ ዐቀደ። በጫካ ውስጥ አብረውት ከነበሩ ሰዎች ጋር በመሆን ጥሩ አጋጣሚን ይጠባበቅ ነበር። የገብስ ማሳ ላይ የበቀለው ገብስ ከተሰበሰበ በኋላ በብዙ አህያዎች ገብሱን ጭነው ይወስዱ ነበር። የተቀዳደደ ልብስ የለበሱ ድኾች በአንድነት ወደ አልቴ መኖሪያ ሰፈር ያቀናሉ። የታጠቁ ሰዎች በግቢው መግቢያ ላይ ያስቆሟቸዋል። አንገታቸውንም ዝቅ እንዳደረጉ ለአልቴ ስጦታ እና

መልእክት እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ ከዚያም የመኖሪያ ቤቱ ደጃፍ ድረስ እንዲሄዱ ይፈቀድላቸዋል፡፡ አልቴ የመጣለትን ስጦታ ከቤት ውስጥ ሆኖ ማየት እንዲችል ሠራተኞቹ የመኖሪያ ቤቱን በር በደንብ ከፍተውታል፡፡

አልቴ በጣም ትልቅና ወደ ኋላ ለጠጥ ባለ ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ክራሩን ይመታል፡፡ በጣም ትልቅ ቡሉኮ ማለትም ወፍራም ብርድ ልብስ መሰል ልብስ፣ እግሮቹን የተከናነበ ሲሆን፣ ክራሩን እየተጫወተ የሚጎነጨው በቂ አረቄ በአጠገቡ ተቀምጦለታል፡፡ ስጦታውን ለመቀበል ከመቀመጫው እንኳ ለመነሣት አይሞክርም፡፡ ገብሬ ገብስ የያዘውን ኩንታል የት ማስቀመጥ እንዳለበት እየጠየቀ በለሆሳስ አጉረመረመ፡፡ በበረንዳው ላይ እንዲያከማች ተነገረው፡፡ ነገር ግን ገብሬ እርሱም ለአልቴ ልዩ መልእክት እንዳለው ሲናገርና ገንዘብ የያዘበትን ከረጢት ሲያሳይ አልቴ ወደ ውስጥ እንዲገባና በእግሮቹ ሥር እንዲያስቀምጥ ነገረው፡፡ አልቴ፣ ገብሬ ማን እንደ ሆነ አላወቀም ነበር፤ እንደ ሌሎቹ ጢሰኞች ለብሷልና፡፡

አልቴን እየቀረበው ሲመጣ፣ ገብሬ በጣም አጐንብሶ የያዘውን ቦርሳ አቃጨለ፡፡ በአልቴም እግር ሥር አስቀመጠውና እንደ ባሪያ የአልቴን እግር የሚስም ይመስል በጣም አጐነበሰ፡፡ በፍጥነት ቦርሳውን አንሥቶ ወደ አልቴ ጭንቅላት ወረወረ፡፡ በፍጥነትም ጩቤውን በማውጣት በአልቴ ደረት ላይ ሰካው፡፡ ‹‹ይህ ለአባቴ ነው፣›› በማለት ሁለት፣ ሦስት እና አራት ጊዜ ያህል ደረቱን ወጋውና የአባቱን ገዳይ ተበቀለ፡፡

ከዚያ ገብሬ በታላቅ ድምፅ፣ ‹‹አልቴ ሞቷል!›› በማለት ጮኸ፡፡ ይህ ከግቢው ውጭ ተደብቀው ላሉት ጓደኞቹ በጥበቃዎቹ ላይ ጥቃት እንዲያደርሱ ምልክት ነበር፡፡ በአልቴ ሞት ግራ ተጋብተው ጥበቃዎቹ ጠመንጃዎቻቸውን ጥለው እየሮጡ ጠፉ! ዜናው ከአንዱ መንደር ወደ ሌላ መንደር ሲሰራጭ ከፍተኛ አግራሞትን ፈጥሯል፡፡ ሰዎች በመጨረሻ አምባገነኑ ስለ ተወገደላቸው በጣም ተደስተዋል፡፡ ብዙዎች መጥተው ከአልቴ ቤት መውሰድ የሚችሉትን ነገር ዘርፈዋል፡፡

ሰዎች በቡልቂ ወደሚገኙት የመንግሥት ባለ ሥልጣናት የአልቴ መሞት ዜና ሲደርስ ሊከሰት ስለሚችለው ነገር ምንም ነገር ማወቅ አልቻሉም፡፡ ገብሬ ግን ምን ሊከሰት እንደሚችል ማወቅ አልፈለገም ወይም እስኪሆንም ድረስ መጠበቅ

አልፈለገም፡፡ ሙሉ ቤተሰቡን እና ያለውን ንብረት ሁሉ ሰብስቦ፣ ማሎን ለቅቆ የአሞን ወንዝ ተሻግሮ በኮንታ ተቀመጠ፡፡ ኮንታም ብዙ ለም መሬትና ጥሩ ውኃ ያለበት አካባቢ ነበር፡፡ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ገብሬ መሬቱን ከቤተሰቡ ጋር ሲያርስ ቆየ፡፡ በዋካ የሚገኘው ገዥ፣ ገብሬን ይቅር ስላለው ገብሬ ወደ ማሎ ተመለሰ፡፡

የማሎም ሰዎች ክፉውን አልቴን ላስወገደላቸው ለገብሬ የጀግና አቀባበል አደረጉለት፡፡ በራሳቸውም ላይ አለቃ አድርገው ሾሙት፡፡ ገብሬ የአባቱን መሬትና ንብረት መልሶ ማግኘት ቻለ፡፡ ገብሬ በአልቴ ሞት ተጠይቆ አያውቅም፡፡ በዚያ አካባቢ ለብዙ ዘመናት ረብሻ ነበር፣ ነገር ግን አሁን ሰላም ሆኗል፡፡ ሁሉም ጸጥ ብሏል፣ ብዙ ጊዜያትም አልፈዋል፡፡

ፈቃ

አንዳንድ እንግዳ ታሪኮች በማሎ የገበያ ስፍራዎች ላይ ተራሮች አቋርጠው መሰማት ጀመሩ፡፡ ገብሬም እነዚህ ታሪኮች እውነት ይሆኑ ወይ? በማለት ተገረመ፡፡ ከጎፋ የመጡ ተጓዦች አዲስ ሕይወትን የሚሰጥ አዲስ ሃይማኖት የመምጣቱን ዜና ተናገሩ፡፡ አንዳንዶች ይህ ፍርሃትን በማስወገድ ሰላምንና ተስፋን የሚሰጥ መልካም ዜና መሆኑን ይናገሩ ነበር፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ይህ መጥፎና የመንግሥት ባለ ሥልጣናት እንዲሁም የሃይማኖት መሪዎች የተቃወሙት ነገር እንደ ሆነ ያወሳሉ፡፡

ከዚያም ፈራኞ፣ ቶማስ እና ናና የተባሉ ወንጌላውያን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል እየሰበኩ ወደ ማሎ መጡ፡፡ ከሕዝቡ መካከል አንዳንዶች ለሰሙት መልእክት ምላሽ በመስጠት አዳኙን ጌታ ሲቀበሉ፣ ተቃውሞው እየባሰ ሄዶ ወንጌላውያን ተደበደቡ፣ እንዲሁም በወኅኒ ተጣሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ከእስር ሲፈቱ ወንጌላውያኑ ሐሜት ሲያደርጉና ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ጸጋ ንግግራቸውን መቀጠላቸውን ሲመለከቱ፣ ሁሉም ሰዎች በጣም ተደነቁ፡፡ ኢየሱስ መንገድ ነው፣ ወደ ታላቁ ፈጣሪ መመለሻ ብቸኛው መንገድ ኢየሱስ ነው በማለት ይናገሩ ነበር፡፡ ምንም እንኳ ድብደባና ስደት ቢደርስባቸውም፣ ወንጌላውያኑ በመንደርና በገበያ ስፍራዎች እንዲሁም በመኖሪያ ቤቶችና በገበሬዎች የእርሻ ማሳዎች አካባቢ ወንጌል ይናገሩ ነበር፡፡

ወንጌላዊ ቶማስ ጥቃት ደርሶበት ነበር፣ በጣም ከመደብደቡ የተነሣም በሞት

አፋፍ ላይ ደርሶ ነበር። ወደ ወላይታ እንዲመለስ ተደርጎ ለብዙ ወራት በሶዶ ሆስፒታል ውስጥ የሕክምና ክትትል ሲያደርግ ቆይቷል። ዶክተሩ ለቶማስ ከእንግዲህ ልጅ ሊኖርህ አይችልም ብሎ ሲነግረው በጣም አዝኖ ነበር። ቶማስ ሰውነቱ እስኪድን ድረስ በወላይታ ለብዙ ወራት ቆየ። በኋላ ላይ ግን ሚስቱ ወዳለችበት ወደ ማሎ ተመለሰ፤ ይህ ነገር በእርግጠኝነት ዶክተሩን አስገርሞታል። ቶማስ ሰባት ሴት ልጆች ሲኖሩት ወንድ ልጅ ግን አልነበረውም።

ገብሬ የኢየሱስን ታሪክ በሰማ ጊዜ ነገሩ ስቦት በጣም ብዙ ጥያቄዎችን ይጠይቅ ነበር፤ ወንጌላውያኑም በደስታ ይመልሱለት ነበር። ገብሬ ይህ አዲሱ ሕይወት በእርሱና በቤተሰቡ ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንደሚፈጥር ማወቅ ይፈልግ ነበር። ወንጌላዊ ፌራኞ ገብሬን ወደ ክርስቶስ መርቶታል። ገብሬ በአደባባይ ኃጢአቱን ተናዝዟል፣ ሰይጣንን ክዷል፣ የመናፍስት አምልኮንና የደም መሥዋዕትን በመካድ በሙሉ ልቡ ወደ አዳኙ መጥቷል። በገብሬ ውሳኔ ውስጥ ምንም ልዩ የሆነ ነገር የለም፣ ነገር ግን ይህ በማሎ ታሪክ ውስጥ ለውጥ የጀመረበት ስፍራ ነበር።

ወዲያው ገብሬ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶችን ማድመጥ፣ የእግዚአብሔርን መንገድ መማርና ወንጌላውያኑን በወንጌል ስርጭት ማገዝ ጀመረ። ሕይወቱ በሙሉ ተለውጦ ነበር። ገብሬ በመኖሪያ ቤቱ አቅራቢያ የሚገኘውን ትንሽ መሬት ለቤተ ክርስቲያን ሰጠ፤ በዚያ ስፍራም የጸሎት ቤት ሠሩበት። ከወንጌላውያኑ ጋር በመሆን ቤተሰቡን ወደ ጌታ መራቸው። እንዲሁም ብዙዎቹ ጎረቤቶቹ ወደ ክርስቶስ ተመልሰዋል። ስደት መጣ፤ ገብሬም ከሌሎች አማኞች ጋር ሆኖ ለብዙ ጊዜ ታሰረ። ተቃውሞና መከራ የገብሬን እምነት የሚያጠነክሩ ነገሮች ብቻ ሆነው ተገኝተዋል።

ገብሬ በማሎ ውስጥ ወደ መሪነት በማደግ ላይ ከነበሩ መሪዎች መካከል አንዱ ነበር። እንደ ሽማግሌ፣ ወጣቶችን ማማከር፣ የቤተ ክርስቲያን ሥራዎችን አቅጣጫ ማስያዝና ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ማሳየት ያሉ አገልግሎቶችን ጀመረ ። ከጊዜ ወደ ጊዜ ብዙ ሰዎች ወደ ኢየሱስ መምጣት ጀመሩ፤ የቤተ ክርስቲያንም ቍጥር እየጨመረ መጣ። በዚያ አካባቢ የቤተ ክርስቲያን ትንሽ ትምህርት ቤት እንዲከፈት እገዛ አድርጓል። የእርሱ የራሱ ቤተሰብ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ እንዲችሉ እና ጌታን እንዲከተሉ ይፈልጋል። ከዚያ መጋቢያንንና ሽማግሌዎች

በማደግ ላይ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት መምራት እንዲችሉ ለማሠልጠንና ወንጌላውያን በዲማ፣ ቦዲ፣ በና እና ጻራ ጎሳዎች እና በወንዝ አካባቢ ባሉ አዳዲስ የሠፈራ ቦታዎች ወንጌል ላልደረሳቸው ሰዎች ወንጌል እንዲያደርሱ ለማስታጠቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተከፈተ፡፡

ገብሬ፣ ጌታ ወደ ራሱ እስከ ወሰደው ጊዜ ድረስ፣ ለአርባ ዓመታት በጣም የሚወድደውን ጌታ አገልግሏል፡፡ ወንድ ልጁ ብርሃኑ የሕክምና ሙያ አጥንቶ በማሎ ዋና ከተማ በላሃ መድኃኒት ቤት ከፍቷል፡፡ የብርሃኑ ሚስት ነርስ ስትሆን፣ በአካባቢያቸው ምንም ዓይነት ሆስፒታል ባለመኖሩ ምክንያት ብዙ ታማሚዎችን በየቀኑ ታክማለች፡፡ ገብሬ ልጁ ብርሃኑ ጌታውን እንዲያገለግል ጥሩ ምሳለኔትን ትቶ አልቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የእርሱ የልጅ ልጅ ዓለማየሁ በ2009 ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እግዚአብሔርን ለማገልገል ወንጌላዊ ሆኖ ተመርቋል፡፡

እግዚአብሔር በማሎ ሕዝቦች መካከል ስላደረገው የጸጋው ታሪክ ቢጻፍ፣ ራሳቸውን ለብዙ አደጋ አሳልፈው የሰጡ፣ የጨለማውን ኃይል የተገዳደሩና የወንጌልን ብርሃን ለሚያስፈልጋቸው ለጠፉ ሕዝቦች ያበሩ ብዙ ወንጌላውያን አሉ፡፡ እንዲሁም በክርስቶስ በማመን የመጡ፣ መደብደብ የደረሰባቸው፣ የታሰሩ እና የተገረፉ፣ ነገር ግን በዓመታት ውስጥ ታማኝ ሆነው የኖሩ በጣም ብዙዎች ናቸው፡፡ ከራሻ ገብሬ በላይ ግን የማንም ስም ገንኖ አይወጣም፡፡

> *‹‹. . . ስለ እናንተ ለብሮኝ የሚሠራ ባልንጀራዬ ነው፤ ስለ ወንድሞቻችን የሚጠይቅ ቢኖርም የአብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞችና የክርስቶስ ክብር ናቸው።››*
>
> 2ኛ ቆሮንቶስ 8፡23

የበና በር

እኔ በር ነኝ፡፡ በእኔ የሚገባ እርሱ ይድናል፡፡

የበና ሴቶች

እውነት እውነት እላችኋለሁ ማንም ቃሌን ቢሰማ፤ የላከኝንም ቢያምን የዘላለም ሕይወት አለው፡፡ አይፈረድበትም፤ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግሯልና፡፡

ሁለት የበና ወንድሞች ወንጌል በማሄ ሲነገር በማድመጥ ላይ



የቦዲ ክርስቲያን
ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ለጠራህ ምስጋናውን አውጅ



በቦዲ ውስጥ ያለ ወንጌላዊ

በጌታ ያለህ ደስታ ጥንካሬህ ነው፡፡

አንድ ወጣት በቦዲ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክራር ሲጫወት

አምላኬ ሆይ! ለአንተ እዘምራለሁ፣ በአሥር አውታር ባለው ዝማሬን አቀርባለሁ!

በቦዲ ውስጥ ባለች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ የኳየር አባላት

ማሄ በጊዩ የእግዚአብሔርን ቃል በመስበክ ላይ



ቃሉ በልቤ ውስጥ እንደሚነድድ እሳት በአጥንቴ ውስጥ ገብቷል፤ ልተወው ፈጽሞ አልችልም።።

ልጆቼ ሆይ፣ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም የኃጢአታችን ማሰተስሪያ ነው፣ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ።

ከእርሱም የሰማናት ለእናንተም የምናወራላችሁ መልእክት እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት።



የጊዩ ክርስቲያኖች ክብ በመሥራት ኅብረት ሲያደርጉ እናንተ ደግሞ ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ ያየነውንና የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ እናወራላችኋለን። ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው።

ጸጋ

መልእክተኛ

በእምነት የሚደረግ ጸሎት የታመመውን ሰው ይፈውሳል፤ ጌታም ያነሣዋል አንድትፈወሱ አንዱ ለሌላኛው ይጸልይ፡፡ የጻድቅ ሰው ጸሎት ታላቅ ኀጢን ያደርጋል፡፡

ክርስቲያኖች ከእስልምና ሃይማኖት ተፈጥሮን ለሚያመልኩበት ሦስት ወጣት ለጠፉት ሰዎች ወንጌልን በልዩ መልእክተኝነት ለማድረስ ጸጋ ከተባለች ሴት ጋር አብረው መጸለይ ጀመሩ፡፡ በክርስቶስ ፍቅር በመነሣሣት ወደ ታማሚዎች ቤት በመሄድ ሰዎቹ ይፈወሱ ዘንድ ከልባቸው ይጸልያሉ፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ያካፍላሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ሁሉም የባህል መድኃኒት አልሠራ ሲል ነው እነዚህ ሰዎች የሚጠሩት፡፡ አምላካቸው በተአምራቱ የታመሙትን ሲፈውስ ተመልክተዋል፡፡ ይህም ብዙ ጊዜ ለመላው ማኅበረሰብ የኢየሱስን ወንጌል ለማካፈል ጥሩ በር ይከፍታል፡፡ ሰዎች ብዙ ጊዜ አለመግባባት ሲገጥማቸው ችግሩን ለመፍታት እነዚህን ሰዎች ይጠራሉ፡፡ ሰላምንም ለማስፈን እና በቤተሰብ ውስጥ ኀብረትን ለማምጣት ወይም በጎረቤታሞች መካከል ፍቅርን ለማደስ የብዙ ሰዓታትን፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለብዙ ቀናት ጸሎትና የምክር አገልግሎት ይጠይቃል፡፡

ዘላን በሆኑት በቦረና ሕዝቦች መካከል በጸሎት ጓድነት የሚያገለግሉ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከራሱ ጋር ካስታረቀን በኋላ የማስታረቅን አገልግሎት ለእኛ ሰጠን፡፡

የቦረና ትንሽ ልጅ

የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲህ ላሉት ናትና፡፡

ባሎቲ

ውበታችሁ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ፣ ገርና ጭምት መንፈስ ያለበት፣ ምን ጊዜም የማይጠፋ የውስጥ ሰውነት ውበት ይሁን፡፡

ሳዊ

የጌታ ባሪያ የሚጣላ አይሁን፣ ነገር ግን ጭምት፣ ለማስተማር የሚበቃ፣ ትዕግሥተኛ ይሁን።።

ጌርሾ

ደልጋ

ባሳ

ነፍሴ ሆይ፣ ጌታን ባርኪው፣ ያገኘሽውን ሁሉ አትርሺ፤ ዓመፃሽን ሁሉ ይቅር ያለልሽን፣ ከበሽታሽ ሁሉ የፈወሰሽን፣ ሕይወትሽን ከጥፋት የታደገውን አትርሺ።

የአሪ የትንባሆ ማጨሻ

የአሪ አዳኝ

ዛሬ የት ነው ያሉት?

እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል።

የኤርቦሬ ሴት
በጌታ ቤት ሆና፡፡

፲፭

ጴጥሮስ

በሸክላ ውስጥ ያለ መዝገብ

የተወለደው ሕፃን ወንድ ልጅ እንደ ሆነ ባዩ ጊዜ፣ ወላጆቹ ከመጠን በላይ ተደሰቱ፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ከንፈሩ የተሰነጠቀና የተጣመመ አፍ እንዳለው ተመለከቱና እጅግ በጣም ፈሩ! በዚያ ኋላ ቀር በሆነ ማኅበረሰብ ውስጥ እንዲህ ያለ አካለ ስንኩልነት በእነርሱ እና በጠቅላላ በማኅበረሰቡ ላይ የመጣ እርግማን እንደ ሆነ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ለዚህም ልጅ ምንም ዓይነት ስም አልሰጡትም፡፡ የአሪ ጎሳዎች እንዲህ ያለውን መርገም ለማስወገድ የሚያውቁት ብቸኛ መንገድ ልጁን ማጥፋት ነበር፡፡ መንትያዎችም ተመሳሳይ ዕጣ ፈንታ ይገጥማቸዋል፡፡ የልጁ አባት ልጁን ወስዶ ከመንደሩ ውጭ በማውጣት ጫካ፣ ቆሻሻ በሆነ ቦታ ላይ ራቁቱን፣ ጅብና ነበር እንዲበሉት ትቶት ሄደ፡፡ እንዲህ ያደረገው እርግማኑን በመፍራት ነበር፡፡ ከጎሳው መካከል ከመገለል፣ ከመናቅ ይልቅ፣ መጀመሪያ ሕይወቱን ማትረፍ መልካም አይደል!

በመንደሩ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ አማኞች የሆኑት ክርስቲያን ጥንዶች ልጁ ሲያለቅስ ሰሙት፡፡ ወደ ውጭ በመውጣት ከሞት ታደጉት፡፡ ልጁን ወደ መኖሪያ ቤታቸው በመውሰድ የዚያ የድኻ ቤተሰብ አባል አደረጉት፣ ስሙንም ጴጥሮስ ብለው ጠሩት፡፡ የክርስቶስ ወንጌል ወደዚያ ደርሶ አንዳንድ ሰዎች ማመናቸው ትልቅ ዕድል ነበር፡፡ ጴጥሮስ በአሳዳጊዎቹ አማካይነት ከሞት እንደ ዳነ አልረሳም፤ እግዚአብሔር ሰዎችን ተጠቅሞ ከሞት የታደገው ለዓላማው እንደ ሆነም ገባው፡፡ የጉዲፈቻ ወላጆቹ ጴጥሮስን እንደ ገዛ ልጃቸው

ይወድዱትና ይንከባከቡት ነበር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክም ያስተምሩት ነበር፡፡ በኋላ ላይም በክርስቶስ ያምን ዘንድ ረድተውታል፡፡ አካላዊ ችግር ለማስተካከል የተደረገ ምንም የቀዶ ጥገና እርዳታ አላስፈለገውም፣ ጠንካራና ጤናማ ሆኖ አደገ፡፡

እንደ እረኛ፣ ጴጥሮስ ከብቶች ለመጠበቅ ከመንደሩ ወጣ ብሎ ወደሚገኝ ሣርና ጅረት ወደ አለበት ስፍራ ይሄድ ነበር፡፡ በዚያም ከበና ጎሳ የሆነ ልጅ ከብት ሲጠብቅ አገኘና በፍጥነት ቋንቋቸውን ተማረ፡፡ ከዚያ በፊት ከሚያውቃቸው ሦስት ቋንቋዎች ላይ ሌላ አንድ ጨመረ ማለት ነው፡፡ አብዛኛው የአሪ ሰዎች በየሳምንቱ የተለያዩ ጐሳዎች ቡና፣ በቆሎ፣ ጨው፣ ሳሙና እና ጥጥ ለመገበያየት የሚረዳቸው ሦስት ወይም አራት ቋንቋ ያውቃሉ፡፡ ትምህርት ቤት ሲከፈትም፣ ጴጥሮስ ከመጀመሪያዎቹ ተማሪዎች መካከል ነበር፡፡ ወዲያውም ማንበብና መጻፍ ለማይችሉ ጓደኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክን ማንበብ ጀመረ፡፡

እግዚአብሔር የወንጌላዊውን አገልግሎት ባረከለትና ኢየሱስን እንደ ግል ጌታቸውና አዳኛቸው የተቀበሉ የአሪ ሰዎች ቍጥር በከፍተኛ ሁኔታ አደገ፡፡ የአብያተ ክርስቲያን ቍጥር ከማደጉ የተነሣ ኤስ ላይ ኤም በባኮ አካባቢ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከፈተ፡፡ ወንድ እና ሴት ልጆች የእግዚአብሔርን ቃል ለመማር ወደዚህ ትምህርት ቤት መጡ፡፡ በዚያም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ መጋቢዎች፣ ሽማግሌዎች እና ወንጌላውያን እንዲሆኑ ተማሩ፡፡ ያንን ተብታባ አንደበትና የተሰነጠቀ ከንፈር ይዞ ጴጥሮስ መጋቢ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም ነበር፡፡ ለበና ጎሳዎች ወንጌልን ይዞ እንዲሄድ ጥሪ ሲቀርብለት በጣም ተደስቶ ነበር፣ ወዲያውም ‹‹እሺ›› በማለት ጥሪውን ተቀበለ፡፡ አሁን ለምን ዓላማ እግዚአብሔር ከሞት እንደ ታደገው (በሥጋውም ይሁን በመንፈሱ) አወቀ፡፡ እግዚአብሔር ይህን ሰው ልዩ መልክተኛ እንዲሆን መረጠው፡፡ በጣም ጥሩ ከሚባሉትም ወንጌላውያን መካከል አንዱ ለመሆን ቻለ፡፡

የበና ጎሳ ጦረኞች አስቸጋሪ፣ ጨካኝና አደገኞች እንደ ሆኑ ለጴጥሮስ ሲነገረው፣ ጴጥሮስ ሕይወቴ በእግዚአብሔር እጅ ላይ ነው፣ እርሱ እንዳሻው ያድርገኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የበና ጎሳ ሰዎች በበቀል ተግባራቸው የታወቁ ነበሩ፡፡ አንድ ወጣት ልጅ የጦረኝነትን ክብር የሚያገኘው አንበሳን፣ ዝሆንን

ወይም ጠላትን - ሰውን በጦርና በጩቤ ብቻ በመግደል ነበር።።

ጴጥሮስ በሕይወቱ አገባለሁ ብሎ አስቦ አያውቅም።። የሁለተኛ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪ ሳለ፣ አንዲት ልጅ ወደ በና ጎሳዎች እግዚአብሔር ጠርቶኛል ብላ ጻሎት ስትጠይቅ እጅግ ተገርሞ ነበር።። ከዚያም ቀልቧ እርሱን እንደ ፈቀደ በተለያየ መንገድ ስታሳየው ደግሞ እጅግ በጣም ተገርሞ ነበር።። ስለ ተሰነጠቀው ከንፈሩና ስለ ገጠጠው ጥርሱ ግድ አልነበራትም።። ጴጥሮስ ከማስጠላቱ የተነሣ፣ ልጅ ሳለ ጅቦች እንኳ ሊበሉት እንደ ተጠየቀት በመናገር በራሱ ላይ ይቀልድ ነበር።። በትንሽ ከሣር በተሠራች የጻሎት ቤት ውስጥ ወዲያው ጋብቻቸውን በመፈጸም፣ እያደገ ባለው የአሪ ቤተ ክርስቲያን ባህል-ዘለል የወንጌል መልእክተኞች ለመሆን የመጀመሪያው ጥንዶች ለመሆን በቁ።።

ከቦታ ቦታ የሚዘዋወረው ወንጌላዊ ማሄ፣ በሌሎች ጎሳዎች ውስጥ መጀመሪያ መንገድን ከፋች ወደ ሆነው ወደ በና ጎሳዎች ተጉዞ ነበር።። ወንጌል ላልደረሳቸው ለበና ጎሳዎችም ሸክም ስለ ነበረው፣ ከልቡ ይጸልይ ነበር።። የበና ቋንቋ ለመማር አስቸጋሪ የሆነ ቋንቋ ነበር፣ ነገር ግን ከወላይታ ጥቂት ወንጌላውያንን እርሱ ወደ አለበት ስንልከለት በጣም ተበረታታ።። ማሄ እና ባለቤቱ ከካናዳ ከመጡ የወንጌል መልእክተኞች ቻርለስና ማሪዮን ቦንክ ጋር ይሠሩ ነበር።። እነዚህ የወንጌል መልእክተኞች በሐመርና በበና ጎሳዎች መካከል በዲመካ የሚገኘውን የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮናውያን ጣቢያን ያቋቋሙ ነበሩ።። ማሄ እርሱ ራሱ ቤት መሥራት በጣም የሚወድድ ቢሆንም እንኳ፣ ቻርለስ ቦንክ ጠንካራ ቤት ሠራተኛ መሆኑን በመናገር ያደንቀዋል።።

ማሄ እርሱ በአካባቢው ውስጥ በከፈተው በር ተጠቅመው ወንጌልን በማሰራጨት እንዲቄጣጠሩ የወላይታ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ተጨማሪ ወንጌላውያንን ለመለመን ወደ ወላይታ ሄዷል።። እኛ በሚሽነሪ አቬሽን ፌሎሽፕ (ኤምኤኤፍ) አውሮፕላን ወደ ዲመካ በረርን።። ጴጥሮስና ሚስቱ እንዲሁም ሁለት ትናንሽ ልጆች ወደ አሪ በእግር ተጉዘው ደረሱ።። ጴጥሮስና ማሄ በጨለማው ተራራ አካባቢ አብረው እንዲሠሩ ተወሰነ።። የጴጥሮስ የቋንቋ ችሎታ ለወንጌል ብዙ በሮችን ከፍቷል።። የበና ገዥ የነበረው ሰው ወንጌላዊው ልጆቹን ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ ያስተምርለት ዘንድ ጠየቀው።። ከመንግሥት ባለ ሥልጣናት ጋር ባለው ግንኙነት የወረቀትን እና በወረቀት ላይ የተጻፈ ነገር

ያለውን ኃይል ለመረዳት ችሏል፡፡

ማሄ እና እኔ በቻርለስ ቦንክ ላንድሮቨር መኪና በእሾሃማው ጫካ ጴጥሮስንና ቤተሰቡን ይዘን ወደ አዲስ ስፍራ ሄድን፡፡ በዚህች ትንሽ መንደር ውስጥ፣ እኔ እና ማሄ ‹‹የኢየሱስን የጥንት ታሪኮች ስንነግራቸው በጥንቃቄ ያደምጡን ነበር፡፡›› ጴጥሮስ መልእክታችንን ይተረጉምልን፣ እንዲሁም ሕዝቡ በቶሎ ከኃጢአቱ ንስሐ እንዲገባና በወንጌል እንዲያምን ያበረታታ ነበር፡፡

ከሕዘቡ መጨረሻ አካባቢ አንዲት በዕድሜ የገፋች ሴት ተቀምጣ ነበር፡፡ የቆዳዋ ቀለም በአካባቢዋ ካሉ ጥቁር የቆዳ ቀለም ካላቸው ጋር ሲነጻጸር ነጣ ይላል፡፡ በትንሽነቷ በጦረኞች የተማረከችና ሕይወቷን በሙሉ ባሪያ ሆና የኖረች ነበረች፡፡ ብዙ ችግር የደረሰባትና የተንገላታች ነበረች፡፡ የምታውቀውም ሕይወት ይህ ዓይነቱን ብቻ ነበር፡፡ አሁንም ዕርቃኗን ትመስላለች፤ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር የሰማችው ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር፡፡ ጭቃ በማቡካት ከሸክላ የተለያዩ ነገሮችን ትሠራለች፡፡ አንዳንድ ጊዜ በትኵረት ከመስማቷ የተነሣ ሥራዋን ታቆማለች፣ ስለዚህም ሸክላው እንደገና በውኃ ይርስባታል፡፡ ይህ በተለያዩ ቅርጾች የተሠራው ሸክላ በእሳት ተጠብሶ ውኃ ለመሸከሚያ እንስራ፣ ቡና ማፊያ ጀበና ወይም ወጥ መሥሪያ ድስት ይሆናል፡፡

የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ ስለ እኛ ኃጢአት ሊሞት ከሰማይ እንደ መጣ መናገሬን ስጨርስ፣ ሴቲቱ፣ ‹‹ይህ ታላቅ ዜና ነው!›› አለች፡፡ ግን ‹‹ይህ እውነት ይሆንን?›› በማለት ጠየቀች፡፡ በእነርሱ አፈታሪክ ውስጥ ስለ እንስሳት፣ ወፎች፣ ነፍሳት፣ የጀግኖች ሥራ፣ የጎሳ ጦርነት፣ የአካባቢ ጠቦች እና ስለ እንግዶች የሚነገሩ በመቶዎች የሚቆጠሩ የተለያዩ ታሪኮች አሏቸው፡፡ አንዳንዶቹ ታሪኮች እውነት ሲሆኑ፣ ብዙዎቹ ግን የሰዎች ፈጠራ እና ውሸት ናቸው፡፡ ጥያቄው እውነት ነው ወይ? የሚል ስለሆነ፣ በአማርኛ እውነት መሆኑን ገለጽሁላት፡፡ ጴጥሮስም እንደገና እውነተኛ ታሪክ መሆኑን አረጋገጠላት፡፡ እንዲህም አላት፣ ‹‹እግዚአብሔር ይወድደናል ልጁን ኢየሱስንም ለኃጢአታችን ዋጋ ይከፍል ዘንድና ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንዲንኖር ይዋጀን ዘንድ አሳልፎ ሰጠው፡፡››

የሴትዮዋ ፊት አበራ! ስለ ጌታ ኢየሱስ የተለያዩ ታሪኮችን ከሰማች በኋላ፣

‹‹ይህ መልካም ነው፣ ነገር ግን እውነት ነውን?›› አለች። በመጨረሻም እኔ እና ማሄ በቀስታ አንድን ገዥ ለመቅረብ ሴቶች በሚያሳዩት የአክብሮት ዓይነት ለሴቲቱ በማሳየት በጉልበታችን ተንበርከክን። እርሷ፣ ባሪያዋ እና እኛ ሚስዮናውያኑ ፊት ለፊት ተያየን። የተጠናቀቀውን ሸክላ በማስቀመጥ እንዲህ አለች፣ ‹‹ይህ በጣም የሚያስገርም ነው፣ አስደናቂ ታሪክ ነው፣ ነገር ግን እውነት ነው ወይ?››

ጭቃ የነካውን እጇን ይዤ እንዲህ አልኳት፣ ‹‹እናቴ፣ ይህ እውነት ነው። ሁሉም እውነት ነው። እግዚአብሔር፣ ታላቁ ፈጣሪ፣ በጣም ይወድደናል። ኢየሱስ ከኃጢአት ሊዋጀን፣ ከእርሱ ጋር በብርሃን እንኖር ዘንድ ከጨለማ ሊያወጣን መጥቷል።›› በዚህ ዓይነት መንገድ ጴጥሮስና ማሄ መልእክቱ እውነተኛ መሆኑንና ኢየሱስ ከኃጢአትና ከሰይጣን ኃይል ሊታደገን እንደ መጣ አረጋገጡላት።

ሴቲቱም ወደ እኛ እየተመለከተች በቀስታ እንዲህ አለች፣ ‹‹ይህ እውነት መሆን አለበት። እውነት መሆን አለበት። *ግን ይህ እውነት ከሆነ፣ ለምን አሰቀድማችሁ መጥታችሁ አልነገራችሁንም?*›› ዓይኖቼ በዕንባ ተሞሉ፤ ዕንባዬን ለመደበቅ ፊቴን ከፊቷ ማዞር ነበረብኝ። እኛ ለብዙ ዓመታት የነበረን ሰዎች ወንጌል ባለማስተላለፋችን ከፍተኛ ኃፍረት ተሰማኝ። ማሄና ጴጥሮስ በትጋት ሴቲቱ ወይም ማንኛውም ሰው እንዴት የኃጢአት ይቅርታን እንደ ነፃ ስጦታ መቀበል እንደሚችልና በክርስቶስ አዲስ ሕይወትን መቀበል እንደሚችል ያብራሩላታል። በቀጣዩ ቀናት ጴጥሮስና ሚስቱ ታሪኩን ደጋግመው ነገሯት። ክርስቶስን ማመን እና እርሱን መቀበሏን ባውቅ ደስ ባለኝ ነበር።

እኛ ጉዞዋችንን መቀጠል ነበረብን፣ ነገር ግን ጴጥሮስና ሚስቱ ከማሄ ጋር በመንደሪቱ ውስጥ በጨለማ ተራራ አካባቢ ቆዩ። ይህ በጣም አደገኛ አካባቢና ተጓጉች ብዙ ጊዜ በመርዛማ ዛፍ እሾሆች ተወግተው ይሞታሉ። ጴጥሮስና ማሄ በብዙ መንደሮች የክርስቶስን ወንጌል ለበና ሰዎች እየሰበኩ ቀስ በቀስ ጓደኞች አፈሩ። በጣም ጥንቁቆች ነበሩ-፤ ስለዚህም ከመጨለሙ በፊት ወደ መንደሩ ይመለሱ ነበር።

የጴጥሮስ ሚስት በከባድ የወባ በሽታ ታመመች፣ እንዲሁም ሕፃኑ ጭምር

በታመመ ጊዜ፣ ጴጥሮስ ለሕክምና ለረጅም ሰዓታት ተጉዞ ወደ ሚስዮን ጣቢያ ደረሰ፡፡ ከሄደበት በመመለስ ላይ ሳለም አንድ ወጣት ልጅ አብሮት መጓዝ ጀመረ፤ በጫካው ውስጥም አብረው መጓዝ ጀመሩ፡፡ ለአንድ ሰዓት ያህል ከተጓዙ በኋላ ወጣቱ ረጅሙን ጩቤውን በማውጣት የጴጥሮስን እግር ወጋው፤ ከዚያም ጎኑን፣ ከዚያም ብዙ ቦታ ወጋው፡፡ ምንም መሣሪያ በእጁ ያልያዘው ጴጥሮስ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ተገደለ፡፡ ገላው ተበሳሳ፣ ልብሱና ሰዓቱ ተወሰደበት፡፡ ለርካሽ ልብስና ሰዓት የሰው ልጅ ነፍስ ማጥፋት፡፡ የበና ጎሳ የሆነው ወጣት ጴጥሮስን በመግደሉ ጀግንነት እንደ ሠራ ለማሳየት የጴጥሮስን ደም ገላውን በጠቅላላ ተቀብቶ ነበር፡፡ ይህም የከበረ ነገር እንዲሁም የዚህ ጎሳ መለያው ነበር፡፡ ይህ የባህላቸው አንዱ ክፍል ነበር፡፡

በሚቀጥለው ቀን በሰማይ ላይ የሚበርሩ ጥምብ አንሣዎች በመሰብሰባቸው የጴጥሮስ ሬሳ የወደቀበትን ቦታ ጠቁሙ፡፡ ማሄና ቻርለስ ቦንከ ጴጥሮስን በወደቀበት ቦታ በጫካው ውስጥ ብቻቸውን ቀብረውት ተመለሱ፡፡ ጅቦች አካሉን ወስደው እንዳይበሉት በመቃብሩ ላይ ድንጋይ ከመሩበት፡፡ ከእንጨትም መስቀል በመሥራት በማቆም በዛፍ የመቃብሩን ቦታ ምልክት አደረጉ፡፡ ጴጥሮስ ሕይወቱን ለጌታ በመስጠቱና ለወንጌል ሲል ለሕልፈት መብቃቱን ምክንያት በማድረግ ቻርለስ እግዚአብሔርን አመስገነ፡፡ ማሄ ደግሞ በዛፎች መካከል የተከሉት ይህ ዘር በመጭው ዓመታት ብዙ ፍሬ ያፈራ ዘንድ ጸለየ፡፡ (የሚቀጥለው ምዕራፍ ይህ ጸሎት እንዴት በእግዚአብሔር እንደ ተመለሰ ያሳያል፡፡)

ቻርለስ መኪናውን እየነዳ የጴጥሮስን ሚስት ወደ አገሯ ሊወስዳት ሲመጣ፣ በጸጥታ ከሦስት ልጆቿ ጋር ተቀምጣ፣ ከሁለት ሳምንት በኋላ እንዲመጣ ስትጠይቀው እጅግ በጣም ተገረመ፡፡ ከበና ጎሳ ለሆኑ ወንዶችና ሴቶች በጌታ ያላትን ሰላምና ተስፋ ማሳየት ፈልጋ ነበር፡፡ በሰማይ ጴጥሮስን እንደገና እንደምታየው ታውቃለች፣ እንዲሁም እነርሱም ይህን ተስፋ እንዲኖራቸው ትፈልጋለች፡፡ እርሷና ጴጥሮስ ለብዙ ዘመናት በዚያ ቦታ ሲኖሩ ወንጌልን ከሰበኩት በላይ በእነዚያ ሁለት ሳምንታት ለብዙ ሰዎች የክርስቶስን ወንጌል ሰብካለች፡፡

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ማሄ እና እኔ በዚያ አካባቢ መኪና እያሽከረከርን እናልፍ ነበር፡፡ ማሄ የጴጥሮስን መቃብር አገኘው፡፡ ድንጋዩ እስከዚያ ጊዜ ድረስ እንደ ተከመረ ነበር፣ ነገር ግን የእንጨት መስቀሉ ‹‹ጴጥሮስ ኢሳ፤ እስከ ሞት ድረስ የታመነ›› የሚለው በስፍራው አልነበረም፤ ከብዙ ዓመታት በፊት በምስጥ ተበልቷል፡፡ ቦታውን የሚያሳየው ዛፍም የለም፡፡ የጨለማ ተራራ የሚባለው የአሞን ወንዝ ሸለቆ ብዙ መንደሮችን ይዞ ቀኑልቀኑል እየተመለከተ ‹‹ኋላ ላይ የመጡትን የመስቀሉን መልእክተኞች ይጠባበቅ ነበር፡፡›› ነገር ግን ዛሬ በተራራው አካባቢ ብዙ ጸሎት ቤቶች ያሉ ሲሆን፣ እነዚህ የጸሎት ቤቶችም ብርሃኑን ልኮ ጨለማን ያስወገደውን አምላክ የበና ሕዝቦች እግዚአብሔርን በዝማሬ የሚያመሰግኑበት ስፍራ ሆኗል፡፡

ማሄ እና እኔ በጴጥሮስ መቃብር አጠገብ ተንበርክከን ጸለይን፡፡ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወታችንን እንደገና አሳልፈን ሰጠን፡፡ በጸሎት ታማኞች ለመሆን እና በዚሁ ታማኝነት ለመጓዝ ቃል ገባን፡፡ በአሞ ወንዝ ሸለቆዎች ውስጥ ያሉ ሁሉም ጎሳዎች እና ሁሉም መንደሮች በጸጋው ወንጌል እስኪጥለቀለቁ ድረስ ወንጌልን ይዘን ለመሄድ ቃል ገባን፡፡

> *‹‹ሰለ ቲቶ የሚጠይቅ ቢኖር ሰለ እናንተ አብሮኝ የሚሠራ ባልንጀራዬ ነው፤ ሰለ ወንድሞቻችን የሚጠይቅ ቢኖርም የአብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞችና የክርስቶስ ክብር ናቸው።››*
>
> 2ኛ ቆሮንቶስ 8፡23

12

ጌርሾ

የበና ጎሳ ዳግም የተወለደው ሰው

በአሞ ወንዝ ሸለቆ ውስጥ ካሉ ጎሳዎች መካከል እንደ በና ጎሳ በጠላቶቹ ልብ ውስጥ ሽብርን የሚፈጥር ጎሳ የለም፡፡ በጭካኔያቸው በአካባቢያቸው ካሉ ጎሳዎች ከብቶችን በመዝረፍ ይታወቃሉ፡፡ የበና ጎሳ ወንዶች በማኅበረሰባቸው ውስጥ ክብርን የሚያገኙበት መንገድ ሰውን በመግደል ነበር፡፡ ይህ በኑሮአቸው ከሚያከናውኑት ድርጊት አንዱ ነበር፤ የአኗኗር ዘይቤያቸው ነበር፡፡ ይህ ነገር ስሕተት እንደ ሆነ አያስቡም፤ መግደል ወይም መገደል ለእነርሱ የተለመደ ነገር ነበር፡፡ የተለያዩ ቀለማት በሆኑ ጭቃዎች ሰውነታቸውን ለማስጌጥና ለመጨፈር የተመረጡ ልማዶች ናቸው፤ አንዳንድ ጊዜም ወደ ኬኒያ ከብቶች ለመዝረፍ ይሄዳሉ፡፡ ይህም ለእነርሱ ክብር ነበር፡፡ ዘርፎ በክብር መመለስ በማኅበረሰቡ ዘንድ የክብርና የጀግንነት ስምን ያስገኛል፡፡ በበና ጎሳዎች ዘንድ የሌላ ጎሳ ሰውን መግደል ለጋብቻ መስፈርት ነበር፡፡ በጣም ትንሽ የመንግሥት ቍጥጥር ያለበት ስፍራ ሲሆን፣ ፖሊሶች ያሉት ከአካባቢው በጣም ርቀው ነበር፡፡

ወንጌላዊ ጴጥሮስ የተገደለ ጊዜ፣ ይህንን የጭካኔ ተግባር ማን እንደ ፈጸመ ሁሉም ሰው ያውቃል፣ ነገር ግን ፈጻሚው በሠራው ወንጀል አልተከሰሰም፡፡ በበና አለቃ አማካይነት ወንጌልን ማስተማር በተከለከለበት ወቅት፣ ይህ ሁኔታ ለወንጌላዊ ማሄ በጣም ጨለማ የሆነበት ጊዜ ነበር፡፡ ከዓመታት በኋላ እግዚአብሔር ምሥጢራዊ በሆነ መንገድ ትላልቅ ተአምራትን ሠራ፡፡ ማሄ፣

ሰይጣን ወንጌል በበና ጎሳ ሰዎች መካከል መሰራጨቱን ለማስቆም እየሠራ ነው ብሎ የተናገረውን ነገር እግዚአብሔር በመገልበጥ ጌታ የራሱን ዕቅድ ፈጸመ።።

ꕥ

በዓመት አንድ ጊዜ፣ በጣም የታጠቁ ፖሊሶች የመንግሥት ባለ ሥልጣናትን አጅበው በመምጣት በበና ጎሳ ግዛት ውስጥ በመዘዋወር ግብር ይሰበስባሉ።። በበና አካባቢ ግብር የመሰብሰብ ጎላፊነት ለበና ጎሳ ገዥ የተሰጠው ሲሆን፣ ይህም ሰውዬ ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ጥቂት ጥቂት ይሰበስባል።። ግብር ብዙ ጊዜ የሚገበረው በከብት ወይም በፍየል ሲሆን፣ ይህም ተሸጦ ወደ ገንዘብነት ይለወጣል።። ይህም ሁኔታ በአንድ በኩል ገዥውን ሀብታም አድርጎታል።። ፖሊሶቹም የሰው ነፍስ ያጠፋ ሰው ሲገኝ፣ በማሰር ራቅ ወዳለ ስፍራ፣ ወደ ባኮ በመውሰድ ፍርድ ፊት ያቀርቡታል።።

ꕥ

ጴጥሮስ ከመገደሉ ከአሥራ አራት ዓመታት በፊት፣ በበና ጎሳ ውስጥ ሰውን በመግደል በጣም ታዋቂ የሆነ ነፍሰ ገዳይ በፖሊሶች ተይዞ ወደ ባኮ ተወሰደ፤ ተከሰሶም የሞት ፍርድ ተፈረደበት።። ከዚያም በጨንቻ አካባቢ ወደሚገኝ ስፍራ ተዛወረ።። አጠቃላይ የሞት ቅጣት የሚፈጸመው በዚህ ስፍራ ነበር።። ጋርሾ ለመገደል በእስር ቤት ውስጥ ሆኖ በመጠባበቅ ላይ ሳለ፣ ዝቅተኛና ሞቃታማ ከሆነ ስፍራ ወደ 9000 ጫማ (2800 ሜትር) ከፍታ ስፍራ በመምጣቱ በቅዝቃዜና በራብ ሊሞት ትንሽ ቀርቶት ነበር።። የእርሱን ቋንቋ የሚያውቅ ወይም ለምን እንደ ታሰረ የሚያውቅ አንድም ሰው አልነበረም።።

እውነት ለመናገር፣ በእግዚአብሔር ዕቅድ እና ዓለማ አሥራ ሦስት የሚያህሉ ክርስቲያኖች በእምነታቸው ምክንያት አጋጣሚ ሆኖ፣ እርሱ ታስሮ በነበረበት እስር ቤት ውስጥ ታስረው ነበር።። ክርስቲያኖቹም ጥሪ ይዞ ለሚንቀጠቀጠውና ከሰዎች ጋር መግባባት ለማይችለው ሰውዬ ርኅራኄ አሳዩት።። የሚከናነበው ጋቢ ሰጡት፣ እንዲሁም ሌሎች ክርስቲያኖችና ወላጆቻቸው ያመጡላቸውን ምግብ አካፈሉት።። እርሱም ቀስ በቀስ የእነርሱን የጋሞ ቋንቋ መማር ጀመረ፤ በደንብ መረዳት ሲጀምርም ወንጌልን አካፈሉት።። ክርስቲያናዊ ፍቅር ስላሳዩት፣ ጌርሾ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙና ጌታው አድርጎ ለመቀበል ዝግጁ ሆነ።። ከዚያም ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ክርስቲያኖች አማርኛ ማንበብ እንዲችል አስተማሩት፣ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ ቋንቋ ብቻ ስለ ነበረ ነው።።

ከሁለት ዓመታት በኋላ ሁሉም የጋሞ ክርስቲያኖች ከእስር ቤት ተፈቱ፡፤ ጌርሾንም በዚያ ላሉት እንዲሰብክና እንዲመግብ ጎላፊነት ሰጡት፡፡ እርሱ ወደ ክርስቶስ ከመራቸው ሰዎች መካከል አንዱ ጠላ እየጠመቀች በእስር ቤት ውስጥ ላሉ መግዛት ለሚችሉ ሰዎች የምትሸጥ ሴት ነበረች፡፡ መልኳ ትንሽ ቀላ የሚል ስለሆነ፣ ይህም በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ዓይን በጣም ቆንጆ መስላ እንድትታይ አድርጓታል፡፡ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ጌርሾ የሚታመን ሰው ሆኖ ስለ ተገኘ ለእስረኞች ወደ ከተማ በመሄድ የተለያዩ ነገሮችን እንዲገዛና አንዳንዴም በትንሽ ገንዘብ መሥራት እንዲችል ተፈቀደለት፡፡ በኋላ ላይም፣ ምንም እንኳ ማታ ማታ በጨንቻ እስር ቤት ውስጥ እንዲያድር ቢደረግም፣ ጌርሾ ያችን ሴት እንዲያገባ ተፈቀደለት፡፡

ከአሥራ ሰባት ዓመታት በኋላ፣ አዲሱ የኮምዩኒስት መንግሥት የፖለቲካ እስረኞችን ማሰር ስለ ፈለገ፣ እስር ቤቶቹን ነፃ ማድግ ጀመረ፡፡ በቂ ቦታም ለማግኘት ሲል የባሕርይ መሻሻል ያሳዩ ወንጀለኞችንና ነፍሰ ገዳዮችን ለቀቀ፡፡ ከሚለቀቁት ሰዎች መካከል እንደ ሆነ ለመጀመሪያ የተነገረው ለጌርሾ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ድንጋጤ ተሰማው፡፡ ሕይወቱ በሙሉ የሚያልፈው በጨንቻ እስር ቤት ውስጥ የሆነ መስሎት ነበር፡፡ ከዚያም ይህ ምናልባት እርሱ ወደ መጣበት ወደ በና ጎሳ ሕዝብ እንዲሄድ እግዚአብሔር ያዘጋጀው መንገድ ሊሆን ይችላል ሲል አሰበ፡፡ ነገር ግን ይህም ሌላው አስቸጋሪ ነገር ሆነ! ምክንያቱም ወደዚያ እንዴት መሄድ እንደሚቻል አያውቅም ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ የእርሱ ወገን ከሆኑት ሰዎች መካከል አንዳቸውም መኖራቸውን አያውቅም፡፡ እንደ ገና እርሱን ለመቀበል ፈቃደኞች ይሆኑ ይሆን? ከእርሱ ወገን መጻፍና ማንበብ የሚችል አንድም ሰው ባለመኖሩ ምክንያት፣ ምንም ግንኙነት ማድረጊያ መንገድ አልነበረም፡፡ ሁሉም ጌርሾ እንደ ሞተ ያስባሉ፡፡ ከ17 ዓመት በፊት ተሰቅሎ ሞቷል ብለው ደምድመዋል፡፡

የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮናዊ የሆነው ማልከም ሃንተር በደቡብ ምዕራብ በኩል ርቀው ወደሚኖሩት ጎሳዎች እንደሚሄድ ጌርሾ ስለ ሰማ፣ መልእክተኛ ወደ ሚስዮናዊው በመላክ እንዲያገኘው ጠየቀ፡፡ ማልከምም ጌርሾን በእስር ቤቱ ደጃፍ ላይ አገኘው፤ ወዲያውም ይህ ሰውዬ እውነትም የበና ጎሳ ጅብደኛ መሆኑን ተረዳ፡፡ የፊት ሁለት ጥርሶቹ ወልቀዋል፡፡ ሰዎች የፊት ጥርሳቸውን የሚያወልቁበት ምክንያት ምን ያህል ሕመምን የመቋቋም ጥንካሬ እንዳላቸው

ለማሳየት ነበር፡፡ ያረጀ ኮትና ሱሪ ለብሶ መጽሐፍ ቅዱስ በእጁ ይዟል፡፡ ይህ ጌርሾ በማንኛው ጊዜ የሚለብሰው ልብስ ነበር፡፡

ማልከም የጌርሾን ጥርስ-አልባ ፈገግታ እንደ ተመለከተ እየጨበጠው የእግዚአብሔርን ጣልቃ ገብነት አስተዋለ፡፡ ጌርሾ ከእስር ቤት ሊወጣ መሆኑን በመናገር ወደ በና እንዲወስደው ጠየቀው፡፡ ማልከም ይህ ሰው በእርግጥም ወንጌልን ወደዚያ ሕዝብ ለማድረስ በእግዚአብሔር የተመረጠና የተዘጋጀ ሰው መሆኑን አወቀ፡፡ ማልከም ዲመካ ወደሚገኘው የሚስዮን ጣቢያ ለመሄድ በበና ሕዝቦች መካከል አልፎ እንደሚሄድ በመግለጽ ከሳምንት በኋላ ለጉዞ እንዲዘጋጅ ነገረው፡፡ በቀጠሮው ቀንም ጌርሾ በባዶ እግሩ መጽሐፍ ቅዱሱን በጉያው ሥር እንደ ሸጐጠ ለጉዞ ተዘጋጅቶ መጣ፡፡ ከዚህ በፊት ብስክሌት እንኳ ነድቶ የማያውቀው ሰውዬ በአውሮፕላን ውስጥ ሆኖ፣ ወደ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት የተለያዩ፣ ጭፈራዎች የጨፈረባቸውንና የተዋጋባቸውን ሸለቆዎች ቁልቁል መመልከት ቻለ፡፡ ጌርሾ፣ ‹‹ያኔ በዚያ ስፍራ ላይ ያደረግነው ጦርነት ጥሩ ነበር፡፡ ይመስለኛል ወደ ሃያ የሚጠጉ ሰዎችን ገድለናል›› አለ፡፡

አውሮፕላኑ ዲመካ ደርሶ ሲያርፍ ዕቃ በማውረዱ ካገዛቸው በኋላ በዚያ መቆየት አልፈለገም፡፡ አሁን አውሮፕላን ውስጥ ሆኖ በላዩ ላይ በርሮ ወዳለፈው ሸለቆ ለመሄድና ወደ ተመለከተው ወደ ቀድሞ ወላጆቹ ቤት ለመሄድ ፈለገ፡፡ የሚያስታውሰው ሰው ይኖር እንደ ሆነ ለማየት በፍጥነት እየሮጠ በደስታ ሄደ፡፡ መንገዱን ሁሉ እየሮጠ ነበር የሄደው፡፡ ከአሥር ቀን በኋላ ተመልሶ መጣ፤ አሁን መጽሐፍ ቅዱሱን በእጁ እንደ ያዘ ነበር፤ ለሚስቱም ማር በቅል ይዟል፡፡ በበና መሬት ውስጥ በሚገኘው የወደ ፊቱ ቤታቸው ያለበትን መልካም ነገር ለማሳየት ፈልጎ ነበር፡፡ ጌርሾ እንዲህ አለ፣ ‹‹ከመሸ በኋላ ወደ ቤት ስሄድ እናቴ በድንጋጤ ሞታ ነበር፡፡ ከአሥራ ሰባት ዓመታት በፊት ስለ መገደሌ በጣም እርግጠኛ ነበረች፡፡ ሞቼ ነበር፣ ግን አሁን በሕይወት አለሁ፡፡›› እርሱ ያንን አካባቢ ከለቀቀ በኋላ አባቱ ሞቱ፣ እንዲሁም ወንድሙ የአካባቢው መንፈሳዊ መሪ አድርገው በባህላዊ ሥነ ሥርዓት ሾሙት፡፡ ጌርሾ እንዲህ አላቸው፣ ‹‹አሁን እኔ ተመልሼያለሁ፤ ስለዚህ እኔ መንፈሳዊ መሪ ነኝ፡፡ እኔ ተመልሼ የመጣሁት ላስተምራቸው መሆኑን ነገርኳቸው እንዲሁም ከፈለጉ ሁሉም

ክርስቲያን መሆን እንደሚችሉ ነገርኳቸው›› አለ።

ጌርሾ ከማልከም ጋር ወደ ጨንቻ ተጉዞ ሚስቱንና የመጀመሪያ ልጁን በመያዝ፣ በሚቀጥለው በረራ ወደ ዲመካ፣ ወደ ሕዝቡ ለመመለስ ዝግጁ ነበር። ማሄ የጌርሾን ታሪክ ሲሰማ ‹‹በደስታ ልሞት ነው!›› አለ። ሰይጣን ያ ወጣት ሰውዬ ጴጥሮስን እንዲገድል በማድረግ፣ ለማበላሸት የሞከረውን ነገር እግዚአብሔር እንዳስተካከለው መንገድ አድርጎ ተመልክቶታል። ከዚያ በመቀጠልም ጌርሾ እንዲህ በማለት የሚገርም ንግግር ተናገረ፣ ‹‹ከእኔ ዘመዶች መካከል አንዱን ጴጥሮስን እንዲገደል በማድረግ ሰይጣን ለጊዜው ያሸነፈ መስሎት ነበር፣ ነገር ግን ይህ ከመሆኑ ከአሥራ አራት ዓመት በፊት እኔን ወደ እስር ቤት ሲልክ እግዚአብሔር ለዚህ ነገር ምላሽ እያዘጋጀ ነበር። በእስር ቤት ውስጥም የክርስቲያኖቹን መልእክት ሰማሁ፤ እንዲሁም ትክክለኛው ጊዜ ሲመጣ፣ ወደ ሕዝቤ ወንጌልን ይዤ ለመሄድ ብቁ እንድሆን በጋሞ አማኞች ሠለጠንኩኝ።›› እግዚአብሔር ጌርሾ በና ወደሚገኙት ዘመዶቹ እንዲመለስ የተጠቀመው የኮምዩኒስቱን መንግሥት መሆኑ በጣም የሚገርም ነበር።

በሚቀጥለው ቀን ማልከም ጌርሾንና ማሄን እንዲሁም ቤተሰቦቻቸውን በመያዝ አልዱባ ወደሚገኘው ወደ ጌርሾ ቤት ወሰዳቸው። ማሄ ከጴጥሮስ ሞት በኋላ ወደ አካባቢው ተመልሶ አያውቅም፣ ነገር ግን በዚያ የነበረው መኖሪያ ቤቱ በደንብ የተሠራ ከመሆኑ የተነሣ ለመኖሪያነት መታደስ ብቻ ነበር ያስፈለገው። በአቅራቢያው ማልከም ለአውሮፕላን መንደርደሪያ የሚሆን 600 ሜትር ርዝመት ያለው ለጥ ያለ አሸዋማ ሜዳ አገኘ፣ በዚህ ሜዳ ላይ እዚህ እና እዚያ የተሰባጠሩ ቀጥቀጦዎች ይታያሉ። ጌርሾ በበና ያሉ አንዳንድ ጎረቤቶቹን ቀጥቋጦውን በመመንጠር እንዲያግዟቸው ጠየቀ፤ ወዲያውም ብዙ ጊዜ የጐልበት ሥራ የማይሠሩ ወንዶች ሳይቀሩ ሙሉ ማኅበረሰቡ ለሥራ ተንቀሳቀሰ።

ጌርሾ እግዚአብሔር የበና ሰዎችን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለመቀበል ልባቸውን እንዳዘጋጀ አብራራ። ወጣቶች የሚያደርጓቸው ሥርዓቶች ጀግና ተብሎ ወደ መጠራት አደረሷቸው። ከእነዚህ ሥርዓቶች መካከል አንዳንዶቹ ልቅና ኢ-ግብረገባዊ ናቸው፣ ነገር ግን በእነዚህ ሥርዓቶች አማካኝነት የበና ሰዎች ኢየሱስ ‹‹ዳግም ልትወለድ ይገባሃል›› ያለውን ቃል

መረዳት ችለዋል።።

በመቶዎቹ የሚቈጠሩ ወጣት ወንዶች ለበሬ ዝላይ ሥርዓት ሲሉ ወደ ስፍራው ከተለያየ አቅጣጫ መጥተዋል።። እኩል ቁመት ያላቸው ብዙ በሬዎች ጎን ለጎን ተጠጋግተው እንዲቆሙ ሆነዋል።። በዚህ ሥርዓት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት ወጣቶች ወደ ላይ እየዘለሉ ሰውነታቸውን በማሟሟቅ ላይ ነበሩ።። በድንገት የመጀመሪያው ወጣት በበሬዎቹ ጀርባ ላይ በመዝለል ወደ መጨረሻው ላይ ደረሰ፣ ከዚያም ፊቱን በመመለስ በሌላው አቅጣጫ በበሬዎቹ ጀርባ ላይ ዘለለ።።

በዚሁ ልማድ የሚሳተፉ ወጣቶች እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ሦስት ጊዜ ያህል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።። ነገር ግን ያ የመጀመሪያው ወጣት ውድድሩን ሳይጨርሰው ወደቀ።። ውድድሩ ተቋረጠ፣ በሬዎቹም ሁሉ ከታሰሩበት ተፈትተው በየአቅጣጫው መሮጥ ጀመሩ።። ወጣቶቹ በሬዎቹን ከለቀቋቸው በኋላ መግረፊያ አለንጋን አነሡ።። የወደቀው ወጣት ዘመድ ወደ ሆነችው ወጣት ሴት ሄዱ።። ወጣቶቹም ሴቲቱን፣ ‹‹የእርሱ መውደቅ ምክንያት አንቺ ነሽ።። በደንብ ብትመግቢው ኖሮ አይወድቅም ነበር›› አሏት።።

ወጣቶቹ ልጃገረዶችም ወደ ወንዶቹ በድፍረት እየተጠጉ በታላቅ ድምፅ ወንዶቹ ላይ እንዲህ ሲሉ ጮኹባቸው፣ ‹‹በሉ፣ የቻላችሁትን ያህል ግረፉን።። እኛ የበና ሴቶች ምን ያህል ጠንካሮች እንደ ሆንን እናሳያችኋለን።። እኛ አንፈራችሁም!›› ወጣቶቹ ወንዶችም እጆቻቸውን ወደ ላይ እያነሡ የሴቶቹን ጀርባ በአለንጋ ሲገርፉ ሴቶቹ ምንም ሳይንቀሳቀሱ ይቆሙ ነበር፣ አለንጋው ጀርባቸውን አልፎ ጡታቸውን ይገሸልጥና ያደማ ነበር።።

ጌርሾ እንዲህ የሚል ገለጻ ሰጠ፣ ‹‹እነዚህ ሴቶች ሲገረፉ በምንም ዓይነት ዓይናቸውን ሲጨፍኑ አልታዩም።። አንዲት ሴት ከመግረፊያው ቦታ ከሸሸች፣ በሕይወቷ ሁሉ የሚያገባት አታገኝም።። ይህ በቤተሰቧ ላይ ትልቅ ውርደትን ያመጣል።። ሸማግሌ መጥቶ እስካላስቆመ ድረስ ሴቶች ራሳቸውን እስኪስቱ ድረስ ጸንተው ይቆማሉ።። በዚህም መንገድ ሴቶቹ ልጅ በሚወልዱበት ጊዜ ምንም ችግር እንደማይገጥማቸው ያሳያሉ።። በመጨረሻም በጀርባዋ ብዙ የግርፋት ቀኑስል ያለባት ሴት ለጋብቻ ተመራጭ ናት።። እንዲህ ያለች ሴት ብዙ ጥሎሽ ታስገኛለች›› በማለት ተናገረ።።

የሴቶቹ መገረፍ እንዳበቃም፣ ወጣቶቹ ወንዶች በአንድነት ወደ መሃል ይሰበሰባሉ፣ ሁሉም በሸማግሌው እግሮች ቁጥጥር ዋሉና ከዚያ ከወገባቸው ጎንበስ ብለው ይቆማሉ፡፡ ሁሉም በአንድነት የሰውየውን ጩኸት በመከተል እርሱ እንደሚለው ይላሉ፡፡ ይህ ድምፅ አንዲት ሴት ልጅ ስትወለድ የምታሰማው ዓይነት ጩኸት ነው፡፡ ጌርሾ እንዲህ ስለ ተናገረ፣ ‹‹ኢየሱስ የተጠቀመበትን ተመሳሳይ ቃል ነው እኛም የምንጠቀመው፡፡ እርሱ ዳግም ተወለደ እንላለን፡፡ ይህ በበና ወንዶች ሕይወት ውስጥ በጣም አስፈላጊ ተግባር ነው፡፡ ከዚህ በፊት እርሱ እንደ አህያ ወይም ውሻ ነበር፡፡ ቢሞት እንኳ ስሙን ማንም አያስታውስም፡፡ በዚህ ቀን ግን እርሱ ጦረኛ ሆኗል፣ እንዲሁም ትክክለኛ ስም ተሰጥቶታል፡፡ ለዚህም ነው የበና ሰዎች *‘ዳግም መወለድ አለባችሁ’* ተብሎ ሲነገራቸው ትርጉም የሚሰጣቸው፡፡››

የዚህ ሥርዓት አካል የሆነ አንድ ሌላ ነገር ነበረ፡፡ ሁለት ቀጥ ያሉ አጠናዎች በአንድ ሜትር ርቀት ላይ ይተከላሉ፣ ከዚያም አንድ እንጨት በአግድሞሽ እነዚህ እንጨቶች ላይ አንድ ሜትር ያህል ከፍ ተብሎ ይታሰራል፡፡ ‹‹ይህ በር ነው›› አለ ጌርሾ፣ ‹‹ሰውዬው በዚህ በር ውስጥ ስሙ ከተጠራው በሬ ጋር ያልፋል፣ ከዚያም ይህ ሰው የበና ጦረኛ ይባላል፡፡ እግዚአብሔር ሆይ፣ ኢየሱስ ‹እኔ በር ነኝ!› ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ ይህንን የእነርሱ በር ለመግባቢያ ድልድይ አድርገህ ተጠቀምበት፡፡ ይህ ሌላኛው ጌርሾ እስኪመጣ ድረስ የቆየ የመዋጀት ምስስል ነው፡፡››

ፍሬድ ቫን ጎርከም የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮናዊና የእንስሳት ሐኪም፣ ጌርሾን ለበና ሰዎች ጠቃሚ የሆነውን የእንስሳትን ማከምና መከተብን ያስተማረው ሰው ነበር፡፡ ከወላይታ የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮናውያን እና በኦሞ ወንዝ ሸለቆ ዙሪያ ከተለያዩ ጎሳዎች ከመጡ ወንጌላውያን ጋር፣ እንዲሁም በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ውስጥ ካሉ የእግዚአብሔር ሰዎች የጸሎትና ድጋፍ አማካኝነት በእግዚአብሔር ጸጋና ኃይል አማካይነት ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን በበና ውስጥ ለማየት ችለናል፡፡

በቅርብ ጊዜ በበና ዙሪያ ባሉ የተለያዩ ጎሳዎች - የጸማይ፣ ኤርቦሬ፣ ካሮ፣ ዳሳነች እና ሁሉም የበና እና የሐመር ዝርያዎች በሆኑት ውስጥ የወንጌል ስርጭት ለማድረግ ዕቅድን ለማውጣት ጌርሾና ጓደኞቹ ኮንፍረንስ በጠሩ ጊዜ

የእግዚአብሔርን መንፈስ ልዩ እንቅስቃሴ ተመልከተዋል፡፡ ወደ 150 የሚጠጉ የበና ወንዶችና ሴቶች ለጸሎትና የወንጌል ስርጭትን ለማቀድ በአልዱባ ተሰብስበው ነበር፡፡

እየጸለዩ ሳሉም፣ ክርስቲያኖቹ ወንጌልን ለመስበክ ያለባቸውን ዕዳ እና ኀላፊነት ተረድተዋል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ዕዳና ኀላፊነት፣ ሰዎችን በወንጌል የመድረስ ዓላማ ከግብ የሚደርሰው በፍቅር እና በአንድነት እንደ ሆነ ተገንዝበዋል፡፡ በመካከላቸው ያለውን ክፍፍልና ለክርስቶስ ያላቸው የመጀመሪያ ፍቅር መቀዝቀዙን ተረድተዋል፡፡ ይህም ወደ እውነተኛ ንስሐ፣ ኃጢአትን ወደ መናዘዝና ከጌታ ጋር እና እርስ በርሳቸው ወደ መታረቅ ደረጃ መርቷቸዋል፡፡ በእግዚአብሔር ቅድስና ላይ ማተኰር እንደ ጀመሩ፣ በቅጽበት ምስጋና፣ አምልኮና መዝሙር ከአንደበቶቻቸው ይፈስሱ ጀመር፡፡ የእነርሱ ጠላቶች ለነበሩ ሰዎች ወንጌል ይደርሳቸው ዘንድ እንስሶቻቸውን፣ ውድ ንብረቶቻቸውን ለእግዚአብሔር መንግሥት ማስፋፊያ ሲሰጡ ማየቱ በጣም የሚያስደስት ነበር፡፡

የእሑድ ዕለቱ ፕሮግራም እስከ አሥር ሰዓት የቆየ ነበር! ሰዎች ምስጋና ለማቅረብ በቂ ጊዜ ነበራቸው፣ እንዲሁም በአልዱባ የነበሩ ድሆች ገበሬዎች ቀድሞ ጠላቶቻቸው ለነበሩ ሰዎች ወንጌል እንዲደርስ በደስታና በልግሥና ይሰጡ ነበር፡፡ በአጠቃላይ የሰጡት አሥራ ስምንት ላሞች፣ በጣም ውድ የሚሉት ንብረታቸውን፣ ሰባ ፍየሎች፣ ከ120,00 ብር በላይ እና በጣም ብዙ በጎች፣ ዶሮዎች፣ ብዙ ኩንታል ጥራጥሬ፣ ልብስ፣ ሰዓት፣ ወዘተ. . .ነበር፡፡ ሰዎች የሚሰጡት ገንዘብ ሳይኖራቸው ሲቀር ደግሞ እንዲህ ይሉ ነበር፣ ‹‹ከዚህ በላይ የምሰጠው ነገር የለኝም፣ ስለዚህ እራሴን እሰጣለሁ!›› በናን ከነፍሰ ገዳይነት ወደ ነፍስ አዳኝነት የለወጠው ነገር ምንድን ነው? ይህንን ማድረግ የሚችል የእግዚአብሔር ፍቅርና ኃይል ብቻ ነው!

በዚህ ሁሉ ውስጥ፣ እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ብሏል፣ እንዲሁም ለእርሱ ምስጋና እና ክብር ተሰጥቷል፡፡ እርሱ የበና ነፍሰ ገዳይ የሆነውን ጌርሾን ከመንፈሳዊ ጨለማው ዓለም አውጥቶ እጅግ ብዙ ለሆኑት ወደ ራሱ ሕዝቦችና ወደ ሌሎች ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስ መልእክተኛ አድርጎ ላከው፡፡ ነፍሰ ገዳይ የነበረውን ሰውዬ ነፍስን ተንከባካቢ አደረገው፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን!

፲፫

ምዕራፍ

ከዲያብሎስ ጨለማ

እነዚህ ሁለት ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚተያዩበትን መንገድ መመልከቱ ራሱ አስቂኝ ነበር- ግንባሮቻቸውን ቋጠር ፈታ እያደረጉ ይጠያየቃሉ፤ እንዲሁም ዐይኖቻቸውን በደንብ በልጥጠውና አትኩረው ለመመልከት ይሞክራሉ፡፡ ከተገናኙ እጅግ በጣም ረጅም ጊዜ ነበር፣ ከሃያ ሰባት ዓመታት በላይ ሆኗቸዋል፡፡ ከጊዜ ብዛት ሁለቱም ብዙ ተለውጠዋል፡፡ በፊታቸው ላይ ያለው ማኅተም ያለፉበትን መከራ የሚያሳይ ነበር፡፡ እርስ በርሳቸው ሲተያዩ ደቂቃዎች አሳልፈዋል፤ በፊታቸው ላይም በጣም የተዘበራረቀ ስሜት ይነበብ ነበር፡፡ ‹‹ይህንን ፊት የማውቀው ሊሆን ይችል ይሆንን? እርሱ ይሆንን? ዐይኖች ተከፈቱ! አስታወሰ! አዎን፣ እርሱ ነው!››

በተመሳሳይ ሰዓትም አንዱ የሌላኛውን ስም ከፍ አድርጎ ጠራና እርስ በርሳቸው ተቃቀፉ! ሳቅና ለቅሶ ከዚያም እርስ በርሳቸው መተቃቀፍ ሆነ ሥራቸው፡፡ በእነዚያ የመለያየት ዓመታት እግዚአብሔር ታማኝ ስለ ሆነላቸው አመሰገኑት፡፡ በእነዚያ ዓመታት ሁሉ ውስጥ አንዱ ከሌላኛው ጋር ለመገናኘት አልቻለም ነበር፤ አሁን ግን ተለያይተው የቆዩም አይመስሉም፡፡ በክርስቶስ አንድ ናቸው፣ እናም ጊዜ፣ ቦታ እና ርቀት የሚለያቸው አይመስልም፡፡

ትንሿ የዲማ ከተማ በስድስት ጎሳዎችና በትልቁ የአሞ ወንዝ የተከበበች ናት፡፡ አንዳንዶቹ ጎሳዎች ሰላማዊ ሲሆኑ፣ የቦዲ እና የሙርሲ ጎሳዎች ግን

ለዘመናት የዲማን ጎሳዎች ሲያጠቁ ቆይተዋል። የዲማ አካባቢ ብዙ ልዩ የሆኑ ነገሮች ያሉት ሲሆን፣ የባዬ ተራራ (የስሚዝ ተራራ) በአካባቢው ካሉ ተራራዎች ሁሉ ትልቁ ነው። በጣም ዐቀበታማ የሆነው ተራራ ሰብልን ለመዝራት እርከን ተሠርቶበት ታርሷል። የብረታ ብረት ሠራተኞች ከተራራው ላይ ብረት ቆፍረው በማውጣት መሣሪያ እና የተለያዩ ቀሳቀሶችን ይሠሩበታል። የብረት ማዕድኑ በትንሽ የሸክላ ማንደጃ ላይ ግማሽ ደርዘን በሚያህሉ ሰዎች አማካኝነት አስፈላጊውን እሳት እያገኘ ይቀልጣል። አብዛኞቹ መኖሪያ ቤቶች የተሠሩት እንደ ሌሎች ጎሳዎች ከትንንሽ እንጨቶችና ቀርከሃዎች ሳይሆን፣ በአካባቢው በብዛት ከሚገኘው ወፍራም የድንጋይ ግድግዳዎች ነው። ይህንንም የሚያደርጉበት ምክንያት ከጠላቶቻቸው ወረራ ለመከላከል ነው።

ከአንድ ሺህ የዲማ ጎሳ ሰዎች መካከል አሥሩ እንደ ኮሌራ፣ ቢጫ ወባ፣ ማጅራት ገትር እና ወረርሽኝ በመሳሰሉት ይሞታሉ፣ በዚህም ምክንያት ቁጥራቸው ይመናመናል። በተጨማሪም ብዙ ጊዜ እነርሱ ከሚኖሩበት ሸለቆ ቀጥለው ከሚኖሩ የቦዲ ፈረስ ጋላቢ ጦረኞች ድንገተኛ ጥቃት ይደርስባቸዋል።

ዳኖ በተወለደበት እና ባደገበት የዲማ መንደር ውስጥ ከፉ፣ የጠንቋዮች ሰይጣናዊ ልምምዶች፣ ዲያብሎሳዊ ሥራዎች፣ በሽታዎች፣ ፍርሃት፣ ጥላቻና በቀልን የመሳሰሉ ነገሮች የተለመዱ ነበሩ። ዳኖ ገና ወጣት ሳለ ነበር አባቱ የሞተው። ቀጥሎም እናቱ፣ ከዚያም ወንዱም እና እኅቱ ሞቱ። በኢጋጣሚ ከቤተሰቡ ውስጥ የቀረው ዳኖ ብቻ ነበር። በፍርሃት ተውጦ፣ ብቸኛ ሆኖ እና ሞትን በጣም ፈርቶና ተስፋ ቁርጦ ነበር።

ዳኖ አንዲት የአካባቢያቸውን ልጃገረድ ያገባ ሲሆን፣ ሚስቱ በጣም የምታምር ትንሽ ሴት ልጅ ስትወልድለት በጣም ተደሰቶ ነበር። ደስታቸው ግን ልጃቸው ከተወለደች በኋላ ወዲያው በመሞቷ ወደ ኃዘን ተለወጠ። ከጥቂት ሳምንታት ቆይታ በኋላ፣ ሚስቱም ሞተች፤ የዳኖ ኀዘን እጅግ የጸና እና ማብቂያ ያልነበረው ሆነ። እርዳታ ያገኝ ዘንድ ብቻውን ወደ ሰይጣን ሄደ። ለመናፍስቱም ራሱን አሳልፎ ሰጠና በሰይጣን የተያዘ ሆነ። ነገር ግን ዲያብሎስ ለዳኖ ዕረፍት ወይም ሰላም አልሰጠውም። አዲስ መኖሪያ ቤት በሠራ ቁጥር ዲያብሎስ ከዚያ ቤት ያስወጣው ነበር። በተለያዩ ቦታዎች ወደ አሥር የሚጠጉ ቤቶችን ሠራ፣ ነገር ግን በአንዳቸውም ውስጥ ከጥቂት ቀናት በላይ መቆየት አልቻለም ነበር።

ዳኖ ለትንሽ ጊዜያት ወደ ተለያዩ ቦታዎች በመሄድ ንግድ ለመነገድ ሞክሯል፣ ነገር ግን ምንም ትርፍ አላገኘም። በሰይጣን ይታለልና በሰዎች ደግሞ ይጭበረበር ነበር። የአካባቢው ጠንቋይ፣ ዳኖ ማታ ማታ ከእንስሳት ጋር እንዲተኛና ቀን ቀን ደግሞ ከብቶችን እንዲያሰማራ አደረገው። በጣም ተስፋ ከመቁረጡ የተነሣ ሞቱን ተመኘ። ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ትንሽ አውሮፕላን በሰማይ ላይ ስትበርር ተመለከተ። በሕይወቱ ለመጀመሪያ የተመለከታት አውሮፕላን ነበረች፤ ስለዚህም እጅግ በጣም ፈራ። ይህ ምንድን ነው? ምንም የሚያውቀው ነገር የለውም! የሚሽኒሪ አቬሽን ፌሎሽፕ (ኤምኤኤፍ) ሴስና አይሮፕላን ወደ ደበቡና ወደ አሞ ወንዝ ሸለቆ እየተጓዘች መሆንዋ ምንም ጥርጥር የለውም። ዳኖ ከዚያ ቀን በኋላ እንደዚህች ያሉ ብዙ አውሮፕላኖችን ሊያይ ነው።

አሁን በዲማ የነበሩት ዘመዶቹ በሙሉ ሞተዋል። የቀረው ማሎ በሚባል ሩቅ ስፍራ ውስጥ ያለው አጎቱ ብቻ ነበር። ዳኖ የሚረዳው አጥቶ ግራ ገብቶት ነበር። ‹‹ማን ሊረዳኝ ይችላል?›› በማለት ግራ ተጋባ። ከዕለታት አንድ ቀን፣ የዋናው ጠንቋይ ወንድ ልጅ፣ ዳኖ አዝኖ ተቀምጦ ሲያየው ለምን እንደሚያዝን ጠየቀው። ዳኖም እንዲህ ሲል መለሰለት፣ ‹‹ምክንያቱም ያለኝን ሁሉ አጥቻለሁ። አሁን ብቻዬን ነኝ።›› ዲያብሎስ በጣም ሩቅ እና በጭካኔ እስከዚያ ቀን ድረስ መርቶታል። አሁን መጨረሻው ላይ ደርሷል። ነፃነት ጠምቶታል።

የጠንቋዩ ልጅ በድንገት ለዳኖ እንዲህ ሲል ነገረው፣ ‹‹እንደ አንተ በሰይጣን የተያዘ አንድ ጠንቋይ ነበር፣ ይህም ሰውዬ በሰይጣን እየተመራ ወደ ተለያየ ቦታ ይሄድ ነበር፣ ነገር ግን ሰይጣን ሊገድለው ሲል ወደ ማሎ፣ የአሞን ወንዝ ተሻግሮ ወደ ዳውሮ ሸሸ። በዚያም ኢየሱስ በሚባል ሰው አመነና አዲስ ሕይወትን ተቀበለ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አዲስ ሰው ሆነ›› በማለት አጫወተው።

ዳኖ በዚህ አዲስ ዜና በጣም ተገርሞ ይህን ኢየሱስ የሚሉትን ሰው እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ማወቅ ፈለገ። ሊመራው የሚችል አንድ ሰው ያስፈልገዋል፣ ከዚያም በማሎ ያለውን አጎቱን አስታወሰ። እርሱ ወንዙን እንድሻገር ይረዳኝ ይሆናል ሲል አሰበ። በልቡም ለማን እንደሚናገር ሳያውቅ

እንዲህ ሲል ተናገረ፣ ‹‹ከዲያብሎስ ነፃ ካወጣሽኝ አገለግልሃለሁ›› አለ፡፡ በዚያም ቀን ወደ ማሎ ጉዞውን ጀመረ፡፡ በሚቀጥለው ቀን በጣም የሞቀውና የደከመው ዳኖ በመንገድ ዳር ባለ ማሳ ውስጥ ሆኖ ከበቆሎ እርሻ ውስጥ ዐረም የሚያርም ሰውን አየ፡፡ ይህ ሰው ወንጌላዊ ናና ነበር፡፡ ሰላም ከተባባሉም በኋላ ዳኖ እንዲህ ሲል ጠየቀው፣ ‹‹የኢየሱስ ሰዎች የሚባሉት ወዴት እንደሚኖሩ ታውቃለህን?›› አለው፡፡

ናና ደግሞ፣ ‹‹እኔ ከእነርሱ አንዱ ነኝ፡፡ ትንሽ ጊዜ ስጠኝና ከእኔ ጋር ቡና ትጠጣ ዘንድ ወደ ቤት ይገፍህ እሄዳለሁ›› አለው፡፡ ለትንሽ ጊዜ ዳኖ በዛፍ ጥላ ሥር ካረፈ በኋላ፣ ለመሄድ ከመጓጓተቱ የተነሣ፣ ናናን ዐረምን በማረም አገዘው፡፡ ናና ዳኖን በአቅራቢያው ወዳለ የቤተ ክርስቲያናቸው ሽማግሌ ቤት ይዞት ሄደ፡፡ በዚያም ናና እና ሰውዬው ስለ ወንጌል ለዳኖ አብራሩለት- ከሰይጣን የበለጠ ጠንካራ የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ብቻ ነው አሉት፡፡ ናና ለዳኖ እንዲህ አለው፣ ‹‹በእውነት በኢየሱስ ክርስቶስ ካመንክና ከኃጢአትህ ንስሐ ከገባህ፣ እንዲሁም ሰይጣንንና መንገዱን ከካድክ፣ ኢየሱስ ያድንሃል፣ እንዲሁም አዲስ ሕይወትን ይሰጥሃል›› አለው፡፡

ናና ለዳኖ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ሲያብራራለት ረጅም ጊዜያት አለፉ፤ ስለ ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ስለ ፍጥረት፣ ስለ የሰው ልጆች ኃጢአት፣ ስለ ዐመፅ፣ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር፣ ኢየሱስ ከሰማይ ስለ መምጣቱ፣ ስለ መሥዋዕትነት፣ ስለ የስርየት ደም፣ ስለ ንስሐ፣ አዳኙን ስለ መቀበል፣ ስለ ደኅንነት፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስላለ አዲስ ሕይወት፣ እንዴት መኖር እንዳለበት፣ ስለ አምልኮ፣ ስለ ምሥጋና፣ ወዘተ. . .አብራራለት፡፡ ዳኖም አመነ፣ እንዲሁም በደስታ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ ተቀበለ፡፡ በሙሉ ልቡም ሰይጣንን ወይም ዲያብሎስን በመካድ ኢየሱስን እንደ አዲስ ጌታው አድርጎ ተቀበለ፡፡ ሰይጣንም በኢየሱስ ስም ለቅቆት ሄደ፣ ተመልሶ ወደ እርሱ አልገባም፡፡ ዳኖ ነፃ ወጣ!

የአዲስ ሕይወት ደስታና ነፃነት፣ አስጮኸው፣ እንዲሁም በደስታ ብዛት ሳቅና ለቅሶ ተቀላቀሉበት፡፡ ወዲያውም አሮጌ ሕይወቱ ምንኛ አስጠሊታ እንደ ነበረ ዳኖ ተረዳ፡፡ ሰውነቱን እና ልብሱን መታጠብ እንዲሁም ረጅሙ ጸጉሩን እና ጥፍሮቹን ለመቁረጥ ፈለገ፡፡ ይህንን እያደረገ ስለ ኢየሱስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ ናና ሲነግርው በተመስጦ ይሰማው ነበር፡፡ ከዚህ የበለጠ አንዳችም

ፍላጎት አልነበረውም። ትክክለኛ ሕይወትን፣ ደስታን እና ሰላምን አግኝቷል። ስለ ኢየሱስ ይበልጥ ለማወቅ ለጥቂት ቀናት በዚያ ቆየ።

ከዚያም ወንጌላዊው እንዲህ አለው፣ ‹‹ወደ ዲማ ወደ ቤተሰቦችህ ዘንድ ሂድና ስለ ኢየሱስ ለሰዎች ንገር። አንተ የእርሱ ምስክር ነህ።›› በማሎ የነበሩ ክርስቲያኖች ለዳኖ ጥቂት አዳዲስ ልብሶች ሰጡት፤ ደስ እያለውም ወደ ዲማ ጉዞውን ቀጠለ። በማሎ እና በዲማ እኩል መንገድ ሜሼላ በተባለ ስፍራ ላይ ዳንኤል ከሚባል ወንጌላዊ ጋር ተገናኙ፤ ዳንኤል ከዚህ ስፍራ ተነሥቶ ወንጌል እየሰበከ ወደ ዲማ ለመሄደ ዕቅድ ነበረው። ዳንኤል ዳኖን ወደ መኖሪያ ቤቱ በመውሰድ የክርስትና ሕይወት እንዴት እንደሚኖር መመሪያዎችን ሰጠው። ይህ በዳኖ ሕይወት ውስጥ መንፈሳዊ እድገትን ያስከተለ ጊዜ ነበር። ከጥቂት ወራት በኋላ ዳንኤል ለዳኖ የጥምቀትን ጠቀሜታ ገለጸለት እና በትንሽዬ ጅረት ውስጥ አጠመቀው። እንዲሁም ለኃጢአት መሞትና በክርስቶስ አዲስ ሕይወትን መኖር ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ገለጸለት።

ዳንኤል ዳኖን ወደ ክርስቲያኖች ጉባኤ ይዞት ሄደ፣ አዳዲሶቹ አማኞችም ዳኖን ወደዱት፣ እንዲሁም ዳኖ ጌታውን ለማመስገን የሚያስችል አዲስ መዝሙር ሲያስተምሩት በደስታ ብዛት ሰከረ። እነዚህ አማኞች ሲያመልኩ፣ ሲያመሰግኑና ሲጸልዩ ዳኖ በመስማቱ እጅግ በጣም ተደንቆና ተገርሞ እንዲህ ሲል ጠየቀ፣ ‹‹በጣም የሚገርም ነው። እኔም ብጸልይ እግዚአብሔር ይሰማኛል ማለት ነውን?›› ከዚያም በማልቀስ ስለ እስራት ዘመን ታሪኩና ስላገኘው ነፃነት ነገራቸው። ስለ ብቸኝነቱ እና በዲማ በፍርሃትና በጨለማ ስላሉት ሕዝቦቹ እንዲጸልዩለት አማኞችን ጠየቃቸው።

የክርስቲያኖች ጎብረት ዳኖን በእምነቱ እንዲጠነክር አደረገው፣ እንዲሁም ከዳንኤል ጋር ሆኖ ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖችን ያገኛቸው ነበር። በእነርሱ ስብሰባ መካከልም ከአንዲት ሴት ጋር ተዋወቀ፣ የአማኟም ስም አስካለች ይባላል። ከባስኬቶ ጎሳ ነበረች። አባቷ ሙስሊም ነበር፣ እርሷንም ገና በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ እያለች ለአንድ ሽምገል ያለ ነጋዴ ድሮአት ነበር። የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን በሰማችና ኢየሱስን እንደ ግል አዳኟ በተቀበለች ጊዜ፣ ባለቤቷ እጅግ በጣም ተቈጣ። በዚህም ምክንያት ከቤቷ አባረራት፣ ነገር ግን እርሱ በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ ሞተ።

ዳኖ አስካለችን አገባት፣ ከዳንኤልም ጋር በመሆን ዲማ ውስጥ በሚገኘው፣

ጌሮ ወደ ተባለ ቦታ ሄደው መኖር ጀመሩ። ዳኖ ከዳንኤል ቤት አቅራቢያ ቤት ሠራ። ለብዙ ዓመታት ከቦታ ቦታ አብረው ይዞሩና ለሕዝቡ ወንጌልን ይሰብኩ ነበር። በዚህ ጊዜ ዳኖ፣ ለወንጌላዊ ዳንኤል ይተረጒምለት ነበር። በጒዞዋቸውና ወንጌልን ለሰዎች በሚናገሩበት ወቅት በጣም ብዙ ስደት ይደርስባቸው ነበር፣ ነገር ግን እነዚህ መከራዎች የዳኖን እምነት የሚያጠነክሩ ሆኑ። ዳኖ ለብዙ ጊዜ ተደብድቧል፣ እንዲሁም ከአርቶዶክስ ቄስ በተወረወረ ድንጋይ ብዙ ጊዜ ተፈንክቷል። ብዙ ጊዜ መጒላላትና ማስፈራራት ይደርስበት ነበር፣ ነገር ግን ይህንን ሁሉ ሥቃይ በመቋቋም ብዙ ሰዎችን ለክርስቶስ ይማርክ ነበር። ሀብታሙ ባላባት ዕድሉን ባገኘ ቍጥር፣ ‹‹ቆሻሻ፣ የማትረባ፣ ባሪያ፣ አህያ›› በማለት ይሰድበው ነበር። ብዙ ጊዜ ይደበድቡትና ያጐሳቍሉት ነበር። ዳኖ ግን በእነዚህም ጊዜያት ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ይነግራቸው ነበር።

ዳኖ ለዳንኤል ከነገረው መሻቶቹ መካከል አንዱ፣ የሚስዮናውያን አውሮፕላን በዲማ ምድር ላይ አርፎ ማየት ነበር። ለአውሮፕላን ማረፊያ የሚሆነው ቦታ ደግሞ ዳኖ ይሰደብበት በነበረው ቦታ ላይ ነበር። ዳኖ እና ዳንኤል ነጮችን ከመድኃኒትና ከትምህርት ጋር ልትመጣ ስለምትችለው፣ ስለ ሚስዮናውያን አውሮፕላን መነጋገር ጀመሩ። ከተቻለም በሌሎች ስፍራዎች እንዳደረጉት ክሊኒክ መክፈት እንደሚችሉ ተወያዩ። በቡልቂ ወደሚገኘው የኤስ ኣይ ኤም ክሊኒክ ለመድረስ ለብርቱ ሰው የሦስት ቀን የእግር ጒዞ ነበር። ዳኖ እና ዳንኤል ተስማሚ ስፍራን እየፈለጉ እንደ ሆነ ዜና ተናፈሰ። ለዲማ ሕዝብ እንዲህ ያለውን ጥቅም የሚያስገኝ ቦታ የሚሰጥ ሰው በማኅበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅ ያደርገዋል።

ቀስ በቀስም ወሬው ለዚያ ተሳዳቢ የመሬት ባለቤት ደረሰውና ዳኖንና ዳንኤልን አስጠርቶ ለአውሮፕላኑ ማረፊያ አስፈላጊ የሆነ አንድ ሰፊ ቀጥ ያለ መሬት ሰጣቸው! ከዚያም በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችን በሙሉ አስጠርቶ በአካባቢው የነበሩትን ዛፎች፣ ቍጥቋጦችና ድንጋዮችን አስነሣ፣ እንዲሁም ማንኛውንም ጒድጓድ፣ አባጣ ጐርባጣ ስፍራ ሁሉ አስሞላ።

ቡልቂ ካሉት የሚስዮናውያን ጋር በመሆን ከዳኖ ጋር መንገድ እየመራን ለአውሮፕላን ማረፊያ ስፍራ መኖሩን ለመመልከት ሄድን። ከዚያም የኤምኤኤፍ አውሮፕላን ሰዎች የሕክምና ቡድን ይዘው መጡ፣ እንዲሁም በየጊዜው እየመጡ የሚያደርጉት የሕክምና እርዳታ ለአካባቢው በጣም ጠቃሚ ነበር።

የበሽታ መከላከያ (አንቲባዮቲክ) እና ሌሎች መድኃኒቶች የሕዝቡን ጤንነት አሻሉ። ስደቱ ረገብ አለ። የወንጌል መልእክትም ከክሊኒክ በበሽተኞቹ አማካኝነት ወደ ተለያዩ ስፍራዎች መሰራጨት ጀመረ። በበቅሎ ረጅም ቀናት ይፈጅ የነበረው ጉዞ አሁን በአውሮፕላን በረራ ለነርሶቹ የአሥራ አምስት ደቂቃ ሆነላቸው። ከዚያም ኢትዮጵያዊ የጤና ረዳት በዚያ አካባቢ ፋርማሲ/ክሊኒክ ከፈተ። ሶዶ ከሚገኘው የኤስ ኣይ ኤም ሆስፒታል ሥልጠና የወሰደው ረዳት የጤና ሐኪም ስሙ ዳንኤል ሲሆን፣ መድኃኒቶችን ከመስጠት በተጨማሪ ወንጌልን ይሰብካል፣ ለበሽተኞቹ ይጸልያል እንዲሁም ፍቅርና እንክብካቤን ይሰጣቸዋል።

ዳኖ እና ዳንኤል በእግዚአብሔር መልካምነት በተከፈተው በር እና ሰላም ተደሰቱ። ከዚያ የወላይታ ሽማግሌዎች ሁሉንም ወንጌላውያን በመጥራት ወደ ተለያዩ ስፍራዎች መደቧቸው። ዳኖ እስከ አሁን ከእርሱ ጋር የነበረውን ዳንኤልን እያመነታ ለቀቀውና መቼ ሊገናኙ እንደሚችሉ ማሰብ ጀመረ። ሌሎች አዳዲስ አማኞች ተካና ገዛኸኝ ከዳኖ ጋር ተገናኙና በክሊኒክ ውስጥ ሕክምና ሲከታተሉ ከነበሩ ሰዎች መካከል ሌሎች ሰዎች በማግኘታቸው የተከፈተ ሌላ በር ተመለከቱ። ሰዎች ሰይጣንን ሲክዱና ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ሲቀበሉ ብዙ የጸሎት ቤቶች በየስፍራው ተከፈቱ።

ኢትዮጵያ በኮምዩኒስት አስተዳደር ሥርዓት መገዛት በመጀመሯ ምክንያት እንደ ሌሎች ስፍራዎች ሁሉ በዲማ አካባቢ በነበሩ ክርስቲያኖች ላይም ስደትና መከራ ይደርስባቸው ጀመር። ሁሉም የኤምኤኤፍ አውሮፕላኖች እንዳይበርሩ ተከለከሉ፣ በመጨረሻም ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ተደረገ። እንደ ሌሎች ክሊኒኮች ሁሉ፣ ክሊኒኮቹ በሕክምና መሣሪያ እጦት ምክንያት ተዘጉ። ቤተ ክርስቲያናት ተዘጉ፣ እንዲሁም መሪዎች በወህኒ ቤት ውስጥ ታጎሩ። ዳኖ ብዙ መከራ ደረሰበት፣ አስፈራሩት፣ ደበደቡት፣ እንዲሁም ለብዙ ጊዜ አሠሩት፣ ነገር ግን ለሚወደው ለጌታው ታማኝ ሆኖ ጸና። የተገለሉት አማኞች በዳኖ መኖሪያ ቤት ውስጥ በምሽት ለጸሎትና ለኅብረት ይገናኙና ለማያምኑ ሰዎች እምነታቸውን ያካፍሉ ነበር። በጣም ብዙ ዓመታት አለፉ። ከሃያ ዓመታት በላይ ማንም ሚስዮናዊ ዲማን ጐብኝቶ አያውቅም ነበር። ለተካ እናት የቦዲ ጎሳዎች ጐበዝ የሆነውን ልጇን መግደላቸውን ሳረዳት በዚያ ስፍራ የነበርኩት የመጨረሻው ሚስዮናዊ እኔው ነበርኩ።

ꕥ

ከወንጌላውያን ቡድን ጋር በመሆን ከባስኬቶ ተነሥተን በተራራማው ሀገር አድርገን ወደ ታች ወደ ዲማ በመኪና ሄድን፡፡ ወንጌላዊ ዳንኤል ከሠላሳ ዓመት በፊት በወንጌል ለመጀመሪያ ጊዜ የጀመረውን አካባቢ እንደገና ለማየት በጣም ጓጉቶ ነበር፡፡ ተስፋዬ፣ ወርቁና ጀማሪ ከእኛ ጋር እየተጓዙ ነበሩ፡፡ ለብዙ ዓመታት ምንም ዓይነት መኪና ተጉዞበት በማያውቀው የአርባ ኪሎ ሜትር ጉዞ ለመጓዝ ሁለት ቀናት ወሰደብን፡፡ ሦስትና አራት ሜትር ርዝማኔ ባላቸው ትልልቅ ሣሮች እንሠቃይ ነበር፡፡

አንድ ጊዜ መንገዱን ስተን ወደ ሸለቆ ውስጥ ወደቅን፣ ባዶና በጣም ጠባብ ነበር፣ ነገር ግን ይህ ስፍራ ሳናውቀው ከባድ ነፋስ ተነሥቶ የከበበንን የዱር እሳት ማምለጫ ብቸኛ መንገድ ሆነልን፡፡ መኪናውን ለማዞር እንዲመቸን የተከመረውን ድንጋይ ስንቆፍር፣ እሳቱ ቀድሞ እኛ የነበርንበትን ስፍራ በሙሉ አቃጥሎት አለፈ፡፡

በሌላ ስፍራ ላይ ደግሞ መኪናችን በድንገት ጥልቅ በሆነ ሸለቆ ውስጥ ገብታ ተቀረቀረች፡፡ ከጫካው ውስጥ በተቈረጠ እንጨት በመታገዝ ጎማውን ከገባበት ስንጥቅ ውስጥ ለማውጣት ታገልን፣ እንዲሁም ሌላኛው ጎማ እንዳይንሸራተት እርከን አበጀንለት፡፡ መኪናውን በደኅና ነድቼ ወጣሁ፡፡ ያን ዕለት እግዚአብሔርን ስለ ጥበቃው አመሰገንነው!

ꕥ

ከሁለት ዓመት በኋላ ወንጌላዊ ዳንኤልና ወርቁ፣ ዳኖንና በዲማ የነበሩትን ክርስቲያኖች በእምነታቸው ይበረቱ ዘንድ ለማበረታታት ከእኔ ጋር ሄደው ነበር፡፡ ዳንኤል እና ዳኖ ለጸሎት አብረው ተንበርክከው ማየት እና በጌታ ደስ እያላቸው የሚወድዱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሲከፋፈሉ መመልከት ምንኛ አስደሳች ነገር ነው፡፡ ዳኖ ከጨለማ ባርነት፣ ከዲያብሎስ እስራት ነፃ የወጣ ነው፣ እናም ከጎዘን ወደ ብርሃን በመሸጋገር፣ በክርስቶስ ብርሃን ውስጥ ያለ ሰው ነው፡፡ በብዙ ጨቋኞች እጅ ተፈትኖ፣ ተሠቃይቶና በብዙ ስደትና መከራ ውስጥ በማለፍ እውነተኝነቱን አረጋግጧል፡፡

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች እንደ ጻፈላቸው፣

‹‹ደግም እናንተ ቃሉን በብዙ መከራ ከመንፈስ ቅዱስ ደስታ ጋር ተቀብላችሁ፣ እኛንና ጌታን የምትመስሉ ሆናችሁ፡፡››

ነኛ ተሰሎንቄ ፩፡6

፲፬

ፍፍ

ጸላዩ እስረኛ

በወጎኒ ቤቱ አጥር ማማ ላይ የነበረው ተረኛ ጠባቂ፣ ባንዲራውን እያውለበለበ በወጎኒ ቤቱ በር ላይ ለቆሙት ዘበኞች እንዲህ ሲል ጮኸ፣

‹‹እየመጣ ነው! በፍጥነት እየሮጠ ነው! በፍጥነት! መዝጊያውን ከፈተ!›› ጠባቂው ከከፍታ ቦታ ላይ ሆኖ እስር ቤቱን ይመለከታል፣ እንዲሁም ከእስር ቤቱ ወደ ከተማው የሚወስደውን መንገድ በደንብ ማየት ይችላል።።

ዘበኞቹም በሩን ከፈቱት፣ በሩ እንደ ተከፈተ ወዲህ እና ወዲያ ይወዛወዛል፤ ጠመንጃዎቻቸውን በደረቶቻቸው ላይ እንደ ወደሩ በጥንቃቄ ይጠብቃሉ፣ ይመለከታሉ።። የእስር ቤቱ ጠባቂዎች ወዲያው በሩን እንደ ከፈቱት ምንም ያዩት ነገር የለም።። ከዚያ ብዙ ጊዜ ሮጦ የማያውቅ እና ድካም ፊቱ ላይ የሚታይበት ሰው ተመለከቱ።። የእርዳታውን ጥያቄ አቀረበ፤ እስር ቤቱ ውስጥ ችግር በመኖሩ ከዚያ በፍጥነት እንደ መጣ ነገራቸው።።

‹‹ምንድን ነው ችግሩ?›› አሉት።። ሰውዬው እንዲሰማቸው ሲሉ የወጎኒ ቤቱ ዘበኞች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ጠየቁት።። እንግዳ የሆነ ነገር እየተመለከተ ስለ ነበረ፣ መልስ ከእርሱ አላገኙም።። በከፍተኛ ድምፅ እየጮኸ፣ እንደ ዕብድና በሰይጣን እንደ ተያዘ ጠንቋይ፣ የወጎኒ ቤቱን አጥርና አንዱን ሕንጻ ለማፍረስ ጥረት ማድረግ ጀመረ።። ሰውዬው ከአጥሩ ጋር ደጋግሞ ይጋጫል።። እንደገና ወደ ቤቱ በመሄድ አጥሩን ለማነቃነቅ ይሞክራል፣ ለማፍረስም ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል።። አጥሩን ለማፍረስ ከመሮጡ በፊት ሁልጊዜ ላንቃው እስኪሰነጠቅ ድረስ ይጮኻል።።

ሁሉም የታጠቁ ዘበኞች ወደ ጠንቋዩ ሰውዬ መቅረብና ለማስቆም መሞከር

ፈሩና በጥበቃ ቤቱ ጎን ቆሙ፡፡ እስረኞቹ በሙሉ- ፍሰ ገዳዮቹ፣ ሌቦቹ እና ብዙ የፖለቲካ እስረኞቹ- እብዱን ሰው ፈርተው በጎጆአቸው ውስጥ ተሸሸገዋል፡፡ የጠንቋዩ ሰውዬ ጩኸትና ተስፋ የቁረጡ በመቶዎች የሚቆጠሩ እስረኞች፣ ዘበኞቹ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ጥሪ በማሰማታቸው ምክንያት በጣም ትልቅ ሁካታ ተፈጠረ፡፡

በዚያ ወጎኒ ቤት ውስጥ የነበሩት ሌሎች ሰዎች አሥር ክርስቲያኖች ብቻ ነበሩ፡፡ እነርሱም ስለ እምነታቸው የታሰሩ ነበሩ፡፡ ጠንቋዩ ሰውዬ ራሱን ለማጥፋት ጥረት ማድረግ በጀመረ ጊዜ፣ እነርሱ አንድ ላይ ሆነው ይጸልዩ ነበር፡፡ ይህንን ሁኔታ እግዚአብሔር በመጠቀም፣ ለራሱ ክብር ይወስድ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር እየጸለዩ ነበር፡፡

አንዱ ዘበኛ ጥቂት ክርስቲያኖች ቆመው ተመለከተ፡፡ ወደ እነርሱም በመጮኽ፣ ‹‹ጸልዩለት! ለዚያ ሰው እባካችሁ ጸልዩለት!›› ሲል ለመናቸው፡፡

ወንጌላዊ ናና እንዲህ ሲል መልስ ሰጠ፣ ‹‹ወደ አምላካችን በመጸለያችን ምክንያት በእስር ቤት ውስጥ አጐራችሁን፣ በሰንሰለት አሰራችሁን፣ ደበደባችሁን፣ እንዲሁም በመጸለያችን ምክንያት ምግብ ከለከላችሁን፡፡ ታዲያ አሁን እንዴት እንድንጸልይ ትጠይቁናላችሁ?››

አንድ በዕድሜ የሸመገሉ ክርስቲያን፣ ናና በተናገረው ነገር ላይ በመጨመር እንዲህ አሉ፣ ‹‹እንዲሁም ወንድማችን ገመዳ ስለ ጸለየ ገደላችሁት፡፡ እኛን አሁን እንድንጸልይ ትጠይቁናላችሁ! ወደ በለጠ ችግር ውስጥ ልታስገቡን ትፈልጋላችሁን?››

ሦስተኛው ሰው በመቀጠል እንዲህ አለ፣ ‹‹ለምን የእናንተን የኮምዩኒስት ትምህርት ሰጥታችሁት ይረዳው እንደ ሆነ አትሞክሩም?››

ዘበኞቹ ነገሩ ገብቷቸው፣ እንዲሁም በነገሩ እጅግ ተስፋ ከመቁረጣቸው የተነሣ፣ ‹‹በጭራሽ፣ ከሰይጣን ኃይል ነፃ ሊያወጣው የሚችል የእናንተ አምላክ ብቻ ነው፡፡ እባካችሁ ይህንን ሰው እርዱት!›› በማለት ክርስቲያኖቹን ለመኗቸው፡፡ ‹‹ልትረዱት ካልቻላችሁ፣ እኛ ተከሰን እንገድለዋለን፣›› አለ አንድ ጠባቂ፡፡ ‹‹የእናንተ አምላክ ብቻ ነው እርሱን ከዚህ ኃይል ነፃ ማውጣት

የሚችለው፡፡ እርሱን መግደል አልፈልግም፡፡ እባካችሁ ጸልዩለት›› አለ በመቀጠል፡፡

ወንጌላዊውም፣ ጠንቋዩ ሰውዬ የወጎኒ ቤቱ ጠባቂ ዘመድ ሊሆን ይችል ይሆንን? ብሎ አሰበ፡፡ ወይም ይህን በሰይጣን የተሞላ ሰውዬን ቢገድል፣ ምን ሊከሰት እንደሚችል ባለማወቁ ምክንያት ግራ ገባቸው፡፡ የጠንቋዩና የጠባቂዎቹ ጩኸት ይበልጥ እየጨመረ ሲሄድ፣ ‹‹እንጸልይለታለን! እባካችሁን ገለል ገለል በሉ፣›› በማለት ናና በታላቅ ድምፅ ተናገረ፡፡

አሥሩ ክርስቲያኖች አቧራማ በሆነው ወለል ላይ በጉልበቶቻቸው ተንበርክከው፣ በግንባራቸው ምድር ላይ ተደፉ፡፡ ተራ በተራ በመጸለይ የእግዚአብሔርን ፊት እየፈለጉ፣ የጌታ ፈቃድ ይፈጸም፣ ኃይሉ ይታይና ክብሩ ይገለጥ ዘንድ ጸለዩ፡፡ የመጨረሻውን ‹‹አሜን›‹ ብለው በእግሮቻቸው ሲቆሙ፣ ናና እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፣ ‹‹የጌታ አእምሮ እንዳለን እኔ እንደማምን እናንተም ታምናላችሁን?›› ሁሉም አማኞች አዎ በማለት በሐሳቡ ተስማሙ፡፡

ክርስቲያኖች እየጸለዩ መሆናቸውን ሌሎች እስረኞች ሲመለከቱ፣ ቀስ በቀስ ጸጥ አሉ፡፡ አሥሩ ክርስቲያኖች የእስር ቤቱን ሜዳ አቋርጠው ጠንቋዩ ሰውዬ ወደ ነበረበት ስፍራ ሄዱ፡፡ ዐይኖቻቸው ወደ ደሙት አፎቹና ወደ ተጐዳው አካሉ ላይ አነጣጠሩ፤ ሰውዬውም ክርስቲያኖቹን ለማጥቃት ተዘጋጀ፡፡

ከዚያም ድንገተኛ ጸጥታ ሆነ፡፡ ጠንቋዩ ሰውዬ መጮኹን አቆመ፡፡ ሌሎችም እስረኞች መጮኻቸውን፣ እንዲሁም የተቈጡት የወጎኒ ቤቱ ጠባቂዎች እርስ በርሳቸው መነጋገር አቆሙ፡፡

ወንጌላዊው እንዲህ አለ፣ ‹‹በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከዚህ ሰውዬ ውስጥ እንድትወጣ አዝዘሃለሁ፡፡ በኢየሱስ፣ በኃይለኛው የእግዚአብሔር ልጅ ስም አሁን ከዚህ ሰውዬ ውስጥ ውጣ፣ ደግመህም ወደ እርሱ እንዳትመለስ!››

ጠንቋዩ በሚያስፈራ ድምፅ ጮኸ፣ ወደ ሰማይ ተነሥቶ በጀርባው አፉ እንደ ተከፈተ ዐይኖቹም እንደ ተከደኑ ወድቆ ቀረ፡፡ ያለ ምንም እንቅስቃሴ ተኛ፡፡

ጠባቂዎቹም ዓይኖቻቸውን ጠንቋዩ ሰውዬ ላይ እንዳፈጠጡ ቀሩ፡፡ ራሱን ስቶ፣ ሞቶ፣ ወይስ ተኝቶ ይሆንን? ወንጌላውያኑ እጁን እስኪይዙት ድረስ ማንም

ሰው ከስፍራው አልተንቀሳቀሰም።

በድንገት ጠንቋዩ ሰውዬ ተነሥቶ ተቀመጠና ዐይኖቹን ከፈታቸው። ክርስቲያኖች ከፊቱ ቆመው አየ። በትክክለኛ ድምፅም፣ ‹‹እናንተ እነማን ናችሁ?›› ብሎ ጠየቃቸው።

አንድ በዕድሜ የገፉ ክርስቲያን ሰውዬ እንዲህ ሲሉ መልስ ሰጡት፣ ‹‹እኛ ከእግዚአብሔር የተላከን መልእክተኞች ነን። በዚህ ያለነው ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልንነግርህ ነው። እርሱ ሰይጣንን ከአንተ ውስጥ አስወጥቶልሃል፤ ስለዚህም አሁን ነፃ ነህ። ስለዚህ የምንልህን በደንብ አድምጥ።››

በጠንቋዩ ላይ በተመለከቱት ለውጥ በጣም ተገርመው፣ የወጎኒ ቤቱ ዘበኞች እነዚህ ሰዎች የሚሉትን ለመስማት ቀረቡ። ወዲያውም እስረኞቹም ከመጠለያቸው ውስጥ እየወጡ፣ በቡድን በቡድን ሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ስለሚገኘው ደኅንነት ክርስቲያኖቹ ሲያስተምሩ ለመስማት ተጠጉ። አብዛኛዎቹ ይህንን ሲሰሙ የመጀመሪያቸው ነበር።

‹‹የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ከሰይጣንና ከሞት በላይ ኃያል ነው። የኃጢአታችንን ዋጋ ለመክፈል በመስቀል ላይ ተሰቅሏል። ኃጢአታችንን ብንናዘዝ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ፍርድ ያድነናል። አዲስ ልብ፣ አዲስ ሕይወት ይሰጠናል። ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንኖራለን፣›› በማለት ወንጌላዊው አስረዳ።

ሌሎች ክርስቲያኖችም የወንጌልን እውነት በአዳኙ ካመኑና እርሱን ከተቀበሉ በኋላ በሕይወታቸው ስለ ተከሰተው ለውጥ ምስክርነታቸውን ሰጡ። የከፉ መናፍስትን ወይም ሞትን ፈርተው ከእንግዲህ ወዲያ አይኖሩም። በክርስቶስ ነፃ ናቸው፣ እንዲሁም ሰላም ልባቸውን ሞልቶታል።

‹‹እኔም አምናለሁ። መንገዱን አሳየኝ፣›› አለ ጠንቋዩ። በእግሮቹ ቆሞ ቀኝ እጁን ወደ ሰማይ በማንሣት ከወንጌላዊው በኋላ እነዚህን ቃላት ደገማቸው፣- ‹‹ሰይጣንንና መንገዱን ክጀያለሁ። ጥንቆላን፣ የደም መሥዋዕትን እና ሁሉንም የጨለማ ኃይላትን ክጀያለሁ። ስለ እኔ የሞተውን የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስን አምኛለሁ። እጆቼን ወደ ላይ አንሥቼ እርሱን እንደ ግል አዳኜና ጌታዬ አድርጌ እቀበላለሁ። ምንም ይሁን ምን፣ ወደ ኋላ

አልመለስም!››

በመጸለያቸውና ወንጌልን በመስበካቸው ምክንያት ወደ ወኅኒ ቤት ተጥለው ነበር፣ ነገር ግን አሁን የደኅንነትን መንገድ ለሰዎች ለማካፈል ነፃነቱን አገኙ፡፡ አብዛኞቹ እስረኞችና የወኅኒ ቤቱ ጠባቂዎች በዚያ ዕለት በፊታቸው በሰይጣን ላይ በታየው የእግዚአብሔር ኃይል በጣም ተገረሙ፡፡ እንዲሁም ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው አምነው ተቀበሉ፡፡ በእያንዳንዱ እስር ቤት ውስጥም እያንዳንዱን አዲስ አማኝ ለማስተማር የጸሎት ስብሰባዎችን ጀመሩ፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችና እግዚአብሔርን እንደሚያመልኩ እንዲሁም ስለ ሁሉም ነገር እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው አስተማሯቸው፡፡ ወዲያውም ቀዝቃዛ በሆነው የአየር ጠባይ ውስጥ የምሥጋና መዝሙር ማስተጋባት ጀመረ፡፡ እኛም ‹‹ትናንትናም፣ ዛሬም እንዲሁም ለዘላለም ለማይለወጥ ጌታ›› ምስጋናችንን አቀረብንለት፡፡

‹‹እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፣ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሸር፣ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፣ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነፃ እንዲያወጣ፣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ።››

ዕብራውያን 2፡14-15

15

ሻንካ

ብርሃኑ ይብራ

እግዚአብሔር ወንጌልን በጎፋ ውስጥ በሩቅ ላሉ ሰዎች ይዞ እንዲሄድ ሲጠራው፣ ወንጌላዊ ላሊሶ በወላይታ ውስጥ የነበረችውን ትንሽ የእርሻ መሬት ትቶ ሄደ። *(ኢትዮጵያውያን የወንጌል ጀግኖች፣* ምዕራፍ 6 ያንብቡ።) ከእርሱም ጋር ሻንካን ይዞ ሄደ። ሻንካ በጎረቤቱ የሚኖር ጌታን የሚወድ ወጣት ነበር። ሻንካን ወደ ጌታ ያመጣውና ደቀ መዝሙር ያደረገው፣ የእግዚአብሔርን ቃል ያስተማረውና ለሌሎች ምስክር መስጠት እንዲችል ያበረታታው እርሱ ነበር። በጎፋ ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ያህል ሻንካ ከላሊሶ ጋር የአገልግሎት ልምምድ አድርጓል፣ ስለ ኢየሱስ ለሰዎች መናገር እንዳለበት ተመልክቷል። ሻንካ ከላሊሶ ሴት ልጅ ጋር የቀረበ ትውውቅ እየኖረው ሲመጣ ደግሞ ሻንካ ይህንን ለማድረግ ይበልጥ ደስተኛ ሆነ። በመጨረሻም እርሷን አገባ።

ሻንካ በወላይታ ሽማግሌዎች አማካኝነት በባኮ ውስጥ ይኖሩ ወደ ነበሩት የአሪ ጎሳዎች ከተላኩት ውስጥ የመጀመሪያው ሚስዮናዊ ነበር። ሻንካ ከአንቦሊ፣ ጌራዴ እና ቡዝዲ ጋር ለብዙ ዘመናት በታማኝነት ጌታን አገልግሏል። በጣም ብዙ ተቃውሞን እና ችግርን፣ መሰደብን፣ መሳለቅን፣ ማስፈራራትን፣ እስርን እና በተለያዩ ጊዜያት ድብደባን አስተናግደዋል፣ ነገር ግን በእነዚህ ሃይማኖት በሌላቸው የአሪ ሕዝቦች መካከል መሣሪያ አድርጎ እግዚአብሔር ተጠቅሞበታል። ቀስ በቀስም በኋላ ላይ ሁሉንም ጎሳ ያጥለቀለቀውን የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ እንዲስፋፋ ምክንያት የሆኑ ጥቂት ሰዎች በማመን ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች። እግዚአብሔር ይባረክ! ዛሬ በአሪ ጎሳ ውስጥ ከ170 በላይ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት አሉ።

ሻንካን ለበለጠ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ወደ ወላይታ ስንጠራው፣ ሁምቦ

ቀጣና ተብሎ በሚታወቀው፣ በእርሱ ቀጣና ውስጥ መጋቢ/ወንጌላዊ ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡ ዋንዳሮና ላሊሶ ለእርሱ ቅርብ በሆኑ ቦታዎች ውስጥ ይሰብኩና አዳዲስ አማኞችን ያስተምሩ ነበር፡፡ እነዚህ ሦስት ሰዎች ከሌሎች አማኞች ጋር በመሆን የጸሎት ቡድን አቋቋሙ፡፡ ይህ አትኩሮት የተሞላበት ጸሎት ብዙ ሰዎች በክርስቶስ አምነው ምላሽ እንዲሰጡ አስቻላቸው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገቡ፣ ሌሎች ደግሞ ሩቅ ወደ ሆኑ ጎሳዎች ወንጌልን ለመስበክ ሄዱ፡፡

አንድ ጊዜ፣ በወላይታ ውስጥ እጅግ በጣም ወሳኝ የሆነውን የእርሻ ሥራውን በመተው ከእርሱ መንደር ውጭ ለሦስት ወራት ወንጌልን ለመስበክ ፈቃደኛ ሆነ፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱም ባርካና በየዕለቱ ለእርሱ ለመጸለይ ቃል በመግባት ለዚያን ጊዜ ያህል ላከችው፡፡ በጣም ድንጋያማና ትልቅ ተራራማ፣ እንዲሁም ጥልቅ በሆነ ሸለቆ ውስጥ እየተጓዘ ወንጌልን ሰምተው የማያውቁ ሰዎችን ፈለገ፡፡ ከመንደር ወደ መንደር እየተዘዋወረ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ለሰዎች ያለውን ፍቅሩን አካፈለ፡፡

በአንድ ከሌሎች በተለየ ሸለቆ ውስጥ ሰዎችን በሙሉ በፍርሃት ሰንሰለት እና በመንፈሳዊ ባርነት ያሰራቸው አንድ ዋራ የተባለ ጠንቋይ አገኘ፡፡ የዚህ ሰውዬ ዕድሜ በግምት መቶ ዓመት ይሆነዋል፡፡ ዋራ የኢትዮጵያን ድንበር ለማስከበርና ብዙ ጎሳዎችን አንድ ለማድረግ በተደረገ ጦርነት ላይ ከሰማኒያ ዓመት በፊት ተዋግቷል፡፡ በኩራት አሥራ አራት ሰዎችን በጦርነት የገደለበትን የአደን ጦርና በሰውነቱ ላይ ያለውን ጠባሳ ለሰዎች ያሳያል፡፡ የዋራ ወንድ ልጆቹና የልጅ ልጆቹ እንዲሁም መላ ቤተሰቡ፣ ሕዝቡን በከፍተኛ ፍርሃት ውስጥ የከተተውን የጥንቆላ ሥራ ይለማመዳሉ፡፡ ሦስት ትውልድ፣ በዋራ መኖሪያ ቤት ደጅ ላይ በሚገኘው የአረጀ የጥድ ዛፍ ሥር፣ ለሰይጣን የደም መሥዋዕት ሲያቀርብ ኖሯል፡፡

ዋራ፣ ሻንካ ክርስቶስ ክፉ መናፍስትን እንደሚያስወጣ፣ ሙታንን እንደሚያስነሣና የታመሙትን ሲያድን በመስማቱ ተደነቀ፡፡ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በፈቃደኝነት መስጠቱን እንዲሁም ስለ እግዚአብሔር ፍቅር፣ ስለ ኃጢአት ይቅርታ እና ስለ መታረቅ ሲሰማ ልቡ ተነካ፡፡ ሻንካ ዋራን ወደ ክርስቶስ በመምራቱ እጅግ በጣም ተደሰተ፡፡ ዋራም እንዲህ አለ፣ ‹‹ቀድሞ በውስጤ ጠንካራና ክፉ መንፈስ ነበር፣ አሁን ግን

የበለጠ ጠንካራው በውስጤ አለ፣ ልቤንም አነጻና ነፍሴን አዳናት፡፡›› ስሜቱንም መቈጣጠር ስላልቻለ፣ ተነሥቶ ይዘልልና በደስታ ብዛት ይደንስ ጀመር፡፡ ዋራ ወዲያው ሲጋራ ማጨሻ ፒፓውን ሰበረ፣ እንዲሁም በእጁ ላይ የነበሩትን ቀለበቶች ሁሉ አውልቆ ጣለ፡፡ እርስ በርሱ የተሳሰረውን ረጅሙን ጸጉሩን ቈርጦ አቃጠለ፣ እንዲሁም ከሰይጣን አምልኮ ጋር ተያያዥነት የነበራቸውን ነገሮች ሁሉ አቃጠለ፡፡ ያንን ያረጀ ትልቅ ዛፍ ቈረጠው፣ እንዲሁም በሥሩ የነበረውን የመሠዊያ ዓለት ሰባበረው፡፡

ዋራ ልጆቹም በኢየሱስ እንዲያምኑ ገፋፋቸው፡፡ ወንድ ልጁና ባለቤቱ ከነልጆቻቸው እንዲሁም በዚህ ቤተ ዘመድ ውስጥ ያሉ ብዙ ወጣቶች ጌታን ሲቀበሉ ሲመለከት ከሻንካ ጋር በጣም ደስ አለው፡፡ ሽምግሎ ስለ ነበር የዋራ ዐይኖቹ ደከሙ፣ ማንበብን መማር አልቻለም፣ ይሁን እንጂ ሻንካ መጽሐፍ ቅዱስን ሰጠው፤ ዋራም በሄደበት ሁሉ ይህንን መጽሐፍ ቅዱስ ይዞት ይሄድና፣ ሻንካ ምልክት ያደረገባቸውን ክፍሎች ሰዎች እንዲያነብቡለት ይጠይቃቸዋል፡፡ ከዚያም ዋራ ክርስቶስ በሕይወቱ ውስጥ ስለ ሠራው ሥራ ምስክርነት ያካፍላል፣ እንዲሁም በልቡ ውስጥ ስላለው ሰላም ይመሰክራል፡፡ ጌታ ወደ ቤቱ እስኪወስደው ድረስ የእግዚአብሔርን ጸጋና ምሕረት ለብዙ ወራት መስክሯል፡፡ ዋራ የክርስቶስን ብርሃን ከሁሉ ይልቅ ተለማምዷል፣ ምክንያቱም ከሁሉም ይልቅ ለረጅም ዓመታት በጨለማው ውስጥ ኖሯልና!

ሻንካ በየሳምንቱ ወደ ገበያ በመሄድ ወንጌልን በአደባባይ ይሰብካል፡፡ አንዳንዶች ይስቁበታል፣ ሌሎች ይሰድቡታል፣ አንዳንዶች ደግሞ ያስፈራሩታል፤ እርሱ ግን መስበኩን ቀጠለ፡፡ በዚህም ምክንያት አንዳንድ ሰዎች ቆይተው፣ የሚለውን ካዳመጡ በኋላ አምነዋል፡፡ ቦጋለ የተባለ አንድ ሰው በኃጢአተኛ ሕይወቱ በመጸጸት በሕዝቡ ፊት ሰይጣንን በመካድ ወደ ክርስቶስ መጥቷል፡፡ ሻንካንም ወደ ቤተሰቦቹ ከእርሱ ጋር በመሄድ ለእነርሱም እንዲነግራቸው ጠየቀው፡፡ ሻንካም ከቦጋለ ጋር ሄዶ ሌሊቱን በሙሉ ወንጌልን ለቦጋለ ቤተሰቦች ሲያካፍል አደረ፡፡ የቦጋለ ሚስትና ልጆቹም በአዳኙ አመኑ፡፡

ብርቱ ዝናብ ጉዞውን በጣም ከባድ አደረገው፡፡ በሚቀጥለው የገበያ ቀን እንዲት ሴት የሻንካን መልእክት በጥንቃቄ አደመጠች፡፡ ሻንካንም ከባለቤቷ ጋር እንዲገናኝ ጠየቀችው፡፡ ‹‹ባሌ ካመነ፣ እኔም አምናለሁ›› አለችው፡፡ ለሁለት

ቀናት ሻንካ ከእነርሱ ጋር በመቆየት የደኅንነትን መንገድ አሳያቸውና መላው ቤተሰቡ በክርስቶስ ሲያምኑ በጣም ደስ አለው። እንዴት መጸለይ እንዳለባቸውም አስተማራቸው፣ ለሌሎችም መመስከር እንዳለባቸው አሳሰባቸው፣ ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት ማድረግ እንዳለባቸውና ስለ እምነታቸው ስደት ሲደርስባቸውም፣ ለጌታ ኢየሱስ ታማኝ መሆን እንዳለባቸው ነገራቸው።

ሌላ ወንጌላዊ ሻንካን ለመርዳት መጣ፤ ሁለቱም በአንድነት በእርሻ ስፍራ እያረሱ ወዳሉ ገበሬዎች ሄዱ። ወጣት ወንዶች እንስሶቻቸውን ውኃ ለማጠጣት ወደ ወንዝ ሲወርዱ ከእነርሱ ጋር ይሄዱ ነበር፣ እንዲሁም ወደ ገበያ ቦታ ከሚሄዱ ሰዎች ጋር ወደ ገበያ ይሄዱ ነበር። ብዙ ጊዜ ወደ ተጋበዙበት ቤት ሁሉ ይሄዱ ነበር። በሦስቱ የዝናብ ወራት ውስጥ ወንጌልን ለመመስከር በሄዱ ጊዜ፣ እግዚአብሔር በእርሱ በመጠቀም፣ ሕፃናት ሳይቈጠሩ፣ 136 አዋቂዎች ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማምጣት በመቻሉና ሁለት አዳዲስ ቤተ ክርስቲያናት በመትከላቸው እግዚአብሔርን አመሰገነ።

ሻንካ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሲመጣ በጣም ጨልሞ ነበር፤ እንዲሁም ደክሞትና ጭቃ በጭቃ ሆኖ ነበር፣ ነገር ግን የጸሎታቸው ምላሽ የሆኑ ብዙ ታሪኮችና ድሎችን ይዞ ነበር። ሚስቱም የምትናገረው ታሪክ እንዳላትና ነገር ግን ምን እያለች እንደ ሆነ ጠዋት ተነሥቶ እንዲያዳምጥ ነገረችው።

ለሦስት ወራት ወንጌልን ለመሰበክ በሄደበት ወቅት፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሥራ ትብብር አደረጉለት። ወንዶች የማረሻ በሬዎቻቸውን፣ ሴቶችና ወጣቶች ደግሞ መኰትኰቻዎቻቸውን ይዘው መጡ። ወጣቶች የሚጠጣ፣ ምግብ ማብሰያና ማሰታጠቢያ ውኃ ሩቅ ቦታ ከሚገኝ ምንጭ አመጡ። በዕድሜ የገፉ ሴቶች ደግሞ በትልልቅ ጀበና ቡና አፈሉ፣ እንዲሁም ለምሳ የሚሆን የበቆሎ ንፍሮ አዘጋጁ። ወንዶቹ በግማሽ ቀን ውስጥ ማሳቸውን አርሰውና ዘርተው ጨረሱ። ከዚያም ሁሉም ክርስቲያኖች ወደ ቤታቸው ከመሄዳቸው በፊት ማዕድ አብረው በመቁረስ ለሻንካ በትንንሽ ቡድኖች ሆነው በመጸለይ የዕለቱ ተግባራቸውን ፈጸሙ።

ሻንካ እንዳይጓዝ ዕንቅፋት የሆነበት ዝናብ ወደ መኖሪያ ቤቱ በትክክለኛው ሰዓት እንዲደርስ አደረገው፤ ሞቃታማው የአየር ሁኔታም የተዘራው ዘር እንዲበቅል አደረገው። አሁን ጥሩ ምርት እያደገ ነው፤ ይህም ለመላ ቤተሰቡ

ቀለብና ለተቸገሩ ሰዎች በጥቂቱ ለመስጠት ይበቃል። ሻንካ በታማኝነት ለሚሰዮን አገልግሎት ስለሚጸልዩና ተግባራዊ እገዛ ስለሚያደርጉ አማኞች እግዚአብሔርን አመሰገነ። እነዚህ ከእርሱ ጋር ወንጌልን የሚያገለግሉ እውነተኛ ‹‹ሠራተኞች›› ነበሩ።

ሻንካ በቀጣዮቹ ዓመታት ሁለት ተመሳሳይ የአጭር ጊዜ አገልግሎቶችን ለማድረግ ችሏል፣ ነገር ግን ጥንካሬው እየቀነሰ ሲመጣ ይበልጥ ወደ ጸሎቱ አዘነበለ። ማማለድ ዋነኛ ሥራው ሆነ፣ ሰዎች ስለ ተለያዩ ነገሮች ይጸልይላቸው ዘንድ ወደ እርሱ ይጐርፉ ጀመር። ይኼውም ስለሚወስኑት ውሳኔ፣ ስለ ጥበብና ምሪት ወይም ስለ ፈውስ እንዲጸልይላቸው ይመጡ ነበር። እግዚአብሔር ወንጌላውያኑን እንዲባርክ፣ ሰዎችን ስለ ኃጢአታቸው እንዲወቅስና እግዚአብሔር በሕዝቡ እንዲከበር ብዙ ክርስቲያኖች ከእርሱ ጋር በመተባበር ይጸልያሉ። ትክክለኛ አምልኮንና ጌታን ማገልገላቸውን ቅድሚያ ያደረጉትን እንደ ሻንካ ያሉ ክርስቲያን ወንዶችንና ሴቶችን ልጆችን እናከብራለን!

> *‹‹በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ፦ በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነውና።››*
>
> 2ኛ ቆሮንቶስ 4፡6

፲፮

ሥነ ፍጡር

በሩን መክፈት

ተስፋዬ ቅጥሩን አቋርጦ በባስኬቶ ወደሚገኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከእኔ ጋር እየሄደ ነበር። በዚያ ትምህርት ቤት ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል ለሚያጠኑ ሃያ ተማሪዎች የእግዚአብሔር ቃል እንዳካፍል ጠየቀኝ። እየተጓዝን ሳለም፣ እንዲህ ብዬ ጠየቅሁት፣- ‹‹ወንጌል እንዴት ወደ ባስኬቶ እንደ ደረሰ ታውቃለህን?››

ተስፋዬ ለጥቂት ጊዜ ያህል አሰብ አድርጎ፣ ‹‹አይ፣ አላውቅም። አንድ ከጎፋ የመጣ ወንጌላዊ ወይም ነጋዴ ወንጌልን ወደዚህ ያደረሰ ይመስለኛል፣›› አለ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መምህራንን እንዲሁም ተማሪዎቹንም ተመሳሳይ ጥያቄ ስጠይቃቸው፣ እነርሱም ወንጌል እንዴት ወደዚያ ስፍራ እንደ ደረሰ የሚያውቁት ነገር አልነበረም፣ ስለዚህም እኔ ነገርኳቸው!

ወንጌል በጎፋ ተራራዎች ላይ በሚገኘው የሚስዮናውያን ጣቢያ ውስጥ ሆነን ብዙ ጊዜ በባስኬቶ ወጣ ገባ ተራራዎች ፀሐይ ስትጠልቅ ያለውን ትዕይንት መመልከት የተለመደ ነገር ነበር። ነገር ግን በተራሮቹ ላይና በጥልቅ ሸለቆዎቹ ውስጥ እንዲሁም በሰማይ ላይ ከሚታየው አስገራሚ ትዕይንት ባሻገር፣ በመንፈሳዊ ድንዛዜ ውስጥ የገባ ሕዝብ በዚያ አለ። ለብዙ ዘመናት ኃይለኛ በሆኑ፣ ሰይጣን ባለባቸው ጠንቋዮች፣ በአካባቢ በሚበቅለው የቡና ተክል ላይ ከፍተኛ ‹‹ቀረጥ›› በማስከፈል ጉቦ በመቀበል ሀብታም በሆኑ፣ ሥነ ምግባር በሌላቸው የመንግሥት ባለ ሥልጣናት እና በእነዚህ ሃይማኖት-የለሽ ሕዝቦች

‹‹ኦርቶዶክሳውያን›› እንደ ሆኑ በሚታሰቡ ቀሳውስት ተጨቍነው ኖረዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ለቀሳውስቱም ሳይቀር ቀረጥ መክፈል ይጠበቅባቸው ነበር፡፡ ተጨቁነው ኖረዋል፡፡ የባስኬቶ ሕዝብ በጨለማ፣ በድህነትና በፍርሃት ውስጥ የሚኖር ሕዝብ ነበር፡፡

በአካባቢያቸው ባሉ ጎሳዎች ውስጥ፣ የከፋ ስደት እና መከራ ቢኖርም፣ ብዙ ሰዎች በሚያስደንቅ ሁኔታ ወደ ጌታ ይመጡ ነበር፣ እንዲሁም አያሌ ቤተ ክርስቲያናት ተመሠረቱ፡፡ በባስኬቶ ግን፣ የወንጌል መልእክተኞች በባርነት ላለ ሕዝብ ወንጌልን ይዘው እንዳይመጡ ለማድረግ አንዳንድ ክፉ ሰዎች ኃይላቸውን ያስተባበሩ ይመስላል፡፡ ለክፉ ዓላማ መነሻን ለማግኘት የተደረገ ማንኛውም ጥረት ብዙ ጊዜ ከሽፏል፡- ብዙዎች የወንጌል መልእክተኞች እንዲወጡ ተነግሮዋቸዋል፣ ወንጌላውያኑ ተደብደበዋል፣ ታስረዋል ደግሞም ከዚህ ስፍራ ተባርረዋል፡፡

በቡልቂ ያለን እኛ ሚስዮናውያን በመኖሪያ ቤታችን ዙሪያ አበቦችን እንደምንተክል፣ ክርስቲያኖችም በቤተ ክርስቲያናቸው ዙሪያ ይህንን እንደሚያደርጉ የኦርቶዶክስ ቀሳውስት አወቁ፡፡ ቀሳውስቱም በአቅራቢያቸው ካለው ትልቅ ከተማ፣ ወደ ሶዶ አምስት ቀን ተጉዘው ብዙ አበቦች ይዘው እንዲመጡ ሰዎችን ከነበቅሎዎቻቸው ላኳቸው፡፡ ይህንንም ማድረግ የፈለጉበት ምክንያት በባስኬቶ መንደሮች መግቢያ ላይ ብዙ አበቦችን ለማስተከል ነበር፡፡ ያሰቡትም፣ ወንጌላውያኑ መጥተው ይህንን አበባ ሲመለከቱ በዚያች መንደር ያሉት ሰዎች ክርስቲያን ሆነዋል ብለው ተሳስተው እንዲሄዱ ለማድረግ ነበር! ለብዙ ትውልዶች ባስኬቶ ባለማወቅና ባለማመን ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ቆይታለች፡፡ ለብዙ ዘመናት በገበያ ስፍራቸው ለመነገድና ለመመስከር የሄደ ክርስቲያን ለሞት ለሽረት በሚያበቃ መልኩ ተደብድቦ፣ ተባርሮ፣ ከተመለሰም እንደሚገደል ይዛትበት ነበር፡፡

መኖሪያ ቤታችን የሚሆነውን ቤት በመገንባት ላይ ሳለሁ፣ እኔ እና ባለቤቴ ቪዳ እንዲሁም ሁለቱ ልጆቻችን እንኖር የነበረው በከፊል በተጠናቀቀው የክሊኒክ ሕንጻ ውስጥ ነበር፡፡ በጊዜያዊነት የተሠራች መጠለያ ቢጤ ሠርተን፣ ቪዳ በየዕለቱ ሕክምና (መድኃኒት) ፈልገው የሚመጡትን፣ በጣም የታመሙ ሰዎችን

ታስተናግድና ታክም ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን፣ ቪዳ፣ መኖሪያ ቤታችንን ወደሚሠራበት ስፍራ ሰዎች ልካ፣ ‹‹ልጆች እንዲወልዱለት ፈልጎ፣ የሕክምና እርዳታ ያገኙ ዘንድ›› ከነበሩት ብዙ ሚስቶቹ መካከል አምስቱን ይዞ ከመጣ ሰው ጋር እንድገናኝ አደረገችኝ። ይህ ሰውዬ በጣም ብዙ ሚስቶች የነበሩት ቢሆንም፣ አንዳቸውም ልጆች አልወለዱለትም። ስለዚህ ተስፋ በመቁረጥ ለሁለት ቀናት ረጅም መንገድ ወደ ምዕራብ ተጉዞ መጣ።

ከሰውዬው ጋር እየተወያየን ሳለን፣ ከበደ በባስኬቶ ካሉት ጥቂት የቀበሌ ባለ ሥልጣናት አንዱ መሆኑን ተረዳሁ። ‹‹ባስኬቶ!›› ስሜቴ በአንድ ጊዜ ተቀሰቀሰና በጣም ደስ አለኝ! ‹‹ለረጅም ጊዜ ስንጸልይበት የነበረው ቦታ፣ ባስኬቶ!›› አልኩኝ። የዚህ ሰውዬ ወንድም በጣም አደገኛ ጠንቋይ ሲሆን፣ በጣም ጨካኝና ክፉ ሰው ነበር። ይህ ሰው እጅግ በጣም ሰፊ መሬትና ብዙ ከብቶች ነበሩት። ቪዳ አሁን የሕክምና እርዳታ የሰጠቻት የመጀመሪያ ሚስቱ ስትሆን፣ ለእርሷ ሠላሳ ከብቶችን እንደ ከፈለ፣ ለሁለተኛዋ 20፣ እንዲሁም ለሌሎች የተለያየ ዋጋ እንደ ከፈለ ነገረኝ። በድንገት ወደ ቪዳ በአገጩ እየጠቁመ፣ ‹‹ለእርሷ ምን ያህል ከፈልክ?›› አለኝ። በእኛ ሀገር ያለው ልማድ የተለየ መሆኑን ማስረዳት አስቸገረኝ። የሚስቴን ወላጆች አግኝቼ ማውራት ብቻ ነበር የሚጠበቅብኝ ብዬ አልነገርኩትም። በቀላሉ እንዲህ አልኩት፣ ‹‹በእኛ ሀገር ሚስቶቻችንን አንገዛም፣ ስለዚህ ለቪዳ ምንም የከፈልኩት ነገር የለም!›› ከበደ ትከሻውን ነቅነቅ አድርጎ በማጉረምረም መልከ ‹‹እንደዚያ ከሆነ፣ ጥሩ አይደለችም ማለት ነው›› አለ።

ቪዳ አምስቱንም ሴቶች ተከታታይ የበሽታ መከላከያ (የአንቲባዮቲክ) መርፌ መውጋት ጀምራለች፤ ጎኖሪያ፣ ቂጥኝና ከርከር የአባለዘር በሽታ እንዳለባቸው ነግራኝ፣ ልጅ መውለድ የማይችሉበት ምክንያት ያ መሆኑን ገለጸችልኝ። እኔም ለአቶ ከበደ የችግሩ ሁሉ መሠረት እርሱ መሆኑን ነገርኩት፣ ምክንያቱም በኃጢአት በሆነው የአኗኗር ዘይቤው የተነሣ መሆኑን በመግለጽ፣ እርሱም በሽታውን ለማስወገድ መርፌዎች መወጋት እንደሚገባው ነገርኩት። በነገሩም ተስማምቶ ወዲያው ሕክምናውን መከታተል ጀመረ።

ከነሚስቶቹ የሕክምና ክትትል ለማድረግ ለአንድ ሳምንት በከተማይቱ

ውስጥ ቆዩ፡፡ ከበደም የክርስቶስን ወንጌል ብዙ ጊዜ ሰማ፣ ልዩ ፍላጎትም በውስጡ አደረ፡፡ ሁለት ‹‹መምህራንን››፣ ወንጌላውያንን ለመውሰድና ለቤት መሥሪያ የሚሆን ቦታ ለመስጠት፣ ለመጠበቅና ለመንከባከብ ቃል ገባ፡፡ ለቃሉም ታማኝ ነበረና በጥቂት ወራት ውስጥ ወንጌላውያኑ ብዙ ዘመዶቹንና ጎረቤቶቹን ለክርስቶስ ማረኩና ቤተ ክርስቲያን ጀመሩ፡፡ በኋላም ላይ ይህቺ ቤተ ክርስቲያን በመላው ጎሳው ውስጥ ተባዛች፡፡ እርሱም ወደ ክሊኒክ ይዞዋቸው የሄደው አምስቱ ሚስቶቹ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ልጅ መውለድ በመቻላቸው በጣም ደስ አለው!

ሩቃ

‹‹እግዚአብሔር ወደ ባስኬቶ ወንጌል እንዲደርስ በር የከፈተው እንዲህ ነው፣›› በማለት ለተስፋዬ፣ ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መምህራንና ለተማሪዎቹ ነገርኳቸው፡፡ እነርሱም፣ ወንጌል ወደ አካባቢያቸው የደረሰበትን መንገድ በመስማታቸው ተደስተው እግዚአብሔርን በማመስገን አጨበጨቡ፡፡ በዚያን ቀን እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን ለመገንባት የሚጠቀማቸውን የተለያዩ መንገዶች በመመልከት በአድናቆት ተሞላን፡፡ እግዚአብሔር ጸሎትን የሚመልስና የተዘጉ በሮችን የሚከፍት አምላክ መሆኑን መመልከት በመቻላችን ምንኛ የታደልን ሰዎች ነን!

እኔ እና ተስፋዬ በባስኬቶ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት ጎብረት አቋርጠን በመመለስ ላይ ሳለን፣ በመቶዎች በሚቆጠሩ አባላት ያሉበት፣ መጽሐፍ ቅዱስና የተማሪዎች ማደሪያ ስፍራ ያለው፣ የቤተ ክርስቲያን ቢሮዎች፣ ለወንጌላውያን፣ ለመጋቢያንና ለሽማግሌዎች መሰብሰቢያ ስፍራ፣ የጸሎት ክፍል እና ለሦስት መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ባስኬቶ ቋንቋ ለሚተረጉሙ ሰዎች ሦስት ትልልቅ ቤቶች ያሉት አንድ በጣም ትልቅ ቤተ ክርስቲያን አሳየኝ፡፡ ከሸለቆው ባሻገር ያለውን፣ በርቀት የሚታየውን ሰንሰለታማ ተራራን ለማየት ለጥቂት ጊዜ ቆምን፣ በሰሜን በኩል የማሎ መንደር በተራሮች ጫፍ ላይ ትገኛለች፣ እንዲሁም የአሞ ወንዝ ሸለቆዎች ዝቅተኛው ስፍራም ይታያል፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ከሚሠራበት ቤት አቅራቢያ ስንደርስ፣ ተስፋዬ እንዲህ ብሎ አስደነቀኝ፣ ‹‹ይህ ቤት የተሠራው ጠንቋዩ ለሰይጣን፣ ለክፉ መናፍስት እና ለቅድመ-አያቶቹ መንፈስ መሥዋዕትን ያቀርብ በነበረበት ቦታ

ላይ ነው፡፡›› ይህ ከሰይጣን የጨለማ ዙፋንነት ወደ ወንጌል ብርሃንነት መለወጡ በጣም የሚገርም ነው!

ወደ ቤቱ ውስጥ ስንገባ፣ ተስፋዬ በውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ይሠሩ ከነበሩት ሰዎች ጋር አስተዋወቀኝ፡፡ ሦስተኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ከሚሠራው ሰውዬ ጋር ሲያስተዋውቀኝ በዐይኖቹ ትኵር ብሎ እየተመለከተኝ፣ ፊቱም ላይ ደስ የሚል ሁኔታ አሳየኝ፡፡ ‹‹ቡልቂ ወደ ነበረው ክሊኒክ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ወደ ባስኬቶ ሕዝብ ያመጡትን ወንጌላውያንን ይዞ የመጣው የከበደ ልጅ ነው፡፡ አብዛኞቹ የቤተሰቡ አባላት ክርስቲያኖች ናቸው›› አለኝ፡፡

‹‹ይህንን ሊያደርግ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው!›› በማለት ጮኽኩኝ፡፡ ‹‹ምስጋና ለእርሱ ይሁን! ነገሮች እንዴት ተለወጡ! የቃሉ ብርሃን በመምጣቱ ምክንያት የሰይጣን ጨለማ ጠፍቷል! እዚያው አካባቢ ባለች ላስካ በምትባል ከተማ ውስጥ ወንጌላዊ ተካ፣ ናና እና እኔ በካድሬዎች ከመረሸን ለጥቂት ነበር የተረፍነው፡፡ (*ሊትዮጵያውያን የወንጌል ጀግኖች* የሚለውን መጽሐፍ ምዕራፍ 8 ይመልከቱ፡፡) አሁን ግን ሰላም ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የብዙዎችን ሕይወት ቀይሯል፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን!››

ተስፋዬ የአንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን መጋቢና በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ በትርፍ ጊዜው አስተማሪ ነበር፡፡ ነገር ግን ከእርሱ ቀጣና ውጭ ወዳሉ፣ ወንጌል ያልደረሳቸው ሰዎች ዘንድ ሄዶ አያውቅም፡፡ ይህንን ለማድረግ የተለያዩ ግፊቶች ሲመጡበት ከወንጌላዊ ዳንኤል፣ ኤርምያስ እና ወርቁ ጋር አብሮ በመሆን፣ በተራራዎቹ አድርገንና ሸለቆውን አልፈን ወደ ዲማ ሄድን፡፡ በእነዚያ ረጃጅም ሣሮች መካከል የተደረገ በጣም አስቸጋሪ ጉዞ ነበር፡፡ ይህ ሣር ‹‹የዝሆን ሣር›› ይባላል፣ የተባለበትም ምክንያት፣ ዝሆንን የሚደብቅ ቁመት ያለው በመሆኑ ነበር፡፡ በመንገዳችን ሁሉ ውስጥ የጌታ ምሪትና ጥበቃ እንዳለን በደንብ እናውቅ ነበር፡፡

አሁን በጨለማውና በኃጢአት ያሉትን፣ ሌላ ቋንቋና ባህል ያላቸውን ወንዶችንና ሴቶችን የመመልከት ልምድ ያለው ተስፋዬ፣ ወደ ክርስቶስ ለመምራት የመስቀሉን መልእክተኞች በመላክ እግዚአብሔር ለተስፋዬ ያሳየውን

ጸጋና ምሕረት አስታውሶታል። ይህንን መጽሐፍ እየጻፍኩ እያለ፣ ተስፋዬ በናይሮቢ፣ ኬኒያ ውስጥ ትምህርቱን እየተከታተለ ነበር፤ እንዲሁም ተስፋዬ በባስኬቶ ቀጣና ውስጥ ጌታን ለማገልገል ቀኑን እየተጠባበቀ ነበር።

> *‹‹በዚያን ጊዜም ስለ እርሱ ደግሞ የታሰርሁበትን የክርስቶስን ምሥጢር እንድንነግር እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ።››*
>
> ቈላስይስ 4፡3

> *‹‹ሥራህን አውቃለሁ፤ እነሆ፣ በአንተ ፊት የተከፈተ በር ሰጥቼአለሁ ማንምም ሊዘጋው አይችልም፤››*
>
> ራእይ 3፡8

፲7

ሰማንያ

የነገሩ ርዝመትና እጥረት

ወንጌላዊ ለማና እና ሚስቱ ጣቢታ እና ልጃቸው ወደ ዛላ የደረሱት ሞቃታማ ቀን በሆነ በክረምት ወራት ውስጥ ነበር። በወላይታ ከሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ተነሥተው በሞቃታማው ሸለቆ ውስጥ የቁጫ ሰንሰለታማ ተራራን አቋርጠው፣ በጣም ሞቃታማና ወባ ወዳለበት ሌላ አካባቢ ለመድረስ አራት ቀን ፈጅቶባቸዋል። በ‹‹ቢጋ ወራት›› በቡልቂ ያሉ ነጋዴዎች የመኪና መጓጓዣ መንገድን ይዘው ነበር የተጓዙት። ብዙ ያገለገለውና ያረጀው፣ በጣልያን ወረራ ጊዜ የተተወ መኪና ለሱቅና ለገበያ የሚሆኑ ዕቃዎችን እንዲሁም በዕቃዎቹ ላይ ብዙ ተሳፋሪዎችን ጭኖ ብዙ ጊዜ በዚህ መንገድ ላይ ይጓዛል። መኪናው ወደ ውጭ የሚላክ ቡናና ቅመማ ቅመም ጭኖ ይመለሳል።

እነዚህ ጥንዶች ከመንገዱ በመገንጠል ወደ ረጃጅሞች ሣሮች ውስጥ ገብተው የእግር ኮቴአቸው እስከሚጠፋ ድረስ ይህንን መንገድ ተከትለው ተጓዙ። ወደ ደቡብ በመዞር ይህንን መንገድ ተከትለው ወደ ሸለቆው የሚወርደውን ረጅም መንገድ ይዘው ሄዱ። በጣም ሞቃታማና የሚሸት ነበር፤ የወባ ትንኞችና ዝንቦች ያለምንም ርኅራኄ ይነድፏቸው ነበር። ከዚያም ሸቅብ ወደ ዛላ የሚወስዳቸው ዐቀበታማ መንገድ አገኙ። ይህንንም መንገድ ተከትለው ሄዱ። ለማ እና ሚስቱ ከአንድ ዛፍ ጥላ ሥር ለማረፍና ልጃቸውን ለመመገብ ለመጸለይም ሲሉ ተቀመጡ።

እነዚህ ወጣት ጥንዶች በማያውቁት እና አደገኛ ሊሆን በሚችለው ክልል ውስጥ ናቸውና የጌታ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ያውቃሉ። የአካባቢው መሪ፣ አባይነህ በሰላም ይቀበላቸው ዘንድ ጸለዩ። ስለ እርሱ ክፉነትና ጨካኝነት ሰምተዋል። አባይነህ በ1890ዎቹ ምንሊክ የደቡብ ጎሳዎችን ሁሉ በማሸነፍ

ዘመናዊቷን ኢትዮጵያ ሲመሠርቱ የተያዘው የመጨረሻ የዛላ ንጉሥ የልጅ ልጅ ነበር። አባይነህ እንደ ንጉሥ ሆኖ ያለ ርኅራኄ ሕዝቡን ይገዛ ነበር። ሁሉም ሰው እርሱን ላለማበሳጨት ጥረት ያደርጋል- በእርሱ ቀኑጡ ባሕርይ እንዳይጐዳ ሰው ሁሉ ይፈራ ነበር።

ወደ ዛላ እንደ ደረሰም፣ የመንደሪቱ አለቃ በመንደሩ ውስጥ እንደሌለ ተነገረው። ለአንድ ሳምንት ያህል ይቆያል፤ አገልጋዮቹም መቼ ሊመለስ እንደሚችል አላወቁም። መሪያቸውን ወክሎ የሚሠራው አገልጋይ ለማና ቤተሰቦቹ እርሱ ጋ ለማረፍ በመምጣታቸው፣ ለመኖሪያ ቤት መገንቢያና ለአትክልት ስፍራ የሚሆን ቦታን መከራየት በመፈለጋቸው ተደሰተ። ብዙ ሰዎች ወደ ዛላ ይመጣሉ፤ ነገር ግን ከእርሱ ጋር ለመቆየት የሚመርጡ በጣም ጥቂቶቹ ነበሩ።

ከብዙ ድርድር በኋላ፣ በአቅራቢያው ባለው መንደር ውስጥ መንገድ ጫፍ ላይ ያለ መሬት ተሰጠው እንዲሁም ሁሉም ሰው ከብቶቹን የሚያሰማራበትን የግጦሽ ስፍራ አሳዩት። ለማም በፍጥነት መኖሪያ ቤት ለመሥራት ተነሣሣ። ረጃጅም ሣሮችን ለጣሪያ መከደኛነት ከሸለቆው ዓጨደ፣ እንዲሁም ለግድግዳ የሚሆን እንጨትን ከጫካው ውስጥ በመቀረጥ ሰበሰበ። አንዳንድ ጎረቤቶቹም ጣሪያውን በመገንባት ረገድ ረዱት፣ ወዲያውም ለማና ጣቢታ በአዲሱ ቤት ውስጥ ገብተው መኖር ጀመሩ።

ሳምንታት ካለፉ በኋላ፣ ለማ መሬቱን አረሰ፤ ባለቤቱ ደግሞ በቆሎ፣ ስኳር ድንች፣ የቡና ተክል፣ የሸንኮራ አገዳ እና ሌሎች ቅመማ ቅመሞችን ተከለች። ለማ በአካባቢው ያሉ መንደሮችንና ጎረቤቶቹን ሁሉ እየዞረ በመጐብኘት ከሰዎች ጋር መተዋወቅ ጀመረ፤ ጣቢታ ደግሞ ሴቶችን ከምንጭ ውኃ ሲቀዱ፣ የማገዶ እንጨት ሲለቅሙ እና በሳምንታዊው የገበያ ስፍራ ታገኛቸው ነበር። ለማ በእርሻው ቦታው ላይ ለምግባቸው የሚሆን ነገርን ያዘጋጅ ነበር፣ ገበሬዎችም በእርሻ ወይም በምስጥ የተበላውን ቤታቸውን በሚያድሱበት ወቅት ያግዛቸው ነበር። ረጃጅም የምስጥ ኩይሳዎች በዛላ ውስጥ በብዛት ይገኛሉ።

ከመጡበት ቀን ጀምሮ፣ ለማና ጣቢታ ለአካባቢው ሕዝብ የመጡበትን ምክንያት ይነግሯቸው ነበር። ይኸውም መልካሙን ዜና ሊያበሥሯቸው ነበር፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስላለው ደኅንነት፣ ሕይወት፣ ተስፋ እና ሰላም መልካም ዜና ለማብሠር ነበር የመጡት። በፍርሃት ለብዙ ዘመናት ለኖሩት የዛላ ሰዎች -

በርኵሳን መናፍስት፣ በሰይጣን፣ ጠንቋዮች እና በሞት ፍርሃት ውስጥ ለኖሩ ሰዎች ይህ በእርግጥ መልካም ዜና ነበር። እነዚህ እንግዶች የዛላ ሰዎች አሁን ያሉበትን ፍርሃትና እስራት እንዲሁም መንፈሳዊ ጨለማ ምን እንደ ሆነ ያውቁታል፣ ምክንያቱም እነርሱም በዚያ ውስጥ ነበሩና ነው፤ ነገር ግን አሁን ይቅር ተብለው በአዳኙ አማካኝነት ሰላምን አግኝተዋል። የዛላ ሰዎችም ይህንን ሕይወት ያገኙ ዘንድ ምኞታቸው ነበር።

ለማና ሚስቱ በየዕለቱ ጠዋት በማለዳ በመነሣት ለዛላ ሕዝብ ይጸልያሉ። ከእነርሱ ጋር ቡና እንዲጠጡ ሰዎችን በመጥራት ጓደኞች አበጁ። ቡናው እየተፈላና ቆሎው እየተቆላ ሳለ፣ ለማ ለሰዎቹ የጨለማውን ኃይል ሁሉ ስላሸነፈውና ለሚያምኑት አዲስ ሕይወትን ስለሚሰጠው የእግዚአብሔር ልጅ ስለ ሆነው ስለ ኢየሱስ ይነግራቸው ነበር።

አንድ ቤተሰብም ለማንና ሚስቱን በእሑድ ማለዳ፣ ለአምልኮ እና አብረዋቸው ለመጸለይ ሲጋብዟቸው ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸውም። ከዚያም ጥቂት ወጣቶች፣ በአሥራዎቹ ዓመት ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ልጆችና ብዙ ሴቶች መጡ። አዳዲሶች አማኞች በየቀኑ እየተገናኙ ስለ ክርስቶስ ይበልጥ የሚማሩበት ቤት በአንድነት ሠሩ። ብዙ ኃይለኞች ወንዶች፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ መሪ የሆኑ ሰዎችና ብዙ ቤተሰቦች አመኑ። ለማ ክርስቲያኖችን ለጥምቀትና ለቤተ ክርስቲያን አባልነት ለማዘጋጀት ትምህርት ማስተማር ጀመረ።

ከዚያም የአካባቢው ሹም አባይነህ ወደ ቤቱ ተመልሶ መጣ።

ꕥ

ወንጌላዊ ለማና አለቃ አባይነህ በሁሉም ነገር ላይ የተለያዩ ናቸው! ለማ አጭርና ቀጭን ነው፣ ከምናውቃቸው ወንጌላውያን ሁሉ አጭሩ እርሱ ነው፤ ቁመቱም ከአምስት ጫማ (ከ1.5 ሜትር) ያንሳል። አባይነህ ግን 6 ጫማ ከሦስት ኢንች (1.9 ሜትር) ሆኖ፣ ጠንካራና ወፍራም ነው። ለማ ቀላ ያለ መልክ ያለው ሲሆን፣ በዛላ ያለው አባይነህ ግን በጣም ጥቁር ነው። ለማ ዝምተኛ፣ ትሑት፣ ትዕግሥተኛ እና ለሰዎች የሚጠነቀቅ ሲሆን፣ አባይነህ ግን የሚጮኽ፣ ትዕቢተኛ፣ ቀኑጡ እና ክፉ ነው። ለማ ታታሪ ሠራተኛ ሲሆን፣ አባይነህ ግን ሰዎች ሁሉንም ነገር እንዲሠሩለት የሚፈልግ ሰው ነው። ለማ

መልካም መሪ፣ ሌሎችም እንዲመሩ ማድረግን የሚወድድ ሰው ሲሆን፣ አባይነህ ግን ሁሉንም ነገርና ሰውን መቈጣጠር የሚወድድ ሰው ነው።



አባይነህ፣ የወረዳቸው ዋና ከተማ ከሆነው ከቡልቂ፣ የክፍለ ሀገራቸው ዋና ከተማ ወደ ሆነችው ጨንቻ ከዚያም ወደ ሀገሪቱ ዋና ከተማ አዲስ አበባ በመጓዝ ለአንድ ወር ቆይቶ ሲመለስ፣ በገዛ ምድሩ ላይ ደስተኞች በሆኑ ሰዎች የተሞላ የጸሎት ቤት በመመልከቱ ደስተኛ አልነበረም። በጉዞውም እንደዚህ ያሉ ቡድኖች በተለያዩ መንደሮች መኖራቸውን ሰምቷል፤ በእነዚህ ‹‹የኢየሱስ ሕዝቦች›› ላይ ከፍተኛ ስደትም እንደ ተነሣባቸው ያውቃል። በጎፋ ውስጥ እንኳ በአቅራቢያቸው እንደ ማሎ እና አሪ ባሉ መንደሮች ውስጥ እንኳ ይህ እንቅስቃሴ ተጀምሯል። ነገር ግን አባይነህ፣ ‹‹እዚህ በራሴ መሬት ላይ? በጭራሽ! አይሆንም››! አለ።

አባይነህ ለማን በማስጠራት አካባቢውን ለቅቆ በፍጥነት እንዲሄድ ነገረው፣ ወንጌላዊው ግን በመሬቱ ላይ ለመኖር የኮንትራት ውል እንዳለውና በኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት ነፃነት መኖሩን አስረድቶ ለመቆየት መወሰኑን ነገረው። ለማ ወንጌልንም ለአባይነህ ለማስረዳት ጣረ። የሀገሩም ሰዎች በክርስቶስ በማመናቸው የተሻሉ እንደ ሆኑ ነገረው። ነገር ግን አባይነህ ሰደበው እንዲሁም አስፈራራው፤ ጀርባውንም በአለንጋ ገርፎ ከአጥር ውጭ አስወጣው።

አባይነህ፣ ልክ እንደ ሌሎች የጎሳው ሰዎች ሁሉ፣ ራሱን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ እንደ ሆነ አድርጎ ይቈጥራል፤ ለቀሳውስቱም አስፈላጊ የሆነውን ክፍያ ይከፍላል፣ ነገር ግን ይህ እምነቱ ከባህላዊ እምነቱ ጋር ተቀላቅሎበታል። ባህላዊው እምነቱ መናፍስትን ማምለክ፣ የደም መሥዋዕትን ማቅረብ፣ መሐላና ለጠንቋዮች ትእዛዝ መታዘዝ ያጠቃለለ ነበር።

አባይነህ በለማና በክርስቲያኖች ላይ ማድረግ ስለሚገባው ነገር እርግጠኛ አልነበረም። ስለ ነፃነትና አዲስ ሕይወት በማውራታቸው ምክንያት ለእርሱ ሥልጣንና ቍጥጥር አስቸጋሪ እንደሚሆን ተሰምቶታል። ‹‹የኢየሱስ ሰዎችን›› በተመለከተ በቡልቂ ስብሰባ ሊደረግ መሆኑ መልእክተኛ ከቡልቂ መጥቶ በነገረው ጊዜ፣ አባይነህ ወደዚያው በፍጥነት በበቅሎው ተጉዞ ሄደ። እነዚህን

ክርስቲያኖች በተመለከተ ምን ማድረግ እንደሚገባው የተወሰነ ምክር አገኛለሁ ብሎ ተስፋ አድርጎ ነበር።

በዛላ ውስጥ ያሉት ክርስቲያን ወንድሞች፣ ከምንጩ ዝቅ ብሎ አንድ ትልቅ ጉድጓድ ቆፍረው ውኃ ይሞላው ዘንድ ቦይ አበጁለት። የመጀመሪያዎቹን የሠላሳ ሰዎች ጥምቀት ለመመልከት በጣም ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ነበር። ለማ ስለ አዲስ ሕይወትና ደኅንነት ሲሰብክ ትልቅ ደስታ የተሞላበትና በጣም ብዙ ሰዎች የሰሙበት ጊዜ ነበር። ሰላምንና የኃጢአት ይቅርታን ያገኙ፣ እንዲሁም በሕይወታቸው ውስጥ ለውጥ የታየባቸውን የዘመዶቻቸውንና የጓደኞቻቸውን ምስክርነት አዳመጡ።

በእነርሱ ላይ እየተዶለተ ስላለው ስደት የትኞቹም ክርስቲያኖች አያውቁም ነበር። ምንም ያህል ዋጋ ያስከፍል እንጂ፣ ሰይጣንን በመካድ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ለመከተል መወሰናቸውን በጥምቀት ዐወጁ።

የመንግሥት ባለ ሥልጣናትን፣ ፖሊሶችን፣ የመሬት ከበርቴዎችን፣ ቄሶችንና ጠንቋዮችን ያካተተው ይህ ስብሰባ በእነዚህ አዲስ ክርስቲያኖች ላይ በጣም የጸና ስደትን አስከተለ። በጎፋ አውራጃ ውስጥ ሁሉም ከሃያ የሚበልጡ የጸሎት ቤቶችና አማኞች ቤቶች ተቃጠሉ። ከአርባ ሁለቱ ወንጌላውያን ውስጥ ከአንዱ በስተቀር፣ ሁሉም እንዲሁም ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ተይዘው ተደበደቡ፣ እንዲሁም ታሰሩ። ቤተሰብ ሲበታተን፣ ንብረታቸው ሲዘረፍ፣ እንስሶቻቸውና እህላቸው ሲወሰድባቸው፣ እንዲሁም መሬታቸው ሲወረስባቸው ከፍተኛ ተስፋ መቁረጥና ትልቅ መከራ ሆኖባቸው ነበር።

አባይነህም ምን ማድረግ እንዳለበት በማወቅ ከቡልቂ በፍጥነት ተመለሰ። ሌሎች በጎፋ ውስጥ ያደረጉባቸውን እርሱም አደረገባቸው። ለማ ከሌሎች ወንጌላውያን ጋር ተያዘና በሰንሰለት ታስሮ ወደ ቡልቂ እስር ቤት ተላከ፤ ከዚያም አባይነህ ሎሌዎቹን ሰብስቦ ቤተ ክርስቲያኒቱንና የለማን ቤት እንዲሁም የሁሉንም ክርስቲያኖችን ቤት አቃጠለ። የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እንዲሆኑም የተመረጡ ሌሎች ሦስት ሰዎችን በጥይት ገደላቸው፣ እርሱ በሚቈጣጠረው መሬት ላይ የነበሩት ጥቂት ቤተሰቦችንም ከመሬቱ ላይ አባረራቸው።

በሚቀጥሉት ዓመታት፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት የሚያልፉባቸውን መከራዎች የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ በእምነታቸው ጸንተው የሚቆሙ ሰዎች ይገደላሉ፣ እንዲሁም በጣም ብዙ መከራ ይደርስባቸዋል፡፡ እኛን የጠየቁን ነገር ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ ሆነው መቆየት እንዲችሉ በጸሎታችን እንድናግዛቸው ብቻ ነበር፡፡

እነዚያ ክፉ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት በሚያደርጉት ጥረት ያልተገነዘቡት ነገር የእሳቱ ፍም ሲበተን ሌላ እሳት እንደሚፈጥር ነበር፡፡ ስለዚህም በክርስቶስ እሳት የተቀጣጠሉ አማኞች ወደሚሸሹበት ስፍራ ሁሉ ወንጌልን ይዘው ይሄዱና አዳዲስ ቡድኖችን በትንሽ ቤት ወይም በጫካ ውስጥ በመጀመር አዲስ ቤተ ክርስቲያንን በዚያ ይተክሉ ነበር፡፡ በእነዚያ አስከፊ የስደት ዓመታት፣ አብዛኞቹ ወንጌላውያን ታስረው እያሉ፣ አዳዲስ ክርስቲያኖች ወንጌልን ለሰዎች በማካፈል በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ለጌታ ኢየሱስ ይማርኩ ነበር፡፡ ‹‹ነበልባሉ›› ከተራሮች ላይ ሲበተን እስከ ታችኛው ሸለቆ ድረስ መድረሱን የሚያመለክት እንደ ዛላ ያለ ምስክርነት አልነበረም፡፡

ለንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ በብዙ ሰዎች በኩል በቀረበ ልመና አማካይነት ይህ የከፋ ስደት ከብዙ ጊዜያት በኋላ እንዲቆምና ወንጌላውያኑ፣ መጋቢያኑና ሽማግሌዎቹ እንዲፈቱ ተደረገ፡፡ ለማ ወደ ዛላ ተመልሶ ሄዶ በየዕለቱ በመንደሩ ውስጥ የተጀመሩትን ትምህርቶች ለማስተማር አዳዲስ ቡድኖችን ያገኝ ነበር፡፡ ሌላ ወንጌላዊ ከወላይታ ወደ ዛላ በመምጣት ለማን ያግዘው ጀመር፡፡ ጋንዳሎ የተባለ የዛላ ሰውም ወንጌላዊና መጋቢ ሆነ፡፡ ሌሎች ጠንካራ ወንዶች በመነሣት የቤተ ክርስቲያኖቹ መሪዎች ሆኑ፡፡ ቡድኖቹም ወደ ቤተ ክርስቲያንነት በማደግ ተባዙ፤ ዛሬ በጎፋ አካባቢ በመቶዎች የሚቆጠሩ ቤተ ክርስቲያናት ይገኛሉ፡፡

በተመሳሳይ ጊዜ፣ ብዙ ሰዎች ስለ ነበረው ምዝበራና ኢ-ፍትሐዊነት ባሰሙት ሮሮ ሊሆን ይችላል፣ ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ ‹‹የአማካሪ ሴኔት›› አቋቋሙ፡፡ (ክርስቲያኖች እነዚያ የተሻሩ ሰዎች ከሥልጣናቸው እንዲነሡ የጸለዩ ሰዎች የጸሎት መልስ እንደ ሆነ ቁጥረውታል!) በጣም ብዙ የአካባቢ አስተዳዳሪዎች፣ ዳኞች፣ የጎሳ መሪዎች እና የግምጃ ቤት ባለ ሥልጣናት የዚህ ጠቃሚ ካቢኔ አባል እንዲሆኑ ተጠሩ፡፡እነዚህ ሰዎች ንጉሡን ለማማከር ዘወትር መገኘት

አለባቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ብዙ መጥፎ ባለ ሥልጣናትን ወደ እስር ቤት ያስገባና ወጣቶቹን የተማሩትን የኃላፊነት ስፍራን እንዲይዙ ያደረገ ክስተት ነበር፡፡ በቡልቂ የሚገኘው የነፋ አስተዳዳሪና አለቃ አባይነህ ከዛላ ወደ አዲስ አበባ ከተጠሩት ሰዎች መካከል ነበሩ፡፡ ወደዚያ ሲሄድ በኩራትና በታላቅ ክብር ነበር፣ ነገር ግን እንደ ሌሎቹ በሙስና እንደ ተበከሉ ሰዎች ሁሉ ላብ በላብ ሆኑ፣ ሥልጣናቸው ሁሉ ተቀምቶ፣ በሀገሪቱ ውስጥ በምትገኝ ከተማ ውስጥ ያለ ምንም ሥልጣን እንዲቀመጡ ተደረገ፡፡

በዋና ከተማ ውስጥ በሚገኙ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ውስጥ ብዙ ታማኝ፣ በሙስና ያልተበከሉ ዳኞች ነበሩ፡፡ አንዳንዶቹም ክርስቲያኖች ነበሩ፡፡ ሙሉ መጃ የተባለው የወላይታ ቤተ ክርስቲያንን ከሃያ ዓመት በላይ የመራው፣ የዳና መጃ ልጅ ከእነዚህ መካከል አንዱ ነበር፡፡ ይህም ሰው በሀገሪቷ ውስጥ ያለምንም ወንጀል የታሰሩት ክርስቲያኖች ፍትሕን እንዲያገኙ አድርጓል፡፡ ሙሉ ለብዙ ጊዜ ደስተኛ ያልነበረውን የዛላውን አለቃ አባይነህን እንደ ጓደኛ በመቅረብ ለብዙ ወራት ወንጌልን ነግሮታል፤ ይህም ሁኔታ በመጨረሻ አባይነህን ወደ ድነት አምጥቶታል፡፡ ይህ ነገር በሕይወቱ የተደረገ ድንቅ ነገር ነበር! ፍጹም የሆነ ለውጥ! አዲስ ሰው መሆን ማለት ይህ ነው!

በኋላ ላይም አባይነህ ዛላን ለመጐብኘት ፈቃድ አግኝቶ ነበር፡፡ ወደዚያም ሄዶ ክርስቲያኖችን ይቅርታ ጠይቆ ከእነርሱ ጋር ዕርቀ ሰላም ፈጠረ፡፡ በዚህም ምክንያት በዛላ ተራሮች ላይና ሸለቆዎች ውስጥ የደስታ ንፋስ ተንሰራፋ፡፡ ለማ በአባይነህ መኖሪያ ግቢ ውስጥ ለብዙ ቀናት የአምልኮ እና የምስጋና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ አዘጋጀ፡፡ ወንጌላዊ ለማ እና ጋንዳሎ ወንጌል በመስበክ፤ አለቃ አባይነህ ደግሞ ምስክርነቱን በመስጠት ሕዝቡ ንስሐ እንዲገቡና አዳኙ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲቀበሉ ገፋፉ፡

ብዙዎች ሰይጣንን እየካዱ ወደ ክርስቶስ በመምጣታቸው ይህ በእርግጥም የመከር ጊዜ ነበር፡፡ አባይነህ አዲስ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን መሥሪያ የሚሆን መሬት፣ ለጣሪያ መሸፈኛ ቆርቆሮ እና ምስማር ሰጠ፡፡ ይህ በአካባቢው በቆርቆሮ የተሠራ የመጀመሪያው ቤት ነበር፡፡ ከሳምንት በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ላይ ሳለ፣ ያንን ትንሽ ሰውዬ አቅፎ ተሰናበተው፡፡ በሀገሩ ባህል መሠረት፣ አባይነህ መመለስ አለብህ ብሎ እስኪያስገድደው ድረስ፣ አክብሮቱን ለማሳየት፣ ለማ ከአባይነህ ጋር ረጅም መንገድ አብሮት ተጓዘ፡፡

የአለቃ አባይነህ አብዛኞቹ ቤተሰቦች ወደ ክርስቶስ ተመልሰዋል፣ እንዲሁም የአዳኙ ታማኝ ተከታዮች ሆነዋል። ዛሬ ብዙዎቹ የእርሱ ልጆችና የልጅ ልጆቹ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጋቢዎች፣ በወጣቶች ቡድን ውስጥ እና በጎብረ ዝማሬ ውስጥ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌነትና አስተማሪነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

ለማ በቡልቂ እስር ቤት ውስጥ እያለና ቤተሰቡ መኖሪያ ቤታቸውን ባጡ ጊዜ ስላደረግንለት ትንሽዬ እገዛ ሁልጊዜ እያነሣ ያመሰግነናል። ወደ ዛላ ለተለያዩ ስብሰባዎች እንድንመጣ ይጋብዘናል። እንዲሁም ለመጓጓዣ ላንድሮቨር መኪና በገዛንበት ወቅትም፣ ለማ የመንደሩን ሰዎች በማስተባበር የመኪና መንገድ አበጅቶልናል። በሌላ ጊዜ ደግሞ በሽለቆ ውስጥ እየተጓዝን ለሦስት ቀናት ያህል በጥቁር አፈር ተይዘን በቆየንበት ጊዜ፣ ለማ መኪናዋን ለማንቀሳቀስ የሚችሉ ወደ ሃያ የሚጠጉ ሰዎችን በማስተባበር፣ በረጅም እንጨት በመታገዝ አንዷን ጎማ በአንድ ጊዜ በማንሣት ወደ ደረቅ ምድር መንዳት እንድንችል አድርገውናል።

ከዓመታት በኋላም፣ በወላይታ የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ወንጌላውያንን እንደገና ጠሯቸው፤ ለማ በተወለደበት አካባቢ በሚገኝ አንድ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጋቢ ሆነ። ያም ቤተ ክርስቲያን በዚህ ወንጌላዊ አመራር ሥር ሆኖ በፍጥነት አደገ።

ይህ ነው እንግዲህ የነገሩ ርዝመትና እጥረት የተባለው።

‹‹ለእኛ ሳይደለም፣ ሳቤቱ፣ ለእኛ ሳይደለም፣ ነገር ግን ለስምህ
ስለ ምሕረትህ ስለ እውነትህም ምስጋናን ስጥ።››

መዝሙረ ዳዊት ፻15፡1

፲፰

ሻምፊ

በጨለማ ውስጥ ያለ ብርሃን

የብርሃን ምንነት በጣም የሚገባው በጥልቅ ጨለማ ውስጥ የነበረ ሰው ነው፡፡ የሳዎል አባት የሆኑት ጠንቋዩ ሰልጌዶ ፈጽመው ለሰይጣን የተሰጡ ሰው ነበሩ፡፡ መላ ቤተሰባቸውና በአካባቢው ያሉ ሰዎች ሁሉ የእርሳቸውን ኃይል ይፈሩ ነበር፡፡ ረቡዕ፣ ዓርብ እና እሑድ ቀናት ሁልጊዜ በአድባር፣ በተለየ ዛፍ ሥር አምልኮ በማካሄድ ለመናፍስት ስጦታዎችን በዛፍ ሥር ትተው ይሄዱ ነበር፡፡ ከቤተሰባቸውም ጋር በመሆን ምግብ በቅጠል በመጠቅለል ለጌታቸው እንዲህ ይሉት ነበር፡- ‹‹ና፣ ወደ እኔ ና እና ይህንን ብላ፡፡›› ቡና በተፈላ ቁጥር የመጀመሪያው ስኒ መሬት ላይ ለዲያብሎስ መሥዋዕት ሆኖ ከፈሰሰ በኋላ ይቀርብ ነበር፡፡

ሳዎል አባቱ በሰይጣን ቤት ውስጥ አሥራ ሰባት ነጫጭ ድንጋዮችን ወደ መሬት በመወርወር ስጦታ ላመጡላቸው ሰዎች የወደፊቱን ነገር ሲጠነቀሉ ተመልክቷል፡፡ እያንዳንዱ ድንጋይም በላዩ ላይ የሞቱትን አያቶቻቸውን ስም ይዘዋል፡፡ የዘሩንም ግንድ ያንን ቁጥር ያህል ወደ ኋላ መቁጠር ይችላል! ሁልጊዜ የወደ ፊት ዕጣ ፈንታቸው ምን እንደሚሆን ማወቅ የሚፈልጉ ሰዎች አሉ፡፡ ሌቦች እንኳ ሩቅ ወዳለ መንደር ሄደው ከመስረቃቸው በፊት ዕድል ፈንታቸው ምን ሊሆን እንደሚችል መጥተው ይጠይቃሉ፡፡ ሳዎል እንዲህ ሲል ነግሮኝ ነበር፡- ‹‹አባቴ ለዚህ አገልግሎቱ በጣም ብዙ ይከፈለው ነበር፣ ነገር ግን ሀብታም ሆኖ አያውቅም፣ ምክንያቱም ሰይጣን ብዙ ነገር እንዲደረግለት ስለሚጠይቅ ነው፡፡››

ፍርሃት የጠንቋዩን፣ የእርሱን ቤተሰብና ሁሉንም ሰዎች ተቆጣጥሮአቸዋል፡፡ ወደ ሌላ ቦታ ጉዞ ለማድረግ አስበው ከተነሡ በኋላ የቁራ ጩኸት ከሰሙ በዚያ

ቀን ያሰቡትን ጉዞ ይሰርዙታል። ያልተለመደ የዳመና ክምችት፣ የቀስተ ዳመና መታየት ወይም የአድባር ዛፍ ቅጠሎችን የሚበታትን ድንገተኛ ንፋስ እነዚህ ሁሉ እየቀረበ ስላለው ጥፋት ወይም ሞት የሚናገሩ፣ ፍርሃትን የሚፈጥሩ የዲያብሎስ ‹‹ክፉ ዐይን›› ናቸው ተብለው ይታሰባሉ። ጠንቋዩ በመኖሪያ ቤቱ አካባቢ አንድ እንግዳ ሰው ከተመለከተ በፍጥነት ወደ መኖሪያ ቤቱ ይሄድና በኋላ በር በኩል ሰይጣን ቤት ይገባል። እንደ ሌሎች ሰዎች ቤት ሳይሆን፣ የሰይጣን ቤት ሁለት በሮች አሉት፣ ጠንቋዩ ግን መግባትና መውጣት የሚችለው በኋላ በር ብቻ ነው።

ሰዎች የበሽታ ወይም የሞት ምክንያት እንደ ሆኑ ከመቁጠሩ በፊት፣ ሰዎች በፍርሃት ስጦታ ይዘው በመምጣት ለእርሱ ብቻ በተሰጠው ስም ይጠሩታል፤ እነርሱም እያመለኩ ሳለ ጠንቋዩ እንዲህ ይላል፣ ‹‹ልታድነንና ልትጐዳን እንዲሁም ልትገድለን የምትችል አምላክ ነህ። አንተ ትልቁ አምላክና የምድራችንም ኃይል ነህ።›› በምሽትም ሰዎች ወደዚያ በመምጣት ለሰይጣን በሚደረገው ጭፈራ ውስጥ ይቀላቀላሉ። ሁልጊዜም ክፉ መናፍስትንና በዛፎች ውስጥ፣ በድንጋዮችም አካባቢ፣ በመንደሩ ውስጥ እንደሚኖሩ የሚያምኑቱ የአያቶቻቸውን መንፈስ ያመልካሉ።

ሳዎል እንዲህ ይላል፣ ‹‹በእኛ ቤት ውስጥ በጣም ብዙ መርዛማ እባቦች ይኖሩ ነበር። አባቴ በጦሩ ጫፍ ላይ ደም በማስቀመጥና በቅል ወተትና ብዙ እንቁላል በማስቀመጥ እነዚህን እባቦች ይመግባቸው ነበር። ብዙ ዓይነት መሐላዎች ነበሩብን፤ የፍየል ሥጋ አንበላም ወይም የፍየልን መልካምነት አናወራም፤ ለፍየሎች ልዩ ስም አለን። ወደ መኖሪያ ቤታችን አካባቢ እንዲመጡም አንፈቅድም። ዱባም መብላት ፈጽሞ የተከለከለ ነው። ከከብቶቻችን የሚገኘው ወተት ለሰይጣንና ለመናፍስት የሚሰጥና በቤተሰቡ አባላት ብቻ የሚጠጣ ይሆናል። ለሰይጣን ልዩ የሆነ ማጠራቀሚያ ነበረን። ጀበናችን ሁለት መቅጃ አፍ ያለው ሲሆን፣ አንድ ለሰይጣንና አንዱ ደግሞ ለእኛ ነበር። አባቴ በመኖሪያ ጎጆአችን መካከል ላይ ያለውን ምሰሶ በማርና በቅመማ ቅመም ቀብቶ ምሶሶውን ያመልክ ነበር። ሁልጊዜ ማታ ማታ ጠንቋዩ አባቴ ገላውን ይታጠብና ቆሻሻውን ውኃ ጥቂት ከጠጣ በኋላ የቀረውን በቤታችን ውስጥ ይረጨዋል።››

በዚህ ጨለማ ውስጥ እግዚአብሔር ልዩ መልእክተኛ የሆነውን ወንጌላዊ ቻንዶን ላከው፡፡ ቻንዶ ከጦርነቱ ከተረፉ ‹‹ተዘዋዋሪ ሰባኪዎች›› መካከል አንዱ ሲሆን፣ በጠመንጃ ሰደፍ ወገቡን፣ ጭንቅላቱንና አንገቱን በመመታቱ ምክንያት ከአንገቱ ተጣምሞ የሚሄድና መስማት የሚያስቸግረው ሰው ነበር፡፡ በሰውነቱ በእውነት ‹‹የኢየሱስን ምልክት›› ይዞ የሚኖር ሲሆን፣ ግን ለአዳኙ ካለው ፍቅር የተነሣ የሚያስቸግረውን አካሉን እየጐተተ ከቀጣናዎች ወደ ቀጣናዎች ይዘዋወራል፡፡

ቻንዶ ጠባብዋን መንገድ ይዞ ሲመጣ ሳለ የሰይጣን ቤትን፣ የተለየ ዛፍና መሠዊያ ሲመለከት፣ ቆም አለና ወንጌልን መስበክ ጀመረ፡፡ ወዲያውም ብዙ ሕዝብ ሊሰማው ተሰበሰበ፡፡ ወደ ጠንቋዩ እንዲህ ሲል ጮኸ፣ ‹‹ወንድሜ ሆይ፣ እባክህ ስማኝ! በአንተ ላይ ያለው ክፉ መንፈስ አታላይ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ጥንቁላዎች፣ መታያዎችና ማስፈራሪያዎች በእውነተኛው ፈጣሪ አምላክ ፊት በጣም ከንቱዎች ናቸው፡፡ እነዚህን ክፉዎችና ጨለማዎች በመተው ወደ ኢየሱስ ተመለስ፣ እርሱም ያድንሃል፡፡ ከእግዚአብሔር ፍርድ ሊያድንህ የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡›› ለአንድ ሰዓት ያህል ቻንዶ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ቦታዎችን እየገለጠ ስለ ኃጢአት፣ ስለ እግዚአብሔር ቅድስና እና ስለ ክርስቶስ ሞት ደግሞም ስለ ትንሣኤ በማንበብ እያንዳንዱ ሰው ንስሐ እንዲገባና እንዲያምን አበረታታ፡፡

ሳዎል እንዲህ አለ፣ ‹‹አታላዩም ጠንቋይ፣ አባቴ ለወንጌላዊው እንዲህ ሲል ነገረው፣ በሦስት ቀን ውስጥ ተመልሰህ ና፣ እኔም አምናለሁ አለው፡፡ ነገር ግን በዚያ ቀን ቻንዶ ተመልሶ መምጣቱን ሲሰማ፣ ሮጦ በቡና ዛፎች ሥር ተደበቀ፡፡ ወንጌላዊው ወደ ቤቱ ሄደ፣ ነገር ግን አላገኘውም፡፡ ቻንዶም ጠንቋዩን ለማግኘት በተለያዩ ጊዜያት በድንገት ይመጣ ነበር፡፡ በኋላ ላይ ቻንዶ ተሳክቶለት አባቴንና እኔን እንዲሁም መላ ቤተሰባችንን ሰይጣንን እንድንክድና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችን እና ጌታችን እንድንቀበል አድርጎናል፡፡ የሰይጣንን ሥራ ሁሉ በመተው ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቃል በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምነናል፡፡ ከጨለማ፣ ከሰይጣን ባርነት በኢየሱስ ነፃ ወጥተናል፡፡››

የምን ዳመራ ነው ያቃጠሉት! የሰይጣን ቤትን ሲያቃጥሉ ቻንዶ ይመለከት

ነበር፡፡ የገዛ መኖሪያ ቤታቸውንና በውስጡ ያሉት እባቦችን እንዲሁም የዲያብሎስ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ እንዳሉ አቃጠሉት፡፡ ዛፉንም ቈርጠው አቃጠሉት፣ እንዲሁም የድንጋይ መሠዊያውንም ሰባበሩት፡፡ መላ ቤተሰቡ ጸጉራቸውን እና ጥፍሮቻቸውን ቈረጡ፣ ገላቸውንም ታጠቡ፡፡ ሳዎል አባቱ መጠለያ ከቀርከሃ፣ ከቅጠል እና ከሣር ሲሠራ አገዘው፡፡ ብዙ ክርስቲያኖች ከቻንዶ ጋር ሐሤት ለማድረግ ከሩቅ ስፍራ ተሰበሰቡ፡፡ ሁሉም እንጨት፣ ቀርከሃ ወይም ሣር ተሸክመው በመምጣት የአዲሱ ቤት ግንባታን ያግዙ ነበር፡፡

ሳዎል በመደነቅ እንዲህ አለ፣ ‹‹በዚያ ቀን ሁሉን ነገር ተለወጠ! እኛ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ሆንን፡፡ ክርስቶስ አሮጌውንና ንጹሕ ያልሆነው ተፈጥሮዋችን ልዩ ይሆን ዘንድ እንኖርበት የነበረውን መንገድ ቀይሮታል፡፡ የጨለማው አምላክ ያስተምረን የነበረው ክፋትና ስሕተትን፣ ንጹሕ ያልሆነውንና ስርቆትን ነበር፡፡ አሁን ያሰረን ሰንሰለት ተበጥሷል፤ እኛ አሁን በክርስቶስ ነፃ ነን! እነሆ፣ ገና ብዙ መማር ያለብን ነገር አለ! በእውነት፣ እኛ በእውነቱ ዳግም የተወለድን ሰዎች ነን! ቻንዶ አዲሱን መንገድ ለማስተማር ብዙ ጊዜ ከእኛ ጋር አሳልፏል፡፡››

ወንጌላዊ ቻንዶ ከአዳዲስ አማኞች ጋር ብዙ ጊዜ ለመጸለይና የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ይመጣል፡፡ ወዲያውም ሌሎች ሰዎች አመኑና ቡድኑን ተቀላቀሉት፡፡ በአሥራዎቹ መጀመሪያ ዕድሜ ክልል ውስጥ የነበረው ሳዎል፣ የእግዚአብሔር ሰው ሲያስተምር በጥንቃቄ ያደምጥና ብዙ ነገር ከእርሱ ይማር ነበር፡፡ ሳዎል ይበልጥ ከቻንዶ ለመማር ከእርሱ ጋር ከቦታ ቦታ ይዘዋወር ነበር- ራቡም በወንጌል ፈጽሞ የሚረካ አይመስልም፡፡ ቻንዶ፣ ሳዎል ማንበብ እንዲችል በመርዳት የመጀመሪያውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል - የዮሐንስ ወንጌልን መግዛት እንዲችል እገዛ አደረገለት፡፡ ቻንዶ ይህንን ደቀ መዝሙሩ የሆነውን ወጣት ልጅ፣ ይወድደው ነበር፡፡ ሳዎልም ይህንን ያውቅ ነበር፡፡ ከወንጌላዊው ያገኘው ምክር ሁሉ ሕይወቱን ለመለወጥ እጅግ በጣም ረድቶታል፡፡ ሁለቱም አንድ ላይ ሆነው አዲስ ቤተ ክርስቲያንን ጀምረዋል፤ እንዲሁም ለሦስት ዓመታት ያክል ሳዎል ለወደ ፊት በአገልግሎቱ የሚያዘጋቸውን ልምድ ወስዷል፡፡

ወንጌላዊ ጣሰው (ኢትዮጵያውያን የወንጌል አርበኞች የተሰኘውን መጽሐፍ ገጽ

148 ይመልከቱ) ከሲዳሞ አካባቢ በመመለስ፣ ተጨማሪ ወንጌላውያን ወደዚያ መጥተው እንዲያግዙት ጠየቀ፡፡ መንፈስ ቅዱስም የሳዎልን ልብ እንዲሄድ አነሣሣው፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ባርካ እንድትልከው ጠየቀ፡፡ ለመሄድ በመመረጡ ክርስቲያኖች ከእርሱ ጋር ደስ አላቸው፣ ስለ እርሱም ለመጸለይ ቃል ገቡ፡፡ ሳዎል በሶዶ ለነበሩ አጠቃላይ የወላይታ ቤተ ክርስቲያናት መሪዎች እግዚአብሔር ወደ ሲዳሞ ሄዶ ወንጌል እንዲሰብክ እንደ ጠራው ሲነግራቸው፣ በሲዳማና ወላይታ መካከል ከፍተኛ ችግር ስላለ እንዲጸልይበት ነገሩት፡፡ በወላይታ ውስጥ ከፍተኛ ድርቅ በመከሰቱ ምክንያት፣ በሩቅ ያሉ ጎሳዎችን በማገልገል ላይ ያሉትን ሰዎች ለመደገፍ የሚውለው አሥራት ቀነሰ፡፡ ሳዎልን ጨምሮ፣ በጣም ብዙ ወንዶች፣ ለመሄድ እየጠየቁ ነበር፣ ነገር ግን ለዕለት ጉርሳቸው የሚሆን በጌታ ላይ መታመን ነበረባቸው፡፡ ሳዎል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲጸልዩለት ጠየቃቸውና ስለሚያስፈልገው ነገር በእግዚአብሔር ላይ እንደሚታመን ነገራቸው፡፡ መሪዎቹም ለሳዎል ባርኮታቸውን ሰጥተው ለጌታ ሥራ ለዩት፡፡

ሳዎል ወደ ቤቱም ሲመለስ፣ ሰይጣንን ለብዙ ጊዜ ሲያገለግል የኖረው ሽማግሌው አባቱ፣ አሁን ግን እያደገች ባለችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ያደርግ ስለ ነበረ እጅግ በጣም ደስ አለው፡፡ ሳዎል የክርስቶስ መልእክተኛ እንዲሆን ሲጸልይ እንደ ነበረ ነገረው፡፡ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የነበሩ ክርስቲያኖችም ከእርሱ ጋር ጌታን አመሰገኑ፣ የጉዞ ወጭውን መሸፈን የሚችል በቂ ገንዘብ አዋጡለትና በደስታ ሸኙት፡፡

ሳዎል ከጣሰው ጋር በመሆን ማገልገል ጀመረ፡፡ ስለዚህም ሳዎል ከወላይታ ወደ ሲዳሞ ሄዶ ካገለገሉት መካከል አሥረኛው ሰው ለመሆን በቃ፡፡ በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት ምንም እገዛ የሌለው ወንጌላዊ መሆን አስቸጋሪ ስለ ነበር፣ ወንጌላዊው ምግብ ለማግኘት ሲል የቀን ሥራ መሥራት ነበረበት፡፡ ሳዎል እንዲህ ብሎ ነበር፣ ‹‹እኛ ወንጌላውያን ስለ ቀን አበላችን ወይም ስለ ቦታው አመቺነት አስበን አናውቅም፡፡ የሄድነው መንፈስ ቅዱስ እንሄድና ወንጌልን እንሰብክ ዘንድ ስለ ነገረን ነበር፡፡ ከዚያም ጌታ በወላይታ ያሉ ክርስቲያኖችን አሥራታቸውን መክፈልና ወንጌላውያንን መደገፍ እንዳለባቸው አስተማራቸው፡፡፡››

ለትንሽ ጊዜ ሳዎልና ጣሰው ወንጌልን እየሰበኩ በየመንደሩ አብረው ይጓዙ

ነበር፡፡ ብዙ ሰዎችም ለእግዚአብሔር የጸጋ መልእክት ምላሻቸውን ይሰጡ ነበር፡፡ ሳዎልና ጣሰው ሁለቱም ጠንቋይ አባት ስለ ነበራቸው፣ የሲዳሞ ሰዎች ምን ያህል በፍርሃትና በጨለማው ውስጥ እንዳሉ ያውቃሉ፡፡ ወደ እያንዳንዱም ጠንቋይ ቤት በመሄድ በኢየሱስ ስም ከፉ መናፍስት ሲወጡና ሰዎች ሲድኑ ተመልክተዋል፡፡ በጣም ብዙ ሰዎች ሰይጣንን በመካድ ክርስቶስ እንደ ግል አዳኛቸው በመቀበላቸው ምክንያት፣ በጣም ብዙ አዳዲስ ቤተ ክርስቲያናት ተመሥርተዋል፡፡ ሳዎል በአምልኮ ለመምራት የሚችሉ መጋቢዎች እና መሪዎች እንዲሆኑ ብዙ አዳዲስ አማኞችን ማንበብ እንዲችሉ አስተምሯል፡፡ ሳዎል አንዳንድ ጊዜ ከሌሎች ሰዎች ጋር፣ ብዙ ጊዜ ግን ብቻውን በመሆን የኢየሱስን ታሪክ ደጋግሞ ይናገር ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ፣ ሳዎል ስብከት በመስበኩ ምክንያት ተይዟል፣ ተደብድቧል እንዲሁም ታስሯል፣ ነገር ግን በእስር ቤት ውስጥ እንኳ ሆኖ አብረውት ላሉ ሰዎች ወዲያው ወንጌልን ያካፍላቸው ነበር፡፡

በወላይታ የሚገኙ መሪዎች፣ በዚያ በሚገኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ትምህርቱን ይከታተል ዘንድ ጠሩት፡፡ በእነዚያ ሦስት ዓመታት ወቅት፣ በሶሪ ቀጣና ውስጥ ባለችው ቤተ ክርስቲያን በሳምንት ሦስት ጊዜ ያህል ይሰበክ ነበር፡፡ በጣም ብዙ ተቃዋሚዎች ተቋቀሙመው ነበር፡፡ አንድ ቀን በቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ እየሰበከ ሳለ፣ ሳዎል በሐሰት ተከስሶ ተያዘ፣ ተደብድቦም ታሰረ፡፡ ነገር ግን በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 4 ላይ እንዳሉት ሐዋርያት ጴጥሮስና ዮሐንስ፣ ሳዎል፣ ከታሰረበት እስር ቤት የበረታና ጥሩ ሥነ ምግባር ያለው በመሆኑ ነጻ ወጥቷል፡፡ ከዚያም ወደ ተመሳሳይ ስፍራ ለጠንቋዮች ወንጌልን ለመንገር ተመልሶ ሄደ-ለሰባቱም በክርስቶስ እንዲያምኑ ነገራቸው፡፡ የወንጌል ዋና ተቃዋሚ የነበረውም ሰውዬ የክርስቶስ አገልጋይ ሆነ፡፡

ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከተመረቀ በኋላ፣ ሳዎል በእርሱ ቀጣና፣ ቦሎሶ ውስጥ ሌሎች መሪዎችን እንዲያስተምር ተጠየቀ፡፡ በዚያም ለአራት ዓመታት ቆየ፡፡ በቆይታው ብዙ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የመራበትን የአንዲት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ በመሆን አገለገለ፡፡ በዚያ ጊዜ እኔ እና ቪዳ በቦሎሶ የሚሰዮናዊ ሥራን የጀመርንበት ጊዜ ነበርና ከሳዎል ጋር እንደገና ተገናኘን፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለመስበክ ወደ ተለያዩ ስፍራዎች ጉዞ በማድረግና አብረን ጎብረት በማድረግ፣ እኔና ሳዎል ይበልጥ ለመተዋወቅ በቃን፡፡ እርሱ ወዴት መሄድ እንዳለበት የእግዚአብሔርን ፍቃድ በሚጠይቅበት ወቅት ብዙ ጊዜ አብረን እንጸልያለን፡፡ ወንጌልን ለመንገር ልቡ ያለው በምዕራብ በኩል፣

ከተራራዎቹ ባሻገር ወዳሉት ወንጌል ወዳልደረሳቸው ጎሳዎች ጋ ለመሄድ ነበር።።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሳዎልን ወደ ከፋ ክፍለ አገር ሲልኩት፣ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት እንዳደረጉት በልቡ ውስጥ ባለው ሰላም አማካኝነት አውቋል።። በቀኑጥራቸው እየበዙ የመጡትን ቤተሰቡን ይዞ ለወንጌል ዝግ ወደ ሆነው አካባቢ አቀና - ይህ አካባቢ ወንጌል በወላይታ ውስጥ እየሰፋ ሲሄድ ብዙ ጠንቋዮች የሸሹበት አካባቢ ነበር።። ሳዎል ከወንጌላዊ ጣሰው ጋር በጋራ በመሆን ለዘጠኝ ዓመታት በከፋ ውስጥ ቆይቷል።። በአንድነትም ወንጌልን ሲሰብኩ በጣም ብዙ ስደት ይደርስባቸው ነበር፤ ብዙ ጊዜም ይያዙ፣ ይደበደቡና ይታሰሩ ነበር፣ ነገር ግን በእስር ቤት ውስጥ ላገኟቸው ሰዎች ሁሉ ወንጌልን በመስበክ ወደ ክርስቶስ ይመሯቸዋል እንዲሁም ማንበብን ያስተማሯቸው ነበር።። ከእስራት ሲፈቱም፣ እንደገና ወንጌልን ወደ መስበክ ይመለሳሉ!

ከዚያም እንደገና ይያዛሉ፣ ይሰደባሉ፣ እንዲፈሩ፣ እንዲራቡ ይደረጋል፣ እንዲሁም ይገረፋሉ፣ ነገር ግን ሳዎል እና ጣሰው በመታሠራቸው ምክንያት፣ በእሥር ቤት ውስጥ ላሉት ሰዎች የሕይወትንና የደኅንነትን መልእክት ለመናገር ልዩ ዕድል እንደ ሆነ አድርገው ይቁጥሩታል።። ሳዎል ከእስር ቤት ሲለቀቅም እንደገና ወደ ጠንቋዮቹ በመሄድ፣ ኢየሱስ በሰይጣን ላይ ኃይል እንዳለውና በአዳኙ ኢየሱስ ስላለው ተስፋ እና ሰላም የግል ምስክርነቱን ይነግራቸዋል።። ሳዎል እንዲህ ይላል፣ ‹‹ሁል ጊዜ እንድሄድ የሚያደርገኝ ነገር እንዲህ የሚለው የኢየሱስ ክርስቶስ የተስፋ ቃል ነው፡- ‹በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ›› (ዮሐንስ 16፡33)።።

በአካባቢው የሚመረተው የመጠጥ አልኮል ለሁሉም ሰው አስቸጋሪ ነበር፤ ሕፃናት እንኳ ሳይቀሩ ይህንን አልኮል በመጠጣት ይሰከሩ ነበር።። በኋላ ግን፣ ብርሃኑ ጨለማውን ሰንጥቆ ማለፍ በመጀመሩ፣ ቀስ በቀስ ከጠንቋዮች ኃይል መሰበር ጋር የአልኮልም ኃይል እየተሰበረ ሄደ።። በጣም ብዙ ሰዎች አምነው ተጠመቁ፤ አዲስ ቤተ ክርስቲያንም በዚያ ተመሠረተች።። ነገር ግን ይህ ተቃውሞ እንዲቀንስ አላደረገም፣ ይልቁንም አባባሰው እንጂ።። የኦርቶዶክስ ቀሳውስት፣ ወንጌላውያን አማኞች፣ ወይም እነርሱ ‹‹የኢየሱስ ሰዎች›› ብለው የሚጠሯቸው ሰዎች፣ ከእንግዲህ ለእነርሱ ግብር እንደማይከፍሉ ተረዱ።። ምግባረ ብልሹ የመንግሥት ባለ ሥልጣናትም፣ አማኞች ከእንግዲህ ጉቦ

ስለማይሰጧቸው ተናደዱ፤ ጠንቋዮችም ከአማኞች ከእንግዲህ ምንም ዓይነት ገቢ ማግኘት ስለማይችሉ ተበሳጩ።

ꕥ

ከዕለታት አንድ ቀን፣ ሳዎል በመንገድ ላይ እየተጓዘ ሳለ፣ ታቦት ሲጓዝ ተመለከተና ከመንገድ ዘወር ብሎ የኦርቶዶክስ ቄሶች እንዲያልፉ አደረገ። ነገር ግን ‹‹ለታቦቱ›› አለመስገዱን የተመለከቱ ቄሶች ሳዎልን ‹‹ሃይማኖታችንን›› ሰድቧል በማለት በሐሰት ከሰሱት። ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ለሦስት ወራት በወህኒ ቤት አቆዩት። አንዳንድ ሰዎችም ወደ እርሱ መጥተው ለዳኛው ጉቦ እንዲሰጥ ጠየቁት። ሳዎል ጎቦ መቀበልም ሆነ መስጠት በመጽሐፍ ቅዱስ የተከለከለ መሆኑን ሲነግራቸው፣ መጽሐፍ ቅዱሱን ቀሙት! ሦስት የሐሰት ምስክሮች በሳዎል ላይ መሰከሩበት፣ የስድስት ሙዶ ብር ቅጣት ወይም የአንድ ዓመት እስራት ተወሰነበት። ሳዎል በእስር ቤት ውስጥ ወንጌልን መስማት ያለባቸው በጣም ብዙ ሰዎች ስላሉ፣ ‹‹ለኢየሱስ መታሰርን›› መረጠ። በእስር ቤት ውስጥም ምንም እንኳ ስድብና የሚሠራ ሥራ ከባድ ቢኖርም፣ ወንጌልን በድፍረት ለመናገር ብርታት እንዲኖረው በየዕለቱ ይጸልይ ነበር።

ከዚያም በሚያስገርም ሁኔታ፣ የእስር ቤቱ ኃላፊ፣ ሳዎል ትምህርት ቤት እንዲከፍትና እስረኞችን ማንበብና መጻፍ እንዲያስተምር ፈቃድ ሰጠው። ከዚህ በተጨማሪ ወንጌል እንዲሰብክ ፈቀደለት። የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮናዊ የሆነው ፖል ባልስኪ ለሳዎል ጥቂት መጻሕፍትን፣ ጥቁር ሰሌዳና ጠመኔ እንዲሁም ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ ሰጠው። በአንድ ዓመት ውስጥም ብዙ እስረኞች ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ተቀበሉት። አንዳንዶቹ ደግሞ በእስር ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ጉድጓድ ቆፍረው ውኃን በመሙላት፣ በመደነቅ በሚመለከቷቸው እስረኞችና የወህኒ ቤት ዘበኞች ፊት ተጠመቁ።

ሳዎል እንዲህ ይላል፣ ‹‹በእያንዳንዱ የእስር ቤት ደጃፍ ላይ ወንጌልን እንድሰብክ እግዚአብሔር በርን ከፍቶልኛል፤ ብዙዎችም በክርስቶስ አምነዋል። አዳዲስ አማኞችም፣ እኔ በምገኝበት እስር ቤት ውስጥ፣ መዝሙር ለመዘመርና ለመጸለይ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ በየምሽቱ ይመጣሉ። የብዙዎቹ እስረኞች ሕይወት በመለወጡ ምክንያት የተፈረደባቸው የብዙ ዓመት እስራት ሊነሣላቸው ችሏል።። በምሽት የምናደረግው ስብሰባችን ለኅብረት በጣም ጠቃሚ ነበር። መላ ወህኒ ቤቱ ወደ ትምህርት ቤት ተለውጦ፣ በእስር ቤት

ውስጥ ከነበሩት ሰዎች መካል አብዛኞቹ ማንበብ ችለው ነበር። መማሪያ መጽሐፋችንም መጽሐፍ ቅዱስ ነበር።››

ሳዎል ንግግሩን እንዲህ ሲል ቀጠለ፣ ‹‹የእስር ቤቱ አለቃ ለምን ለትምህርት ቤት ፈቃድ እንደ ሰጠ አልገባኝም። አንድ ቀን ግን እንዲህ ብሎ አጫወተኝ፣ ‘ከዓመት በፊት አንድ ክርስቲያን በዚህ እስር ቤት ውስጥ ነበር። ይህም ክርስቲያን ራሱን ከሌሎች አግልሎ ለብቻው የሚቀመጥና ለሌሎች የወንጌልን መልእክት የማይናር ነበር። ነገር ግን አንድ ጊዜ፣ የእስር ቤቱ ሌሎች ክፍሎች ሙሉ ሲሆኑ፣ ጥቂት እስረኞች ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ተደረገ። እናም ሁሉንም ወደ ክርስቶስ መራቸው! እነዚያ ሰዎችም መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እየቻሉ ሲመጡ ሕይወታቸው ፈጽሞ ተለወጠ። ስለዚህም ይህ የወህኒ ቤት አለቃ ስለዚህ ነገር፣ እውነቱን ይበልጥ ለማወቅ ፈለገ’።››

በዓመቱ መጨረሻ ላይ፣ ሳዎል በወህኒ ቤት ውስጥ የነበሩትን ተማሪዎቹን ሁሉ ፈተና ይወስዱ ዘንድ ከእስር ቤት ወደ መንግሥት ትምህርት ቤት በወህኒ ቤት ዘበኞች እየተጠበቁ ወደ ቦንጋ ይዟቸው ሄደ። ከፈተናውም በኋላ ወደ እስር ቤት በሰልፍ ተመለሱ። ሁሉም እስረኞች ፈተናውን አለፉ። በኋላ ላይም የአውራጃው አስተዳደር ለተማሪዎቹ ሁሉ የምስክር ወረቀትና ለሳዎል ደግሞ የምስጋና ደብዳቤ ሰጣቸው። ሳዎል እንደገና በፊልጵስዩስ 1፡12 ላይ ያለውን የሐዋርያው ጳውሎስን ቃል በሕይወቱ አረጋገጠ፣ *‹‹ነገር ግን፣ ወንድሞች ሆይ፣ ይህ የደረሰብኝ በእውነት ወንጌልን ለማስፋት እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ።››*

ሳዎል በእስር ቤት ቆይታው፣ ምግብ ይዘው በመምጣት ከእርሱ ጋር በሚጸልዩ ብዙ አማኞች የክርስቲያኖችን ፍቅር፣ ለጋሽነት እና ጎብረትን ቀምሷል። የወህኒ ቤቱ ዘበኞችና እስረኞች በክርስቲያኖች መካከል ባለው ፍቅር በጣም ይገረሙ ነበር። አንዳንዶች አንድ ጊዜም እንኳ የሚጎበኛቸው ሰው አግኝተው አያውቁምና። አንድ ሰው ከአዲስ አበባ አምስት ሙቶ ኪሎ ሜትር ተጉዞ ሊጐበኘው መጥቶ፣ የሳዎልን የተቀደደ ልብስ ሲመለከት ወዲያው ልብሱን አውልቆ ለሳዎል ሰጠው፤ በዚህም እስረኞቹ በጣም ተደነቁ! ይህ ሰውም የሳዎልን የተቀደደ ልብስ ለብሶ ወጣ።

እርሱ ለአንድ ዓመት በእስር ቤት በቆየበት ጊዜ፣ የሳዎል ሚስትና አራቱ ልጆቻቸው በኤስ ላይ ኤም ሚስዮን ጣቢያ ውስጥ ከፖል እና ላይላ ባልስኪ

ብዙ እገዛ እያገኙ ቆይተዋል። ሳዎል ከባልስኪ ጋር በመኪና ወይም በበቅሎ ወይም በእግር በጭቃና በዝናብ ውስጥ እየተጓዘ ወንጌልን ይሰብክ ነበር። አንድ ጊዜ፣ ሳዎል ሩቅ ወደ ሆነ ከተማ በአውቶቡስ ተሳፍሮ በመጓዝ ላይ እያለ፣ የጎማ እርዳታ ማግኘት አስቸጋሪ በሆነበት ቦታ ላይ ደርሶ ፈነዳ። ሁለተኛው አውቶቡስ ደግሞ ባሉት ወንበሮች ልክ ተሳፋሪዎችን ይዞ ቢመጣም፣ ሳዎልና ሌሎች ተሳፋሪዎችን ደርቦ ጭኗቸው ሲሄድ አንሽራታች መሬት ገጥሞት ጫካው ውስጥ ተገለበጠ፤ አንዳንድ ሰዎችም ተጐዱ! ሳዎል ግን፣ በሌላ አውቶቡስ ምንም ሳይሆን ተመለሰ። ‹‹እግዚአብሔር ጠበቀን›› ሲልም ተናገረ።

ሳዎል በጣም ኃይለኛ የሆነ የጠንቋይ ቍጥጥር ወዳለው ሌላ አካባቢ ሄዶ፣ ጨለማ ከሆነው ከዲያብሎስ ኃይላት ጋር የፊት ለፊት ውጊያ አድርጓል። ሳዎልና ሌሎች ወንጌላውያን ሌሊቱን በሙሉ ሲጸልዩ ካደሩ በኋላ፣ በቀን ከመናፍስቱ ጋር ውጊያ ገጠሙ። ከዚህም በተጨማሪ፣ ጊዜው ፖለቲካዊ መረጋጋት ያልነበረበትና ከቦታ ቦታ መጓዝም አደገኛ የሆነበት ጊዜ ነበር። በዚያው አካባቢ ወንጌላዊ ተሰማ ከጠንቋይ በተላከ ሰውዬ የተገደለ ሲሆን፣ ሳዎል ራሱ እንኳ ከዚህ ነገር መትረፉ ያስገርመዋል።

የኮምዩኒስት መንግሥት የኢትዮጵያን አስተዳደር ከመቈጣጠሩ የተነሣ፣ አብያተ ክርስቲያናት ተዘግተው፣ በክርስቲያኖች ላይ ስደት በመነሣቱ ምክንያት፣ እንደ ሳዎል ያሉ ወንጌላውያን ሥራ ተደናቀፈ። ሁሉም ወንጌላውያን ወደ ወላይታ ተጠሩ፣ ነገር ግን ሳዎል ያለምንም እርዳታ ወደ ከፋ ተመልሶ አምስት አብያተ ክርስቲያናትና ከሦስት መቶ በላይ የሆኑ ሰዎች በክርስቶስ ሲያምኑ ለመመልከት ችሏል። በኋላ ላይ ግን በመንግሥት ግፊት ወደ ወላይታ ተመልሷል።

በቦሎሶም፣ ሳዎል ማታ ላይ ድብቅ ስብሰባዎችን፣ የቡድን ጸሎትና የቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ያዘጋጅ ነበር። ነገር ግን የኮምዩኒስት መንግሥት ከሥልጣን በወረደ ጊዜ፣ ሳዎል እንደገና አካባቢውን ለቅቆ ወንጌል ያልደረሳቸው ሙስሊሞች ወደሚኖሩበት አርሲ አካባቢ ሄደ። ለአገልግሎት ወደ ኢትዮጵያ ስሄድ፣ እኔ እና ሳዎል ጸሎትና ጉብረትን ለማድረግ ብዙ ጊዜ እንገናኛለን። ጌታ ለጠራው ነገር ታማኝ መሆን እንዲችል እንጸልይለት ዘንድ ጠይቆኛል። ሳውል በመከራ ውስጥ ያለው ጽናትና ለጌታ ሥራ ‹‹አለመተው›› ያለው ቈራጥነት ሁልጊዜ ራሴን እንድመለከት ያደርግኛል።

በ2008 በኮንታ ውስጥ በተደረገ ስብሰባ ላይ የእግዚአብሔርን ቃል አካፍል ነበር። በዚያ ስፍራም ሳዎል ነበር። ስላሳለፈነው ጊዜ ተጨዋወትን፣ በዓመታት ውስጥ እግዚአብሔር ለእኛ ታማኝ ሆኖ ስላገኘነው እግዚአብሔር አመሰገንን። ሳዎል፣ መንግሥት ከሌሎች ቦታዎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ሰዎች በማምጣት፣ ወዳሰፈረበት ወደ ኮናታ በመሄድ፣ በሺህዎች በሚቆጠሩ ሰዎች መካከል ትልቅ ቤተ ክርስቲያንን ተከለ።

ከተራራዎቹ በሻገር ወንጌል ላልደረሳቸውና በጨለማ ውስጥ ሆነው ብርሃንን ለሚጠባበቁ ጎሳዎች በአንድነት ሆነን ጸልየናል። አንድ ቀን ሳዎል እንዲህ አለኝ፣ ‹‹የጌታ ኢየሱስ ትእዛዝ ወንጌልን ስበኩ ነው። የእርሱን ትእዛዝ መታዘዝና ሥራችንን መፈጸም አለብን። ይህንን ሳናደርግ ከቀረን ግን፣ በመጨረሻው ቀን በፊቱ ስንቆም ምን ምላሽ እንሰጠዋለን?››

ስንሰነባበትም፣ አሁንም ሳዎል ወደ ስንሰለታማ ተራሮች እየተመለከተ ነበር። ወንጌላዊው አሁንም ልቡ በሰይጣን እስራት ውስጥ ባሉት በጻራ እና ከዚያ ባሻገር ባሉት ሕዝቦች ላይ ነበር። ደካማ የሆኑት እግሮቹ ጠንክረው ወደዚያ ከተጓዙት ሦስት ወንጌላውያን ጋር አብሮ ዓቀበት ቀጎልቀጎለቱን ከእነርሱ ጋር መጓዝ በወደደም ነበር። ‹‹የወንጌል ዐርበኞቹ›› በአንድነት ሳዎል ለመሄድ ከእንግዲህ ጥንካሬ እንደሌለው ደምድመው በእያንዳንዱ እርምጃቸው ውስጥ ግን ሳዎል በጸሎት ከእነርሱ ጋር እንዳለ አረጋግጠዋል።

‹‹ይህ ሰለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ ሰለ እርሱ መከራ ደግም ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ ኣይደለምና፤››

ፊልጵስዩስ 1፡29

፲፱

ማሕሌሙ

ለኢየሱስ መዘመር

ዓለሙ ለራሱ መዝሙር በቀስታ እየዘመረ፣ ድንጋይ የተነጠፈበትን መንገድ እየተሻገረ ሳለ፣ ከጀርባው በኩል የመኪና ጡሩንባም እስከ ሰማበት ጊዜ ድረስ መኪና መኖሩንም አላስተዋለም ነበር። በክርስቲያኖች የአምልኮ ስፍራ፣ በሠርግና በቀብር ስፍራዎች ሲዘምር የሚጠቀምባትን ውድ አኮርዲዮኑን ተሸክሟታል። መኪናው የአቧራ ደመና ሠርቶ አጠገቡ በፍጥነት ሲቆም፣ በጫካው ውስጥ ገብቶ ለመደበቅ እንኳ ጊዜ አላገኘም ነበር።

እርሱ ይኖርበት በነበረው ስፍራ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ኮምዩኒስት ካድሬ አዘግቶ፣ መጋቢዋንና የቤተ ክርስቲያኒቱን ሽማግሌዎች አሠራቸው፤ መጽሐፍ ቅዱስን፣ የሙዚቃ መሣሪያዎችን እና ሁሉንም መቀመጫዎች አቃጠላቸው። አጋጣሚ ሆኖ፣ ዓለሙ በመኖሪያ ቤቱ ትንሽ አኮርዲዮን ነበረችው፤ በጥንቃቄም ይጠበቃት ነበር። በምንም ምክንያት እንደማይቆም ተስፋ በማድረግ በፍጥነት እየተጓዘ ነበረ። ነገር ግን ሦስት ሰዎች በመኪናው ውስጥ ሆነው እንዲመለስ ጮኹበት። ጠመንጃቸው ለሆነ ሥራ እየሄዱ መሆኑን ያሳያል።

ካድሬዎቹ ዓለሙ በያዘው በአኮርዲዮን ሻንጣ ላይ አትኩረው ከተመለከቱ በኋላ፣ ዓለሙ ከእነርሱ ጋር ወደ መኪናው ገብቶ እንዲሄድ አስገደዱት። ወደሚቀጥለው ከተማ በመሄድ በዚያ መዝናናት ፈልገው ነበር። እነዚህ ሰዎች መጠጥ መጠጣታቸው በግልጽ የሚታይ ነበር፣ ስለዚህም ዓለሙ ወደ መኪናው ለመግባት ፈራ። በዊስኪ ከታጨቀች መኪና ውስጥ ለእርሱ ያለው ቦታ በጣም ትንሽ ነበር። በኋላ እንደ ምንም ብሎ መቀመጫ ላይ ተቀመጠ።

ዓለሙ ሰዎቹን ፈርቷል፣ ስለዚህም በቀስታ አምላኩ ይጠብቀው ዘንድ ጸለየ። ካድሬዎቹም የሙዚቃ መሣሪያውን እንዲጫወትና የኮምዩኒስቶችን

መዝሙር እንዲዘምር ጠየቁት፡፡ ሊጐዱት እንደሚችሉ ስለሚያውቅ በጣም ቢፈራም፣ ዓለሙ በድፍረት እርሱ ክርስቲያን እንደ ሆነና ለእግዚአብሔርና ለአዳኙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋናን ብቻ ለመዘመር ቃል እንደ ገባ ነገራቸው፡፡ በድፍረት መመስከሩ በጣም አበሳጫቸውና ወዲያው ስሜታቸው ይበልጥ እያስጠላ መጣ፡፡ ዓለሙ ስለ ሕይወቱ ፈራ፡፡ ምንም እንኳ ካድሬዎቹ የኮምዩኒስቶችን ዜማ እንዲያዜም ቢጠይቁትም፣ ዓለሙ ግን እንቢ አለ፡፡

ከመጠን በላይ የጠጣው ሹፌር በድንገት ፍሬን በመያዝ መኪናዋን አቆመ፣ መኪናዋም ስትቆም ዓለሙን ከመኪናዋ እንዲወርድ ነገረው፤ ዓለሙ ከኋላው መሣሪያቸውን አውጥተው ስላልተኮሱበት በጣም ይገረማል፡፡ በጥይት ተመትተው የተገደሉ ክርስቲያኖችን ያውቃልና፡፡ እነዚሁ ነገር ግን ሲመለሱ እንደሚያገኙት በማስፈራራት ትተውት መኪናቸውን እያሽከረከሩ ወደ ተራራው ላይ ሄዱ፡፡

ዓለሙ ከመንገዱ ዳር ተንበርክኮ ሕይወቱን የታደገውን አምላኩን አመሰገነ፡፡ በጣም ብዙ ክርስቲያን ወጣቶች፣ እንደ እርሱ ተማሪዎች የሆኑ፣ በእምነታቸው ምክንያት መገደላቸውን ያውቃል፡፡ በእስር ቤት ብዙ መከራ እየተቀበሉ ያሉ ብዙ ጓደኞች አሉት፡፡ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን በመጨረሻ ነፃ በመውጣቱ ደስ ብሎታል፡፡ ይህ ምናልባትም ሦስቱ ካድሬዎች ተመልሰው እስኪመጡ ድረስ ሊሆን ይችላል፡፡ አኮርዲዮኑን እንደ ተሸከመ፣ ዓለሙ በመኪና ይዘውት የመጡትን መንገድ በእግሩ በፍጥነት መሄድ ጀመረ፤ ከዚያም ጓደኞቹ ወደሚገኙበት መንደር በሰላም ደረሰ፡፡ ቀኑን እና ምሽቱን ሙሉ የሙዚቃ መሣሪያውን እየተጫወተና መዝሙር ከመጽሐፍ ቅዱስና ራሱ የጻፈውን እየዘመረ ቆየ፡፡ ዝማሬዎቹም ስለ ክርስቶስ ማንነት፣ ስለ ሕይወት ሰጪነቱና ስለ ጥበቃው እንዲሁም ስለ እንክብካቤውና ስለ ኃይሉ የሚያወሱ ነበሩ፡፡ ክርስቲያኖች መዝሙሩን የሚያውቁት ሆነው ሲገኙ ከእርሱ ጋር ይዘምሩና እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር፡፡

አስደሳች የአንድነት ጊዜ ነበር፣ ነገር ግን ዓለሙ ካድሬዎቹ አድነው እስኪያገኙት ድረስ ምን ያህል ጊዜ ይወስድ ይሆን? እያለ ይጨነቅ ጀመረ፡፡ ወደ መኖሪያ ሰፈሩም ከመሄዱ በፊት፣ በመንገድ ላይ ስለ ገጠሙት ሦስት ካድሬዎችና እንዴት እንዳስፈራሩት ነገራቸውና እንዲጸልዩለት ጠየቃቸው፡፡ በዚያ የነበሩ ክርስቲያኖች በጉልበታቸው ተንበርክከው ለዓለሙ ጸለዩለት፡፡ በቀጣይነትም እንደሚጸልዩ ነገሩት፡፡

ከዚያም፣ ከቦሎሶ የመጣ አንድ ሰውዬ የኮምዩኒስት ካድሬዎች የቤተ ክርስቲያን ሕንጻን በወሰዱ ጊዜ ስለ ሆነው ነገር ነገረው፡፡ ያገኙትን መጽሐፍ ቅዱስን በጠቅላላ አቃጠሉ፣ እንዲሁም አማኞች ተሰብስበው እንዳያመልኩ ከለከሉ፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ጣሪያ ላይ መስቀሉን አነሡ፣ በግድግዳዎቹ ላይ የተጻፉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን አጠፏቸው፤ ቤቱንም የአዲሲቷ ኢትዮጵያ አዲስ መንገድ የሆነውን የማርክሲዝም/ሌኒንዝም ርዕዮተ ዓለም ማስተማሪያ ትምህርት ቤት አደረጉት፡፡ ለውጥንና አዲስ ርዕዮተ ዓለም ለማስተማር ካድሬ ተመደበ፡፡ እያንዳንዱ ቤተሰብም አንድ ሰው እንዲማር ይልክ ዘንድ ትእዛዝ ተሰጠ፡፡

ይሁን እንጂ፣ ትምህርቱ በተጀመረ በመጀመሪያው ቀን መብረቅ አካባቢውን መታው፡፡ ነጐድጓድ አንጐዳጐደ፣ ዝናብ ዘነበ፣ ከዚያም መብረቅ ወድቆ አስተማሪ የሆነውን፣ ካድሬ መትቶ ገደለው፡፡ ኮምዩኒስቶቹ አካባቢውን ጥለው ሸሹ፤ ክርስቲያኖችም እንደገና ሕንጻውን በመቆጣጠር አምልኮዋቸውን በዚያ ማካሄድ ጀመሩ፡፡

‹‹ስለዚህም እግዚአብሔር አንተንም ከእነዚህ ሦስት ክፉ ሰዎች ይጠብቅሃል፣›› በማለት ዓለሙን አበረታቱት፡፡

የተበሳጩት ካድሬዎች ዓለሙ ስለ ናቃቸው በጣም ተበሳጭተዋል፡፡ ወደሚቀጥለው ከተማ አረቄያቸውን እየጠጡ መኪናቸውን እየነዱ ሄዱ፡፡ ነገር ግን ወደ ከተማው አልደረሱም፡፡ ዓቀበት እና ቍልቍለት በበዛበት መንገድ ላይ ከተገቢው ፍጥነት በላይ ያሽከረክሩ ነበርና በአንድ መታጠፊያ ላይ በፍጥነት ለመታጠፍ ሲሞክሩ ድንጋያማ ወደ ሆነ ሸለቆ መኪናዋ ተገለበጠች፡፡ ሦስቱም ካድሬዎች ሞቱ፡፡

‹‹በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያሰፈራ ነው።››

ዕብራውያን 10፡31

‹‹ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፣ ያውም እናንተ ናችሁ።››

1ኛ ቆሮንቶስ 3፡17

20

ጃዮሩ

አባልነት

ኳየሩ አሥራ አምስት ወጣት ወንዶችንና ሴቶችን የያዘ ሲሆን፣ ተራቸው ደርሶ ሲጠሩ፣ ለመዘመር ዝግጁ ሆነው፣ በጉባኤው ፊት ቆሙ። የሚለብሱት ልዩ የሆነ ልብስ አልነበራቸውም። ሁሉም የራሱን ልብስ ለብሶ ይመጣል። ሁሉም በአሥራዎቹ መጨረሻ ወይም በሃያዎቹ መጀመሪያ ዕድሜ አካባቢ ያሉ ልጆች ነበሩ። በዳዊት መዝሙር ላይ የተመሠረቱ ሦስት ዝማሬዎችን አዜሙ። ስለ እግዚአብሔር ታማኝነትና የመጠበቅ ኃይሉ ሲዘምሩ ፊታቸው ያበራ ነበር። ይህ ለእነርሱ እውነት ነበር፣ በሕይወታቸው ተለማምደውታልና። ኳየሩ ወደ ወንበሩ ሲመለስ፣ ወደ 2000 ሰው የሚጠጋ ሕዝብ ያለበት ጉባኤ በታላቅ አድናቆት በማጨብጨብ ባረካቸው።

ጓደኛዬ ኤርምያስ የኳየሩ አባላት ቀጥር ከዚህ በብዙ እንደሚበልጥ፣ ነገር ግን አብዛኞቹ በክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት በወህኒ ቤት ውስጥ እንደሚገኙ እንዲሁም አንዳንዶቹም መገደላቸውን ነገረኝ።

የኮምዩኒስቱ የ17 ዓመታት አገዛዝ ሊወድቅ አቅራቢያ ነበር ይህ የሆነው። የማርክሲዝም/ሌኒኒዝም ኃይል- የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ያዳከመና የኢትዮጵያን ጎብረተሰብ ያጐሳቆለው የደርግ መንግሥት ማብቂያው ነበር። በሰሜን የነበረው ጦር መሸሽ ጀምሯል፤ ሕዝቡም ለዐመፅ ከመነሣቱ በፊት ይወድቃል። እንዲሁም አብዛኞቹ መሪዎች ከሀገሪቱ በሰላም የሚወጡበትን መንገድ በማመቻቸት ላይ ነበሩ።

ወንጌላዊ ማርቆስ፣ በእርሱ አካባቢ በወላይታ ውስጥ ባዘጋጀው ልዩ ፕሮግራም ላይ የእግዚአብሔርን ቃል እንዳካፍል ለመነኝ። በአካባቢው ካለ የኮምዩኒስት ባለ ሥልጣን ይህንን ስብሰባ ለማካሄድ ፈቃድ እንዳገኘ ገለጸልኝ። ‹‹ብዙዎቹ ኮምዩኒስቶች በክርስቶስ አምነዋል፤ ከእኛ ጋር በየዕለቱ ጠዋት ጠዋት

መጽሐፍ ቅዱስ እናጠናለን፣›› ሲል አረጋገጠልኝ፡፡ ‹‹የኮምዩኒስቶች ኢ-አማኒያን ርዕዮተ ዓለም ለሰዎች ተጨባጭ እውነታ፣ ሕይወትና ተስፋ አጠያያቂ ነገር እንደሌለው አውቀዋል፡፡››

ኳየሮቹ ዝማሬያቸውን እያቀረቡ፣ ኤርምያስ እንዲህ ሲል አጫወተኝ፡- ‹‹ወደ ኳየሩ ለመግባት በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ ሦስት መስፈርቶች አሏቸው፡-

(1) ማንኛው አባል መሆን የሚፈልግ ሰው ጥሩ ድምፅ ሊኖረው ይገባል፣ በአንድነት መዘመር መቻል አለበት፣ እንዲሁም የመሪውን ትእዛዝ ማክበር አለበት፡፡ (‹‹ይህ የተገባ ነው›› ብዬ አሰብኩኝ፡፡)

(2) በማንኛውም ሰዓት ለአገልግሎት ቅርብም ሆነ ሩቅ ወደ ሆነ ስፍራ ለመጓዝ ፈቃደኛ መሆን አለበት፡፡ (‹‹ይህ ለደኻ ተማሪዎች መሥዋዕትነትን የሚጠይቅና አስቸጋሪ ነው - በጣም ጥልቅ የሆነ መሰጠትን ይጠይቃል›› አልኩኝ በልቤ፡፡)

(3) ለኢየሱስ ክርስቶስ ቢያንስ ለሦስት ወር ያህል በእስር ቤት ውስጥ መከራን መቀበል መቻል አለበት! (የደረሰባቸው መከራ በአንዳንዶቹ ፊት ላይ ይታያል)፡፡

እኔም ለኤርምያስ እንዲህ ብዬ ነገርኩት፣ ‹‹እኔ ከመጣሁበት ሀገር የዚህን ኳየር መስፈርት የማያሟሉ ብዙ ዘማሪዎች አሉ፣ እንዲሁም በጣም ጥቂቶች ሊሆንላቸው ይመርጣሉ!›› አልኩት፡፡

‹‹እግዚአብሔር ጌታዬን፦ ‘ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ
እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ’ አለው።››

መዝሙረ ዳዊት ፻10፡1

‹‹እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ
ተቈጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ፤››

የሐዋርያት ሥራ 5፡41

21

ዴልጋ

የጠንቋዩ ልጅ

ጊዜው ጨለማ ነበር፤ ወጣቱን ዴልጋ በእኛ ሚስዮን ግቢ ውስጥ በዚያን ሰዓት መመልከቴ አስገርሞኛል። ማታ ማታ በሚደረገው ስብሰባ ላይ ለመሳተፍ በተሰበሰቡ ሰዎች መካከል እኔና ሚስዮናዊ ጓደኛዬ አልበርት ብራንት በማለፍ ላይ ሳለን፣ እርሱ ከመንደሩ ልጆች ጋር ነበር። የሰዎች ቍጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሲሄድ፣ ሰዎች ይበልጥ ይጓጉ ጀመር። አንድ እንግዳ ነገር ሊከሰት መሆኑን አውቀዋል። ኑ እና ተመልከቱ የሚል መልእክትን በመንደሩ ሁሉ ውስጥ አሰራጭተናል።

ወደ ዴልጋ በጣም ስቀርብ ይህ ለእኔ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር። ሁልጊዜ በቅሎዬ ላይ ተቀምጬ በአባቱ መኖሪያ ቤት ደጃፍ ሳልፍ አየው ነበር። እጆቼንም በማወዛወዝ ፈገግ ብዬ ሰላም ብለውም ለሰላምታዬ ግን ምንም ምላሽ ሰጥቶኝ አያውቅም፣ ነገር ግን በፍርሃት እንደ ተዋጠች ጥንቸል ወደ ቤቱ ጓሮ በመሮጥ ይደበቅ ነበር። መኪናዬን እያሽከረከርኩ በመኖሪያ ቤታቸው በኩል በማልፍበት ጊዜ፣ ዴልጋ ከመኖሪያ ቤቱ ብቅ በማለት ይመለከተኛል እንጂ፣ ፈጽሞ ከቤት አይወጣም ነበር። አባቱ በመኖሪያ ቤታቸው አቅራቢያ ለመኖር ስለ መጡት ሚስዮናውያን ምን ብሎ እንደ ነገረው አላውቅም።

አዛዝ የተባለው የዴልጋ አባት ‹‹የዝናብ አባት›› ተብሎ የሚጠራ የአካባቢው ጠንቋይ ነበር። ዝናብን የመቈጣጠር ኃይል እንዳለው ስለሚናገር፣ ለበቆሎና ለጉበስ ሰብሎቻቸው እንዲሁም ለስኳር ድንች እና ለእንስሶቻቸው ሣር ለማብቀል በዝናብ ላይ በሚደገፉ በአካባቢው ሰዎች ላይ ትልቅ ሥልጣን ነበረው። ዝናብ ሳይዘንብ ከቀረ፣ አዛዝ ሕዝቡን እንዲህ ይላቸዋል፣ ‹‹ዝናብ ያልዘነበበት ምክንያት በቂ የሆነ መሥዋዕት ባለማቅረባችሁ መናፍስቱ

ተቈጥተው ነው።።›› ገበሬዎቹም በፍራቻ ተውጠው መሥዋዕት ወደሚያቀርበው ወደ አዛዝ እንስሶቻቸውን ይዘው ይመጣሉ።። እርሱም አንዳንዶችን እንስሳት ‹‹ዝናብ ለማዝነብ›› ለመሥዋዕት ሲያቀርባቸው፣ ሌሎቹን ደግሞ ከራሱ መንጋ ጋር ይቀላቅላቸዋል።። እንደ ተለመደው ዝናብ ሲዘንብ እንዲህ ይላቸዋል፣ ‹‹የቅድመ-አያቶቻችን መናፍስት በመሥዋዕታችን ረክተዋል፣ ደስም ብሏቸዋል።።››

ዴልጋ ከሦስት ወንድ ልጆች መካከል ትንሹና የዐሥር ዓመት ዕድሜ ያለው ልጅ ነበር፣ ሁሉም ልጆች የአባታቸውን ሰይጣናዊ መንገድ መከተል ይጠበቅባቸዋል።። ነገር ግን ዴልጋ በልቡ ውስጥ ሌላ መሻት ነበር።። እንደ ሌሎች ልጆች ሁሉ ወደ ሚስዮናውያን ትምህርት ቤት የመሄድ ፍላጎት ነበረው።። አንዳንድ ጊዜ የአባቱን ከብቶች ውኃ ለማጠጣት ወደ ምንጭ እየነዳ በሚስዮናውን ቅጥር ግቢ አካባቢ ሲያልፍ፣ ልጆች በዕረፍት ጊዜያቸው ሲጫወቱ ወይም በመኖሪያ ቤታቸው ክፍል ውስጥ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ አጮልቆ ይመለከት ነበር።።

ለሳምንታት በየገበያ ስፍራው ‹‹ሲኒማ›› እንደምናሳይ ስናስተዋውቅ ቆይተናል።። በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ከዚያ ቀን በፊት ፊልም የሚባል ነገር አይተው ስለማያውቁ፣ ሆን ብለን በጉጉት እንዲጠባበቁ አደረግን።። ቀጠሮ በተሰጠበት ቀን፣ በጣም ብዙ ሺህ የሚሆኑ ሰዎች በስፍራው ተገኙ፤ አንዳንዶቹ ይህንን ፊልም ለመመልከት የአንድ ቀን ጉዞ ተጉዘው መጡ።። በጣም ተጠጋግተው በሣሩ ላይ በመቀመጥ ፊልሙ እስኪጀመር በመጠበቅ ላይ ነበሩ።። ለሦስት ምሽቶችም ክርስቲያናዊ ፊልሞች ታዩ፣ ወንጌል ተሰበከ፣ እናም ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲከተሉ ጥሪ ቀረበላቸው።።

ዴልጋ እየተመለከተው፣ ሚስተር ብራንት ወደ ጀነሬተሩ በመሄድ አስጀመረው።። ብርሃን በተዘረጋው ሸራ ላይ ፈነጠቀ፣ ከዚያም ምሥል መታየት ጀመረ፤ ሁሉም ነገር እንግዳ ነገር ነበር።። ከኬንያ የተገኘው ፊልም በጣም የታወቀ አንድ ምሳሌያዊ ንግግርን በውስጡ አዝሏል፣ ‹‹ዝሆኖች ሲጣሉ የሚጐዳው ሣሩ ነው›› ይላል።። የፊልሙ ታሪክ የሚያጠነጥነው አንድ በሕመም የተጠቃ ትንሽ ልጅ ክርስቶስን እንደ አዳኙ በመቀበሉ ምክንያት የኢ-

አማኒያን ሰዎችን ባህላዊ ሕክምና ለመቀበል አሻፈረኝ በማለቱ፣ በዚህም ምክንያት እንዴት ስደት እንደ ደረሰበት፣ ነገር ግን ይህ ልጅ በእምነቱ ጸንቶ በመቆሙ ምክንያት የብዙ ሰዎች ሕይወት መለወጡንና ማኅበረሰቡም ለክርስቶስ ምላሽ በመስጠቱ ዙሪያ ነበር።

ስብሰባው እንደ ተጠናቀቀም፣ ዴልጋ በጨለማው ውስጥ እየሮጠ ወደ ቤት ሄደ። ኢየሱስን ቢቀበልና ለመከተል ቢወስን ምን ሊከሰት እንደሚችል ግራ ገባው። ዴልጋ በታላቅ ደስታ ተውጦ ታሪኩን ለአባቱ አዛዝና ለወንድሞቹ አጫወታቸው። ታሪኩም ኢየሱስ ከሰይጣን በላይ ኃያል መሆኑን ነገራቸው። ሁሉም ነገር አዲስ ነበር። እውነት ሊሆን ይችላልን? የዴልጋ ወንድሞችም በሚቀጥለው ምሽት ራሳችን ከእርሱ ጋር ሄደን ሲኒማውን እናያለን አሉ። አባታቸው፣ ከትንሽ ማቅማማት በኋላ፣ በመሄዳቸው ተስማማ።

በሰማያዊ ስፍራ ስለሚደረገው ጦርነት የምናውቀው ነገር የለም፣ ነገር ግን በጥፋት ጐዳና ውስጥ ያሉ ሰዎች ደኅንነት ያገኙ ዘንድ፣ የጨለማው ኃይል ይሰበር ዘንድ፣ ሰዎች በክርስቶስ ያለውን ነፃነትና ደኅንነት ይቀበሉ ዘንድ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ለረጅም ጊዜ ሲጸልዩ ነበር። ቀን ቀን ይደረግ በነበረው ልዩ የአምልኮ ፕሮግራም ላይ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ያደምጡና ብዙዎች በቅርብ ጊዜ ስለ ጀመሩት በክርስቶስ ስላለው አዲስ ሕይወት ይማሩ ነበር።

ወደ ምሽት አካባቢም፣ ላሞች ከታለቡና ወደ በረታቸውም ከገቡ በኋላ፣ በአካባቢው ካሉ መንደሮች ወደ ሚስዮን ጣቢያው መንገዱን ይዘው የሚጐርፉ ሰዎችን ዴልጋና ወንድሞቹ ተቀላቅለው መጓዝ ጀመሩ። ተቀምጠውም መዝሙርና ስብከት ካደመጡ በኋላ፣ ለዓይን ያዝ ማድረግ ሲጀምር፣ በትልቅ ሸራ ላይ በሚታየው ምሥል አማካኝነት የኢየሱስን ታሪክ ተመለከቱ። የክርስቶስን ንግግር ሲያደምጡ፣ ተአምራቱን ሲመለከቱ፣ በሽተኞች ሲፈወሱ፣ ዓይነ ሥውራን ዐይናቸው ሲበራ፣ አካለ ስንኩላን ሲራመዱ፣ ለምጻሞች ከለምጻቸው ሲነጹ፣ በጣም ብዙ ሕዝብ ሲመግብና ሙታንን ሲያስነሣ በመመልከታቸው ትንፋሻቸውን ውጠው ቁጭ አሉ። ከዚያም ክሕደት፣ ትክክለኛ ያልሆነ ፍትሕ፣ ስድብ፣ ማላገጥ፣ መከራ፣ በመስቀል ላይ አሟሟቱን ተመለከቱ፣ ክርስቶስ ኃጢአት የሌለው ቢሆንም እንኳ፣ እኛን ሊዋጅና ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ በመስቀል ላይ ሞተ፣ ከዚያም ታላቅ

ትንሣኤውን እና ወደ ሰማይ ማረጉን ተመለከቱ፡፡

ፊልሙም እንደ ተጠናቀቀ፣ ሚስተር ብራንትና ወንጌላዊ ጣሰው ሕዝቡን ከኃጢአቱና ከአለማመኑ ንስሓ እንዲገባና ጌታ ኢየሱስን እንደ አዲስ ጌታው አድርጎ እንዲቀበል ጥሪ አቀረቡ፡፡ ከሌሎች በጣም ብዙ ሰዎች ጋር፣ ዴልጋና ወንድሞቹ ወደ ፊት በመምጣት በግልጽ ሰይጣንን ካዱ፡፡ ኢየሱስን ‹‹ሁለት እጃቸውን ዘርግተው›› ሙሉ በሙሉ ያለምንም ገደብ ተቀበሉት፡፡

ወንጌላዊ ጣሰው የዴልጋን ወላጆች ያውቃቸው ስለ ነበር ሦስቱን ወንድማማቾች ለልዩ ምክር ወደ ኋላ እንዲቀሩ አደረጋቸው፡፡ ‹‹ዝናብ አዝናቢ›› የሆነው አባታቸው ለዚህ ነገር የሚሰጠውን ምላሽ ያውቀዋል፡፡ ጣሰው ጠንቋይ የነበረው የገዛ አባቱ ሐሳብና እርሱ ጌታ ኢየሱስን ሲቀበል ምን ያህል ተናድዶ እንደ ነበር ያስታውሳል፡፡ አባቱ በመኖሪያ ቤታቸው መሃል ላይ ባለው ምሰሶ ላይ እጅና እግሩን አስሮት በፍም እሳት ያቃጥለው ነበር፡፡ ይህንንም ጣሰው ራሱን ስቶ እስኪወድቅና እናቱ የድረሱልኝ ጥሪዋን በታላቅ ድምፅ እስከታሰማ ድረስ ያደርግ ነበር፡፡ ቀኖሎቹም እስኪድኑ ድረስ ብዙ ሳምንታት ወስዷል፡፡ (*ኢትዮጵያውያን የወንጌል አርበኞች* የተሰኘውን መጽሐፍ ምዕራፍ 17 ያንብቡ፡፡)

ጣሰው ለዴልጋና ለወንድሞቹ ጸልዮላቸው በሚቀጥለው ቀን አባታቸውን ለማነጋገር እንደሚመጣ ቃል ገባ፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ጠንካሮች ይሆኑ ዘንድና የጨለማ ኃይል ይሰበር ዘንድ አበረታታቸው፡፡ እነዚህ ሦስት ልጆች ከሄዱ በኋላ ወንጌላዊው የተወሰኑ ሰዎችን ጠርቶ ለእነዚያ ሦስት ልጆችና ስለ አባታቸው ሌሊቱን በሙሉ ጸለዩ፡፡

በሚቀጥለው ቀን፣ ወንጌላዊ ጣሰው ከሌሎች ሁለት ወንጌላውያን ጋር በመሆን ዝናብ አዝናቢ የሆነውን የዴልጋ አባት፣ አዛዝን፣ ለመጐብኘት ሄዱ፡፡ በሚያስገርም ሁኔታም፣ እንግዳ ተቀባይ፣ የወንጌል መልእክት ተቀባይና ለክርስቶስ በዝምታ ምላሽ የሚሰጥ ሆኖ አገኙት፡፡ እነዚህ ሦስት ወንድ ልጆች ለአባታቸው ስለ ክርስቶስ የተመለከቱትን ፊልም ነግረውት በድፍረት ኢየሱስን እንደሚከተሉ ነግረውታል፡፡

በዚያን ዕለትም የዴልጋ አባት ሰይጣንን በመካድ አዳኙን ተቀበለ፡፡ ወሬውም እንደ ሰደድ እሳት ተዛመተ፣ ብዙ ሰዎችም ሁኔታውን ለመመልከት ተሰበሰቡ፡፡

ዴልጋ ከጥንቁላ ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ነገሮች በመሰበሰብ አባቱን ከረዳ በኋላ፣ ሁሉንም በእሳት አቃጠሏቸው፡፡ ለአምልኮ የተለየውን ዛፍ ቈርጠው ጣሉት፣ እንዲሁም በሥሩ ያለውን የመሠዊያ ድንጋይንም አፈረሱ፡፡ ለብዙ ዓመታት የጠነቈለበትን የሰይጣን ቤትን አፈረሰ፡፡

የዝናብ አዝናቢው መለወጥ ዜና በተሰማ ጊዜ በአካባቢው እና በሚስዮን ጣቢያው ውስጥ በጣም አስደሳች ጊዜ ሆነ! በሚቀጥለውም ቀን በአካባቢው የቀረው ጠንቋይ መልእክተኞችን ወደ ወንጌላውያኑ በመላክ ‹‹አዲሱን መንገድ›› አሳዩኝ ብሎ ሲጠይቅ አስገራሚ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ እርሱ ወደ ክርስቶስ መጣ፣ በቀድሞ ሕይወቱ ውስጥ የነበሩትን አልባሌ ነገሮችን ሁሉ አቃጠለ፣ ለቤተ ክርስቲያን መሥሪያ የሚሆን መሬትም ሰጠ! ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን!

‹‹ታናሽም ልጅ ይመራቸዋል።››

ኢሳይያስ ፲፩፡6

‹‹እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ ኢይገባበትም አላቸው።››

ማርቆስ ፲0፡15

22

ፌንቾ

የጌታ እስረኛ

ፌንቶ በእስር ቤቱ ወለል ላይ በተነጠፈ የሣር ፍራሽ ላይ ተጋድሞ ለመተኛት እየሞከረ ነበር። ቁንጫ፣ ቅማል እና ትኋን ደሙን ሲመጥጡት ለመቋቋም እየሞከረ ነበር። ሰውነቱን አከክ አከክ እያደረገ ተመቻችቶ ለመተኛት ጥረት እያደረገ ነበር። ጨለማው እና ረጅሙ ምሽት ሁኔታውን አባብሶታል።

የእነርሱ ክሕደት! በጣም የሚጐዳው ይህ ነበር! ልቡን ሁለት ስፍራ ላይ ነው የሰበረው። ፌንቶ ስለ ጓደኞቹ ይበልጥ እያሰበ በሄደ ቍጥር ንዴት፣ መራራነት እና ኃዘን ይቈጣጠሩታል። የቅርብ ጓደኞቼ የሚላቸው ሰዎች ለኮምዩኒስት ባለ ሥልጣናት አሳልፈው ሰጥተውታል። እንዴት በእርሱ ላይ ይህንን ያደርጋሉ? እርሱን እንዲክዱት ያደረጋቸው ነገር ምንድን ነበር? ለብዙ ሳምንታት ፌንቶ በኃዘን ተሠቃይቶ በጣም ታምሞ ነበር።

መጸለይም ሆነ መዘመር እስኪያቅተው ድረስ ልቡ ቂም ቋጥሮ እያለቀሰ ነበር። ኃዘንና ተስፋ መቍረጥ እንደ ጥቁር ደመና በራሱ ላይ ተጭነውበት ነበር። ፌንቶ ከቀዝቃዛው ንፋስ ራሱን ለመከላከል ቀጭን ጋቢውን ወደ ላይ ሳብ አድርጎ የንጋት ብርሃንን፣ ሞቃታማ ፀሐይን በጉጉት ይጠባበቅ ጀመር። ነፃ መሆን፣ ከቤተሰቡ ጋር እንደ ገና አብሮ መሆንንና ከክርስቲያኖች ጋር አብሮ ማምለክን ተመኘ። በትልቅ ግራ መጋባት ውስጥ ነበር። ከዚህ ነገር ውስጥ በሰላም ይወጣ ይሆንን? አምስት ዓመታት! ይህንን እንዴት መቋቋም ይችላል?

በወላይታ ሜዳዎች፣ በሶሪ አካባቢ በጣም ብዙ መንደሮች አሉ። በቡድን

በቡድን የሆኑ በንብ ቀፎ ቅርጽ በሣር የተሠሩ መኖሪያ ቤቶች በበቆሎ፣ ስኳር ድንች እና የጥራጥሬ አዝርእት ተከብበው ይታያሉ። የሸንኮራ ተክል፣ ቅመማ ቅመምና የቡና ዛፎች መኖሪያ ቤታቸውን የከበቡ ሲሆን፣ የባሕር ዛፍ ድንበራቸውን እና የመጓጓዣ መንገዱን ይከልላል። በጎች፣ ፍየሎችና አህያዎች በሕፃናት እየተጠበቁ በጋራ የግጦሽ መሬት ላይ ይሰማራሉ፤ በጣም ትንንሾቹ ልጆች በጎችና ፍየሎችን ይጠብቃሉ፣ ከእነርሱ በዕድሜ የሚበልጡት ደግሞ ጥጆችንና አህዮችን ያግዳሉ። ጐረምሶች ደግሞ ጦራቸውንና ትልልቅ ጩቤያቸውን ይዘው ላሞችና በሬዎች ያሰማራሉ።

ከተራራው ባሻገር ፀሐይ መጥለቅ ስትጀምር፣ እንስሳቱን ወደ መኖሪያ ቤታቸው እየነዱ በማምጣት በመኖሪያ ቤት ውስጥ ያጐራቸዋል። እያንዳንዱ ልጅም ወደ ቤት ሲመለስ ለእንስሶቹ መኖ የሚሆን ሣር አጭዶው ወይም ለእናታቸው እንጨት ለቅመው ወይም በእንስራ ውኃ ከምንጭ ቀድተው ተሸክመው ወደ ቤት ይመጣሉ።

ቀኑን ሙሉ በመስክ ሲሠሩ ከቆዩ በኋላ፣ የመንደሯ ወንዶች ማታ ላይ በዛፍ ጥላ ሥር ሆነው ያወጋሉ። አንዳንዶች ጠላ ሲጠጡ ሌሎች ደግሞ ጋያ ያጨሳሉ። ፌንቶ እና የቅርብ ጎረቤቶቹ የሆኑት አምስቱ ወንድሞቹ ተቀምጠው ያን ቀን በመንደራቸው ስላለፈው እንግዳ እየተወያዩ ነበር።

ከዚያ በፊት እንደ ነበሩት በሺህዎች የሚቈጠሩ ቀናት ሁሉ፣ የምሽቱ ጸጥታ በሶሪ ውስጥ ለኖሩት በሺህ የሚቈጠሩ ሰዎች ተስማሚ ሁኔታን የፈጠረላቸው ይመስላል። ነገር ግን የማይነገር የውስጥ ስጋት ነበረባቸው። ይህ ስጋት በውስጣቸው የሚኖርና ሕይወታቸውን የሚቈጣጠር ሆነ። የቅድመ-አያቶቻቸው መንፈስ በአካባቢው በሚገኙ ዛፎችና ድንጋዮች ውስጥ እንደሚኖርና የተወለዱበትን፣ ለሕይወት ዘመናቸውን የኖሩበትን፣ የሞቱበትንና የተቀበሩበትን መንደር ፈጽመው ለቅቀው እንደማይሄዱ ያምናሉ። እነዚህን መናፍስት በትንንሽ መሥዋዕቶች ማባበል አስፈላጊ ነበር።

በቀርከሻ ጫካ ውስጥ የሚኖረው ጠንቋይ ተጨማሪ እንስሳትን ይፈልጋል። ለሰይጣን መሥዋዕት ማቅረብ ይሻል። ጠንቋዩ እንዲህ ብሎ ተናዟል፣ ‹‹አንድ ወጣት፣ ቀላ ያለች ጊደር ካልተሰጠች በቀር፣ በሽታ አካባቢውን እንደሚያጥለቀልቅና ብዙ ሰዎች እንደሚሞቱ ተናግሯል።›› የታይፎይድና

የኮሌራ በሽታ ከዚህ በፊት በሶሪ ውስጥ ተከስቶ ስለ ነበር፣ ሰዎቹ በጣም ፈርተዋል። ጠንቋዩ ሰውዬ የታረደ እንስሳን የሆድ ዕቃን በመመልከት የማኅበረሰቡን ‹‹ሰላምና ጤንነት ለመመለስ›› ለጠንቋዩ ስጦታ ይዞ መምጣት ያለበት ማን እንደ ሆነ ይወስናል። በሶሪ የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ‹‹ለመናፍስት›› ማብቂያ የሌለው መሥዋዕት (እንስሳትን፣ ዶሮዎችን፣ ጥራጥሬን፣ እንቁላልን፣ ወተትን እና ቅቤን) ማቅረብ የተለመደ ነበር። የማይታወቅ ነገርን፣ መናፍስትን፣ ጠንቋዮችን፣ መካከለኛ የሚሆኑ መናፍስትና ትንቢት ተናጋሪዎችን መፍራት ሕዝቡን በጨለማ ውስጥ ለብዙ ትውልድ ያስቀመጠ ነገር ነበር። እንዲህ ያለው ነገር ሊለወጥ ይችላልን?

ፌንቶ እና አምስቱ ጓደኞቹ እንግዳው ሰው በነገራቸው ነገር ተረብሸዋል። አዲስ ጎጆ በመሥራት ላይ ሳሉ ነበር ወደ እነርሱ የመጣው። ወተት ለመጠጣትና በመስቀል ላይ ስለ ሞተ አንድ ሰው ለእነርሱ ለመንገር የቆየው ለግማሽ ሰዓት ያህል ነበር። በሚቀጥለው ቀን መልካም ዜና ይዞ እንደሚመለስ ነግሯቸዋል። ይህ እንግዳ መልካም ዜና ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ አልገባቸውም።

❧

እንግዳው ሰውዬ እመለሳለሁ ባለበት ቀን ሲመለስ፣ ሊነግራቸው ቃል የገባውን መልካም ዜና ለመስማት አዋቂዎች ሁሉ ተሰበሰቡ። ወንጌላዊውም እንዴት መናፍስትን ይፈራ እንደ ነበርና እንዴት በተለየው የአድባር ዛፍ ሥር በመሠዊያው ላይ መሥዋዕት ያቀርብ እንደ ነበር፣ ከዚያ ግን ከሁሉም ጠንቋዮችና መናፍስት በላይ ኃያል ስለ ሆነ እንዲያውም ከሰይጣንና ከዲያብሎስ ራሱ እንኳ የሚበልጥ ስለ አንድ ሰው እንደ ሰማ ነገራቸው። ወንጌላዊው እንዴት ኢየሱስ የታመሙትን እንደ ፈወሰ፣ ለምጻሞችን እንዳነጻ፣ ዐይነ ሥውራንን ዐይናቸውን እንዳበራ፣ የተራቡትን እንዳበላ፣ የሞቱትን ከሞት እንዳስነሣ እና በውኃ ላይ እንዴት እንደ ተራመደ ነገራቸው።

ፌንቶ እና ቤተሰቡ ታሪኩን በተመስጦ አዳመጡት። ሰዎች ከኃጢአታቸው ይድኑና ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ይችሉ ዘንድ እንዴት ኢየሱስ ራሱን ለሞት አሳልፎ እንደ ሰጠ ሲተረክላቸው፣ የመንደሪቷ ሰዎች ሁሉ በንቃት ይሰሙ ነበር። ‹‹ነገር ግን እርሱ አሁን ሕያው ነው! ሞትን ድል አድርጎ

ተነሥቷል! ሰይጣንንና ኃይሉን ከመፍራት ነፃ መውጣት እንችላለን!›› ወንጌላዊው ወንጌልን ለሰዎቹ ለብዙ ሰዓታት ነገራቸው፡፡ በዚያ አካባቢ ወንጌል ሲነገር ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነበር፡፡ በጣም ደስ የሚልና አዲስ የሆነ ነገር ነበር፡፡ ከበደለኝነት፣ ከፍርሃት፣ ከሰይጣን ነፃ መሆን፤ ይህ በእርግጥም መልካም ዜና ነበር! ይህ እውነት ሊሆን ይችላልን?

ወንጌላዊው የተሰበሰበውን ሕዝብ ይህንን የእግዚአብሔር ስጦታ ይቀበሉና ይድኑ ዘንድ፣ ኢየሱስን እንደ አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉት በጠየቃቸው ጊዜ፣ በመጀመሪያ ምላሽ የሰጠው ፌንቶ ሲሆን፣ ከዚያም ሚስቱ፣ ሁለት ወጣት ልጆች፣ ጥቂት ሴቶችና ወጣት ባለ ትዳሮች ነበሩ፡፡ ሙሉ በሙሉ መሰጠታቸውን ለማሳየት ‹‹እጆቻቸውን ወደ ላይ በማንሣት›› ሰይጣንን እንዲክዱና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ይቀበሉ ዘንድ ወንጌላዊው በጸሎት መራቸው፡፡ ወንጌላዊው ከእርሱ ጋር በመጸለይ ለምግባቸው እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው አስተማራቸው፡፡ በመኖሪያ ቤታቸውም ሁል ጊዜ መጸለይ እንዳለባቸውና አብረው ለመጸለይና የእግዚአብሔርን መንገድ ለመማር መሰብሰብ እንደሚገባቸው ነገራቸው፡፡ በየሳምንቱም እነርሱን ለማስተማር እንደሚመጣ አሳሰባቸው፡፡

ፌንቶ አምስቱ ጓደኞቹም በኢየሱስ ያምናሉ ብሎ ጠብቆ ነበር፣ ነገር ግን እነርሱ ፈቃደኞች አልሆኑም፡፡ ይህ ሁኔታ ፌንቶን ጐድቶታል፣ ነገር ግን ወንጌላዊው ወንጌል የግል ጉዳይ መሆኑንና በወንጌል ምክንያት ቤተሰብና ማኅበረሰብ ሊከፋፈል እንደሚችል ነገረው፡፡ ፌንቶ የሚችለውን ጊዜ ያህል ከአምስቱ ወዳጆቹ ጋር ለማሳለፍ ይጥር ነበር፡፡ አሁን አብረው የሚሠሩ ሲሆን፣ አብረው ማሳቸውን ያርሳሉ፣ እንስሶቻቸውን ያሰማራሉ እንዲሁም ወደ ገበያ ቦታ አብረው ይሄዳሉ፡፡ ፌንቶ ዘወትር፣ ያደርግ እንደ ነበረው ምግብ ለመብላትና ቡና ለመጠጣት ወደ ቤቱ እነርሱን መጋበዙን ቀጥሏል፡፡

ነገር ግን በፌንቶ ሕይወት ውስጥ ብዙ ነገር ተለውጧል፡፡ ቀኑራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉ ለመጡ አማኞች የሚሆን የጸሎት ቤት ለመገንባት ትንሽ መሬት ሰጥቷል፡፡ የጸሎት ጊዜና መጽሐፍ ቅዱስ መማሪያ ጊዜ ለእርሱ እጅግ በጣም ጠቃሚ ጊዜዎች ሆኑ፡፡ ፌንቶ ብዙ ጊዜ አማኝ ለሆኑም ሆነ ለማያምኑ የታመሙም ሰዎች እንዲጸልይ፣ እርስ በርሳቸው የተጋጩ ሰዎችን ለማስታረቅ፣

ስብሰባዎችን እንዲመራ እንዲሁም ከሌላ ስፍራ ተጉዘው የመጡ አማኞችን ለመቀበል ብዙ ጊዜ ይጠራል፡፡ ራሱንም በሶሪ ውስጥ ያሉ አማኞች መሪ ሆኖ አገኘው፡፡

ቀስ በቀስም የፌንቶ አምስቱ ወዳጆቹ ከእርሱ እየራቁ ሄዱ፣ ነገር ግን ብዙ ሰዎች ክርስቶስን ተቀበሉ፤ ቤተ ክርስቲያንም አደገች፡፡ ፌንቶ ወንድሙ ወደ ጌታ የመጣ ጊዜ በጣም ተደሰቶ ነበር፣ ሁለቱ ወንድሞቹ ግን በከተማ ትምህርት እየተማረ ያለውን የአጎታቸውን ልጅ የካሮታን መንገድ በመከተል የንጉሠ ነገሥት አገዛዝ ማብቃት አለበት ብለው ከተነሡ ሰዎች ጋር በዐመፅ መተባበር ጀመሩ፡፡ ካሮታ ከመንግሥት ባለ ሥልጣናት ጋር ግጭት ውስጥ ይገባል ብለው ሰጉ፡፡ ይህ ነገር ከዚህ በፊት ተከስቶ ነበር፡፡ ከአሥራ ሦስት ዓመት በፊት በፖሊስ አማካኝነት ዐመፁ በርዶ የዐመፁ መሪዎች የሆኑ ሁለት ወንድማማቾች ተገድለው በአደባባይ እንዲሰቀሉ ተደርገዋል፡፡ አሁን ደግሞ ከእነርሱ ቤተሰብ አንዱ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ተሳታፊ ሆኗል፡፡ ምናልባት ይህ ተራ ወሬ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ እንደዚያም እንዲሆን በእርግጥ ይመኛሉ፡፡

ෛ

የኮምዩኒስቶች ወደ ሥልጣን መምጣት ኢትዮጵያን ለዘላለም ለውጧታል፡፡ ጓደኝነት፣ የቤተሰብ ትስስር፣ መተማመን፣ መተባበር እና የሥራ ሥነ ምግባር በፍርሃት፣ በጥርጣሬ፣ በአለመተማመን፣ በሐሜት እና እርስ በርስ ስለላ በማድረግ ተተክቷል፡፡ በጣም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ተገደሉ፤ እንዲሁም እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች ታሠሩ፤ ሌሎች ደግሞ ሀገር ትተው ሸሹ፡፡ ክርስቲያኖች ተሰደዱ፤ እንዲሁም ሁሉም ሰው ከአዲሱ የማርክስና ሌኒን ርዕዮተ ዓለም ጋር እንዲስማማ ተገደደ፡፡

የፌንቶ የአጎቱ ልጅ የወላይታ ግማሽ ክፍልን ትልቅ ፍርሃት ውስጥ የከተቷት ካድሬዎች መሪ ሆነ፡፡ ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍል ይህንን ርዕዮተ ዓለም ለማስተማር በአንድነት ሰበሰቡ፤ በዚያም እያንዳንዱ ሰው እጆቹን ጨብጦ መፈክሮችን እንዲልና ከዚህ ኢ-አማኒያን ርዕዮተ ዓለም ጋር ራሱን ያመሳስል ዘንድ ተገደደ፡፡ ክርስቲያኖች ‹‹ክርስቶስ ብቻ ጌታ ነው›› ማለት ሲጀምሩ፣ ‹‹ፀረ አብዮተኞች›› ተብለው ማስፈራራት፣ መታሠር፣ መደብደብና ወደ ወህኒ ቤት መጣል ተጀመረ፡፡

ፌንቶ በቆርቆሮ ጣራ በተሠራ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማለዳ የአምልኮ ፕሮግራምን እየመራ ነበር። መሣሪያ የታጠቁ ካድሬዎችና ፖሊሶች ቤተ ክርስቲያኒቱን ሲከብቡ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች እያመለኩ ነበር። ፌንቶ የአጎቱ ልጅ ካድሬዎችን እየመራ ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሕንጻ ይዞ መምጣቱን ሲመለከት ተስፋ ቈረጠ።

ከብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ፌንቶ አብሮ ታስሮ በአካባቢው የገበያ ስፍራ ወደሚገኘው ‹‹ፍርድ ችሎት›› ተወሰደ። በታላቅ ድምፅ የሚጮኹ፣ የተበሳጩ ሰዎች አደባባዩን ሞልተውታል። ፌንቶ አንዳንድ ጎረቤቶቹንም በዚህ ስፍራ ላይ አይቶዋቸዋል። አምስቱ የቅርብ ወዳጆቹም በዚያ ስፍራ ላይ አጠገብ ለአጠገብ ተፋፍገው፣ አኮርፈውና ዝምታ ተላብሰው ተቀምጠዋል። ያልተደሰቱ ይመስላሉ፤ አቀርቅረው መሬት መሬቱን ይመለከታሉ። በድንገት ከፍርድ ቤቱ መሪ መልእክት ተሰጠ፤ የፌንቶ ጓደኞች የለውጥ-ጠላት፣ የአዲሱ መንግሥት ተቃዋሚ፣ ሰላም-አዋኪ እና ለማኅበረሰቡ አስጊ የሆነ ሰው መሆኑን በመግለጽ ከሰሱት።

ፌንቶ በዚያን ሰዓት ማድረግ የቻለው ነገር አፉን ከፍቶ እነርሱ ላይ ማፍጠጥ ብቻ ነበር! ጆሮዎቹን ማመን አልቻለም! አምስቱ ጓደኞቹ ይህ ነገር እውነት እንዳልሆነ ያውቃሉ። ተገድደው ነበር ወይስ በሐሰት በእርሱ ላይ እንዲመሰክሩ ተከፍሏቸው? ትብብር የማያደርጉ ከሆነ፣ እነርሱ እንደሚከሰሱ አስፈራርተዋቸው ይሆንን? የእርሱን ንብረት ለማግኘት ተስፋ አድርገው ይሆንን? ፌንቶ ምን ማድረግ እንዳለበት አላወቀም። በስፍራው የተሰበሰበው ሰው ደጋግሞ ‹‹ቅጣት፣ ቅጣት›› እያለ በመጮኹ ምክንያት፣ መልስ ለመስጠት እንኳ አልቻለም ነበር። እንዲያውም አንዳንዶች ‹‹ይሙት›› ብለው ጮኸው ነበር። ሕዝቡ ዕጣ ፈንታውን ወሰነበት። ፌንቶ ሶዶ ወደሚገኘው የአውራጃው ፍርድ ቤት ተወስዶ የአምስት ዓመት እስራት ተወሰነበት።

❧❧

በወህኒ ቤቱ ወለል ላይ ተኝቶ፣ ፌንቶ በክፍሉ ውስጥ ያሉ የሌሎች እስረኞችን ለቅሶ እና ማጉረምረም ያደምጣል። በወህኒ ቤቱ ውስጥ በመቶዎች የሚቈጠሩ ሰዎች ነበሩ-ወንጀለኞችና የፖለቲካ እስረኞች እንዲሁም ጥቂት እንደ እርሱ ክርስቲያን እስረኞች በዚያ ነበሩ። ፌንቶ በፊልጵስዩስ ወህኒ ቤት ውስጥ

የነበሩትን የጳውሎስንና የሲላስን ታሪክ አስታወሰ፤ ተደብድበው በእስር ቤት ውስጥ ሆነው እንኳ እግዚአብሔርን በዝማሬ ያመሰግኑ ነበር፡፡ ፈንቶ መዝሙር መዘመር እንዳለበት አልተሰማውም!

በልቡ ውስጥም እንዲህ የሚል ጥያቄ መጣበት፣ ‹‹እዚህ እንድትገባ ያደረገው ማን ነው?›› ደርግ፣ የኮምዩኒስት መንግሥት፣ የአጎቱ ልጅ፣ ሕዝቡ፣ በሐሰት የከሰሱት አምስቱ ጓደኞቹ! የሚሉ ሐሳቦች በፍጥነት ወደ አእምሮው መጡበት፡፡ በደረሰበት ነገር፣ ኢ-ፍትሐዊነት፣ ትክክል ያልሆነ ሥራና የአምስቱ ወዳጆቹ ክሕደት ተቈጣጥሮት ቂም ያዘ፡፡ ይህ እጅግ በጣም ጐዳው! ለምን?

በሚቀጥለውም ምሽት፣ ለመጸለይና ቅሬታውን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ጥረት ለማድረግ ሲነሣ፣ ተመሳሳይ ጥያቄ ወደ አእምሮው እንዲህ ሲል መጣ፣ ‹‹እዚህ እንድትገባ ያደረገው ማን ነው?›› እንደገና ፈንቶ የኮምዩኒስት ባለ ሥልጣናት፣ የለውጥ ኃይላት፣ ሕዝቡ እና ሐሰተኞች ወዳጆቹ መሆናቸውን አሰበ፡፡ ለዚህ ነገር ሁሉ ሁሉም ተጠያቂዎች ነበሩ!

እንደገና በሦስተኛው ምሽትም ተመሳሳይ ጥያቄ ወደ ልቡ መጣ፡፡ ከዚያም በሰማይ ያለው አባቱ እግዚአብሔር ክፉ ሰዎችን ለመጥቀም፣ መሆን በሚገባው ስፍራ ላይ እንዲሆን እንዳደረገው ተረዳ፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው እርሱ ወደዚያ ስፍራ ይመጣ ዘንድ ነበር፡፡ ጌታ በዚያ ስፍራ ይሆን ዘንድ አስቀምጦታል! ‹‹የጌታ እስረኛ›› እንዲሆን መላኩን ፈንቶ መመልከት ቻለ፡፡ ጥልቅ የሆነ ሰላም ልቡንና አእምሮውን ሞላው፤ ፍጹም አዲስ የሆነ አመለካከትና ደስታ አነቃቃው! ከዚያ ምን ሊሆን እንደሚችል መጠባበቅ ጀመረ!

ምንም እንኳ ፈንቶ የክርስቲያን ማኅበረ ምእመኑን ቢያጣም፣ በእስር ላይ ያሉ በመቶዎች የሚቈጠሩ ክርስቲያን ያልሆኑ አድማጮች እንዳሉት ተገነዘበ! አቢራማ በሆነው ሜዳ ላይ በተሠሩ ጎጆዎች ውስጥ በሺህ የሚቈጠሩ እስረኞች አሉ፡፡ ወህኒ ቤቱ በረጅም አጥር የታጠረ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ ማዕዘን ላይም ማማዎች ተሠርተው የወህኒ ቤቱ ጠባቂዎች ቆመውባቸዋል፡፡ በብረት የተሠራው በር አጠገብ የጠባቂዎቹ ቤት ተሠርቷል፤ ይህ የወህኒ ቤቱ ብቸኛ መግቢያና መውጫ ነበር!

ፈንቶ ስለ ጓደኞቹ ባሰበ ቍጥር፣ በፊት በእነርሱ ላይ የነበረው ቍጣ እና ቂም ቀስ በቀስ ወደ መከፋትና ማዘን በመለወጥ ምናልባት በሐሰት እርሱን

ይከስሱት ዘንድ ተጽዕኖ ተደርጎባቸው ሊሆን ይችላል ብሎ ማሰብ ጀመረ፡፡ በየዕለቱም የአምስቱን ጓደኞቹን ስም ተራ በተራ እየጠራ ይጸልይላቸዋል፤ ይህንንም በእስር ቤት በቆየባቸው አምስት ዓመታት በየቀኑ አድርጎታል፡፡

ፌንቶ በእስር ቤት ውስጥ ከእርሱ ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ስላሉት እስረኞችም መጸለይ ጀመረ፤ በጨለማ ውስጥ የጸሎት ስብሰባን ማድረግ ጀመረ፡፡ ለእስረኞቹም ስለ ኢየሱስ ሕይወት፣ ተአምራት እና ስለ ተፈረደበት ኢ-ፍትሐዊ ፍርድ፣ ሞቱ እና ክብር የተሞላው ትንሣኤው ነገራቸው፡፡ አንዳንድ ሰዎች አመኑ ወዲያውም ፌንቶ በቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ማጥናት እንዲጀምሩ አደረገ፡፡ ማለዳ ጠዋት ይነሣና በመሬት ላይ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በመጻፍ በቃላቸው እንዲያጠኑት ያደርጋል፡፡ ቀንም ሲሆን የቀኑጉን ትርጉም ያስተምራቸዋል፡፡ ኮምዩኒስት የሆኑት ጠባቂዎች ወደ እነርሱ ከቀረቡ፣ ፌንቶ በቀላሉ በእግሩ የጻፈውን ነገር ያጠፋና በኋላ ላይ መልሶ ይጽፈዋል፡፡

ፌኔቶ ወደ ሌላ ክፍል በመዘዋወር ከአንድ ክርስቲያን ጋር በአንድነት መጸለይ ጀመረ፡፡ ከዚያም ወደ ሦስተኛው ክፍል እያለ በክርስቶስ እናምናለን የሚሉ ክርስቲያኖች ሁሉ መጸለይ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እስኪጀምሩ ድረስ ከክፍል ወደ ክፍል ተዘዋወረ፡፡ በዓመታት ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች በአዳኙ አመኑ፤ ፌንቶም ከሚያውቀው በላይ በሥራ ተወጠረ፡፡ ያማከር፣ ያስተምርና ከአዳዲሶች ጋር ይጸልይ ነበር፡፡ እንዲሁም ለእነዚያ የሐሰት ጓደኞቹ በየዕለቱ መጸለዩን አላቋረጠም ነበር፡፡

የኮምዩኒስቱ መንግሥት መፈረካከስ ሲጀምርም፣ የፌንቶ የአምስት ዓመት የእስር ቅጣትም ተጠናቀቀ፡፡ በእያንዳንዱ እስር ቤት ውስጥ የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚመሩ ሰዎችን አሠለጠነ፡፡ ፌንቶ ‹‹በእስር ቤት ውስጥ ያለውን ማኅበረ ምእመኑን›› መተው አልፈለገም ነበር፡- ነገር ግን በመልካሙ እጅ ተዋቸው፡፡ ይህ መልካሙ እጅ የጌታ ነው፡፡

ፌንቶ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሲመለስ በጣም ብዙ ሰዎች እንኳን ለቤትህ አበቃህ በማለት ሞቅ ያለ አቀባበል አደረጉለት፡፡ የቤተ ክርስቲያን ንብረት ወድሟል፤ የክርስቲያኖች ቍጥር ግን በእጥፍ አድጎ አገኘው፡፡ ‹‹ጌታችን ምናልባት ትልቅ ቤተ ክርስቲያን እንድንሠራ ፈልጎ ይሆናል፣›› ሲል ተናገረ፡፡ ‹‹ነገር ግን ለአሁኑ

በመኖሪያ ቤታችን ውስጥ መገናኘታችንን እንቀጥል›› አላቸው::

ከጥቂት ቀናት በኋላም፣ ሁለት ሰዎች ወደ መኖሪያ ቤቱ በመምጣታቸው እጅግ ተገረመ:: ሰዎቹም በእግሩ ሥር ወድቀው ይቅር እንዲላቸው ለመኑት:: ጓደኞቹ ነበሩ:: በካድሬዎች ተጽዕኖ ሥር ሆነው ፌንቶን የለውጥ ተቃዋሚ አድርገው ከከሰሱት በኋላ፣ ጓደኞቹ በትልቅ ጥፋተኝነት እና ኀፍረት ሥር ሲኖሩ ቆይተዋል:: ከብዙ ጊዜ በፊት ይቅር እንዳላቸው ፌንቶ ነገራቸው:: በየዕለቱም ኃጢአታቸውን ተናዝዘው በኢየሱስ ያምኑ ዘንድ ይጸልይላቸው እንደ ነበር ነገራቸው:: ሰዎቹንም ከእግሩ ሥር አንሥቶ አቀፋቸውና ጉንጫቸው ላይ ሳማቸው:: በሣር ወደ ተሠራ ቤቱ ውስጥም እንዲገቡ በማድረግ የገዛ ወንድሞቹ ለባርነት የሸጡትን የዮሴፍን ታሪክ አጫወታቸቸው:: ዮሴፍ ወንድሞቹን ይቅር ብሎዋቸዋል:: እግዚአብሔር እነርሱንና መላ ቤተሰቡን ከረሃብ ለመታደግ ዮሴፍን ተጠቅሞበታል:: የዮሴፍ ወንድሞች ያንን ያደረጉት በክፋት ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ግን ለበጎ ነገር አደረገው::

‹‹እንደዚሁም፣ እግዚአብሔር በዚያ የእኔን ደኅንነት ጠብቆ ለአዳኙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብዙዎችን ማምጣት እንድችል ረድቶኛል:: ሁሉም ኃጢአታችሁ እንዴት ይቅር ሊባል እንደሚችልና እንዴት ፍጹም አዲስ ሕይወት (ዘላለማዊ ሕይወትና ሰላም) ሊኖራችሁ እንደሚችል እንደገና እነግራችኋለሁ:: ኢየሱስ ብቸኛው መንገድ ነው፣›› በማለት ፌንቶ ለሰዎቹ ነገራቸው:: ቀኑን ሙሉ ከእነርሱ ጋር ሲያወራ ቆየ፣ ሁለቱንም በክርስቶስ እንዲያምኑ አደረገ!

‹‹እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው።››

ዘፍጥረት 50:20

23

አልቋጠ

በሶሪ ውስጥ ያለ ምሥጢር

አትፍራ፡፡ ይህ ምሥጢራዊ ስብሰባ ነው፡፡ በጣም ጥቂት ሰዎች- ከሶሪና ከቦሎሶ የመጡ መሪዎች ብቻ የሚገኙበት፣ በአጠቃላይ ወደ መቶ የሚጠጉ ሰዎች የነበሩበት ስብሰባ ነው›› በማለት አልዳቦ አረጋገጠልኝ፡፡ ‹‹በጊዜ ከተነሣንና በጨለማ ከተጓዝን፣ ጠዋት ማለዳ ፀሐይ ገና ሳትወጣ እዚያ እንደርሳለን፡፡ ካድሬዎቹም ስለ እኛ መምጣት አይሰሙም፡፡ በመጣንበት መንገድ በጨለማ እንመለሳለን›› አለኝ፡፡ እኔ እና ባለቤቴ ቪዳ ለብዙ ዓመታት ጌታን ወደ አገለገልንበት ወደ ወላይታ ጐበኝ ሆኜ ተመልሼ ነበር፡፡

በተለመደው ደስታ በተሞላ ፊት፣ መጋቢ/ወንጌላዊ አልዳቦ ከሶሪ ከሁለት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ሊጠይቀኝ መጣ፡፡ ሶሪ ከወላይታ ሜዳዎች የሁለት ሰዓት ጉዞ ያህል ርቃ የምትገኝ መንደር ናት፡፡ ወደዚያ ስፍራ ሄጀ በዚያን ሰዓት በእምነታቸው ምክንያት ወደ እስር ቤት ላልገቡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንድሰብክ ይፈልጋሉ፡፡ ጨካኝ በሆነው የኮምዩኒስቶች አገዛዝ ሥር ብዙ መከራን ተቀብለዋል፡፡ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች ተዘግተዋል ወይም ወድመዋል፣ አብዛኞቹ መጋቢዎች ታስረዋል፤ ይህ ጓደኛችን ፊኔቶንም ያካትታል፡፡ ነገር ግን ስብሰባው የታቀደው በፊንቶ መንደር ውስጥ ነበር፡፡ በቀደሙት ዓመታት፣ በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ለመስበክ ብዙ ጊዜ ተጉዘናል፡፡ ‹‹የሁለት መቶ ሰዎች ትንሽ ስብሰባ›› ማዘጋጀት እንኳ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ስብሰባ መደረጉን ለኮምዩኒስት ባለ ሥልጣናት ለመናገር ፈቃደኞች የሆኑ እጅግ በጣም ብዙ ሰላዮች አሉ፡፡

ደረቅ በሆነ ጊዜ እንኳ ለመጓዝ አስቸጋሪ የሆነ ቦታ ነበር፤ ስብሰባው

የተዘጋጀበት ጊዜ ደግሞ የክረምት ወራት በመሆኑ፣ ለመጓዝ በጣም አስቸጋሪ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ጊዜው ‹‹ቀይ ሽብር›› የተፋፋመበትና ‹‹የባህል አብዮት›› ተብሎ የሚጠራ የማርክሲዝም/ሌኒኒዝም አገዛዝ በኢትዮጵያ ውስጥ በመንሰራፋት፣ ሁሉንም ተቃውሞዎች ለማጥፋት ጥረት የሚደረግበት ጊዜ ነበር። ሀብታሞች፣ ባለ ርስቶች፣ ነጋዴዎች፣ የተማሩና ኃያላን የተባሉ ሰዎች ትዝረት ውስጥ የገቡበት ወቅት ነበር። ንብረቱን ‹‹ለመልቀቅ›› ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም ሰው ይገደል ነበር። ጨካኝ የሆኑ የኮምዩኒስት ካድሬዎች፣ ፖሊሶችና የመንግሥት ባለ ሥልጣናት አዲሱን ርዕዮተ ዓለም በግዴታ በሰው ላይ ይጭኑ፣ ገበሬዎችንም በጎብረት ሥራ ማኅበር በማደራጀት በጋራ እንዲያርሱ ያስገድዱ ነበር።

በአንድነት ጸልየን፣ አደጋ ሊኖረው ቢችልም፣ ለዚህ ዋጋ መክፈል የሚገባ መሆኑን ወሰንን። ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ተነሥተን በዝምታ፣ እርስ በርሳችን አንዳች ነገር ሳንነጋገር በሶዶ ከተማ ጀርባ ባለ መንገድ ላይ መጓዝ ጀመርን። መኖሪያ ቤቶቹን አንድ ጊዜ ካለፍን በኋላ፣ አንድ ያረጀ መኪና ይጠብቀን ነበር። መብራት ሳያበራና በብዙ ጭቃማ ጉድጓዶች ውስጥ፣ በሶሪ ሜዳዎች ላይ ይጓዝ ጀመረ። መኪናውን በጫካ ውስጥ ደብቀን ካቆምን በኋላ፣ ለተጨማሪ አንድ ሰዓት ያህል ወደ ስብሰባው ቦታ በፍጥነት ተጓዝን። ቡና ተፈልቶ ወደ ተዘጋጀበት አንድ ቤት ውስጥ እንድንገባ ተደረገና የበቆሎ ንፍሮ ቀረበልን። ከቀሩርስ በኋላ አልዳቦ ሲጸልይልን ሳለ ሰዎች ከተለያየ ቦታ መጥተው በዛፍ ሥር እየተሰበሰቡ መሆኑን ሰማን።

ንጋት ላይ ስብሰባው ሲጀመር፣ ቦታው በሰዎች ተሞላ። ወዲያውም 6000 ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑ ሰዎች ተሰበሰቡ! አልዳቦ ራሱ ተገረመ! በኢትዮጵያ ውስጥ ምሥጢርን መጠበቅ በጣም አስቸጋሪ ነው! ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብቻ የታሰበው ስብሰባ የተለመደው ዓይነት ስብሰባ ሆነ! የሕዝቡ ደስታ በጣም የሚገርም ነበር። ለአምልኮ፣ ለዝማሬ፣ በአንድነት ለመጸለይና የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ዋጋ ቢከፈልበት እንኳ የሚቆጭ አይደለም። ያ ቀን ትልቅ የአምልኮ ቀን ነበር። አልዳቦና እኔ ሁለታችንም ሁለት ሁለት መልእክቶችን አቀረብን፣ ሕዝቡም ለእግዚአብሔር ቃል ምላሽ ሰጠ። ጥቂቶች ኢየሱስን እንደ አዳኛቸው አድርገው ለመቀበል ወሰኑ፣ አልዳቦም በንስሐ ጸሎት መራቸው።

ምንም እንኳ ከባድ ዳመና ቀኑን ሙሉ በሰማይ ላይ ቢታይም፣ ቀኑን በሙሉ ግን ደረቅ ሆኖ ዋለ! ወደ አመሻሽ ላይ ግን፣ ሰማዩ ይበልጥ እየጠቆረ መጣ። ትልቅ ማዕበል ሊመጣ መሆኑን ሁሉም ሰው አወቀ። አልዳቦ ስብሰባውን በጸሎት በመዝጋት ክርስቲያኖች ወደ መኖሪያ ቤታቸው እንዲሄዱና ያገኙትን ደስታ ለቤተሰቦቻቸው እንዲያካፍሉ ነገራቸው። ኢትዮጵያውያን ወዳጆቻችንን ባርከን ሸኘናቸው፣ *‹‹ጌታ ይባርካችሁ ይጠብቃችሁም። ጌታ ፊቱን ያብራላችሁ ይራራላችሁ። ሰላምም ይስጣችሁ።››* ከዚያ ሕዝቡ በየአቅጣጫው በፍጥነት ተበተነ። ከብበውን የቆሙትን ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እየጨበጥንና እያቀፍን እንደምንጸልይላቸው ቃል ገባን።

ከዚያ ዝናብ መዝነብ ጀመረ! ቀጣይነት ያለው ነጎድጓድና መብረቅ በሰማይ ላይ ይታይ ጀመር። የዝናብ ዶፍ ይወርድ ጀመር። ወደ ወዳጆቻን ፈንቶ ጎጆ እየሮጥን ገባን። ለአንድ ሰዓት ያክል ከባድ ዝናብ ዘነበ፣ ጐርፉ አካባቢውን ሁሉ በማጽዳቱ የተነሣ ሰዎች መሰብሰባቸውን የሚያመለክት ምንም ነገር በስፍራው አይታይም ነበር። ዝናቡ እስኪያባራ ለአንድ ሰዓት ያክል መጠበቅ ነበረብን፤ ከዚያም ቀስ በቀስ እያቆመ ሄደ። ትኩስ ምግብ ቀርቦልን እየተመገብን ስለ ፈንቶ መታሠር፣ ካድሬዎችን ስለሚመራው የፈንቶ የወንድሙ ልጅ እንዲሁም በመላው ኢትዮጵያ መከራን እየተቀበሉ ስላሉ ክርስቲያኖች አወራን። ለሁሉም ጸለይንላቸው።

ከውጭ አንድ ሰው ሲስል ስንሰማ ዝናቡ አቁሞ ነበር። ጸጉሩ የሸበተና ረጅም ነጭ ጺም ያለው አንድ ሰው ራሱን ከዝናብ ለመከላከል የሙዝ ቅጠል በራሱ ላይ ይዞ ቆሟል። ወደ ቤት እንዲገባና ቡና ከእኛ ጋር እንዲጠጣ ተጋበዘ። ሰውዬውን አላውቀውም። አልዳቦ ወይም በቤት ውስጥ ካሉት የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች መካከል ሰውዬውን የሚያውቅ ማንም አልነበረም። ከየት እንደ መጣ ማንም ሰው አያውቅም።

የቡና ግብዣውን አልተቀበለም፣ ነገር ግን እንዲህ ሲል ተናገረ፣ ‹‹እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን፤ ከእናንተ ጋር ብዙ መቆየት አልችልም፤ ለአቶ ማክሌላን ጌታ ምሥጢራዊ መልእክት አስይዞ ነው የሰደደኝ›› በማለት ተናግሮ ካበቃ በኋላ፣ በቀስታ ወደ ጆሮዬ ተጠግቶ እንዲህ አለኝ፣ ‹‹እኔ ማንበብ አልችልም፣ ስለዚህ መልእክቱ ምን እንደ ሆነ አላውቅም፣ ነገር ግን ጳውሎስ

ለፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው መልእክት ውስጥ፣ ምዕራፍ አንድ ቍጥር ሃያ ዘጠኝ ላይ ይገኛል፣›› ብሎኝ አንገቱን ዝቅ አድርጎ ተሰናብቶን ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ገብቶ ተሠወረ።።

አንድ ወጣት ልጅ እየሮጠ፣ ‹‹ጠላቶቻችን እየመጡ ነው፣›› ብሎ በታላቅ ድምፅ ስለ ጮኸ የማነብበት ምንም ጊዜ አልነበረኝም።። የኮምዩኒስት ካድሬዎች ስለ ስብሰባው ሰምተዋል፣ ነገር ግን በኃይለኛ ዝናብ ምክንያት በጊዜው መድረስ አልቻሉም።። ይህም ሁሉንም ሰዎች እንዲያመልጡ አድርጓል።። ስለዚህም እኛም በፍጥነት መሄድ አለብን።። በጠባብ መንገድ በመኖሪያ ቤቶቹ መካከል በጭቃ ውስጥ እየተንሸራተትንና እየተሸለኮለክን በጫካ ውስጥ ተደብቃ ወደ ቆመችው መኪና ደረስን።። መኪናዋ በጭቃ በተበላሸው መንገድ ላይ እየተጓዘች የከተማው ዳር ለመድረስ አንድ ሰዓት ያህል ፈጀባት።። በጨለማ ውስጥ በጭቃ በተጨማለቀው መንገድ ላይ በዝምታ ተጉዘን ጠዋት ትተነው ወደ ሄድነው ቦታ ተመለስን።።

እኔ እና አልዳቦ ሻይ እየጠጣን ሽማግሌው ሰውዬ ያመጣውን መልእክት ለማንበብ ተቀመጥን።። አነበብነው፣ እንዲህ ይላል፣ ‹‹ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም።።›› እርስ በርሳችን ተያየን።። አልዳቦ ለወደፊት ብዙ አደጋዎች፣ ብዙ ጊዜ መያዝ፣ ድብደባዎች እና መታሠር ይጠብቀዋል።። በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ መከራን ለሚቀበሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ብዙ ሽክም በልቤ ውስጥ አለ፣ እንዲሁም ለራሴም ብዙ መከራዎች አሉብኝ።። በአንድነትም መዝሙር 27፡5 አነበብን፣ ‹‹በመከራዬ ቀን በድንኳኑ ሰውሮኛልና፣ በድንኳኑም መሸሸጊያ ሸሽጎኛልና፣ በዓለት ላይ ከፍ ከፍ አድርጎኛልና›› ይላል።። ለእርሱና ለጠራን አገልግሎት ታማኞች ሆነን መቆየት እንድንችል እግዚአብሔር ይረዳን ዘንድ ጸለይን።።

ከዓመታት በኋላ፣ ወደ ኢትዮጵያ ለአገልግሎት ሄጄ ሳለ፣ እኔና አልዳቦ በሶሪ ስብሰባ ላይ ቃል እንድናካፈል ተጋበዝን።። አስጨናቂው የኮምዩኒስቶች የለውጥ ጊዜ አብቅቷል።። ፌንቶ ከእስር ቤት ከወጣ ጥቂት ዓመታትን አስቆጥሯል።።

ከፈንቶ ጋር በመኖሪያ ቤቱ ተቀምጠን በሚጠብቀንና በሚንከባከበን የእግዚአብሔር ጸጋ ሐሤት እናደርግ ነበር። ፈንቶ በእስር ቤት ውስጥ ስለ ነበረው አገልግሎት እና በዚያ ስላገኘው በረከት አጫወተኝ። የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ በመፍረሱ ምክንያት ምን ያህል አዝኖ እንደ ነበረና ነገር ግን እግዚአብሔር ከዚያ የሚበልጥ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን እንዲገነቡ መፈለጉን እንደ ተረዳ አጫወተኝ። ያንን ትልቅ ቤተ ክርስቲያንም ገነቡ፣ ቤተ ክርስቲያኑ አሁን በሰዎች ተጨናንቋል። አሁን ከመንደራቸው ትንሽ ራቅ ብሎ በሚገኝ መንደር ውስጥ አዲስ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመር በጸሎት ላይ ናቸው።

ፈንቶ በወህኒ ቤት ውስጥ ሳለ፣ መኪና ተከራይቼ ከሶሪ አልፎ ወዳለው፣ በቦሎሶ ውስጥ የሚገኘውን የአጆራ ቈቈቴን ለማስጐብኘት ጐብኝዎችን ይገፎ መሄዴን ነገርኩት። ባለፉት ጊዜያት እኔ እና ቪዳ ከጐበኝዎች ጋር ብዙ ጊዜ ወደዚያ ተጉዘናል። ያን ዕለት በመጓዝ ላይ ሳለን፣ በቈቈቴው ስፍራ በመቶዎች ቤት የሚቈጠሩ ክርስቲያኖች ተገኝተው እንደ ነበር ነገርኩት። ከቈቈቴው ተነሥተን መኪናችንን እያሽከረከርን ሶሪን በማለፍ ላይ ሳለን፣ ብዙ ሰዎች አንድ ቤተ ክርስቲያንን ሲያፈርሱ ተመለከትን። ቤተ ክርስቲያኑ በመንገድ ዳር ነበር የሚገኘው። ስለዚህም የመኪናውን ሞተር አጠፋሁና መኪናውን አቆምኩ፤ ኮፈኑን ከፍቼ ሞተሩን የሚሠራ ሰው በመምሰል ሰዎቹ ቤተ ክርስቲያንን ሲያፈርሱ ፎቶግራፍን ለማንሣት ቻልኩ።

ጣፋጭ የሆነ ቡና በቅቤ እየጠጣን፣ ፈንቶ እንዴት ሁለቱ ጓደኞቹ አልቅሰው ይቅርታ እንደ ጠየቁትና ሰይጣንን በመካድና ክርስቶስ ወደ መቀበል እንደ መራቸው አጫወተኝ። ሁለቱም ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳሉ ነገረኝ። ከሳምንት በኋላም ሦስተኛው ወዳጁ ይቅርታ ለመጠየቅ ወደ ፈንቶ መጣ። እርሱም አሁን በክርስቶስ አምኗል! ከወር በኋላም አራተኛው ወዳጁ በጎፍረት ልቅሶ እና ጸጸት ወደ እርሱ መጣ። ለእርሱም እውነተኛ ንስሐና ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም መሆን የሚቻልበትን መንገድ አስረዳው፣ ወዳጁም ኢየሱስን አዳኙ አድርጎ ተቀበለ! እግዚአብሔርን ስለ ጸጋውና ምሕረቱ ምን ያህል ልናመሰግነው ይገባል!

እዚያ ተቀምጠን ሳለ፣ በጣም ብዙ ሕዝብ የመጀመሪያውን ስብሰባ ለመካፈል በተከፈተው በር በኩል እያለፈ ከተሰበሰበው ሕዝብ ጋር ተቀላቀለ። ፈንቶ ከሕዝቡ መካከል አንድን ሰው ተመልክቶ ከመቀመጫው ተስፈንጥሮ

በመኑሣት ‹‹ይኼውና›› በማለት ተናገረ፡፡ ወደ ውጭም ሄዶ ከሰውዬው ጋር ሰላምታ ተለዋወጠ፡፡ ሰውዬውንም እጁን ይዞ ወደ ቤት አመጣው፡፡

ፌንቶ በደስታ ራሱን አያውቅም ነበር! ‹‹ይኼ እርሱ ነው!›› አለኝ፡፡ ይህ አምስተኛው ነው! ትናንትና ልክ እንደ ሌሎቹ ከእኔ ጋር ለመታረቅ መጣ፡፡ ወንጌልንም ሰምቶ ኃጢአቱን ተናዘዘ፡፡ እርሱ አሁን ጓደኛዬ ብቻ ሳይሆን፣ በክርስቶስ ወንድሜ ነው›› አለኝ፡፡

‹‹ወንድሞች ሆይ፣ ይህ የደረሰብኝ በእውነት ወንጌልን ለማሰፋት እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ፡፡››

ፊልጵስዩስ 1፡12

24

ክሮታ

ግራ እጅ

ካሮታ በጣም ትንሽ ልጅ ሳለ፣ በመኖሪያ ቤት ውስጥ ወጣ ገባ በሆነ ወለል ላይ መራመድ እየተለማመደ ደፍ ደፍ ሲል ወለሉ ላይ በነበረው እሳት ላይ ወደቀ፡፡ እናቱ ጀርባዋን ሰጥታው ሥራ እየሠራች ነበር፡፡ በሸክላ ድስቱ ውስጥ ውኃ እየጨመረች ምግብ በማብሰል ላይ ሳለች፣ ልጇ መራራ ለቅሶ ሲያለቅስ ሰማች፡፡ በቅጽበትም ልጇን ከእሳት ውስጥ መንጭቃ በማውጣት በልብሱ ላይ ያለውን እሳት አራገፈችለት፡፡ ምንም እንኳ ካሮታ ከእሳቱ የተረፈ ቢሆንም፣ አደጋው በግራ እጁ በኩል ጀርባው ላይ አስቀያሚ ጠባሳ ትቶ አለፈ፡፡ አሁን በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ይህን ጠባሳ ተሸክሞ ይኖራል፡፡

ሁሉም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከገበሬ ማኅበረሰብ ወጥተው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደሚገኙበት ትልልቅ ከተማዎች በመሄዳቸው፣ በቤተሰብ ሕይወት ላይ ትልቅ ችግር ፈጠረ፡፡ አንዳንዶቹ በሳምንቱ የዕረፍት ቀናት ወደ መንደራቸው የሚመለሱ ቢሆኑም፣ አብዛኞቹ ግን በከተማ ውስጥ የሚገኘውን ደስታ ለማጣጣም በዚያው ቀሩ፡፡ ብዙ ወጣቶች በደረሱበት የትምህርት ደረጃ የሚኩራሩና አሁን በእጃቸው የመሥራቱን ደረጃ እንዳለፉት ያስባሉ፡፡ የሚፈልጉት ማስተዳደር፣ ማስተማር፣ መነገድ ወይም በቢሮ ውስጥ መሥራት ብቻ ነበር፡፡ ነገር ግን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ላጠናቀቁ ጥቂት ተማሪዎች ብቻ ሥራ በመኖሩ ምክንያት ወንጀል፣ ዐመፅና አለመረጋጋት እየተባባሰ ሄደ፡፡

ወታደሩ በመፈንቅለ መንግሥት የኮምዩኒስት መንግሥት አቋቁሞ ሥልጣን እስከ ያዘበት ጊዜ ድረስ ለብዙ ዓመታት በየቀኑ ወሬ፣ ውሸትና የተሳሳተ መረጃ፣ አለመረጋጋት፣ ሽብር እና ግራ መጋባት ነበር፡፡ ይህ አለመረጋጋት በመላው

ሀገሪቱ ውስጥ ተንሠራፋ፡፡ የዩኒቨርሲቲና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሰልፍ ወጡ፤ ባንዲራ እያውለበለቡ መንግሥት ለውጥ እንዲያደረግ መፈክሮችን እያሰሙ፣ የመሬት ለውጥ፣ የጉቦ እና የተበላሸ ሥልጣን እንዲሁም ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ጠየቁ፡፡ የማርክሲዝምን ርዕዮተ ዓለም ከሚያራምዱ ሰዎች የሚሰራጨው ፕሮፖጋንዳ አለመረጋጋቱን አባባሰው፡፡

ለውጡ በፍጥነት ባለመከሰቱ ምክንያት፣ ተቃዋሚዎቹ ተቃውሞአቸውን በሰላማዊ ሰልፍ ገለጡት፣ ሰላማዊ ሰልፉም ወደ ረብሻ ተለወጠ፡፡ በሁሉም ስፍራዎች ተማሪዎቹ ከተቃዋሚዎቹ ጎራ ቆሙ፡፡ ከዚያም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችና የሚሰጡን ትምህርት ቤት ተማሪዎችም በእንቅስቃሴው ውስጥ ተሳትፎ እንዲያደረጉ ተገደዱ፡፡ በሀገሪቱ ውስጥ ወሬና የተሳሳተ መረጃ እንደ ሰደድ እሳት በመዛመቱ ምክንያት፣ ክርስቲያን ወላጆች ምን ማመን እንዳለባቸው ግራ ገባቸው፡፡ ስለ ልጆቻቸው ደኅንነት ጨነቃቸው፡፡ ሁሉም ትምህርት ቤቶች በመዘጋታቸውና አለመረጋጋቱ እየሰፋ በመሄዱ ምክንያት፣ ብዙ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤት ወሰዷቸው፡፡

ካሮታ በሶዶ ከተማ ውስጥ በመቆየት እያደገ በመጣውና ዐመፅ በተሞላበት መንግሥት ላይ በሚደረገው ተቃውሞ ተቀላቀለ፡፡ በወላይታ አደባባዮች ላይ በሚደረገው ዐመፅ ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሰዎችን ከሚመሩት ሰዎች መካከል አንዱ ሆነ፡፡ የአካባቢው ፖሊስ ሁኔታው ከቁጥጥሩ በላይ በመሆኑ ምክንያት ከአዲስ አበባ የአድማ-በታኝ ፖሊስ እንዲመጣ ጥሪ አስተላለፈ፡፡ ነገር ግን በመላው ሀገሪቱ ውስጥ የኢኮኖሚ አለመረጋጋት፣ ሰላማዊ ሰልፍ እና ዐመፅ እየተቀጣጠለ ስለ ነበር ለውጥ ተጠነሰሰ፡፡ ከዋናዋ ከተማም የኮምዩኒስት ፕሮፖጋንዳ ሰላማዊ ሀገርን የመመሥረት የተሰፋ ቃል ይናፈስ ጀመር፡፡ ወጣቶች ብዙ ሰዎችን እንዴት በማርክሲዝም ርዕዮተ ዓለም ማጥመቅ እንደሚቻል ሥልጠና ወሰዱ፡፡

በሰሜን ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ራብ ተከሰተ፣ ነገር ግን ንፉግ የሆኑ የአካባቢው አስተዳዳሪዎች ለብዙ ወራት መሬታቸውን፣ እንስሶቻቸውን፣ መኖሪያ ቤታቸውንና ነገራቸውን ሁሉ ያጡትን የገበሬዎች ችግር ደበቁ፡፡ የችግሩ መጠን ምን ያህል መሆኑ በታወቀበት ጊዜ፣ በመቶና በሺህ የሚቈጠሩ ሰዎች ለሞት በሚያበቃ ራብ ውስጥ ነበሩ፡፡ የዓለም አቀፉም ማኅበረሰብ የሁኔታውን አሳሳቢነት አወቀ፡፡ ሁሉም ሰው ሁኔታውን ባለማሳወቃቸውና የእርዳታ ጥሪ ባለማስተላለፋቸው ምክንያት ንጉሠ ነገሥቱን ኰነናቸው፡፡ ነገር ግን ንጉሠ

ነገሥቱ ነገሩን ያወቁት ከዘገየ በኋላ ነበር።።

ከዚያም ወታደሩ፣ ፖሊስና የደኅንነት ኃይላት መፈንቅለ መንግሥት በማድረግ ሀገሪቱን ተቈጣጠሩ።። የንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ፈረሰ፤ እርሳቸውና ቤተሰቦቻቸው ታሰሩ፤ አብዛኞቹ የካቢኔ አባላት ተገደሉ ወይም ወደ ወህኒ ተጣሉ።። ንጉሠ ነገሥቱም ተገደሉ።። ማምለጥ የቻለ የመንግሥት ባለ ሥልጣን ሀገሩን ትቶ ተሰደደ።። በሁሉም ስፍራ ሰላዮች ነበሩ፤ ማንም ማንን ማመን እንዳለበት ማወቅ ተሳነው።።

ካሮታ አዲሱን ርዕዮተ ዓለም በግድ በወላይታ ሕዝብ ላይ ይጭኑ ከነበሩ የካድሬ መሪዎች መካከል አንዱ ነበር።። ቀኑ የተጀመረው በማለዳ የኮምዩኒስቶችን መፈክር በታላቅ ድምፅ እየተባለ በሚደረግ ሰልፍ ነበር።። ሀብታም ባለ ሱቆችን፣ ነጋዴዎችን እና ባለ ርስቶችን ዒላማ ያደረገ ሀብታቸውን ‹‹ለሕዝቡ ነፃ ማድረግ›› የሚል መፈክር ነበር።። ይህንን የተቃወመ ማንኛውም ሰው ይገደል ነበር።። የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች ተራ በተራ እንዲፈርሱ ተደረገ ወይም አንዳንዶቹ ‹‹መሰብሰቢያ›› ኡዳራሻ እንዲሆኑ ተወረሱ።። መጋቢያንና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በወህኒ ቤት ውስጥ ተጣሉ።። ከአራት ሰው በላይ ሆኖ መሰብሰብ የተከለከለ ሆነ።።

ከካድሬዎች ጋር ሆኖ ካሮታ ወደ አጎቱ ፌንቶ ቤተ ክርስቲያን የእሑድ የአምልኮ ፕሮግራም እየተካሄደ ሳለ ደረሰ።። ከዚያ ቀን በፊት ባለው ሌሊቱን ሙሉ ሲጠጡ ያደሩ በመሆኑ፣ በጥሩ ስሜት ውስጥ አልነበሩም።። ከገበያ ስፍራ ሰዎች ጥቂት ገንዘብ እንደሚሰጧቸው ቃል በመግባት ይዘዋቸው መጡ።። መፈክራቸውን በታላቅ ድምፅ እያሰሙ ቤተ ክርስቲያኒቷን ከበቧት።። ካሮታ እና ብዙ የታጠቁ ፖሊሶች እንዲሁም ካድሬዎች በመሆን በሕዝቡ ውስጥ አልፈው ወደ መድረኩ አመሩ።። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ከመድረክ ላይ ገፍትረው አወረዷቸው።።

ፌንቶ የወንድሙ ልጅ እንዲህ በማድረጉ እጅግ ተገረመ።። ፌንቶ ብዙ ጊዜ ካሮታን ከኃጢአቱ ይመለስና በክርስቶስ ያምን ዘንድ ይመክረው ነበር።። የከተማ ሁካታን ትቶ ወደ መንደሩ ይመለስ ዘንድም ይገፋፋው ነበር።። በሚቀጥለውም ቀን ፌንቶ የሕዝብ ሽንጎን ለመጋፈጥ ሄደ።። ካሮታ የተሰበሰበውን መባ ተመልክቶ ገንዘቡን ወደ ኪሱ ከተተው።። አንዱ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ፣ ‹‹የእግዚአብሔርን ገንዘብ አትውሰድ።። ከእግዚአብሔር ከሰረቅህ ትቀጣለህ፣››

ሲል ተናገረው።።

ካሮታ እየሳቀ፣ ‹‹አሁን ሁሉም ነገር የደርግ ነው፣›› አለ።። በሃይማኖት ላይ እየዛተ ረጅም ንግግር ማድረግ ጀመረ።። በንግግሩም መካከል የማርክሲዝምን መፈክር ደጋግሞ ይናገር ነበር።። በመደጋገም እጆቹን ወደ ላይ በማንሣት፣ ‹‹ከእንግዲህ ወዲያ ምንም ዓይነት የአምልኮ ፕሮግራም በዚህ ስፍራ አይካሄድም።። ሁሉም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ማስረከብ አለበት፣›› አለ።። በጣም ጥቂት ሴቶች መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በቀሚሳቸው ውስጥ ሸሸጉ።። ነገር ግን ወዲያው መጽሐፍ ቅዱሶችና አዲስ ኪዳን መጻሕፍት መቀደድ ጀመሩ።። ካሮታ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሞቷል! እግዚአብሔር ሞቷል! የእናንተ ኢየሱስ ሞቷል! ሃይማኖት ሞቷል፣ አብቅቶለታል! የለውጥ ሕዝቦች ለዘላለም ይኑሩ!›› በማለት ደጋግሞ ይጮኽ ነበር።።

ክርስቲያኖችን አዲሱን መንገድ የማይከተሉ ከሆነ፣ ለወደፊት ቅጣት እንደሚጠብቃቸው ያስፈራሯቸው ነበር።። ሁሉንም ከአዳራሹ ሲያስወጧቸው፣ በአንዳንዶቹ ላይ ድብደባ ተፈጽሟል።። አንዳንድ የማያምኑ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን በመዝረፍ ሂደት ውስጥ ተሳትፈዋል።። በጣራው ላይ የነበሩት ወንዶች ቆርቆሮውን እየነቀሉ ለሌሎች ያስተላልፉ ነበር።። ሴቶች በር፣ መስኮትና መቀመጫዎችን በመውሰድ ያግዙ ነበር።። በጥቂት ሰዓታት ውስጥም የቤቱ ግድግዳ፣ የተበታተኑ የቀርከሻ እንጨቶችና የተቀደዱ እንዲሁም የተቃጠሉ መጽሐፍ ቅዱሶች ብቻ ቀሩ።።

ክርስቲያኖች ከመደንገጣቸው የተነሣ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እንኳ አላወቁም።። የጸሎትና የአምልኮ ስፍራቸው ፈርሷል፣ መጋቢያቸው ፈንቶ በሐሰት ተከስሷል፣ ስለዚህም እርሱን ማግኘት አይቻልም።። ይህ ሁሉ የሚያበቃው የት ላይ ነው? ነገር ግን በቀጣዩ ጥቂት ቀናት ሰዎች ከአስደንጋጩ ነገር ማገገምና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችም በፈንቶ ቤት ውስጥ ለመጸለይ ችለዋል።። ወዲያውም በጣም ብዙ ትንንሽ ቡድኖችን በማደራጀት በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ቡና አብረው በመጠጣት፣ በመጸለይ እና ኅብረት በማድረግ እርስ በርሳቸው እንዲደጋገፉ አደረጓቸው።።

ክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው ስደት ወራት እያለፉ በሄዱ ቍጥርም እየጨመረ ሄደ፤ ካሮታም አብዛኞቹን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ወደ ወህኒ ቤት ጨመራቸው።። በተመሳሳይ ጊዜም፣ ሌላ አስገራሚ ነገር ተከሰተ።። በጣም

ብዙ ወጣት ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመሥርተው አዳዲስ ዝማሬዎችን መጻፍና መዘመር ጀመሩ። አብዛኞቹ የራሳቸውን የሙዚቃ መሣሪያ ሠሩ። ሁለት ሁለት ሆነው ወይም በትንንሽ ቡድኖች በመሆን በሥርግ ስፍራዎች ላይ ወይም በዘመዶቻቸው ቤት ውስጥ ዝማሬያቸውን ያቀርቡ ጀመር። አንዳንዶቹ ትንሿን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ለመደበቅ ያመቻቸው ዘንድ በሙዚቃ መሣሪያቸው ውስጥ ትንንሽ ክፍሎችን ያዘጋጁ ነበር።

የማያምኑት ሰዎች ‹‹የኢየሱስ ሰዎች›› የሚባሉት የሚጠነቀቁ እንጂ፣ የማይፈሩ፣ ጠንቃቆች እንጂ፣ የማይደነግጡ መሆናቸውና በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥም እንደሚሰበሰቡ ተረዱ። ውድቅት ሌሊት ወይም ማለዳ በጠዋት አካባቢ ድምጻቸውን ቀንሰው ሲጸልዩ ወይም ሲያዜሙ ይሰሟቸው ነበር። የማያምኑ ሰዎች እንኳ የኮምዩኒስት ካድሬዎችን በሚፈሩበት ወቅት፣ እነዚህ ክርስቲያኖች እንዴት በእርጋታ ሊቀመጡ ቻሉ በማለት ይገረሙ ነበር። አንዳንዶቹ ክርስቲያኖች ወደ መኖሪያ ቤታቸው ቡና ለመጠጣት ይጋብዟቸው ነበር።

ፌንቶ በእስር ቤት ውስጥ ባሉ ሰዎች መካከል ጥሩ አገልግሎት በማገልገል ላይ ሳለ፣ የወንድሙ ልጅ ካሮታ በውጭ ያላችውን ቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት ጥረት ያደርግ ነበር። የእግዚአብሔር መንፈስ ደግሞ የራሱ ተራ ሕዝብን ለአገልግሎት ያስታጥቅ ነበር። በዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን አደገች! አዳዲስ ክርስቲያኖችን በአደባባይ ማጥመቅ ቀረ። ከተለያዩ ቀጣናዎች የመጡ አዳዲስ አማኞች በወንዝ ውስጥ በሚጠመቁበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቷ መጋቢ በጣም ጥቂት ሰዎችን-ስድስት ወይም ስምንት ወይም ኣሥር ሰዎችን-በአንድ ጊዜ በመውሰድ፣ በምሽት ወይም ጠዋት ሳይነጋ በወንዝ ውስጥ ያጠምቃቸው ነበር። ያ ካድሬዎች ከምሽቱ ስካራቸው የማይነቁበት ሰዓት በመሆኑ፣ ጥሩ ሰዓት ነበር። ብዙ ጊዜ ካድሬዎች እስከ እኩለ ቀን ድረስ በደንብ አይነቁም ነበር። በዚያ ወቅት መጋቢያቸው/ወንጌላዊው ፌንቶ በወህኒ ቤት ውስጥ የነበረ ሲሆን፣ ቤተ ክርስቲያንም በዚያ ወቅት በቀጥር በዕጥፍ አድጋ ነበር!

ካሮታ እና ካድሬዎቹ ሰዎችን በግዴታ የኮምዩኒስቶችን ርዕዮተ ዓለም መማርና መቀበል እንዳለባቸው ያስገድዱ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ‹‹የጎበረት እርሻ›› ማኅበር ውስጥ መታቀፍን ያስገድዱ ነበር፤ በእርግጥ ይህ ስኬታማ

አልሆነም፣ እንዲያውም በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የምግብ እጥረት እንዲከሰት አድርጎ ነበር። የካሮታ የመጠጥ ሱስ በጣም ከፍተኛ ደረጃ ላይ እየደረሰ መጣ፣ እንዲሁም ሰዎች የማርከሲዝምን ርዕዮተ ዓለም በዝምታ መቃወማቸው እየሰፋ በመጣ ቍጥር ይበልጥ ይበሳጭ ጀመር።

በመጀመሪያ የተለያዩ ሐሜቶች ተሰሙ፣ ከዚያም ካሮታ በታላላቅ ባለ ሥልጣናት ዘንድ ተከሰሰና ተጠራ። በሶሪ መንገድ ላይ በትልቅ ዛፍ ሥር ካለው የገበያ ቦታ መጠጥን እየጠጣ አመሸ። ሌሊቱም እየገፋ ሄደ። በገበያው ስፍራም በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ቀሩ። አንድ ሁለት የሚሆኑ ሴተኛ አዳሪዎችና ጥቂት የአካባቢው ሰዎች ብቻ ቀርተው ነበር። ካሮታ ፈጽሞ ሰክሮ ብቻውን በዚያ ስፍራ አደረ።

ካሮታ እየተንገዳገደ ብዙ ጊዜ ወደቀ፤ ብዙ ጅቦችም መጥተው አጠቁትና ገደሉት። ጅቦቹም በትልቅ ጥርሳቸው አካሉን ቦጫጭቀው፣ አጥንቱን ሰባብረው ምንም ሳያስቀሩ በሉት። በጨለማ ውስጥም የሚያስፈራው የጅቦች ጩኸት ይሰማ ነበር። ጠዋት ላይም በጣም ጥቂት ቍርጥራጭ ሥጋዎች፣ የተሰባበሩ ጥቂት አጥንቶቹ እና የግራ እግሩ ቍራጭ ብቻ ተገኙ። በእጁ ላይ ያለው ጠባሳ ሰዎች የተበላው ሰው ማን እንደ ሆነ መለየት እንዲችሉ አደረገ።

> *‹‹አትሳቱ፤ እግዚአብሔር ኣይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤ በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና፣ በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል።››*
>
> ገላትያ 6፡7፣ 8

25

ምዕራፍ

የወጎኒ ቤቱን ደጃፍ ከፈተ

የሌሊቱ ጸጥታ በድንገት ‹‹እንድገባ ፍቀዱልኝ! እንድገባ ፍቀዱልኝ!›› ብሎ በሚጮኽ የአንድ ሰው ድምፅ ደፈረሰ፡፡ ሰውዬው የወህኒ ቤቱን የብረት በር በዱላ እየደበደበ ይጮኻል፡፡ በመግቢያ በሩ ላይ የነበሩት ዘበኞች ነቅተው መሣሪያቸውን አነሡ፡፡ ምን እየተፈጠረ ነው? እስረኞች አምልጠው ነውን? ከዚያ ቀን በፊት እንዲህ ያለ ነገር ተከስቶ አያውቅም፡፡ ማን ሊሆን ይችላል?

‹‹አንተ ማን ነህ? የምትፈልገው ነገር ምንድን ነው?›› በማለት አንዱ ዘበኛ ድምፁን ከፍ አድርጎ ጠየቀው፡፡

‹‹እኔ ነኝ፡፡ በሩን ክፈቱልኝ፡፡ እንድገባ ፍቀዱልኝ!›› በማለት ውጭ የቆመው ሰውዬ መልስ ሰጠ፡፡

ዘበኞቹ የበሩን ቀዳዳ ከፍተው በሩን ሲከፍቱት አንድ ነጭ ጸጉር ያለው ምንም ያህል ጉዳት ማድረስ የማይችል ሽማግሌ ቆሞ አገኙ፡፡ ከዚያም መሣሪያቸውን ዝቅ በማድረግ እንዲገባ ፈቀዱለት፡፡

ወላይታ ውስጥ ካሉቱ በጣም ብዙ የእምነት ጀግኖች መካከል፣ ማለትም ስለ እምነታቸው ሲሉ የተሰደዱ፣ በመታሠር መከራን የተቀበሉ እና የተገረፉ፣ ነገር ግን ለጌታ ኢየሱስ ታማኝ ሆነው ከቆዩ ሰዎች መካከል እንደ ዋንዳሮ ስሙ ከሁሉ በላይ ገንኖ የሚወጣ ሰው የለም፡፡ የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮናውያን ኢ-አማኒ ወደ ሆነው አንዱ የወላይታ ጎሳ ወንጌልን ይዘው ሲመጡ እርሱ፣ በመጀመሪያ ምላሽ ከሰጡ ሰዎች መካከል አንዱ ነበር፡፡ ዋንዳሮ በሶዶ ውስጥ በሚገኘው ድፍርስ ገንዳ ውስጥ በታኅሣሥ ወር 1926 ዓ.ም ከተጠመቁ ከአሥራ

ስምንት ወንዶችና ሁለት ሴቶች መካከል አንዱ ነበር።

ሁምቦ ከሚባል አካባቢ በግብርና ይተዳደር የነበረው ዋንዳሮ፣ ከጅማሬው አንሥቶ የኢየሱስ ለመሆን ራሱን ‹‹አሳልፎ የሰጠ ሰው›› ነበር። ያለምንም ፍርሃት ለሚያውቃቸውና ለሚያገኛቸው ሰዎች ሁሉ ስለ ኢየሱስ ይመሰክራል። ሰዎች ኃጢአታቸውን ይናዘዙና ከሚመጣው ቅጣት ያመልጡ ዘንድ ይጐተጕታቸዋል። ወዲያውም ከቤተሰቦቹ አብዛኞቹና ጎረቤቶቹ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር ይከተሉት ጀመር።

ዋንዳሮ የአካባቢው አስተዳዳሪ ወደ ሆነው ወደ ዳና መጃ በመሄድ ስለ አዳኙና ኃጢአታቸውን ተናዝዘው የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ የማያምኑ ሰዎች ስለሚጠብቃቸው የእሳት ቅጣት ነገረው። በሲኦል ያለው ‹‹የእግዚአብሔር እሳት›› ከምድር በታች ካለው እሳተ ገሞራ ጋር ፈጽሞ እንደማይነጻጸር ገለጸለት። ትዕቢተኛው የአካባቢው አስተዳዳሪ ግን ብዙ አሽከሮችና አገልጋዮች ያሉትና በብዙ ሰዎች የሚፈራ ሰው ስለ ነበር፣ የዚህን የተራ ገበሬ ማስጠንቀቂያ ንግግር ለመስማት አልፈለገም።

ከሌሎች ሰዎች በተለየ መልኩ አስተዳዳሪውን በቀረበ ጊዜ፣ ዋንዳሮ በጥቂቱ ደንግጦ ሊሆን ቢችልም፣ ምንም ዓይነት ፍርሃት አልተሰማውም፣ እንዲሁም አልተደናበረም ነበር። ከኃጢአት ንስሓ ስለ መግባት፣ ብቸኛና መካከለኛ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ አስፈላጊ መሆኑን፣ እየመጣ ስላለው ፍርድና ከዚህም ፍርድ ሊያድን የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ስለ መሆኑ ሰበከ። ዳና መጃ፣ ዋንዳሮ የተናገራቸውን ቃላት ከአእምሮው ማስወጣት አልቻለም። በጣም ለብዙ ሌሊቶች ያለ እንቅልፍ እየተወቀሰ አደረ፣ እጅግም በጣም ፈራ።

ዋንዳሮ በመጀመሪያ ደረጃ የጸሎት ሰው ነበር። ለዳና መጃ ደግሞ ትልቅ ሸክም ስለ ነበረው ሁልጊዜ ይጸልይለት ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ስለ ራሱ ቤተሰብ፣ ስለ ጎረቤቶቹ፣ ስለ ጠንቋዩ፣ አገልጋዮቹና ስለ ድኾች ይጸልይ ነበር። ከዚያም ጣልያን ኢትዮጵያን ወረረች። ዳና መጃም በሶዶ ከተማ ውስጥ ከፈነዳ ቦምብ ለጥቂት ተረፈ። ይህ ደግሞ ይበልጥ እንዲፈራ አደረገው። ከዕለታት አንድ ቀን ሰዎች በፍጥነት በከተማው አቅራቢያ ወደሚገኝ ጅረት ሲሄዱ ተመልክቶ ምን እየሆነ እንዳለ ጠየቃቸው። ሕዝቡንም ተከትሎ መጓዝ

ጀመረ፡፡ በዚያም ዋንዳሮ አዳዲስ አማኞችን ሲያጠምቅ ተመለከተ፡፡

ዋንዳሮ በድፍረት የከተማዋን አስተዳዳሪ ተጠግቶ የደኅንነት መንገድን እንደገና ነገረውና ክርስቶስን ይከተል ዘንድ ገፋፋው፡፡ በዚያ ቀንም ዳና መጀ ክርስቶስን ተቀበለ፤ ሕይወቱም ፈጽሞ ተለወጠ፡፡ ሁሉንም ባሮቹን በነፃ አሰናበታቸው፤ የአዲሱ ጌታውም ትሑት አገልጋይ ሆነ፡፡ በጣም ብዙ መከራንና ስደትን ተቋቋመ፡፡ በኋላ ላይም ዳና መጀ የወላይታ ክርስቲያኖች መሪ ሆኖ ተመረጠ፡፡ ይህንን ኃላፊነት ከሃያ ዓመታት በላይ ይዞ ቆይቷል፡፡

የጣልያን ፋሽስት ኢትዮጵያን በተቆጣጠረበት ወቅት፣ ዋንዳሮ ከታሰሩት፣ በራብ እንዲቀጡና ይከዱ ዘንድ ከተገረፉት ሃምሳ ክርስቲያኖች መካከል አንዱ ነበር፡፡ ከድብደባው የተነሣ ሁለት ሰዎች የሞቱ ሲሆን፣ ከሃምሳዎቹ መካከል ግን ማንም ሰው ጌታን አልካደም፡፡ ዋንዳሮ በጅራፍ መቶ ጊዜ የተገረፈ ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት ዕድሜ ዘመኑን ሁሉ በጀርባው ላይ ጠባሳ ይዞ ይዞራል፡፡ በመስቀል ላይ ስለ እርሱ ሲል መከራን ስለ ተቀበለው፣ መከራን መቀበሉ በጣም ያስደስተዋል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ዋንዳሮ አርባ የጅራፍ ግርፋትን ተቀብሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ መስበኩን ያቆም ዘንድ በዱላ ተደብድቧል፡፡ አንድ ጊዜ አምስት ሰዎች ራሱን እስኪስት ድረስ ደብድበውታል፤ ለአንድ ዓመት ያህልም በወህኒ ቤት ውስጥ ቆይቷል፡፡

አንድ ጊዜ ወደ ሠላሳ የሚሆኑ፣ መሣሪያ የታጠቁ ሰዎች እርሱን ፍለጋ መጡ፡፡ እርሱን ለመግደል ትእዛዝ ተሰጥቷቸዋል፣ ነገር ግን ዋንዳሮ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ስለ ነበር አመለጣቸው፡፡ በሌላ ጊዜ የአካባቢው አስተዳዳሪ ዋንዳሮን ገልብጦ በማሠር ሲገረፍና ሲገደል ይመለከቱ ዘንድ ሰዎችን ጠራ፡፡ የመንግሥት ባለ ሥልጣኑ ወንበሩ ላይ እንደ ተቀመጠ ወደ ኋላው ወድቆ ሞተ፡፡ ይህም የትዕይንቱ መጨረሻ ሆነ!

ዋንዳሮ የአንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ፣ በሁምቦ ቀጣና ውስጥ እያደገ ባለው ማኅበረ ምእመናን ውስጥ የመሪዎች ሽማግሌና በቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ያሉ አለመግባባቶችና ችግሮች አማካሪ ሆኖ ለብዙ ዓመታት አገለግሏል፣ ነገር ግን ሁልጊዜም የእርሱ ዋና አገልግሎት የምልጃ ጸሎት እንደ ሆነ ይሰማዋል፡፡ ከእርሱ ጋር ተመሳሳይ አእምሮ ካላቸው ክርስቲያኖችና በሶዶ ከነበሩ ሚስዮናውያን ጋር ለመጸለይ ለሰዓታት በእግሩ ይጓዝ ነበር፡፡ ጸሎቱ ቀላል፣ ቀጥተኛና በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ የተመረኰዘ ሆኖ

አግኝተነዋል፡፡ ሁልጊዜ ምላሽ ለማግኘት ተስፋ ያደርጋል፡፡ ዋንዳሮ በጣም ጥሩ ጓደኛ ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ በአገልግሎታችን ያበረታታናል እንዲሁም ይገፋፋናል፡፡

የክርስትና ሕይወቱን ያሳለፈው ሥነ-ምግባር በጐደላቸው የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ሲሰደብ እና ሲሰደድ ነበር፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት፣ እርሱ ታማኝና ጉቦ ለመክፈል እንቢ ስላለ ነበር፡፡ ጠንቋዮች ደግሞ የሚጠሉት የእነርሱን የሰይጣን ኃይል በጸሎት ስለሚሰባብርባቸው ሲሆን፣ ክፉ ሰዎች ደግሞ የእርሱን ንጹሕ የሆነ ሕይወትን ይጠላሉ፡፡ ኢትዮጵያን የወረሩ ጣልያኖችም እምነቱን ስለሚያካፍላቸው ይጠሉት ነበር፤ የኦርቶዶክስ ቄሶችም፣ ብዙ ሰዎች የእነርሱን እምነት እየተዉ በመሄዳቸው የሚያገኙት ነገር ስለሚቀንስባቸው ይጠሉት ነበር፤ እንዲሁም ኢትዮጵያን ለአሥራ ሰባት ዓመታት የገዛ የኮምዩኒስት አገዛዝ ይጠላው ነበር፡፡

በማርክሲዝም የ‹‹ቀይ ሽብር›› እንቅስቃሴ ወቅት መጽሐፍ ቅዱሶች ተቃጥለዋል፤ ከአራት ሰዎች በላይ መሰብሰብ የተከለከለ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያናት ተዘግተው ነበር፣ ዋንዳሮ ግን ቤተ ክርስቲያኑን ክፍት አድርጎ አቆይቶ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ታስሯል፤ ከእስር ሲፈታም ወደ ቀዬው ተመልሶ እንደገና ቤተ ክርስቲያኑን ከፈተ! ወጣቶች፣ በተለይም ተማሪዎች፣ በካድሬዎች ሒላማ ውስጥ የነበሩ ሲሆን፣ ብዙ ጊዜም ‹‹የለውጥ ተቃዋሚዎች›› ተደርገው ይከሰሱ ነበር፡፡ በክርስቲያኖች የሠርግ ሥነ-ሥርዓት ወቅትም የኮምዩኒስቶች ካድሬዎች መጥተው በስፍራው ያለውን ሰው ሁሉ አስረው ያውቃሉ፡፡ ዋንዳሮም የጀመረውን የማጋባት ሥነ ሥርዓት በእስር ቤት አጥር ግቢ ውስጥ አጠናቅቆታል!

ዋንዳሮ ወንድ ልጁና የእርሱ ጓደኞች በጸሎት ፕሮግራም ላይ ሳሉ ተይዘው፣ መወሰዳቸውን ሲሰማ ወዲያው በፍጥነት ወደ እስር ቤት ሄደ፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች በእምነታቸው አዲስ ከመሆናቸው የተነሣ፣ ተጽዕኖው ሲበዛባቸው ምናልባት ያፈገፍጉ ይሆናል ብሎ አሰበ፡፡ ዋንዳሮ ወህኒ ቤቱ የደረሰው እኩለ ሌሊት ካለፈ በኋላ፣ ነበር፡፡ ዘበኞቹ ይከፍቱለት ዘንድ ከተጣራ በኋላ፣ የብረት በሩን በያዘው ዱላ መደብደብ ጀመረ፡፡

‹‹እንድገባ ፍቀዱልኝ! እንድገባ ፍቀዱልኝ!›› እያለ ዋንዳሮ ጮኸ፡፡ ዘበኞቹ

ምላሽ እስኪሰጡት ድረስ ይህንን ደጋግሞ ይለው ነበር፤ በመጨረሻም ከፍተውለት ወደ ወህኒ ቤቱ ቅጥር ግቢ እንዲገባ አደረጉት፡፡

የወህኒ ቤቱ ዘበኞች አለቃ ዋንዳሮን እንዲህ ሲል ጠየቀው፣ ‹‹ለምን ወደ ውስጥ ለመግባት ፈለግህ? በዚህ ያለ ሰው ሁሉ መውጣት ይፈልጋል! ለመሆኑ አንተ ማን ነህ፣ ለምን መጣህ?›› ብሎ ጠየቀው፡፡

ዋንዳሮ ስሙን ነገረውና ወንድ ልጁንም ለማየት እንዲፈቀድለት ጠየቀ፡፡ በዚህ ጊዜ ግማሽ ያህሉ እስረኞች ከእንቅልፋቸው ነቁ፡፡ የዋንዳሮ ልጅም አባቱን ተጣራ፡፡

ዘበኞቹ ዋንዳሮ እንዲሄድላቸው ፈልገው ነበር፣ ነገር ግን እርሱ ለመሄድ እንቢ አለ፡፡ ከልጁ ጋር መሆን እንደሚፈልግ ተናገረ፡፡ የእስር ቤቱን ደጃፍ ከፍተው ዋንዳሮን ከአዳዲሶቹ ወጣት ክርስቲያኖች ጋር እንዲሆን አስገቡት፡፡ ከሳምንት በኋላ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከእስር ቤት እስኪለቀቁ ድረስ ዋንዳሮ በእስር ቤት ውስጥ ቆየ፡፡ በእስር ላይ ለነበሩት እስረኞችና ዘበኞች መሰከረላቸው፡፡ ከእነርሱም ጋር በመሆን ስለ ቤተሰቦቻቸው ጸለየ፡፡ የእርሱ ጀግንነት ለአዳዲሶቹ ወጣት ክርስቲያኖች ትልቅ ማበረታቻ ነበር፡፡ እንዲሁም በሳምንት ቆይታው ያሳያቸው ፍቅር እና እንክብካቤ በእስር ቤቱ ውስጥ ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች ጌታን እንዲቀበሉ አደረጋቸው፡፡

‹‹በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር
መከራ መቀበልን መረጠ፡፡››

ዕብራውያን ፲፡25

26

ኢያሱ

ዛሬ እነርሱ የት ናቸው?

ወደ ሦስት መቶ ይጠጋሉ፤ አብዛኞቹ ወጣቶችና ተማሪዎች ነበሩ፤ ሁሉም እርስ በርሳቸው ተጠጋግተው ጥልቅና ጠባብ በሆነው ገደል አፋፍ ላይ ቆመዋል። ይህ ሸለቆ የሚወስደው ብዙ ሰዎችና በመቶዎች የሚቈጠሩ እንስሳት ለውኃ ወደሚሄዱበት ምንጭ ነበር። በየዓመቱ በተራራው ላይ የሚዘንበው ከባድ ዝናብ ይበልጥ አፈሩን እየሸረሸረ ገደሉ ከ13 እስከ 15 ጫማ (አራት ወይም አምስት ሜትር) ጥልቀት እንዲኖረው ያደርጋል። ገደሉም ቆሻሻ፣ የሚሸትና በጭቃ የተሞላ አንሸራታች ነበር። በጣም ቀዝቃዛማና ጨለማ በሆነው ሌሊት የሚስዮን ጣቢያውን ለማፍረስ ሜሬ እየዶለቱ ለነበሩ ሰዎች ትክክለኛ ስፍራ ነበር። ኢያሱ አዳላጩ ሸለቆ አናት ላይ ሆኖ ለተሰበሰቡት ሰዎች መመሪያ ያስተላልፋል።

ሰላማዊ ሰልፍ! ዐመፅ! ሥራ የማቆም አድማ! ከዚያም አሁን ደግሞ ለውጥ! ለብዙ ዘመናት ወሬው በጨለማ ውስጥ በሹክሹክታ ሲወራ ኖሯል። በማኅበረሰቡ ውስጥ የነበረው ቀኑጣ ኮምዩኒስቶች ከውጭ በሚያደርጉት ፕሮፖጋንዳና በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አማካይነት ገንፍሎ ወጥቷል። ከዩኒቨርሲቲዎች አልፎ ወደ ማሠልጠኛ ተቋማት፣ ከዚያም በትልልቅ ከተሞች ውስጥ ወደሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ በመጨረሻም ወደ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ደረሰ። የግል እና የሚስዮናውያን ትምህርት ቤቶችም ከዚህ ነገር አላመለጡም።

ሁሉም ሰው ሙስናን፣ ጉቦንና የድኾች በሀብታሞች መበዝበዝ፣ ኢ-ፍትሐዊነትን እና በእኩል አለመታየት አንገሽግሾት ነበር። ብዙ ሰዎች ለውጥን

ፈልገዋል፤ ይህ ደግሞ በማርክሲዝም/ሌኒኒዝም ርዕዮተ ዓለም ይገኛል ተብሎ የሚናፈሰውን የሐሰት ወሬ ሁሉንም ሰው አሳምኗል። በዚህ ለውጥ ሁሉም ነገር ይስተካከላል! ሁሉም ሰው ሀብታም ይሆናል! ሁሉም እኩል ይሆናል! ብለው አምነዋል።

ሰላማዊ ሰልፉ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይበልጥ ዐመፅ የተሞላበት እየሆነ በሄደ ጊዜ፣ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተዘጉ። ሱቆች ተዘረፉ፣ እንዲሁም ተቃጠሉ፣ ባንኮች ተወረሩ፣ እንዲሁም ሀብታም ነጋዴዎችና የመሬት ከበርቴዎች ተገደሉ። አንዳንድ የወታደር አዛዦች ይጠብቁት የነበረው ነገር ይህ ነበር! አድመኞቹ የንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴን ሥረወ መንግሥት በመናድ የደርግ፣ የኮምዩኒስቶች የለውጥ ፓርቲ ሥልጣኑን ተቈጣጠረው።



ከጥቂት ቀናት በፊት፣ ወደ መቶ የሚጠጉ ተማሪዎች መንገድ ላይ ሲራወጡ፣ ትምህርት ቤታቸውንና የመንግሥት ቢሮዎችን ሲያፈራርሱ፣ ሱቆችንና የሀብታሞችን ቤት ሲዘርፉ የተመለከቱ የዋካ ነዋሪዎች ተደናግጠው ነበር። በቀኑጥር በጣም ትንሽ የሆነው የፖሊስ ግብረ ኃይል ለማስቆም ዓቅም አልነበረውም። አሁን ደግሞ ከትምህርት ቤቱ አጠገብ ያለውን የሚስዮናውያንን ጣቢያ ማፍረስና ‹‹ኢምፔሪያሊስቶቹን›› አሜሪካውያንን የማባረር ሥራ ሆነ። በዚያ ስፍራ የነበርነው አምስታችንም አውስትራሊያውያን እንጂ፣ አሜሪካውያን አልነበርንም፤ ነገር ግን በእኛ መካከል የነበረውን ልዩነት አያውቁም ነበር። ከከተማ የመጡ ተማሪዎች፣ ሌቦች እና ነውጥ ማስነሣት የሚወድዱ ሰዎች የሚስዮን ትምህርት ቤት ተማሪዎችም በሰርጥ ውስጥ ባደረጉት ስብሰባ ላይ ተገኝተው ነበር።

ኢያሱ የሚለው ስም በኢትዮጵያ ውስጥ ለወንድ ልጅ የሚሰጥ የተለመደ ስም ነው። በሚስዮናውያን ትምህርት ቤት ውስጥ ኢያሱ ተብሎ የሚጠራ ልጅ ነበር። ይህ ልጅ ወንጌልን ለመጀመሪያ ጊዜ ከወላይታ ወደ ዳውሮ አካባቢ በመሄድ ያደረሰው የአንዱ ጐበዝ ወንጌላዊ ልጅ ነው። ኢያሱ በጣም ጐበዝ የሆነ ልጅ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ብዙ ጊዜ በማታለልና ከተማሪዎች ጋር ግጭት ውስጥ በመግባት የሚታወቅ ልጅ ነበር። ምንም እንኳ ወላጆቹ ቢለምኑትም፣

ኢያሱ ከከተማ ከመጡ ወጣት ተማሪዎች ጋር ጎብረት በማድረግ በአገሪቱ ዋና ከተማ፣ አዲስ አበባ ውስጥ እየተደረገ ስላለው ነገር የተነገረውን የሐሰት ወሬና ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ሁሉ አምኖ ነበር። በትምህርት ቤት ውስጥ ሊከተሉት የሚችሉ ሰዎችን ሰበሰበና ለመምህራቸውና በሥልጣን ላይ ላለ ማንኛውም ሰው ታማኞች እንዳይሆኑ፣ እንዳይታዘዙ እና እንዳያከብሩ አነሣሣቸው።

ኢያሱ ከከተማ ከመጡት ጓደኞቹ ጋር በመሆን ድንጋይ፣ ዱላዎችንና ለመሣሪያነት ጩቤዎችን ሰበሰቡ። ዕቅዳቸው በላይ በኩል ባለው የሚስዮናውያን ቅጥር ግቢ ላይ ጥቃት በመፈጸም ትምህርት ቤቱንና ክሊኒኩን ማውደም፣ ከዚያም መንገዱን ተከትሎ ወደ ታች በመሄድ በቅጥር ግቢው መሃል ላይ በሚገኘው የሚስዮናውያን መኖሪያ ቤት ላይ ጥቃት ማድረስ፣ ከዚያ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሄዶ የተማሪዎችን ማደሪያ ማውደም ነበረ።

ብዙ የክርስቲያኖች ልጆችና ወጣቶች ወይም ከክርስቲያን ቤተሰብ የመጡ አብዛኞቹ የዕቅዱን ክፋት በሰሙ ጊዜ ከዐመፁ ቡድን ራሳቸውን ለዩ። ነገር ግን ኢያሱና ከከተማ ተሰብስበው የመጡት ወዳጆቹን ወደ ተግባር ይሄዱ ዘንድ አነሣሣቸው። ስሜታቸውም መጥፎ እየሆነ መጣ። በዚህ ከቀጠሉ ሰዎች የሚጐዱ ሆነ።

ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ገደማ ላይ የመኖሪያ ቤታችን በር በቀስታ ተንኳኳ። ሉቃስ የተባለ ልጅ፣ እኛ ከትምህርት በኋላና በሳምንቱ የዕረፍት ቀናት ሥራ እየሰጠን ትምህርቱን እንዲማር የምናግዘው ጠንካራ ልጅና ሁለት መምህራን በቤታችን ደጃፍ ላይ ቆመዋል። ትልቅ ዱላና የእንስሳት መግረፊያ አለንጋ ይዘዋል። ሉቃስ እየታሰበ ያለው ነገር ምን እንደ ሆነ ለመምህራኑ ስለ ነገራቸው እነርሱ በፍጥነት ወደ እኔ መጡ። እናንተን አሁን ሊያጠቋችሁ ስለ ሆነ፣ እናንተ የውጭ ሀገር ሰዎች በቶሎ ሸሽታችሁ በአቅራቢያው በሚገኙ ክርስቲያኖች ቤት ውስጥ ተደበቁ አለኝ። በአንድነት ጸሎት አደረግን። ከዚያም እንዲህ አልኳቸው፣ እነዚህ ልጆች ጥፋት ከማድረሳቸው በፊት እንበትናቸው። ምንም እንኳ ዕቅዴ ሊሥራ መቻሉን ቢጠራጠሩም፣ ከእኔ ጋር ለመሄድ ተስማሙ።

ረጅሙን፣ አምስት የባትሪ ድንጋዮችን የሚጐርሰውን፣ ባትሪዬን ይገፍ ሳላበራ በዝምታ እየመራኋቸው በፍጥነት እስከ መንገዱ ድረስ ተጓዝን። ወደ ሸለቆው አናት ላይ ስንደረስ ድቅድቅ ጨለማ ነበር። ለዐመፁ የተሰበሰቡት

ሰዎች እኛን ማየት፣ እኛም እነርሱን ማየት አንችልም ነበር። ነገር ግን ንግግራቸውን እንሰማ ነበር። ሁሉም ዐመፁን ለመጀመር ተዘጋጅተዋል። የደረስነው በትክክለኛው ሰዓት ነበር! የተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ ወደ ላይ በመመልከት ላይ ነበሩ፤ በሸለቆው አናት ላይ እኛ መቆማችንን ግን ፈጽመው አላወቁም ነበር። የዐመፁ መሪ የሆኑ ጥቂት ሰዎች ከእኛ ትንሽ ራቅ ብለው ሸለቆውን ወደ ታች እየተመለከቱ የተሰበሰበውን ሕዝብ ያነሣሡ ነበር።

ኃይለኛ ብርሃን የሚሰጠውን ባትሪዬን በጨለማ ውስጥ ነጩ ፊቴ ብቻ ይታይ ዘንድ አገጩ ላይ አበራሁት። ለዐመፅም የተሰበሰቡት ሰዎች ከእነርሱ ብዙ ሜትር ርቀት ላይ የሚታየውን ፊቴን ብቻ በጨለማ ውስጥ አዩ። ይህ ምን ሊሆን እንደሚችል አላወቁትም! ሁሉን ቻይ አምላክ? ሰይጣን? ክፉ መንፈስ? ቡዳ? መለየት አልቻሉም።

ምን ሊሆን እንደሚችል ምንም ፍንጭ ስለሌላቸውም በፍርሃት መጮኽ ጀመሩ! መሪያቸው የፍርሃት ጩኸት ያስከተለው ነገር ምን እንደ ሆነ አላወቀም! ባትሪውን አጠፋሁት። ከዚያ ፍጹም የሆነ ጨለማ በስፍራው ላይ ሰፈነ! ከዚያም አራታችን በታላቅ ድምፅ ‹‹ዋ!›› ብለን ጮኽን። ይህ የኢትዮጵያውያን የጥንት ማስፈራሪያ መንገድ ነበር! ይህ የእኛው የ‹‹ዋ›› ጩኸት ደግሞ ይበልጥ የሚያስፈራ ነበር!

ከዚያም አራታችን ከሸለቆው አናት ወደ ታች ወደ መሪዎቹ መሄድ ጀመርን! ምን እንደ መታቸው አላወቁም! በስፍራው ስንድረስ በጣም ብዙዎቹ ተፈነካክተዋል! በጣም የሚያስገርም ነበር! ፍጹም የሆነ ትርምስ በመካከላቸው ተፈጠረ! ለዐመፅ የተሰበሰበው ሰው ተበጣበጠ! ጩኸትና ግርግር ሆነ፣ ሁሉም በተለያየ አቅጣጫ ሮጡ! በሰማይ ላይ ከተመለከቱት የሚያስፈራ መንፈስ ለማምለጥ እርስ በርሳቸው ተረጋገጡ፣ አንዱ በሌላኛው ላይ ተረማመደ።

ጭቃማ እና አንሸራታች የሆነው ሰርጥ ሁኔታውን ይበልጥ መጥፎ አደረገው! ‹‹የሲኦል አዳኝ›› ከኋላቸው ይከተላቸው ነበር። እዚህም እዚያም በወደቀው ሰው ላይ እየተረማመዱ ሲሮጡ እርስ በርሳቸው ተጐዳዱ። ሁሉም ማምለጥ ፈለገ! ከዚያ ስፍራ ብቻ መውጣት የሁሉም ፍላጐት ነበር! ሁኔታው በጣም የሚያስፈራ ነበር! አንዳንዶቹ ከሸለቆው አናት ላይ መውጣት ቻሉ፣ ነገር ግን ወዲያው የሮጡበት አቅጣጫ አጥር ግቢውን ወደ ከበበው እሾኽ ነበር።

የእሾኹ መቧጨር ወይም የልብሳቸው መቀደድ አላስቆማቸውም። እንዲሁ በሸቦ አጥር በኩል የሄዱትንም ሸቦው አላስቆማቸውም!

ከባድ ብርሃን የሚያመነጨውን ባትሪዬን በሁለት እጆቼ እንደ ያዝኩ በጉልበቴ በአንድ ወጣት ልጅ ወገብ ላይ አረፍኩኝ። ወጣቱም ወደ ፊት ወደቀ። ከእርሱ ጋርም ብዙዎች አብረውት ወደቁ! ባትሪው ማጅራቱን መታው፣ ፊቱ በጭቃ ውስጥ ተቀበረ። ከእኔ ሥር ሆኖ ለማምለጥ ይወራጭ ጀመር፣ ነገር ግን ከእኔ አምልጦ ሲሮጥ የመምህሩ ዱላ አገኘው! መምህራኑና ሉቃስ ዱላቸውን መጥረግ ተያያዙት። ምንም እንኳ እነርሱ ብዙ ሰዎችን በዱላ ቢመቱም፣ ብዙ ጉዳት በራሳቸው ላይ ያደረሱት ግን ለዐመፅ የተበሰቡት ሰዎች ነበሩ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ሸለቆው ባዶ ሆነ፤ የብዙ ሰዎችም ድምፅ በኰረብታው አናት ላይ እስከ ዋካ ከተማ ድረስ በየአቅጣጫው ይሰማ ነበር! ድሉ በዚህ ተጠናቀቀ! እነርሱም ምን እንደ ተፈጠረ ወይም ማን ይህን ፍርድ በእነርሱ ላይ እንዳመጣ አላወቁም!

ቀዝቃዛው አየርና የዘነበው ዝናብ የደረሰባቸውን ነገር አባባሰው። መምህራኑ፣ ሉቃስና እኔ በጨለማ ዝናብ እየዘነበ ለመታጠብና ለመተኛት ወደ ቤት አመራን። ወደ አልጋ የሄድነው ለመተኛት ሳይሆን፣ በአእምሮአችን የተከሰተውን ነገር ደጋግመን ለማሰላሰል ነበር።

ጠዋት በማለዳ የተመለከትነው ነገር አስገራሚ ነበር! አንድ ትንሽ ልጅ በሸለቆው ውስጥ በጣም ብዙ ዱላዎችና ድንጋዮች አሳየን። በዳመና ውስጥ ፀሐይ ብቅ ማለት ስትጀምር፣ ጥቂት ተማሪዎች ሰብሰብ ብለው ማታ ስለ ገጠማቸው ነገር ያወራሉ። አንዳንዶቹ ሰውነታቸው የተቧጨረ በመሆኑ፣ ሊያፈርሱት በፈለጉት ክሊኒክ ውስጥ ሕክምና ለማግኘት በመጠበቅ ላይ ነበሩ። ሌሎች ደግሞ የተቀደደ ልብሳቸውን እንደ ለበሱና ሰውነታቸው ላይ የተለያየ የመቁረጥና የመቧጨር ሁኔታ ስላደረሰባቸው፣ በትምህርት ቤቱ አቅራቢያ ቆመው ከእጃቸውና ከእግራቸው ላይ እሾኽ ለመንቀል ጥረት ያደርጋሉ። የተገረምን በመምሰል ተጣልተው እንደ ሆነ፣ ይህን ጉዳት ያደረሰባቸው ማን እንደ ሆነ ጠየቅናቸው። በጨለማ ውስጥ አንድ አስደንጋጭ ኃይል እንደ መታቸው እንጂ፣ ማን እንደ ሆነ አላወቁም!

የተማሪዎች አባቶች በሙሉና ከሩቅ መንደሮች የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ለስብሰባ ይጠሩ ዘንድ ጥቂት መልእክተኞችን ላክኩኝ። መጋቢያኑና የቤተ

ክርስቲያን ሽማግሌዎቹ፣ ሁሉንም ተማሪዎችና የልጆቹን አባቶች ነገሩን እስኪመረምሩት ድረስ ትምህርት ቤቱ ለአንድ ሳምንት ያህል ተዘጋ፡፡ ዋናዎቹ መሪዎች እነማን እንደ ሆኑ ለመለየት በጣም ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸውም፡፡ ከተማሪዎቹ መካከል አሥራ ሁለቱ ከትምህርት ቤት እንዲባረሩ ጠየቁ፡፡ የተቀሩት ኃጢአት በመፈጸማቸው ምክንያት ይቅርታ እንዲጠይቁና ንስሓ እንዲገቡ ነገሯቸው፡፡

በመላ ሀገሪቱ ውስጥ አለመረጋጋት፣ ሰላማዊ ሰልፍ እና ዐመፅ ተባብሶ ቀጠለ፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች እንዲያውም ትምህርት ቤቶች ሥራቸውን በአግባቡ ማከናወን ተሳናቸው፡፡ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምክር መሠረት ትምህርት ቤቱ ተዘግቶ ተማሪዎች ወደየ ቤታቸው እንዲመለሱ ተደረገ፡፡ በዚያ ምሽት፣ በሸለቆ ውስጥ ስለተከሰተው ነገር የተለየ ነገር ለወላጆቻቸው እንደሚናገሩ ምንም ጥርጥር አልነበረም! ሁሉም ተማሪዎች አንድ የትምህርት ዓመታቸውን አቃጠሉ፡፡ የዐመፁ መሪ የሆነው ደግሞ ከዚያ በላይ ትምህርቱን አጣ፡፡

ወንጌላዊ አባቱ ኢያሱን በታላቅ ጎዘን ይዞት ወደ ቤቱ ሄደ፡፡ ትምህርት ቤት እንደገና ሲከፈት እንኳ ተመልሶ እንደማይገባ ነገረው፡፡ በቤት ሆኖ እርሻ ማረስ እንዳለበት ነገረው፡፡ ለሁለት ዓመታት በትጋት ከሠራና የተለየ አመለካከትን ካሳየ፣ ወደ ተጨማሪ ችግር ውስጥ ካልገባ፣ እንዲሁም ከኢ-አማኒያን የለውጥ አራማጆች ጋር የማይገናኝ ከሆነ ብቻ አባቱ ወደ ትምህርት ቤት መሄዱን እንደሚደግፍ ነገረው፡፡ ኢያሱም አባቱን ታዘዘ፡፡ ኢያሱ ጐበዝ ተማሪ ነበር፤ ከክፍሉ ተማሪዎች ጐበዝ ከሚባሉት መካከል አንዱ ነበር፣ እንዲሁም ለመማር ሁልጊዜም ልዩ ፍላጎት አለው፡፡ ስሕተት እንደ ሠራ አውቋል፡፡ በተፈጥሮው መሪ ስለሆነ፣ ሌሎችን ወደ ስሕተት መርቷል፣ ስለዚህም ቅጣት ይገባዋል፡፡

ꕥ

በ2001 (እ.ኤ.አ) ለሦስት ወራት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሼ በመጣሁበት ወቅት፣ በዳውሮ ያለው የቤተ ክርስቲያኖች ጎብረት አስተባባሪ ወደ ዋካ መጥቼ እንድሰብክ ጋበዘኝ፡፡ በዚያ ስፍራ ላይ በሚደረጉ ስብሰባዎች ከተካፈልኩ ብዙ ዓመታት ሆኖኛል፡፡ የኮምዩኒስቱ መንግሥት የሚሰዮን ጣቢያውን ወርሶታል፣

ነገር ግን የደርግ መንግሥትን የገረሰሰው አዲሱ መንግሥት በዋካ ከተማ አቅራቢያ ወደ ተራራው ላይ ትልቅ መሬት ሰጥቶአቸዋል። ትልቅ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ፣ የቤተ ክርስቲያን ቢሮ፣ የተማሪዎች ማደሪያ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በዚያ ስፍራ ላይ ተሠርቷል።

አስተባባሪውም ከእያንዳንዱ ቀጣና በሺህ የሚቈጠሩ ሰዎች ይመጣሉ ብሎ እንደሚጠብቅ ነገረኝ። ወጣቶች ከ2000 ሰዎች በላይ መያዝ የሚችል መጠለያ ዳስ ከሣርና ከቀርከሃ እንዲያዘጋጁ አቀናጅቷል። ሞቃታማ በሆነ ቀን ከተሠራው መጠለያ የተረፉ ሰዎች በተራራው ሥር ጥላቸውን ዘርግተው ተቀምጠዋል። በሰው በኃይል ሞልቶ በነበረው በአንደኛው ስብሰባ ላይ የቀጣናው አስተባባሪ እያስተረጐመልኝ ሰበክኩኝ። የተጠቀምኩት ርእስ ‹‹ዛሬ እነርሱ የት ናቸው?›› የሚል ነበር።

‹‹ዛሬ እነርሱ የት ናቸው?›› በቅጽበትም በአእምሮዬ ውስጥ ለዐመፅ የተሰበሰቡት ተማሪዎች ትዝ አሉኝ። ሁኔታው ከተፈጸመ ሃያ ሰባት ዓመታት አልፈዋል። እነዚያ ወጣት ተማሪዎች በአሁን ሰዓት በአርባዎቹ የዕድሜ አጋማሽ ላይ ናቸው። ምን ሆነው ይሆን? አሁን የት ይሆኑ ይሆን? በዚያ ዕለት ምሽት ስለ ተፈጸመው ታሪክ ለተሰበሰበው ሕዝብ አጫወትኳቸው፤ ታሪኩን ለመጀመሪያ ጊዜ መስማታቸው ነበር። እንዴት አራታችን ብቻ በመቶዎች የሚቈጠሩትን እንዳስደነገጥን፣ እንዳስፈራራን ነገርኳቸው፣ እነርሱም ታሪኩን እየተናገርኩ ይስቁና ያጨበጭቡ ነበር።

ከዚያም እንዲህ ስል ተናገርኩ፡- ‹‹እነዚህ ተማሪዎች በአሁን ወቅት ዕድሜያቸው 44 ወይም 45 ዓመት ይሆናቸዋል። በዚያን ጊዜ ልጆች አሁን ትዳር መሥርተው ወልደው ሊሆኑ ይችላሉ። ዛሬ እነዚህ ልጆች የት ይሆኑ? ብዬ እጠይቃለሁ። ምን እንደ ሆኑ ማወቅ እፈልጋለሁ። በኢየሱስ አምነው ድነው ይሆን? እነርሱ ዛሬ የክርስቶስ ተከታዮች ይሆኑን? በሕይወት ይኖሩ ይሆን? ከጦርነቱ ተርፈው ይሆን?›› በሕዝቡ መካከል ትልቅ ዝምታ ሰፈነ። ብዙ ወንዶችና ሴቶች አንገታቸውን ሲያቀረቅሩ ተመለከትኩኝ። ከዚህ በላይ በነገሩ ሳልገፋበት ወደ መልእክቴ ተመለስኩኝ።

በኋላ ላይም ከመጋቢዎችና ከወንጌላውያን ጋር እራት ለመብላት በማዕድ ዙሪያ ተቀምጠን ሳለ፣ የአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያኖች አስተባባሪ አንጉቱን

እንዳቀረቀረ፣ ኢያሱ መጥቶ የዐመፁ መሪ እርሱ እንደ ነበር ተናገረ! በዚያ ምሽት ወጣቶቹን እንደዚያ ያስፈራቸው ነገር ምን እንደ ሆነና ከኋላ የወደቀበት ነገር ምን እንደ ሆነ እንዲሁም ማጅራቱን የመታው ብረት ምን እንደ ሆነና በጭቃ ውስጥ ፊቱን የዘፈቀው ነገር ምን እንደ ሆነ ማወቁን ተናገረ፡፡

‹‹ሁሉም ነገር ይገባኛል፡፡ ከሸለቆው ውስጥ ከመውጣቴ በፊት በዱላና በአለንጋ ተመትቼ ነበር፣›› በማለት ተናገረ፡፡ ‹‹በጣም ፈርቼ ስለ ነበር የማስበውን እንኳ አላውቅም ነበር፡፡ የት እንደምሄድ እንኳ ሳላውቅ ዝም ብዬ እሮጥ ነበር፡፡ ልቤ በጣም ይመታል፣ መላ ሰውነቴም ይንቀጠቀጥ ነበር፡፡ እንዲያውም ከድንጋጤ የተነሣ መኖሪያ ቤታችን ጠፍቶብኝ አልፈው ሄጃለሁ! በመጨረሻም ኃይሌ ሁሉ ተሟጥጦ ደክሞኝ በመሬት ላይ ወደቅኩኝ፡፡ ተረጋግቼ ለማሰላሰልና የልብ ምቴን ለማስተካከል ሰዓታት ወስደውብኛል፡፡ ከዚያም ወደ ቤት ቀስ ብዬ ተመለስኩኝ፡፡ የፈለግኩት ነገር መደበቅ ብቻ ነበር!››

‹‹በሚቀጥለውም ቀን አባቴ ወደ ሚስዮኑ ጣቢያ ተጠራ፡፡ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር በመሆን ሁሉንም ተማሪዎች መረመረ፡፡ አባቴ አስፈላጊውን ቅጣት ቀጣኝ፣ ኃጢአቴ ምንኛ ከባድ እንደ ሆነና በእግዚአብሔር ፊት ዐመፅ እንደ ሆነም አስተማረኝ፡፡ በእርሻ ቦታ ከባድ ሥራ እንድሠራ አደረገኝ፣ እንዲሁም እንደ እውነተኛ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ተከታይ ሆኜ እንዴት መኖር እንዳለብኝ አስተማረኝ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም አስፈላጊውን እገዛ ሁሉ አደረገልኝ፡፡ የእግዚአብሔርንም ቃል አስተማረኝ፡፡ እግዚአብሔርን ስለ አባቴ አመሰግናለሁ፣ እንዲሁም እኔም ለልጆቼ የእርሱ ዓይነት አባት ለመሆን እሞክራለሁ በማለት ተናገረ፡፡›› ኢያሱና እኔ በጌታ ሐሤት እያደረግን ጥሩ ጊዜ አሳለፍን፡፡ እንዲሁም ስለ ጸጋውና ሰዎችን ስለሚለውጠው ኃያሉ እግዚአብሔርን አመሰገንነው፡፡

ከዚያም ኢያሱ አንድ ክርስቲያን ነጋዴ ይዞ በመምጣት በዚያ ዕለት ምሽት በሸለቆ ውስጥ ከነበሩት ሰዎች መካከል መሆኑን ነገረኝ፡፡ አሁን ንስሓ ገብቶ ሕይወቱ ታድሷል፡፡ አሁን የክርስቲያኖች ቤተሰብ ነው፡፡ በአካባቢያችንም የጌታን ሥራ በለጋስነት እንደሚደግፍ ነገረኝ፡፡ በኋላ ላይም አንድ ገበሬ መጥቶ በዚያ ዕለት ምሽት እርሱም በሸለቆው ውስጥ እንደ ነበር ተናዘዘ፡፡ አሁን በጣም

ትልቅ ቤተሰብ ያለውና ልጆቹንም ለጌታ እንደሚያሳድግ ተናገረ፡፡ መምህራን፣ ሌሎች ብዙ ገበሬዎች፣ ባለ ሱቆች እና የከባድ መኪና ሹፌሮች፣ ልጆቻቸውና አሁን በዚያው ትምህርት ቤት በመማር ላይ ያሉ ተራ ክርስቲያኖች እርሱን ተከትለው በመምጣት ተናዘዙ፡፡

በዳውሮ ውስጥ በደርግ መንግሥት ለተጐዱ ብዙ ወጣቶች አዘንን፡፡ እነዚህ ወጣቶች፣ በጣም ትንሽ ሥልጠና ከተሰጣቸው በኋላ፣ በሰሜን የጦር ግንባር ለውጊያ ይላኩ ነበር፡፡ በሚያሳዝን መልኩ፣ አብዛኞቹ ከጦርነቱ አይተርፉም ነበር፡፡

ቅጣይ

ይህን መጽሐፍ እየጻፍኩ ሳለ፣ ኢያሱ በዳውሮ ውስጥ ለብዙ ዓመታት የነበረውን አገልግሎት አጠናክሮ ይረዳው ዘንድ፣ ኬኒያ፣ ናይሮቢ በሚገኘው በዴይስታር ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የማስትሬት ዲግሪውን በመሥራት ላይ ይገኝ ነበር፡፡ በዚያ አካባቢ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት በከፍተኛ ፍጥነት በመጨመሩ ምክንያት፣ የበሰለ መንፈሳዊ መሪነትን ከአስተዳደራዊ ክህሎትና ችሎታ ጋር በማያያዝ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ማስተማር የሚችል ሰው በጣም አስፈላጊ ነበር፡፡

> *‹‹ነፍሴን የሚሹ ሁሉ ይፈሩ ይጐስቍሉም፤ ክፉትን በእኔ ላይ የሚያስቡ ይፈሩ ወደ ኋላቸውም ይበሉ። በነፋስ ፊት እንዳለ ትቢያ ይሁኑ፣ የእግዚአብሔርም መልአክ ያሳድዳቸው።››*
>
> መዝሙረ ዳዊት 35፡4፣ 5

27

ጀሬናይ

የተበላሸ ሸክላ - አዲስ ዕቃ

ይህ ታሪክ ሙሉ በሙሉ የሚያስተምረን ‹‹ትዕቢት ከውድቀት እንደሚቀድም›› ነው፡፡ እንዲሁም ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሰጠውን ትእዛዝ እውነትነት ያስታውሰናል፡፡ ‹‹በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ፣ አዲስ ክርስቲያን አይሁን።›› ከዚህ በተጨማሪ ታሪኩ ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ርኅራኄው ገደብ-የለሽነት እንዲሁም የይቅርታ ጸጋው፣ የተበላሸ ሸክላን በማደስና ሌላ አዲስ አድርጎ በማበጀት መጠቀሙን ያሳያል፡፡ ነገር ግን ጠቃሚ የሆኑትን ዕቃዎች ደግሞ ወደ ፈተና እንዳይገቡ ሊጠነቀቁና ሊጸልዩ እንደሚገባ በማሳየት ትሕትናን ያስተማራል፡፡ 1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡6፤ ኤርምያስ 18፡4፤ ማርቆስ 14፡38፡፡

ጄሬናይ የጦረኛ ጎሳ ወገን ነበር፤ በዚህም ኩራት ይሰማዋል! በጣም ጐበዝ አታላይ እንደ ሆነም ይታወቃል፡፡ ማሄ በመጀመሪያ ወደ አካባቢው መጥቶ ለቤተሰቡ ስለ ኢየሱስ ከነገረ በኋላ አክስቱ ለጄሬናይ እንዲህ ብላ አለችው፣ ‹‹ያ ሰባኪ ልብህን ይሰርቀዋል፤ ይበላሃል፤ እርሱን በጭራሽ እንዳትሰማ፡፡›› ስለዚህም ማሄን እስኪሄድ ድረስ ሁሉም ተቃወሙት፡፡

ገዳይ የሆነ ወረርሽኝ በአካባቢው ተከስቶ ብዙ ሰዎችን በመግደሉ ምክንያት፣ በጣም ብዙ ሰዎች ፈሩ፡፡ ሁሉም እንስሶቻቸው ሞቱ፡፡ ሚስቱ በጣም ታመመች፤ ጀሬናይ መድኃኒት ለማግኘት ወደ ጠንቋዩ ሄደ፣ ነገር ግን ሊረዳው አልቻለም፡፡ አንዱ ጠንቋይ ደግሞ አሥራ ሰባት ነጫጭ ድንጋዮችን በመሬት ላይ ወርውሮ የወደፊት ነገሩን ለመተንበይ ሞክሮ ነበር፣ ነገር ግን

ምልከቱን ማንበብ አልቻለም።።

ክፉ መንፈስ ጀሬናይ አዲስ ቤት እንዲሠራ ይነግረዋል፣ ነገር ግን ቤቱን ሠርቶ ሲገባበት መንፈሱ ከዚያ ቤት ያስወጣዋል።። በአንድ ዓመት ውስጥ አራት ቤቶችን ሠራ፣ ነገር ግን መንፈሱ ይመጣና፣ ‹‹ቤቱን ለቅቀህ ውጣ ወይም ትሞታለህ!›› ይለው ነበር።። ጀሬናይ ሚስቱን ትቷት ሄደ፤ በመጨረሻም ፈታት።። ወደ ማሄ ሄዶ ለራሱ ትንሽዬ የሣር ቤት አቆሙ፤ ትንባሆ ማጨስ ጀመረ።። በጣም በታመመ ጊዜ እኅቱ ምግብና ቡና ይዛለት መጣች።። ሌሎች የታመሙ ሰዎች ጸሎታቸው ሰምሮ ድነትና ፈውስን ማግኘታቸውን ሰምቷል፣ ነገር ግን ይህ ለእርሱ አልሆነም።።

ወንጌላዊ ተክሌ አግኝቶት ወንጌል ነግሮት ነበር፣ ጀሬናይ ግን ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረም።። መተኛት አይችልም ነበር፣ እንዲሁም ዕረፍትና ሰላም አልነበረውም።። አእምሮው ተበጥብጧል፤ ከዕለታት አንድ ቀን፣ ከምሽቱ ስምንት ሰዓት ገደማ ላይ አንድ በቅርብ ጊዜ ጌታን ያገኘ ጎረቤቱ ‹‹ዬማዳ›› እርዳኝ ብሎ ወደ እግዚአብሔር በጸሎት ሲዘምር ሰማው።። ጀሬናይ ወባ ይዞት፣ እንዲሁም ፈርቶ እና ነቅቶ ነበር።።

ጀሬናይ እንዲህ አለ፣ ‹‹በድንገት በዙሪያዬ ደማቅ ብርሃን ተመለከትኩኝና ኢየሱስን አየሁት።። እርሱም እንዲህ አለኝ፡- ‹ብርሃኔ በልብህ ውስጥ ይብራ።። እመንና ተከተለኝ።።›› በጣም ከመፍራቱ የተነሣ፣ ጀሬናይ መናገር የቻለው ‹‹እሺ›› የሚለውን ቃል ብቻ ነበር።።

ጠዋት ላይ እኅቱ ስትመጣ፣ ምን እንደ ተከሰተ ነገራት።። እንደገናም ሰላም ሆነ።። ኢየሱስን ለመቀበልና በእርሱ ለማመን ወንጌላዊውን ለማግኘት እንደሚሄድ ነገራት፣ ነገር ግን እኅቱ በጣም ተናድዳ እንዲህ አለችው፡- ‹‹አይሆንም።። ይህ ስሕተት ነው!››

ስለዚህም ጀሬናይ ወጥቶ አማኝ ወዳልሆነው የቅርብ ጓደኛው ሄዶ ማታ ስላጋጠመው ነገር ነገረው።። ጓደኛውም እንዲህ የሚል ምላሽ ሰጠው፡- ‹‹አዎ፣ አንተ በእርሱ ማመንህ ልክ ነው።።››

ከዚያም ይበልጥ እርግጠኛ ለመሆን ፈልጎ ዘመዱ ወደ ሆነው ወደ አንድ ጠንቋይ ሰውዬ ሄዶ ሁኔታውን እንደገና ነገረው።። በሚያስገርም ሁኔታ ጠንቋዩም እንዲህ ብሎ መልስ ሰጠው ‹‹አዎ፣ በኢየሱስ ማመን አለብህ።።

ጐርፍ እንኳ መጥቶ ከረምቱን በሙሉ ቢያጠፋ፣ እንዲሁም ነፋስ በጋውን ሁሉ ቢያበላሽም፣ አንተ ግን ኢየሱስን መከተል ይገባሃል።››

ጂሬናይ እርግጠኛ ሆነና ለእጎቱ እንዲህ ሲል መልእክት ላከባት፣ ‹‹እባክሽን ቤቱን አጽጅልኝ። ወደ ቤት እየመጣሁ ነው።›› እርሷም እንደ ተባለችው አደረገች፣ እንዲሁም ጥቂት ምግብና ቡና አመጣችለት።

ጂሬናይ ፈገግ እያለ እንዲህ አለ፣ ‹‹‘እጸልያለሁ› ብዬ በመናገሬ አስደነገጥኳት። ከዚያም ‹ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ እኔ ሰይጣንን ክጃለሁ። አንተን ሁልጊዜ እከተላለሁ። ስለ ምግቡ አመሰግናለሁ። አሜን።’››

በመቀጠል እንዲህ አለ፣ ‹‹ከዚያም የሲጋራ ሱሰኛ ያደረገኝን ጋያ ሰበርኩት። እኅቴ በጣም ተናደደች፣ ነገር ግን እኔ እንዲህ አልኳት፣ ‘እኔ ኢየሱስን መርጫለሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህም እርሱ እኔ እንዳደረግ የሚፈልገውን ነገር ብቻ አደርጋለሁ።’››

‹‹ያን ዕለት ሌሊት የሚያስፈራ ሕልም አለምኩ- ከዲያብሎስ የተሰነዘረ ጥቃት ነበር። በጣም ትልቅ አውሬ ጎሮሮዬን አንቆኝ ነበር። በዚያን ወቅት እኔ አዲስ ክርስቲያን ነበርኩ፣ ነገር ግን ‘ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ እርዳኝ’ ብዬ ጩኸቴን አሰማሁ፤ አውሬውም ለቀቀኝ። በኢየሱስ ስም ነፃ ወጣሁኝ!›› ይህ ለአዲስ ክርስቲያን እጅግ በጣም አስፈሪ የሆነ ገጠመኝ ነበር።

ጂሬናይ በቤት ውስጥ የሚጸልዩ ክርስቲያኖችን አግኝቶ ነበር፣ እነርሱ ግን ፈርተውና መለወጡንም ተጠራጥረው ነበር። ‹‹በኢየሱስ አምኛለሁ እንዲሁም እንደ ጌታዬ አድርጌ ተቀብዬዋለሁ፣›› ብሎ ሲናገር ከመካከላቸው አንዱ በሰማ ጊዜ፣ ጌታ ይመስገን ብሎ አቀፈውና በጌታ ወንድሙ አድርጎ ተቀበለው።

ጂሬናይ ሄዶ ከሚስቱ ጋር ታረቀ። ሚስቱ ዘሯ ከጠንቋዩ ወገን ነበር። ትኖር የነበረው በወላጆቿ ቤት ውስጥ ነበር። በጂሬናይ ሕይወት ውስጥ የተከሰተውን ለውጥ በተመለከተች ጊዜ፣ እርሷም ኢየሱስን ተቀበለች፣ ስለዚህም ቤተሰቦቿ አባረሯት። የመጀመሪያ ሴት ልጃቸው ሞተች፤ ከዚያም ወንጌላዊ ጃራ ወደሚያስተምራቸውና እምነታቸውን ወደሚንከባከብበት ዛንጋ ወደ ተባለ፣ በሸለቆው ውስጥ ወደሚገኝ ስፍራ ሄደው በዚያ መኖር ጀመሩ።

ወዲያውም ጂሬናይ ከወንጌላውያኑ ጋር እየሄደ ወንጌልን መመስከር ጀመረ። በኋላ ላይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እርሱን እና ባለቤቱን፣ ከትንሽ

ሴት ልጃቸው ጋር፣ በማሄ አጠገብ ወደሚገኝ አንድ መንደር ሄደው እንዲኖሩና እንዲሰብኩ ላኳቸው፡፡ ይህ ጊዜ ከፍተኛ ራብ ተከስቶ ብዙ ሰዎች የሞቱበት ጊዜ በመሆኑ፣ በጣም አስቸጋሪ ጊዜ ነበር፡፡ ለሳምንታት ያህል ምንም ምግብ አልነበራቸውም፡፡ በሕይወት መቆየት የቻሉት ከጫካ ውስጥ በሚለቀም ቅጠላ ቅጠል፣ ፍራፍሬ እና ሥራ ሥር አማካይነት ነበር፡፡

ከዚያም ጀሬናይ በቡልቂ በሚገኘው የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ትምህርቱን ይከታተል ዘንድ ተላከ፡፡ በዚያ ስፍራም መምህር ሆነ፣ እንዲሁም በጎፋ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ መሪ እንዲሆኑ ከተመረጡት ሰዎች መካከል አንዱ ሆነ፡፡ የማርክሲዝም/ሌኒኒዝም አብዮት ሀገሪቱን የተቆጣጠረበት ጊዜ በመሆኑ፣ ጊዜው በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤትና የሚስዮናውያን ጣቢያዎች እንዲዘጉ ተደረገ፡፡ ጀሬናይ በኃዘን፣ ተስፋ በመቁረጥና እና በዕንባ ተሞልቶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡

አዲስ የተደራጀው የገበሬዎች ሥራ ማኅበር ጀሬናይን አጠቃላይ ጸሐፊያቸው አድርጎ ሾመው፡፡ በኋላ ላይም በአዲስ አበባ ያለው የኮምዩኒስቶች መንግሥት፣ ደርግ ‹‹በሕዝብ ተወካዮች-ፓርላማ›› እንዲቀመጥ አስጠራው፡፡ በፓርላማው ውስጥም ሁለት ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ ሰዎችን አገኘ፣ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች በኢ-አማኒያን ተጽዕኖ ምክንያት እምነታቸውን ወዲያው ለመተው ተገደዱ፡፡

ጀሬናይ እንዲህ ሲል አጫወተኝ፣ ‹‹ባለኝ ቦታና ሥልጣን ትዕቢት ያዘኝና ከጌታ ራቅኩኝ፡፡ ከጊዜ በኋላም በኃጢአትና በአልኮል፣ እንዲሁም በሲጃራ ውስጥ ወድቄ እነዚህ ነገሮች የሕይወቴ መገለጫ ሆኑ፡፡ ለስድስት ወራትም በምላሴ ውስጥ እንዳለ እሳት እስክመስል ድረስ ንዴቴ ይነድድ ነበር!›› ሚስቱም ተስፋ በመቁረጥ በየዕለቱ በዕንባ፣ ጌታ ሆይ፣ ጀሬናይን ይቅር በለው እያለች ትጸልይ ነበር፣ እርሱ ግን ልቡን አደነደነ፡፡

በፓርላማ ውስጥ ከነበሩ ሁለት ሰዎች ጋር በመሆን፣ ጀሬናይ የእርሻ ማሳዎችን፣ ፋብሪካዎችንና የነዳጅ ማምረቻ ጣቢያዎችን እንዲጐበኙ ወደ ቡልጋሪያ ተላኩ፡፡ ወደ ሀገራቸው በመመለስ ላይ ሳሉ፣ በግሪክ ሀገር አቴንስ ውስጥ ታሪካዊ ቦታዎችን በመጐብኘት ላይ ሳሉ ጀሬናይ ‹‹ለማይታወቅ አምላክ›› የሚለውን መሠዊያ ተመልክቶ ጳውሎስ የተመለከተውን አስታወሰ፡፡

ጌታም የጀሬናይን ልብ ነካው፡፡ በዚህም ምክንያት ማልቀስ ጀመረ፡፡ ከዚህም እንዲህ ሲል ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ፣ ‹‹ይህንን አምላክ እኔ አውቀዋለሁ- እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ቀድሞ እርሱን እከተል ነበር፡፡ እርሱ ብቸኛ እውነተኛ አምላክ ነው፡፡››

ከእርሱ ጋር የነበሩት ሰዎች ጀሬናይ ጭንቅላቱን ያመመው መሰላቸው፡፡ እዚያው እንዳለ ሊገድሉት ተመካከሩ፣ ነገር ግን እንደ ግሪክ ባለ የሰው ሀገር ውስጥ ይህንን ላለማድረግ ወሰኑ፡፡ ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ ግን ከሰሱት፡፡ ጀሬናይ ዓለማቸን በማይረባ ነገር የተሞላች መሆኗን ተገንዝቧል፡፡ ከሁሉም ነገር ይልቅ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ግንኙነት ብቻ ጠቃሚ መሆኑን ተረዳ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ የተሰበረና በጸጸት የተሞላ ሰው ሆነ፡፡

ጀሬናይ ከገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር ገንዘብ በመስረቅና በማባከን ወንጀል ተከሰሶ ታሠረ፡፡ በጣም ተደብድቦ፣ መሣሪያውን ተቀማና ‹‹ለሦስት ወራት›› በወህኒ ቤት ውስጥ ታሠረ፡፡ የኢትዮጵያ ምክትል ፕሬዚዳንት ጀሬናይ እንዲገደል ትእዛዝ አስተላለፉ፣ ነገር ግን እርሱ ራሱ ከመገደሉ በፊት እራሱ ማዘጋጋ ወረቀቱ ላይ አልፈረመም ነበረ፡፡ ጀሬናይ ‹‹የስድስት ወራት ቅጣት›› ተበየነበት፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ ባለቤቱ ትጸልይለት ነበር፡፡ ወደ 7000 የሚጠጉ የፖለቲካ እስረኞች በሚገኙበት ከፍት በሆነ መጥፎ እስር ቤት ውስጥ ሆኖ፣ ጀሬናይ መጽሐፍ ቅዱስ ያለው አንድ ሰው አገኘ፡፡ ምንኛ ውድ የሆነ ስጦታ ነበር! በሙሉ ልቡ ወደ ጌታ እንደገና ተመለሰ!

ለአሥር ወራት ‹‹ከተቀጣ›› በኋላ፣ ጀሬናይ ከእስር ቤት ተለቀቀና ወደ እርሻው ተመለሰ፡፡ የራሱ ውድቀት ሌሎችን እንዲወድቁ እንዳደረገው ተሰማው፡፡ ከሌሎች ክርስቲያኖች ፈጽሞ ለመደበቅ ፈለገ፡፡ ለብዙ ጊዜ ስትጨነቅ የኖረችው ሚስቱ ትጸልይለት ነበር፡፡ ሁለቱ የእርሻ በሬዎቹ ጠፍተው በአንበሳ ከተበሉ በኋላ፣ ጌታ ወደ አገልግሎት እንዲመለስ እንደሚፈልግ አወቀ፡፡ ተሰበረ፣ ተሸማቀቀም፡፡ እግዚአብሔርን ስለ ኃጢአቱ ይቅርታን ጠየቀው፤ ይህ ደግሞ ከጎፋ ቤተ ክርስቲያን ጋር ሙሉ በሙሉ እርቅ ለመፈጸም አዘጋጀው፡፡ ከጎፋ ክርስቲያኖች ጋርም ለብዙ ዓመታት የቆየውን የኮምዩኒስቶችን ጭቆና ተቋቋመ፡፡ የኮምዩኒስት ባለ ሥልጣናት ጥያቄ ሲጠይቁት እንዲህ በማለት ይመልስላቸው ነበር፣ ‹‹እግዚአብሔር ይወድደኛል! ኢየሱስ የእኔ ጌታ

ነው!››

የጂሬናይ የተለወጠ ሕይወት ሰዎች እንደገና እርሱን መሪ አድርገው እንዲመርጡት አሳመናቸው፡፡ በበሬዎቻቸውና በጉልበታቸው ከእርሱ ጋር በእርሻው ስፍራ በመሥራት ያግዙት ነበር፡፡ የኮምዩኒስት አገዛዝ መውደቅ ጂሬናይ ራሱን እንዲያሳድግ በጣም ብዙ ዕድሎችን ከፍቶለት ነበር፡፡ ነገር ግን ሁሉንም ዕድሎች የማይጠቅሙ አድርጎ ቁጠራቸው፡፡ እንደገና በዓለም መንገድ መሄድንም አልፈለገም፡፡

ከሚስቱና ቤተሰቡ ጋር እየጸለየ ሳለ፣ እግዚአብሔር እርሱን ወንጌላዊ እንዲሆን እንደሚፈልግ በልቡ ተሰማው፡፡ አብዛኞቹ ልጆቹ ትምህርት ቤት ገብተው ነበር፣ የእርሻውንም ሥራ እነርሱና ሚስቱ መሥራት ጀመሩ፡፡ ወደ ተራራው ጫፍ ወጥቶም ቤተ ክርስቲያን ተከለ፡፡ ያች ቤተ ክርስቲያን በደንብ ስትደራጅም፣ ትንሽ ከዚያ ፈቀቅ ብሎ በአሪ ሕዝቦች መካከል ሌላ ቤተ ክርስቲያን ጀመረ፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ለጂሬናይ ኃይል እንዳስታጠቀው ግልጽ ነበር፣ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች እርሱ ለሚሰብከው ወንጌል ምላሽ ይሰጡ ነበርና ነው፡፡ ይህ ወንጌላዊ ትሑትና የአገልጋይነት ልብ ነበረው፡፡ ያችም ቤተ ክርስቲያን አድጋ የራሷ መጋቢና ሽማግሌዎች ሲኖሯት፣ ጂሬናይ ወደ ሌላ ራቅ ወደ አለ ስፍራ ሄደ፡፡ በዚያም አዲስ ቤተ ክርስቲያን ተክሎ ማሳደግ ጀመረ፡፡

ᚕᚖᚗ

እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱና ርኅራኄው እያመሰገነው ለሁለት ቀናትና ሌሊት ስንጸልይ ቆየን፡፡ ሁሉም የቤተሰቡ አባላት በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ማመን በመምጣታቸው እግዚአብሔርን አመሰገንን፡፡ አንዱ ልጁ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ ሲሆን፣ ሌላኛው ልጁ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ውስጥ ዳኛ ነው፣ ሌላኛው ደግሞ በአንድ የመንግሥት ሆስፒታል ውስጥ ዶክተር ነው፣ ሴት ልጁ ደግሞ ሁለተኛ ዲግሪዋን በውጭ ሀገር በመሥራት ላይ ትገኛለች፡፡

ጂሬናይ እንዲህ አለ፣ ‹‹እግዚአብሔር በዚህ ሁሉ ውስጥ እንዲሄድ ፈቀደ፣ ነገር ግን ደግሞ ደኅንነቴን ጠብቆ እንድመለስ አደረገ፡፡ ብዙ ሰዎች በኢየሱስ የሚያምኑት በእርሱ ጸጋ ብቻ ነው፡፡ ይህ ከእኔ አይደለም፡፡ ስለዚህም እርሱን አመሰግናለሁ›› አለኝ፡፡ በዚያም ምስጋና ከእርሱ ጋር ተባበርኩኝ፣ እንዲሁም በታማኝነት ስትጸልይ ለነበረችው ሚስቱ ለጸሎቷ ምላሽ እግዚአብሔር በመስጠቱ አመሰገንኩት!

❧

እንደ አውስትራሊያ ባሉ ሀገራት የመኖር ዕድል ኖሮኝ እንዲህ ያለውን ነገር ከመመልከት ርቄ፣ ነገር ግን ከኢ-አማኒያን የጨለማ እምነት፣ ብዙ ክፋትና ፍራቻ ካለበት የመጡ ሰዎች ሲደናቀፉና ሲወድቁ ተመልክቼ ሰዎችን የመተቸት ወይም የመውቀስ መንፈስ ካለን፣ ከእኔ የራቀ ይሁን፡፡ ብዙ የክርስቲያኖች ትውልድና ትምህርት ከኋላዬ ያለኝና አስፈላጊ የሆነው መንፈሳዊ መረጃዎችና የመጽሐፍ ቅዱስ ማስተማሪያ በገዛ ቋንቋዬ ያለኝ፣ እንዲህ ያለ ያለፈ ታሪክ ወይም ትምህርት ወይም መረጃ መሣሪያና በራሳቸው ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ የሌላቸውን፣ ነገር ግን በሁለተኛ ወይም በሦስተኛ ወይም በአራተኛ ቋንቋዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ የሚገደዱ ሰዎችን እምነት የመተቸቱ ነገር ከእኔ ይራቅ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱሴ ውስጥ ‹‹የእግዚአብሔር ልብ ያለው›› የተባለለትን የዳዊትን ታሪክ ሳነብብ እንዲሁም ከኢየሱስ ጋር ለሦስት ዓመታት በመቆየት የእግዚአብሔር ልጅን ትምህርት በቀጥታ ሲሰማ የቆየውን የጴጥሮስን ታሪክ ሳነብብ፣ ከታላቁ ሚስዮናዊ ጋር አብረው የነበሩትን ዮሐንስ ማርቆስንና ዴማስን ስመለከት፣ እንዲሁም የራሴን የጥርጣሬና ውድቀት ጊዜያት ሳስታውስ፣ እኔ ምንም ስደት ደርሶብኝ የማላውቅ፣ ተደብድቤ፣ ተገርፌ ወይም ታሥሬ የማላውቅ ሰው በክርስቶስ ወንድሜ የሆነውን የመተቸትና የመውቀስ ነገር ከእኔ የራቀ ይሁን፡፡ በጭራሽ እንደዚያ ማድረግ የለብኝም! ይልቁንም፣ ስለ ኢየሱስ ለታሠሩትና መከራን እየተቀበሉ ላሉት ሰዎች በዕንባ ልማልድ፡፡

❧

‹‹ለዘላለም የሚኖር ሰሙም ቅዱስ የሆነ፣ ከፍ ያለው ልዑል እንዲህ ይላል፦ ‹‹የተዋረዱትን ሰዎች መንፈስ ሕያው ሊደርግ ዘንድ፣ የተቀጠቀጠውንም ልብ ሕያው ሊደርግ ዘንድ፣ የተቀጠቀጠና የተዋረደ መንፈስ ካለው ጋር በከፍታና በተቀደሰ ሰፍራ እቀመጣለሁ።››

ኢሳይያስ 57፡15

28

ጫጫ

በጌታ መዳሰስ

ባሳ እየሞተ ነው፡፡ ለሳምንታት ሲታመም ቆይቷል፣ አሁን ደግሞ በጣም ደክሟል፡፡ ቤት ሄዶ እንዲሞት ከሶዶ ሆስፒታል ሐኪሞቹ ወደ ቤቱ ሰድደውታል፡፡ በእርግጥም እየሞተ ነው፡፡ ወደ አርባ ምንጭ እባክህን ነገ ይዘኸው ሂድ፡፡ በዚያ ከውጭ ሀገር የመጡ ዶክተሮች ስላሉ እነርሱ ምናልባት ሊረዱት ይችሉ ይሆናል፣›› በማለት አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለመነኝ፡፡

ይህ ወቅት ‹‹ቀይ ሽብር›› ተብሎ የሚጠራና የደርግ ኮምዩኒስት አብዮታዊ ፓርቲ ሁሉንም ተቃዋሚዎችን በመደምሰስ የማርክሲዝም/ሌኒኒዝም ርዕዮተ ዓለም ብቻ እንዲኖር ለማድረግ ጥረት የሚያደርግበት ጊዜ ነበር፡፡ በወታደራዊ ኃይል የሚገዛው የደርግ መንግሥት ኮምዩኒስቶችን እያሠለጠነ የተለያዩ አውራጃዎችን እንዲያስተዳድሩ ያደርግ ነበር፡፡ የእነዚህ አስተዳዳሪዎች ሥልጣን ፈጽሞ ገደብ-የለሽ ነበር፡፡ በጣም ብዙ ካድሬዎችን በመጠቀም ሰዎችን የማርክሲዝም/ሌኒኒዝም ርዕዮተ ዓለም አስተምህሮን ያስተምሩ ነበር፤ እንዲሁም ማንኛውንም የሚቃወማቸውን ሰው ያጠፉ ነበር፡፡

በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ተገድለዋል፤ የዚህ ጥቃት ተጐጂ ብዙ ጊዜ የሚሆኑት ሰዎች ሀብታሞች፣ የተማሩ፣ ባለ ሥልጣናት እና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበሩ፡፡ በጣም ብዙ ሺህ የሚሆኑ ሰዎች በወህኒ ቤት ውስጥ ታጉረዋል፣ ተገርፈዋል እንዲሁም በግዴታ ‹‹እንደገና ሥልጠና›› እንዲወስዱ ተደርገዋል፡፡ ሰላዮችም በየስፍራው ‹‹ሕዝባዊውን አብዮት›› የሚቃወሙ ሰዎችን ያድኑ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያናት ተዘግተዋል፣ ክርስቲያኖች እርስ

በርሳቸው እንዳይገናኙ ታግደዋል፣ መጽሐፍ ቅዱሶች ተቃጥለዋል፣ እንዲሁም ምንም ወንጀል የሌለባቸው ንጹሕ ሰዎች እስር ቤቶችን ሞልተውታል። በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ አጎራባች ሀገራት ተሰድደዋል። ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ይህ ያለ ጥርጥር በጣም መጥፎ ጊዜ ነበር።

ለሁለት ወራት ወደ ወላይታ ለጉብኝት በሄድኩበት ጊዜ መጋቢያን፣ ወንጌላውያንን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች፣ ‹‹በዚህ ኢ-አማኒ መንግሥት ውስጥ እንዴት ህልውናችንን ጠብቀን መቆየት እንችላለን?›› ሲሉ ጠየቁኝ። ሚስዮናዊ በመሆን በዚያ አካባቢ ለብዙ ዓመታት አገልግለናል። ከእነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር በምሽት በተለያዩ ቦታዎች በምሥጢር ተገናኝተን ስብሰባ አድርገናል። እኔም ለተሸበሩ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል አካፍያለሁ፣ በዚያ አጋጣሚ በተመሳሳይ ሁኔታ በሩሲያ፣ በቻይና እና በኩባ ውስጥ ያሉትን ሕዝቡን እግዚአብሔር እንዴት እንደ ጠበቀ ነገርኳቸው። ስለዚህ እኛም እንዲሁ እግዚአብሔር ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስና ለቃሉ ታማኞች እንሆን ዘንድ እንዲጠብቀን አንዱ ለሌላው ጸሎት አደረግን።

በሚቀጥለው ቀን፣ በጠዋት ወደ አርባ ምንጭ መሄዴን ሲሰሙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ባሳን ይገፎው እንድሄድ ለመኑኝ። ይህ የባሳን ሕይወት ለማትረፍ የመጨረሻው ዕድል እንደ ሆነ አድርገው ተመለከቱት። በድፍረት ስለ ክርስቶስ የሚመሰክር በመሆኑ ምክንያት ብዙ መከራ የቀመሱ ሚስትና ሰባት ልጆች ያሉት፣ በጣም ተወዳጅ የሆነ መጋቢና ወንጌላዊ ነበር። ባሳን ይገፎ ለመሄድ ተስማማሁ፣ ነገር ግን በመንገድ ላይ እንዳይሞትብኝ ተሰፋ አደረግኩኝ።

የቤተሰቡ አባላትና ጎረቤቶቹ ባሳን ሌሊቱን በሙሉ ተሸክመውት ጠዋት በጊዜው ፀሐይ መውጣት ሊጀምር ሲል ደረሱ። ባሳ በጣም ቀጭን፣ ደካማና ሊሞት የተቃረበ በመሆኑ፣ አስቸጋሪ በሆነው የአርባ ምንጭ መንገድ ላይ እርሱን ይዞ መሄድ ብልህነት መስሎ አልታይ አለኝ። በአባያ ሐይቅ አጠገብ ስንሄድ ከአንድ ጉድጓድ ወደ ሌላኛው እየተንገጫገጭን ዘለልን፣ ነገር ግን ሆስፒታሉ ወደሚገኝበት ስፍራ ስንደረስ ባሳ ገና በሕይወት ነበር። ለሕክምና ባለሙያዎቹ በደስታ እርሱን አስረክቤ ወደ መንግሥት ባለ ሥልጣናት ቢሮ በፍጥነት ሄድኩኝ።

ከስካንዲኔቪያን ሀገሮች የመጡ ዶክተሮችና ነርሶች ባሳን ከተቀበሉ በኋላ፣ በጣም ብዙ ምርመራ አደረጉለት፣ መርፌ ወጉት እና አረጋጉት፡፡ የምርመራው ውጤት ባሳ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ የስኳር በሽታ እንዳለበት ያሳየ ሲሆን፣ ይህም የምርመራ ውጤት ከዚህ በፊት ምርመራ ካካሄደበት ሦስት የሕክምና ማዕከላት ውጤት ጋር ተመሳሳይ ነበር፡፡ የእኛ ጓደኛ የሆነ ሚስዮናዊ ለባሳ በቅርቡ እንደሚሞት ነገረው፡፡ ስለዚህም ‹‹ለቤትህ ሥርዓት አበጅለት›› አለው፣ ‹‹ያለብህን ዕዳ ሁሉ ክፈል፡፡ ያበደርካቸውን ሁሉ ሰብስብ፡፡ ያዳነህን ጌታ ለመገናኘት ራስህን አዘጋጅ›› ብሎ ነገረው፡፡

ባሳ በሆስፒታል ሳለ የሰማው መጥፎ ዜና ኢንሱሊን የሚባለው መድኃኒት በኢትዮጵያ ውስጥ በዚያን ጊዜ እንዳልነበረ ነው፡፡ የማርክሲስቶች መንግሥት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ስላናጉትና በጣም ብዙ ብድር ስለ ተበደሩ፣ ወደ ሀገሪቱ የሚመጡ ምግቦችና መድኃኒቶች መግባት አቁመው ነበር፡፡ ዶክተሮቹ ለባሳ የነበራቸውን የተወሰኑ እንክብሎች የሰጡት ሲሆን፣ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ግን ኢንሱሊን መወጋት እንዳለበት ነገሩት፡፡ በእርግጥ፣ ለባሳ የወደፊቱ ነገር ጨለማ ሆኖበት ነበር፡፡

ከመንግሥት ባለ ሥልጣናት ቢሮ ወደ ሆስፒታሉ ስመለስ መሸቶ ነበር፡፡ (ዶክተሩ በመመለሴ ተገርሟል፣ ነገር ግን ያ በራሱ ሌላ ታሪክ ነው!) ባሳ በጣም ተሸሎት ተመለከትኩኝ፣ እንዲሁም ወደ ቤቱ ይገፍው እንድመለስ ጠየቀኝ፡፡ መንገዳችንን ከመጀመራችን በፊት ጸለይን፣ ከዚያም እኩለ ሌሊት ላይ በሰላም በመድረሳችን እግዚአብሔርን አመሰገንን! ከዚያ ባሳን፣ ‹‹እግዚአብሔር ይባርክህ እንዲሁም ይጠብቅህ›› ብዬ፡፡ ተሰናበትኩት፣ ያለ ኢንሱሊን መርፌ ለረጅም ጊዜ በሕይወት ይኖራል ብዬ አልገመትኩም ነበር፡፡

ꕥ

ባሳ እግዚአብሔር ‹‹በመከራና በችግር›› ውስጥ በማሳለፍ እንደ ወንጌል መልእክተኛ ሊገጥመኝ የሚችለውን ችግርና ተቃውሞ መቋቋም እንድችል አዘጋጅቶኛል በማለት ተናገረ፡፡ የባሳ አባት የዚያ ጎሳ ኃይለኛ የጠንቋይ ዘር ነበር፡፡ የሞተው ባሳ በተወለደበት ዓመት ነበር፡፡ አጎቱ በጣም ዐመፀኛና የወንድሙን መሬት ለራሱ ለማድረግ የቈረጠ ሰው ነበር፡፡ መሬቱ የባሳ አባት

ለልጁ ለባሳ ያወረሰው ርስት ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ አጎቱ የወንድሙን የሰይጣንን ኃይል ለማግኘትና የጎሳውን መሪነት ለመውሰድ ይፈልግ ነበር፡፡ ይህንን ለማድረግ በመንገዱ ላይ ያለው ይህ ትንሽ ልጅ ብቻ ነበር፡፡

ይህንንም በጣም የፈራችው የባሳ እናት ወደ ወላጆቿ ቤት ተመልሳ ሄደች፡፡ ነገር ግን ልጁን በደንብ አልያዙትም፣ እንደ ባሪያ ያሠሩት ነበር እንጂ፡፡ በመጨረሻም፣ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ገደማ ሲሆነው ሊገድለው ወደሚፈልገው አጎቱ ዘንድ፣ ወደ አባቱ መሬት ተመልሶ መጣ፡፡ ‹‹ይህ ደግሞ ከመጣሁበት ይበልጥ በጣም የከፋ ስፍራ ነው፣›› ሲል ባሳ ተናገረ፡፡ ‹‹ዕለት ዕለት ስለሚዝትብኝ እፈራው ነበር፡፡ የምሄድበት ቦታም አልነበረኝም›› አለ ባሳ፡፡

ባሳ ማንበብን መማር እፈልጋለሁ ብሎ ሲጠይቅ፣ አጎቶ ይህን ኢጋጣሚ ተጠቅሞ ባሳን ከዚያ አካባቢ በማራቅ የጎሳው መሪ ሆነ፤ በዚሁ ለመቀጠል መልካም ኢጋጣሚ የሚፈጥረለት መስሎት ነበር፡፡ ወደ አንድ ሽማግሌ የኦርቶዶክስ ቄስ ዘንድ ወስዶ ባሳን እንዲያስተምረውና ኦርቶዶክስ እንዲያደርገው ጠየቀው፡፡ ሽማግሌው ቄሱም ባሳን በደንብ ከመረመረ በኋላ፣ ‹‹ይህ ልጅ መቼም ቢሆን ኦርቶዶክስ አይሆንም፤ እንዲሁም መቼም ቢሆን እስላምም አይሆንም፤ የሰይጣን ተከታይም አይሆንም፡፡ ይህ ልጅ የሌላ መንፈስ ነው- ይህ መንፈስ ደግሞ ከሁሉም በላይ ኃይለኛ ነው›› አለው፡፡ በቄሱ መልስ የተበሳጨው የባሳ አጎት የተለያዩ ‹‹አደጋዎችን›› በእርሱ ላይ ለማድረስ ሙከራ አደረገ፡፡ ነገር ግን በእያንዳንዱ ሙከራ ባሳ ላይ ጉዳት አይደርስም፡፡ ይህ ሁኔታ የእግዚአብሔር ጥበቃ እንደ ሆነ ተረድቷል፡፡

ባሳ ለመጀመሪያ ጊዜ የክርስቶስን ወንጌል ሲሰማ የነ6 ዓመት ልጅ ነበረ፡፡ ለእግዚአብሔር ፍቅር ምላሽ በመስጠት የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታን ተቀበለ፡፡ የሰይጣንን መንገድ በመካድ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙና ጌታው ተቀበለ፡፡ ‹‹ኢየሱስ ጣፋጭ ሆኖ አገኘሁት፣›› አለኝ፡፡ አጎቱም አሁንም ይህን ኢጋጣሚ በመጠቀም ወዲያውኑ ባሳን ከመሬቱ ላይ አባረረው፡፡ ስለዚህም ኢየሱስን መከተል የሚያስከፍለውን ዋጋ መቀኑጠር ጀመረ፡፡ ለብዙ ወራት ችግርና ራብን ቀመሰ፤ አንዳንድ ጊዜም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በትንሽ

ምንጣፍ ላይ ይተኛ ነበር፡፡ በቤተ ክርስቲያን መጋቢው ለትንሽ ወራት ትምህርት ከተከታተለ በኋላ፣ በአካባቢው በሚገኝ አንድ ትንሽ ጅረት ውስጥ፣ ባሳ ከሌሎች ብዙ ሰዎች ጋር ተጠመቀ፡፡ መጽሐፍ ቅዱን ለራሱ ለማንበብ ልዩ ራብ ነበረው፡፡ ስለዚህም ትምህርት መማር ጀመረ፣ አራተኛ ክፍል ድረስም ተማረ፡፡ በክርስቲያኖች እንቅስቃሴ በእያንዳንዱ ውስጥ ተሳትፎ ያደርግ ነበር፣ እንዲሁም ለሌሎች መመስከርም ጀመረ፡፡

አማኞችን የእርሱን መንፈሳዊ ስጦታ ተረድተው ብዙ ጊዜ ከእርሱ ጋር ይጸልዩ ነበር፣ እንዲሁም ጌታን ያገለግል ዘንድ ባሳን ያበረታቱት ነበር፡፡ በሕጋዊ መንገድም የአባቱን መሬት ማግኘት የሚችልበትን መንገድ ክርስቲያኖች ያሳዩት ነበር፡፡ ትንሽ የሣር ጎጆ መሥራት እንዲችልና አንዲት ክርስቲያን እኅት ፈልጎ እንዲያገባም ረዱት፡፡ ባሳ እያደገ የነበረውን ቤተሰቡን በደንብ ማስተዳደር እንዲችል በእርሻው ተግቶ ይሠራ ነበር፡፡ ከዚያም አማኞች ባሳን መጋቢያቸው አድርገው መረጡትና በጸሎት፣ ስብከትን በማዘጋጀትና የእግዚአብሔር ቃል በማጥናት ብዙ ሰዓታትን ያሳልፍ ጀመረ፡፡

እግዚአብሔር ቃሉን እየባረከ፣ ሰዎችም ለስብከቱ ምላሽ እየሰጡ በሄዱ ቍጥር፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከሳምንት ወደ ሳምንት እያደገች ሄደች፡፡ እነዚያ ጊዜዎች በጣም ጥሩ የባርኮት ጊዜዎች ነበሩ፣ ነገር ግን ያለ ምንም ተቃውሞ አልነበሩም፡፡ ብዙ ሰዎች ወደ ክርስቶስ እየመጡ ሲሄዱ፣ የኢ-አማኒነትን አኗኗር መንገዳቸውን ተዉ፡፡ በአንጻሩም፣ ብዙ ጊዜ ሰዎች ባሳን ‹‹ሃይማኖታችንን አጠፋ›› በማለት በሐሰት ይመሰክሩበት ነበር፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ሁልጊዜም ባሳን በነፃ ያሰናብተው ነበር፡፡ ባሳ በስኳር በሽታ ታምሞ የተኛ ጊዜ እርሱና ባለቤቱ ሰባት ልጆች ነበሯቸው፡፡

ﻩﻩﻩ

ለትንሽ ቀናት ባሳ ጥሩ ሁኔታ ላይ ነበረ፣ መድኃኒቱንም ሐኪሙ እንዳዘዘው ጠዋት ጠዋት ይወስድ ነበር፡፡ ከዚያም ቀስ በቀስ የጤናው ሁኔታ እየተበላሸ ሄደ፤ ጥንካሬውም እየመነመነ ሄደ፡፡ በጣም ትንሽ ይመገብና አብዛኛውን ጊዜ በአልጋው ላይ ተኝቶ ያሳልፍ ነበር፡፡ ወደ መጸዳጃ ቤት ለመሄድ ብቻ ቀስ ብሎ እየተንፏቀቀ ይሄድ ነበር፡፡ ብዙ ክርስቲያኖች መጥተው ጸልየውለታል፣ ነገር ግን ከዕለት ወደ ዕለት የጤናው ሁኔታ እየባሰበት መጣ፡፡ እንደሚሞት ስላወቀ፣

እግዚአብሔር ወደ ቤቱ ወደ ሰማይ ይወስደው ዘንድ ጠየቀ፡፡

የተቀሩትን እንክብሎች ይዞ እየተንቋቀቀ በጓሮው በኩል ወደሚገኘው መጸዳጃ ቤት ሄደ፡፡ ‹‹በኢየሱስ ስም›› ብሎ በመጮኽ ሁሉንም እንክብሎች ወደ ጉድጓዱ ውስጥ ጨመራቸው፡፡ ‹‹ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ እባክህ ዳስሰኝ፣ አንተን ብቻ አምናለሁ፣›› በማለት ጸሎት አደረገ፡፡ አንድ በጣም አስገራሚ ነገር ተፈጠረ! በድንገት ሙሉ በሙሉ አካሉ ጥንካሬ ተሰማው! ተነሥቶም ቆመ- ይህንን ነገር ለብዙ ወራት አድርጎት አያውቅም ነበር፡፡

‹‹እግዚአብሔር ይመስገን! እግዚአብሔር ይመስገን! ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ፈውሶኛል!›› ብሎ ጮኸ፡፡ ‹‹ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ዘመኔን በሙሉ አንተን አገለግላለሁ፡፡ በፍቅርህና በጸጋህ ሙላኝ፡፡ ስለ አንተ ለሰዎች ሁሉ እመሰክራለሁ፡፡ ለአንተ ታማኝ እንድሆን ጠብቀኝ›› እያለ ጸለየ፡፡ ባሳ እየጮኸና እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሳለ፣ ሚስቱና ልጆቹ እየሮጡ መጡ፡፡ ወዲያውም ጎረቤቶቹ የተፈጠረውን አስገራሚ ነገር ለመመለክት ተሰበሰቡ፡፡ ‹‹እየሞተ የነበረ ሰው›› አሁን ደኅና ሆኖ በደስታ ሲዘልል በመመልከታቸው እጅግ በጣም ተገረሙ፡፡

ባሳ ሁሉም ሰው ወደ ጸሎት ቤት መጥቶ ከእርሱ ጋር እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን ተማጠነ፡፡ ነገር ግን የኮምዩኒስት ባለ ሥልጣናት ቤተ ክርስቲያንን ዘግተው ነበር፣ እንዲሁም ክርስቲያኖች እንዳይሰበሰቡ ተከልክሎ ነበር፡፡ ይህ ነገር ባሳን አላገደውም፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻን እንደገና በመክፈት ከቤተሰቡና ወደዚያ ስፍራ ለመምጣት ድፍረቱን ካገኙ ሰዎች ጋር በመሆን አምልኮን መምራት ጀመረ፡፡ ከዚያም በኋላ እስኪጨልም ድረስ በመንደር ውስጥ ይመላለስና ለሰዎች ሁሉ ኢየሱስ እንደ ፈወሰው ይናገር ነበር፡፡ ማንኛውም ዓይነት ምግብ ይመገብ ጀመር፣ ይህም በእርሱ ላይ ምንም ችግር አላስከተለበትም ነበር፡፡

ይህ ሁኔታን ባሳን አዲስ ዓይነት የወንጌል አገልግሎት እንዲጀምር አደረገው፡፡ በእያንዳንዱ ቀን በአካባቢው ወዳሉት መንደሮች በመሄድ ወንጌልን በመስበክና ስለ እግዚአብሔር ጸጋና ስለ ፈወሰው ኃይል ምስክርነት ይሰጥ ነበር፡፡ በጣም ረጅም ጉዞ ይጓዝ ነበር፣ በየቀኑም ወደ ገበያ ስፍራዎች፣ በሶዶ

ወደሚገኘው ትልቁ የገበያ ስፍራ እንኳ ሳይቀር - በምሥራቅ ወደ ፋንጎ ለሁለት ቀናት፣ በምዕራብ ወደ ኪንዶ ለሁለት ቀናት፣ በሰሜን ወደ ቦሎሶ ለሁለት ቀናት፣ በደቡብ ወደ ሁምቦ እና በእነዚህ መካከል ወዳሉት መንደሮች ሁሉ፣ እንዲሁም ከብላቴ ወንዝ ጀምሮ እስከ ምሥራቅና ከአሞ ወንዝ እስከ ምዕራብ ድረስ ይሄድ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ 10000 ጫማ (3050 ሜትር) ከፍታ ወዳለው ዳሞታ ተራራ ላይ ወደሚገኙ መንደሮች እንኳ ይሄድ ነበር። ከዚያ ወዲህ ወንጌል ስርጭት ሕይወቱ፣ ሥራው ሆነ። በየቀኑ ባሳ ስለ እግዚአብሔር ኃይል ይመሰክር፣ ብዙ ሰዎችንም በክርስቶስ እንዲያምኑ ያደርግ ነበር።

እሑድ ማለዳ ቤተ ክርስቲያንን ለጸሎት ለመክፈት፣ በየሳምንቱ ቅዳሜ ምሽት ወደ መኖሪያ ቤቱ ይመለስ ነበር። የሚመግባቸውን ሰዎች በአምልኮና ምስጋና ይመራቸው ነበር። አንዳንድ ሰዎች ለመንግሥት ባለ ሥልጣናት የሆነ ሰው ቤተ ክርስቲያንን እንደገና በመክፈት የመንግሥትን ትእዛዝት መጣሱን ነገሯቸው። ባሳ ለጥያቄ ተጠራ፣ ነገር ግን ማንም ሰው እርሱ በተኣምራት መዳኑን ወይም የእርሱን ምስክርነት መካድ አልቻለም። ይሁን እንጂ፣ ይህንን ነገር ማድረግ እንዲተውና አርፎ እንዲቀመጥ ማስጠንቀቂያ ተሰጠው። ለሁለተኛ ጊዜ ይህን ነገር አድርጎ ቢያዝ እንደሚቀጣ ማስፈራሪያ ደረሰው። ከዚያም ያንኑ ሲያደርግ ተያዘ፣ ነገር ግን በእስር ቤት ውስጥ መስበኩን በመቀጠል የጸሎት ቡድን አቋቋመ!

ከሦስት ወራት በኋላም፣ ባሳ ከእስር ሲፈታ ወደ ቤቱ ሄደና እንደገና ቤተ ክርስቲያኒቱን ከፈተ። መስማት ለሚፈልጉ ሰዎች ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነቱን መስጠቱን ቀጠለ። እሑድ እሑድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰበከ! ከባሳ ቤተ ክርስቲያን ውጭ፣ በወላይታ ውስጥ ከ700 በላይ የሚሆኑ ቤተ ክርስቲያናት ተዘጉ ወይም ፈርሱ። ከዚያም እርሱ ታሰረ፣ ተደበደበ እንደገናም ወደ ወህኒ ቤት ተወሰደ። በዚያ እስር ቤት ውስጥ ግን የሚያደምጡት ሰዎች ነበሩት። ለእስረኞቹና ወህኒ ቤት ጠባቂዎቹ ስለ እግዚአብሔር ጸጋና ፍቅር እንዲሁም በክርስቶስ ለሚያምኑ ሰዎች ክርስቶስ ልብንና ሕይወትን ለመለወጥ ስላለው ኃይል ይመሰክርላቸው ነበር። ለአዳዲስ አማኞች ሌላ የጸሎት ቡድን አቋቋመ!

ባሳ አሁን ከእስር ቤት ሲፈታ ወደ ቤቱ ሄደና እንደገና ቤተ ክርስቲያኒቱን ከፈተ! እንደገና ተይዞ ታሰረ! ሰባት ጊዜ ያህል ተይዞ ታሰረ! በእርግጥም፣ ሰባት

ጊዜ ያህል ወደ ወህኒ ቤት ተጥሏል፡፡ አንዳንድ የኮምዩኒስት ባለ ሥልጣናት ይህ ሰው ዕብድ ነው ብለው አሰቡ፡፡ በመጨረሻም ባለ ሥልጣናቱ ተስፋ ቆረጡ! በዚያ ጊዜም የማርክሲዝምን/ሌኒኒዝም መንግሥት ውጥረት ውስጥ ገባ፣ ሠራዊቱም ተሸነፈና አዲስ መንግሥት ኢትዮጵያን ማስተዳደር ጀመረ፡፡

ሚስቱና ሴት ልጁ ትኵስ ምግብ እያዘጋጁልን ሳለ፣ እኔና ባሳ በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ አብረን ተቀምጠን ነበር፡፡ ባሳ በእኔ ላይ እየሳቀ እንዲህ አለ፣ ‹‹እግዚአብሔርን የማመሰግንበት ብዙ ነገር አለኝ፡፡ ከአጎቴ ጥላቻና እኔን ለማጥፋት ከሚያደረግው ጥረት ሁሉ አድኖኛል፤ በልጅነቴ ባሳለፍኳቸው አስቸጋሪና የጭንቅ ጊዜያት ሁሉ ውስጥ ተንከባክቦኛል፣ ከአርቶዶክሳውያንና በዘሬ ውስጥ ካለው የጥንቁላ ሥርዓትም ነፃ አውጥቶኛል፤ ከዚያ መጥፎ የስኳር በሽታ ፈውሶ ከዚህ በኋላም ለሃያ አምስት ዓመታት በሕይወት እንድኖር አድርጎኛል፣ ለሰባት ጊዜያት ያህል በኮምዩኒስቶች እስር ቤት ውስጥ ስታሰር ጠብቆኛል፡፡ እንዲሁም በቦሎሶ ውስጥ ከሚገኘው የአጆራ ፏፏቴ ላይ ተወርውሬ እንድገደል ከተወሰነብኝ የሞት ውሳኔም አድኖኛል፡፡›››

ምግብም አብረን እየተመገብን ሳለ፣ ባሳ በመቀጠል እንዲህ አለ፣ ‹‹ጌታ ኢየሱስ ዳስሶ ፈጽሞ ፈውሶኛል፡፡ ይህንን ሁኔታ ትናንት እንደ ተፈጸመ አድርጌ አስታውሰዋለሁ፡፡ ቀኑ (የካቲት 29፣ 1967 ዓ.ም (ማርች 6፣ 1984) ወደ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ ነበር፡፡ ወደ ሃያ አምስት ዓመታት አልፈውታል፤ እግዚአብሔር በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ጤናማ አድርጎ አኑሮኛል፡፡ ሁሉንም ነገር እበላለሁ፡፡ አሁንም ጠንካራ ነኝ፡፡ ወደ ፈለግኩበት ቦታ ሁሉ እሄዳለሁ፡፡ እግዚአብሔርን ስለ ጸጋ ስጦታውና ስለ ፈውሱ አመሰግነዋለሁ፡፡›››

ባሳ እና ሚስቱ በነበራቸው ሰባት ልጆች ላይ፣ በእነዚያ ሃያ አምስት ዓመታት ውስጥ፣ አምስት ተጨማሪ ልጆችን ወልደዋል፡፡ ጥቂቶቹ ትዳር መሥርተዋል፤ አንዲ ሴት ልጃቸው በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ስትሆን፣ ሦስቱ ግን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ብቻ አጠናቅቀዋል፤ የተቀሩት ሦስቱ ግን ገና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ናቸው፡፡ በትልቁ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ ከአንድ ሺህ በላይ የሚሆኑ ሰዎችን ይይዛል፣ ሁላችንም በጉልበታችን ተንበርክከን በአንድነት ጸሎት አደረግን፡፡ ባሳ ያችን ቤተ ክርስቲያን ለሠላሳ ሰባት ዓመታት

አገልግሏል መግቧል፡፡ በወላይታ ቀጣና ውስጥ በሚገኙ ሰማኒያ አምስት ቤተ ክርስቲያናትን ባቀፈው የወላይታ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የቦርድ አባል ነው፡፡

ትዝስ ቡናችንን በጨውና በቅቤ እየጠጣን እግዚአብሔር በእርሱ ለሚታመኑት አሁንም የመፈወስና ጸሎትን የመመለስ ኃይል ስላላው አመሰገንነው፡፡

‹‹እኔ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ መሆን እፈልጋለሁ፡፡ ‹እኔ ለጌታ ባሪያ ነኝ፡፡- ሩጫዬን በትዕግሥት፣ በሰጡኝ ቀናት ሁሉ ሁሉንም ነገሬን ትቼ ለወንጌል መሮጥ እፈልጋለሁ›› አለኝ፡፡

ከዚያም ባሳ መጽሐፍ ቅዱስን ከፍቶ ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አነበበ፡-

> *‹‹ስለዚህ፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን ለውታችኋልና የምትደላደሉ፣ የማትነቃነቁም፣ የጌታም ሥራ ሁልጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ።››*
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡58

29

ዳንኤል

ሐቀኝነትና ፍትሕ

የማለዳው ጸጥታ በድንገት በጠመንጃ ጩኸት ደፈረሰ። ከዚያም የድረሱልኝ ጥሪ መሰማት ጀመረ። የጭንቀት ጩኸት በከፍተኛ ድምፅ ተሰማ። በፍጥነትም ሰዎች ከየቤታቸው እየሮጡ ወጡ፣ በቀፋፊው መንገድ ላይ፣ በማኅበረሰቡ የውኃ ቧንቧ አጠገብ ወንጌላዊ ዳንኤል በመሬት ላይ ተጋድሟል። ተንበርክኮ የወጣት ጓደኛውን ጭንቅላትና ትከሻ ለመደገፍ ይሞክራል። ጓደኛው ከቄሰለው ጎኑ ደም ይፈስሰዋል። ወንጌላዊው ደንግጦና ግራ ተጋብቶ ዕንባ በፊቱ ላይ ይፈስሳል። ‹‹ድንገተኛ ነው!›› በማለት ደጋግሞ ይናገራል።

ዳንኤል ከወንድሙ ወንጌላዊ ማሄ ጋር ወደ ጎፋ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሄድ ገና በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ ያለ ልጅ ነበር። ለወንጌል ስርጭት ከፍተኛ ፍላጎት ስለ ነበረው፣ ለሁለት ዓመታት ያህል ከወንድሙ ሥር ሆኖ ተግባራዊ ሥልጠና ሲወስድ ቆየ። ከዚያም ከወንጌላዊ አመንታ ጋር በመሆን በሼፊቲ ውስጥ አገልግሏል። አገልግሎታቸውም ምንም እንኳ ብዙ ስደትና መከራ የበዛበት ቢሆንም፣ በዚያ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ተመሥርታለች።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ዳንኤል ወደ አይዳ ተዛወረና በወላይታ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት እርሱን እንደ ወንጌላዊ አድርገው ገና ስላልተቀበሉት ራሱንና ቤተሰቡን ለመደገፍ የሽመና ሙያን ተማረ። የአይዳ ማኅበረሰብ በመንፈሳዊ ጨለማ እስራት ውስጥ የኖሩ፣ ፊጽሞ የተለየ ባህል ያላቸውና ሁልጊዜ በፍርሃት የሚኖሩ ነበሩ፣ አካባቢያቸውም የመናፍስት፣ የጠንቋዮችና የሙተተኞች ፍርሃት ያለበት በጣም ጭካኔ የተሞላበት ልምድ ያለበት አካባቢ ነበር። የወንጌል ብርሃን በጨለማው ውስጥ መብራት ሲጀምር፣ ዳንኤል ሕዝቡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ጥሩ ምላሽ ሲሰጥ ተመለከተ። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን

ከፍተኛ መከራ ተቋቁሞ፣ በዚያ አካባቢ በሚገኙ መንደሮች ውስጥ አምስት ቤተ ክርስቲያናትን ተከለ።

አመንታ፣ ካሉት ወንጌላውያን ሁሉ፣ ዳንኤል የተሻለ መሆኑን ለወላይታ ሽማግሌዎች ነገራቸው፤ ስለዚህም ዳንኤልን ተቀብለው እንደ ወንጌላዊ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጉለት ጀመር። እነዚያን ቤተ ክርስቲያናት ለሌላ ወንጌላዊ በመስጠት፣ ዳንኤል በመጀመሪያ ወደ ማሺላ ለሁለት ዓመት ያህል ጊዜ፣ ከዚያም ጠንቋዩን ዳኖን ወደ ጌታ ወደ መራበት ወደ ዲማ ሄደ። በእያንዳንዱ አካባቢም፣ በዳንኤልና በአዳዲስ አማኞች ላይ ስድብ፣ ማስፈራራት፣ ድብደባና መታሠር ይደርስባቸው ነበር። ነገር ግን በተጀመሩት ብዙ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ የእግዚአብሔር እሳት መንደዱን ቀጥሎ ነበር፣ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናቱ ማደጋቸውን ቀጠሉ።

የወላይታ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወንጌላውያኑን ለበለጠ ሥልጠና እና ወንጌል ፈጽሞ ወዳልደረሰበት ቦታ ለመደልደል ጠሯቸው። ለትንሽ ጊዜ ዳንኤል ሙስሊሞች ወደ አሉበት ወደ ምዕራብ አካባቢ ተላከ፣ ነገር ግን በጣም ሩቅ ስፍራ የነበሩ ሌሎች ወንጌላውያን እንዳደረጉት ሁሉ፣ የኮምዩኒስቱ መንግሥት ሀገሪቱን በተቈጣጠረ ጊዜ አካባቢውን ለቅቆ ለመሄድ ተገደደ። ከቤተሰቡ ጋር በመሆን፣ እኅቱን መስቀሌንና ወንድሙን ማሄን በመቀላቀል (በመዳበል) ሶዶ በሚገኘው ትንሽ መሬት ላይ መኖር ጀመረ።

ፈለገ

የክርስቶስን ወንጌል ለመስበክ እንዲህ ወዳለ ‹‹መንፈሳዊ ተራራ ጫፍ›› ላይ ደርሰው፣ ብዙ ሰዎችን ወደ አዳኙ ካመጡ በኋላ የኮምዩኒስት ባለ ሥልጣናት ብዙ ወንዶችን፣ እርሱንም ጨምሮ፣ በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት ሕንጻዎችን የሚጠብቁ ‹‹የሌሊት ዘበኞች›› ማድረጋቸው ለእርሱ በጣም ዝቅ ማድረጋቸው ነበር።

ከሌላ ሰው ጋር ሆኖ፣ ዳንኤል የደርግ መንግሥት የወረሳቸውን በቀድሞ የኤስ ላይ ኤም ቅጥር ግቢ ውስጥ ያሉትን ቤቶች፣ ትምህርት ቤትና ሆስፒታል የመጠበቅ ኃላፊነት ተሰጠው። በየምሽቱም የኮምዩኒስት ባለ ሥልጣናቱ ያረጀ ጠመንጃ እስከነ ጥይቱ ይሰጧቸው ነበር። ተራቸውም በየአሥራ ሁለት ሰዓት ውስጥ ይቀያየርላቸው ነበር። ምንም እንኳ ሌሊቱ በጣም ቀዝቃዛ ቢሆንም፣ ዳንኤልና ጓደኛው ኮትና የሚሞቅ ልብስ በመልበስ፣ ያለ ፍላጎታቸው የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻ በታማኝነት ይወጡ ነበር። በየዕለቱ ለብዙ ወራትና

ዓመታት ተራቸውን ያጠናቀቁ ሰዎች መሣሪያውን ለጠዋት ተረኛ ያስረክቡ ነበር።።

ﻩﻩﻩ

የማለዳው ጸጥታ በድንገት በጠመንጃ ጩኸት ደፈረሰ።። ከዚያም የድረሱልኝ ጥሪ መሰማት ጀመረ።። የጭንቀት ጩኸት በከፍተኛ ድምጽ ተሰማ።። በፍጥነትም ሰዎች ከየቤታቸው እየሮጡ ወጡ፣ በቀፋፊው መንገድ ላይ፣ በማኅበረሰቡ የውኃ ቧንቧ አጠገብ ወንጌላዊ ዳንኤል በመሬት ላይ ተጋድሟል።። ተንበርክኮ የወጣቱ ጓደኛውን ጭንቅላትና ትከሻ ለመደገፍ ይሞክራል።። ጓደኛው ከቆሰለው ጎኑ ደም ይፈስሰዋል።። ወንጌላዊው ደንግጦና ግራ ተጋብቶ ዕንባ በፊቱ ላይ ይፈስሳል።። ‹‹ድንገተኛ ነው›› በማለት ደጋግሞ ይናገራል።።

ብዙ ሰዎች በዙሪያው እንደ ተሰበሰቡ፣ ወደ እርሱ ቀርበው ምን ተከሰተ፣ ይህንን ያደረገው ማን ነው በማለት ይጠይቁታል።። ወጣቱ እንዲህ አለ፣ ‹‹ድንገት የተፈጠረ ነገር ነው።። ዳንኤል ጓደኛዬ ነው።። እርሱ አልገደለኝም።። ይህ ድንገት የተፈጠረ ነገር ነው።።›› ብዙ ሰዎች የተናገረውን ሰምተውታል፣ እርሱም ያንኑ ደጋግሞ ይናገራል።። ከዚያም ሰውዬው ሞተ።።

ዳንኤል እና ሰውዬው ለመጨረሻ ጊዜ በሆስፒታሉ ዙሪያ ቅኝት ማድረጋቸውን ሲፈጽሙ ድካምና ራብ ተሰማቸው።። ልክ እንደ ሌሎቹ ሌሊቶች ሁሉ ሌሊቱን በሙሉ በዚያ ስፍራ ነበሩ።። ይህ ምንም ጥቅም የሌለው እንቅስቃሴ ነበር።። ምንም የሚከሰት ነገር አልነበረም።። በጣም ከባድ የሆነ ጠመንጃና ባትሪ ተሸክሞ መዞር ብቻ ነበር።። የሚከፈላቸው ነገር ደግሞ ዝቅተኛ ክፍያ ብቻ ነበር።። በዚህ አጥር ውስጥ እስከ መቼ እንደሚሸከረከሩ ግራ ገባቸው።።

በውኃ ቧንቧው አጠገብ ሲደርሱ፣ ሁልጊዜም እንደሚደርጉት፣ ፊታቸውን ለመታጠብና ውኃ ለመጠጣት ቆም አሉ።። የዳንኤል ጠመንጃ በድንገት ከትከሻው ተንሸራተተና ሰደፉ ከድንጋይ ጋር ተጋጨ፤ ከዚያም ጠመንጃው ተተኰሰ (ባረቀ)።። ዳንኤል የጓደኛውን ደም ከመፍሰስ ማስቆም አልቻለም።። ጓደኛው በሞት እስከ ተለየው ድረስ በእጁ ይዞት ነበር።።

ዳንኤል እጁን ታጥቦ ጠመንጃውን በስፍራው ለነበረ ለኮምዩኒስት ባለ ሥልጣን አስረከበ።። ከዚያም ከብዙ ጎረቤቶቹ ጋር በመሆን ስለ ተከሰተው አደጋ ለማመልከት ወደ ሶዶ ፖሊስ ጣቢያ ሄደ።። ስለ ተፈጠረው ነገር በጽሑፍ

ሪፖርት እንዲያደርግ ተጠየቀ፡፡ የሞተውን ሰው የመጨረሻ ኑዛዜ የሰሙ አንዳንድ የዳንኤል ጎረቤቶችም በጻፈው ወረቀት ላይ ፈረሙበት፡፡

ዳንኤል ተይዞ ታሰረ፣ እንዲሁም ሰው በመግደል ወንጀል ተከስሶ በሶዶ እስር ቤት ውስጥ ታሰረ፡፡ ለሁለት ወራት ያህልም እርሱን ለመልቀቅ ጉቦ የፈለጉት የመንግሥት ባለ ሥልጣናት አስፈራሩት፡፡ ዳንኤል ግን ተቃወማቸው-ዳንኤል ገንዘብ የለውም፣ ቢኖረውም አይዋሽም ወይም ለመንግሥት ባለ ሥልጣናትም ጉቦ አይከፍልም፡፡ ወደ ችሎትም በተወሰደ ጊዜ፣ የሆነውን ነገር እንደገና በመናገር ድንገተኛ አደጋ እንደ ሆነ ተናገረ፡፡ እነርሱ ግን አላመኑትም፡፡ የእርሱም ጉዳይ ወደ ክፍለ ሃገሩ ዋና ከተማ፣ ወደ አዋሳ፣ ከፍተኛ ችሎት ተዛወረ፡፡ የነፍስ ማጥፋት ወንጀሎች ሁሉ የሚታዩት በዚያ ነበር፡፡

አዋሳ በነፍስ ማጥፋት ወንጀል የተከሰሱ እስረኞች ቅጣታቸውን ከሞት ቅጣት ወደ እስራት ለማስለወጥ ለዳኞቹ ብዙ ገንዘብ እንደሚከፍሉ የታወቀ ነበር፡፡ ይህንን ገንዘብ ካልከፈሉ ግን፣ ሁልጊዜም ጥፋተኞች እንደ ሆኑ ተወስኖ ይገደሉ ነበር- ማንም ሰው ከዚያ በነፃ ተለቅቆ አያውቅም፡፡ ለወራት፣ ዳንኤል የፍርድ ሂደቱን ሲጠባበቅ በእስር ቤት ቆየ፡፡

በወላይታ ያሉ ቤተሰቦቹና በመቶዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች በጽናት ስለ ዳንኤል መለቀቅና ወደ ቤተሰቡ መመለስ ይጸልዩ ነበር፡፡ በማርክሲዝም ርዕዮተ ዓለም ትመራ በነበረችው ኢትዮጵያ ውስጥ ፍትሕን ማግኘት የማይታሰብ ነገር ነበር፡፡

በክሱ ሂደት በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ችሎት ውስጥ ዳንኤልን የወከለው ጠበቃ የሞት ቅጣት እንዳይቀጣ በመጀመሪያ የሰጠውን ቃል ለመለወጥ ለምን እንዳልፈለገ ሊገባው አልቻለም፡፡ ዳንኤልንም እንዲህ ሲል ለመነው፣ ‹‹ደርግ ሁልጊዜ ሰዎችን ይገድላል፡፡ እነዚህ ሰዎች ሰውን በነፃ ለቅቀው አያውቁም፡፡ ዳኞቹ የመጀመሪያውን ቃልህን እንድትለውጥ ይፈልጋሉ፡፡ ቃልህን ከቀየርህ፣ በእስር ቤት ውስጥ ለብዙ ጊዜ በሕይወት ትኖራለህ፡፡ ይህንን ካላደረግህ ግን፣ የሞት ቅጣት ይፈረድብሃል፡፡ በጥይት ትረሸናለህ፡፡ ስለ ቤተሰቦችህ አስብ፡፡ ቃልህን ቀይርና በሕይወት ኑር፡፡››

አምስቱ የከፍተኛ ችሎት ዳኞች አጠገብ ለአጠገብ ተቀምጠዋል፡፡ ዋናው ዳኛ ዳንኤል ቃሉን ይቀይር እንደ ሆነ ጠየቀው፡፡ ‹‹ተጨማሪ ቀናት እንሰጥሃለን፡፡ ዋስ ሊሆንህ የሚችል ሰው አለህን?›› በማለት ጠየቀው፡፡

ዳንኤል መመለስ የቻለው፣ ‹‹እኔ ከእግዚአብሔር ውጭ ማንም የለኝም›› በማለት ነበር፡፡ ዳኛውም ዳንኤል ዋስ የሚሆነው ሰው ስለሌለው 1000 ብር አስይዞ በቀጠሮው ቀን መምጣት እንደሚችል ተናገረ፤ ነገር ግን ዳንኤል፣ ‹‹ምንም ገንዘብ የለኝም፣ አሥር ሳንቲም እንኳ የለኝም፣›› በማለት ምላሽ ሰጠ፡፡ ዳኛውም የፍርድ ቤቱን ሥርዓት አስከባሪ ፖሊስ ዳንኤልን ይዞ ከችሎት እንዲያስወጣውና እስኪጠራ ድረስ በውጭ እንዲቆይ አደረገ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ዳንኤል ወደ ችሎቱ ክፍል ተመለሰ፤ ዳኛውም፣ ‹‹ሌላ መናገር የምትፈልገው ተጨማሪ ነገር አለህን?›› ሲል ጠየቀው፡፡

ዳንኤልም፣ ‹‹እውነቱን ጽፌያለሁ፡፡ የምናገረው ሌላ ነገር የለኝም፡፡ ይህ ነገር በአጋጣሚ የሆነ ነው፡፡ ይህ ነገር በመሆኑ በጣም አዝናለሁ፡፡ እኔ በእናንተና በእግዚአብሔር እጅ ነኝ፡፡ እናንተ ‹ሞት ይገባሃል› ካላችሁኝ፣ እሞታለሁ፡፡ ‹በነፃ ሂድ› ካላችሁኝ፣ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡›› ሲል መልስ ሰጠ ፡፡

እንደገና አምስቱ ዳኞች እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ፡፡ በችሎቱ ውስጥ የነበረ ሰው ሁሉ የሞት ፍርድ ይፈረድበታል ብሎ ጠብቆ ነበር፡፡ በሚያስገርም ሁኔታ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ዋና ዳኛው እንዲህ ሲል ተናገረ፣ ‹‹ወንጀለኛ አይደለህም፣ በነፃ መሄድ ትችላለህ፡፡››

ዳንኤል ጆሮውን ማመን አልቻለም! በድንጋጤ፣ ዳኞቹን አጎንብሶ አመሰገነና በችሎቱ ክፍል ውስጥ ያለውን ጠቢቃንና በአግራሞት የተሞሉትን ባለ ሥልጣናት አልፎ ሄደ፡፡ ጸጥታ ባለው ስፍራም ተንበርክኮ ነጻ ስለ ወጣ እግዚአብሔርን ደጋግሞ አመሰገነ፡፡ በአውቶብስ ተራም አንድ ሰው ዳንኤልን ወደ ወላይታ በነፃ ይዞት ሄደ፡፡

ዳንኤል ወደ መኖሪያ ቤቱ ሲደርስ ምንኛ አስደሳች ጊዜ ይኖረው ይሆን! ሚስቱ በደስታ ብዛት እልልታዋን አቀለጠችው፣ ከዚያም ጎረቤቶቹ የደስታው ተካፋይ ለመሆን ተሰበሰቡ፡፡ ወንድሙ ማሄም እግዚአብሔር ለጸሎታቸው ምላሽ በመስጠቱ የምስጋና ጊዜን መምራት ጀመረ፡፡

ይህን ነገር ከሆነ በጣም ብዙ ዓመታት አልፈዋል፣ ዳንኤልም ጌታውን እስከ አሁን በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌላዊ ሆኖ

ወደሚሄድባቸው አካባቢዎች ሲሄድ ከእኔ ጋር ይጓዛል። ዳንኤል ሁልጊዜ በመንገድ ላይ ጥሩ ረዳት ነው፣ የሚሠሩ ነገሮች ሲኖሩ ጥሩ አጋዥ፣ ለመኪና መጓጓዣ መንገድ በመሥራት የሚያግዘና፣ ዕቃዎችን የሚሸከም፣ ውኃ የሚቀዳ፣ ማደሪያ ስፍራዎችን የሚያዘጋጅ እርሱ ነው። ሁል ጊዜ ደስተኛና የጸሎት ሰው ሲሆን፣ ወንጌልን ለሰዎች ለማካፈል ዘወትር የተዘጋጀ ሰው ነው።

በ23 ዓመታት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ዲማ መሄዴን ዳንኤል ሲሰማ ከእኔ ጋር ለመሄድ ተነሣ። ከእኔ ጋር ይዤው እንድሄድም ለመነኝ። ወደዚያ ስፍራ ከተመለሰ 27 ዓመታት አስቈጥሯል። የሚያስታውሰው ሰው ይኖር እንደ ሆነ ለማየት ጓግቷል። ብዙዎቹን አስቸጋሪ ነገሮች ጠንቅቆ ያውቃቸዋል፣ እንዲሁም በዝቅተኛና ሞቃታማ በሆነው በረጃጅም ሣሮች ውስጥ የተሸፈነውን መንገድ ፈልጎ ማግኘት ለእርሱ በጣም ቀላል ነው። እርሱና ሌሎች ሰዎች ብዙ ኪሎ ሜትር ድረስ በመሄድ፣ ለዘመናት መኪና ሄዶበት የማያውቀውን መንገድ ደኅና መሆኑን አረጋግጠዋል።

በመጀመሪያ፣ ዳንኤል ወደ ክርስቶስ ካመጣው፣ ቀድሞ ጠንቋይ ከነበረው ዳኖ ጋር ሊተዋወቁ አልቻሉም ነበር፣ ከትንሽ ቆይታ በኋላ ግን ሰላምታ ተለዋወጡ፣ ተቃቀፉና እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ጀመር። እግዚአብሔር የሠራቸውን ታላላቅ ነገሮች ለሰዓታት ሲያወሩ ቆዩ። የመጀመሪያዎቹን አስቸጋሪ ጊዜያት- የስደትና የመከራ ጊዜያት አስታወሱና አሁን በዲማ ውስጥ ስላሉት ብዙ ቤተ ክርስቲያናት ሐሤት አደረጉ።

‹‹ለምን መጥፎ ነገር በጥሩ ሰዎች ላይ ይደርሳል?›› በማለት ብዙ ሰዎች ይጠይቃሉ። ዳንኤል ‹‹ለምን እኔ?›› ብሎ ጠይቆ አያውቅም። ይልቁንም፣ ሐቀኝነቱን ጠብቆ ለእግዚአብሔር ፈቃድ በጸሎት ለመገዛት እራሱን ሰጠ። ከዚያም እግዚአብሔር ለጸሎት ምላሽ የሚሰጥ የታመነ አምላክ መሆኑን አረጋገጠ።

‹‹ነገር ግን፣ ወንድሞች ሆይ፣ ይህ የደረሰብኝ በእውነት ወንጌልን ለማሰፋት እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ።››

ፊልጵስዩስ 1፡12

30

የቀብር ሥነ ሥርዓት

የመሪው ስንብት

በተራሮቹና በሸለቆዎቹ ውስጥ የጭንቀት ጩኸት በተሰማ ጊዜ በዚያ ብሩህ፣ እና ፀሐያማ ማለዳ ላይ የተጀመረው የእርሻ ሥራ ተቋረጠ። አንድ ሰው ከሸለቆ ውስጥ የማስጠንቀቂያ ጩኸት አሰማ፣ ሌሎችም የእርሱን ጩኸት እየሮጡ ደጋግመው አሰሙ። ሰዎች የማረሻ ሞፈራቸውን በመተውና ጦራቸውን ከተከሉበት በመንቀል ወደየ ቤታቸው መሮጥ ጀመሩ። እየሮጡም ለሴቶቹ ልጆቹን ወደ ቤት እንዲያስገቡ ነገሯቸው። በጓሮ ውስጥ እየሠሩ የነበሩት ሴቶች ሁሉንም ነገር በመተው፣ ትንንሽ ልጆቻቸውን በማቀፍ ወደየ መኖሪያ ቤቶቻቸው ሮጡ። የመኖሪያ ቤታቸውን በር በመዝጋት ልጆቻቸውን ሸፍነው፣ ራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን ለመከላከል መሣሪያና ቀሩጭ እንጨት ወይም ማንኛውንም ነገር አነሡ። የመኖሪያ ቤታቸውን በር የሚከፍቱት ወንዶቹ እንዲገቡ ብቻ ነበር።

ሜዳዎችም በፍጥነት ሰው-አልባ ሆኑ፤ እንስሳትም ያለ እረኛ ተሰማሩ፤ ሕዝቡ በሙሉ በፍርሃት ተዋጠ። የማስጠንቀቂያ ጩኸቱ በተራራው ላይ ወደሚቀጥለው መንደር እየተዛመተ ሄዶ እስከ ሚቀጥለው ተራራው ጫፍ ድረስ ደርሷል። በዚህ አካባቢ የነበሩ ጥቂት የፖሊስ ሠራዊት አባላት በፍጥነት መሣሪያ በመታጠቅ ጥቂት የማስጠንቀቂያ ጥይቶችን ተኰሱ። የከተማዋ መንገዶች ከፖሊሶች፣ ከመንግሥት ባለ ሥልጣናትና መሣሪያ ካላቸው ነጋዴዎች በስተቀር ጭር ብለዋል። በትልልቅ ድንጋዮች፣ ዛፎች ወይም ሱቆች ሥር ስፍራ ስፍራቸውን ይዘዋል። ተዋጊዎቹ ወደ ከተማዋ አቅራቢያ ከመድረሳቸው በፊት፣ የወረደባቸው የተኵስ እሩምታ ከከተማዋ ለሚሲዮን ጣቢያው ቅርብ ወደ ሆነው ሌላ አቅጣጫ ፊታቸውን እንዲያዞሩ አደረጋቸው።

ዜናውን ያመጣው ሰው፣ በሚሲዮን ጣቢያው አጥር፣ በቀኝ በኩል አለፈ። እኛም ይህ ሁሉ ምንድን ነው ብለን በመገረም ቆመን ነበር፤ ለጥቂት ጊዜ ቆም ብሎ፣ ወደ ቤት እንድንገባ ጮኸብን። ‹‹ሻንቅላዎች እየመጡ ናቸው፣›› አለ በታላቅ ድምፅ፣ ‹‹የሚመጡት የሚገድሉትን ትንሽ ልጅ ለመስረቅ ነው።›› የጎረቤታችን ሰው ወደ ኋላው ሲመለከት ጦረኞቹ እየመጡ መሆኑን ተመለከተና በአቅራቢያው ወደሚገኝ ቤት እየሮጠ ሄደ።

ከዚያ ሰው ኋላ በጣም ብዙ ራቁታቸውን የሆኑና ገላቸውን የተለያዩ ዓይነት የጭቃ ቀለማት የተቀቡ ሰዎች መጡ። በጣም ጥቂቶቹ ጠመንጃ ያነገቡ ቢሆንም፣ አብዛኞቹ ግን የያዙት ጦር ነበር። የአካባቢው ሰዎች አስቀድመው ማስጠንቀቂያ እንደ ተሰጣቸው ባወቁ ጊዜ፣ በዚያው አልቆሙም፣ ወደ ተራራው ጫፍ ላይ ወጡ።

ሰዎቹ ከሄዱ ቆይተዋል፣ እንዲሁም ሁሉም ነገር ጸጥ ብሏል። ነገር ግን ማንም ሰው ከመኖሪያ ቤቱ አልተንቀሳቀሰም። ቀኑን በሙሉ በዚያ ቆዩ። ወደ አመሻሽ ላይ ወንዶች በቡድን በቡድን ሆነው፣ ጦራቸውን አስተካክለው ከያሉበት ወጡ። በሬዎቻቸውን ወደ በረት፣ ላሞቻቸውን ለመታለብ አስገቡ፣ በቅሎዎቻቸውንም፣ አህያዎቻቸውንና በጎቻቸውንም አስገብተው አሰሩ። እነዚያ ጦረኞች የመጡት ለእንስሳት እንዳልሆነ ለሁሉም ግልጽ ነበር!

ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ እንድንደበቅ የጮኸብንን ገበሬ አነጋገርኩት። ስለ አደጋው ሁሉንም ሰው ያስጠነቀቀው ይህ ሰው ነበር። ያለጥርጥር የብዙ ሰዎችን ሕይወት አድኗል። ይህ ገበሬ ከአንድ ወር በፊት በገበያ ስፍራ ሆኖ መሪው መሞቱን ይሰማል። ይህ ሰው ከዚያ ጎሳ ጋር ለብዙ ዓመታት የቡናና የእህል የእንስሳትም የንግድ ልውውጥ አድርጓል። ስለዚህም የእነርሱን ጥቂት ቋንቋና ባህል በጥቂቱም ቢሆን አውቋል። ይህን ጎሳ ወደ ጦርነት ሲሄድ በጣም ይፈራል። የዚህ ጎሳ መሪ የመሞቱ ዜና በገበያ ስፍራው እየተዛመተ ነበር፣ እንዲሁም ወደ ክሊኒክ ከመጣ ታካሚ ይህንን ወሬ ሰማን። ለጉዳዩ እምብዛም ትኩረት አልሰጠነውም፣ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ሰዎች አርጅተው፣ ታምመው ወይም በጦርነት መሞታቸው የተለመደ ነገር ነውና። ጎረቤታችን የሆነው ሰውዬም ለምን የእርዳታ ጩኸት እንደ ሰማ አስረዳን።

አንድ በኢትዮጵያና ኬኒያ ድንበር ላይ ያለ፣ በዕድሜ የገፋ መሪ ዕድሜው

ወደ ዘጠና ዓመት አካባቢ ሲሆነው ሞተ፡፡ በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ፣ የአማራ ዘር በደቡብ ያሉትን ጎሳዎች ሁሉ በጦርነት መግዛት በጀመረበት ጊዜ የእርሱ አባት የዚያ ጎሳ የመጨረሻ ንጉሥ ነበር፡፡ ንጉሡም የጎሳው ‹‹አለቃ›› ተደርጎ ተሹሞ ነበር፡፡ (ሊኖር የሚችለው አንድ ንጉሥ ብቻ ነበር- ይህም ንጉሥ ‹‹የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት›› ነው፡፡) እርሱም ነገሮችን እንደ ቀድሞ ማስተዳደር ቀጠለ፤ ልዩ የሆነው ብቸኛው ነገር በየዓመቱ ለመንግሥት ሥልጣን የሚገዛ መሆኑን ለማሳየት ቀረጥ መክፈሉ ብቻ ነበር፡፡ ይህ አሁን የሞተው መሪ የዚያ ሰውዬ ወንድ ልጅ ነበር፡፡

በጣም ቀጭጡ፣ ጨካኝ ሰው መሆኑ እየታወቀ፣ የገዛ ሕዝቡን ከስልሳ ዓመታት በላይ ገዝቷል፡፡ በጣም ይፈራና ይከበር ነበር፡፡ ትልቅ ተዋጊ እንደ መሆኑ መጠን፣ አጎራባች ከሆኑ ጎሳዎች ጋር የሌሎችን ከብቶች ለመዝረፍ ወይም እነርሱ እንዳይዘረፉ ለመከላከል ሲል ብዙ ጦርነቶችን አድርጓል፡፡ ይህ አካባቢ ልቅ፣ ሕግ የሌለበት፣ ምንም ዓይነት መንገድ ወይም መረጃ ማስተላለፊያ መንገድ የሌለበትና ትንሽ የመንግሥት ባለ ሥልጣናትና ትንሽ የፖሊስ ቍጥጥር ያለበት አካባቢ ነው፡፡ የመንግሥት ባለ ሥልጣናት በየዓመቱ ለመሪያቸው ግብር መሰብሰብ ከቻሉ ለእነርሱ ያ በቂ ነበር፡፡ የጎሳ መሪው እንስሳት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ ሲሄዱ፣ መንግሥት ግን የሚቀበለው ግብር በጣም ትንሽ ነበር፡፡

በባህላቸውም መሠረት፣ የመሪያቸውን በድን አካል በትከሻ የበሬ ቆዳ ይጠቀልሉና ከሣር በተሠራ ጥላ ሥር ዘንበል ባለ መሬት ላይ ያስተኙታል፡፡ በዚያ ስፍራ ለዘጠኝ ወራት ተቀምጦ እንዲበሰብስ ይደረጋል፡፡ በአቅራቢያውም ወንዶች በእንጨትና በኩበት እሳት በማንደድ በየቀኑ ዕጣን ያጨሳሉ፡፡ ቀን ቀን ጥንብ አንሣዎችንና ውሾችን ማታ ማታ ደግሞ ጅቦችን ያባርራሉ፡፡

እነዚህ ተዋጊዎች ከሄዱበት አደን ሁለት ትንንሽ ወንድ ልጆችን ይዘው ይመጣሉ፡፡ የእነዚህን ልጆች ወላጆች በመግደል ይዘዋቸው የሚመጡት ለመሪያቸው ባሪያ ሆነው እንዲያገለግሉት ነበር፡፡ ከዚያም ትልቅ መቃብር ይቆፍራሉ -አሥር ጫማ (ሦስት ሜትር) ርዝመት፣ አሥር ጫማ (ሦስት ሜትር) ጥልቀት እና ሁለት ጫማ (ስልሳ ሴንቲ ሜትር) ስፋት ያለው ጉድጓድ ይቆፍራሉ፡፡ የመሪያቸው የቀረው አካሉ የሚቀመጥበት በጉድጓዱ አፋፍ ላይ

በጎን በኩል ይቆፈራል። ይህ ጉድጓድም በእበት ይለቀለቅና የላይኛውን ክፍል ለመሸፈን ብዙ ድንጋይ ይሞላበታል።

የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ብዙ ቀንና ሌሊት የሚፈጅ ነበር። ሴቶች በመቃብሩ ዙሪያ ትልቅ ክብ ሠርተው የላም ቆዳቸውን እንዳገለደሙ፣ በክንዶቻቸውና በእግሮቻቸው ላይ የብረት አንባር እንዳሠሩ ይደንሳሉ። የሚደንሱት ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ሲሆን፣ ሁለት እርምጃ ወደ ፊት አንድ እርምጃ ወደ ሰማይ ነው። መሬቱንም በእግሮቻቸው እየተመተሙ ጡቶቻቸውን በመምታት በታላቅ ድምፅ ይዘፍናሉ። ‹‹እርሱ ወደ ጨለማ ሄዷል። እርሱ ወደ ጨለማ ሄዷል›› ይላሉ። በዚህ ዓይነት መንገድ ቀን ከሌሊት እስኪደክሙ ድረስ ይቀጥላሉ። ከድካም የተነሣ ከቀኑጥራቸው ውጭ ሆነው ራሳቸውን ሲስቱ ከከቡ ውስጥ ተጎትተው ይወጣሉ፤ በእነርሱ ፈንታም ሌላ ሰው ተተክቶ ይሠራል።

የጠንቋዩ ከበሮም ቀን ከሌሊት ያለማቋረጥ ይመታል፣ መልእክቱ ግን ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ሆኖ ‹‹እርሱ ወደ ጨለማ ሄዷል›› የሚል ነው። ጠንቋዩ ይህንን መልእክት ከበሮውን እየደለቀ ደጋግሞ ይናገረዋል። ክብ ሠርተው ከሚደንሱት ሴቶች ውጭ፣ ጦረኞቹ ከጉማሬ ቆዳ የተሠራ ጋሻና ጦር ይዘው ይደንሳሉ። መሬቱን በእግሮቻቸው እየደበደቡና ጦሮቻቸውን ከጋሻዎቻቸው ጋር እያጋጩ ይደንሳሉ። ይህንን ነገር ያለማቋረጥ፣ ዜማውን በተከተለ እንቅስቃሴ ‹‹ወዴት እንደ ሄደ አናውቅም። ወዴት እንደ ሄደ አናውቅም›› በማለት ያዜማሉ። ሴቶቹም ያለማቋረጥ ‹‹ወደ ጨለማ ሄዷል›› ይላሉ፣ ከዚያም ወንዶቹ ደግሞ ‹‹ወዴት እንደ ሄደ አናውቅም፣›› የሚለውን ይደግሙታል።

ጩኸቱን መስማት ብትችሉ፣ ከበሮውን፣ ለቅሶውን፣ የእግር መሬት ረገጣውንና ሽታውን ማሽተት ብትችሉና ግለቱ ቢሰማችሁ፣ እንዲሁም ጦረኞቹ ቀስቶቻቸውን ወደ ሰማይ አንሥተው ከጋሻቸው ጋር ሲያጋጩ ድምፅ ብትሰሙና የሚፈጠረውን አቧራ ብትመለከቱ፣ እንዲሁም ቀን ከሌሊት የሚደበደበውን ከበሮ ብታዳምጡ ተስፋ የሌላቸው መሆናቸው በጥቂቱም ቢሆን ይገባችኋል። እነዚህ ሰዎች ከጠፉትም ሰዎች ውስጥ በጣም የጠፉ መሆናቸውን፣ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ምሕረት እንዲሁም ጸጋና እነርሱን ለማዳን በነፃ የተሰጠውን ሕይወት ሰምተው የማያውቁ፣ በመንፈሳዊ ጨለማ

ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች መሆናቸውን ትረዳላችሁ፡፡ በእርግጥ ይህን መረዳት ከቻላችሁ፣ ፈጽሞ የቀድሞው ዓይነት ሰው ልትሆኑ አትችሉም!

ከብዙ ለቅሶ፣ ዋይታ፣ ጩት መቊረጥና ጦረኞቹ ግንባራቸውን በጦር ከተለተሉ፣ ሴቶቹም በእሾህ ፊታቸውን ከቧጠጡ በኋላ በሺህ የሚቈጠር ሕዝብ፣ ሁሉም የዚያ ጎሳ አባላት ማለት ይቻላል፣ በመቃብሩ ዙሪያ ይሰበሰባሉ፡፡ አስከሬኑ በተጠቀለለበት አሮጌው የላም ቆዳ ላይ አዲስ የላም ቆዳ ይጠቀለላል፡፡ ከዚያም በጉድጓዱ ውስጥ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ በመቃብሩ ውስጥም በርጩማ ይቀመጣል፣ በዚህ ላይ የመሪው ተወዳጅ ሚስት እንድትቀመጥ ይደረጋል፡፡ ፍዝዝ ብላ ትቀመጣለች፡፡ ከእርሷ ቀጥሎ ሁለት ፍየሎች ከእንጨት ጋር ይታሰራሉ፡፡ በጕድጓዳ ሳሕን ጥራጥሬ፣ ውኃ፣ በገንቦ ደግሞ ማር ይቀመጣል፡፡

በጉድጓዱ ሌላኛው መጨረሻ ላይ ሁለቱ ትንንሽ ልጆች ከእንጨት ጋር ታስረው ቆመዋል፡፡ በጣም ሲያለቅሱ ከመቆየታቸው የተነሣ አሁን ደክመዋል- ምናልባትም ደንዝዘው ይሆናል፣ የሚያደዝ መድኃኒት ተደርጎባቸውም ሊሆን ይችላል፡፡ በድንገት ዳንሱ ቆመ፡፡ ‹‹ወደ ጨለማ ሄዷል፡፡ - ወዬት እንደ ሄደ አናውቅም›› የሚለው ዝማሬም አቁሟል፡፡ ወንዶች በፍጥነት አፈሩን ወደ ጉድጓዱ መለሱት፡፡ ከመሪያቸው አጥንት ጋር ሁሉም ነገር - ፍየሎቹ፣ ሚስቱ፣ ሁለቱ ልጆች በአፈር ተሸፈኑ- በሕይወት እያሉ ተቀበሩ፡፡

እውነትም፣ ወደ ጨለማ ሄዷል!

> *‹‹ወደማልመለስበት ሰፍራ፣ ወደ ጨለማና ወደ ምት ጥላ ምድር፣ እንደ ጨለማም ወደ ጨለመች፣ ሥርዓትም ወደሌለባት ወደ ምት ጥላ፣ ብርሃንዋም እንደ ጨለማ ወደ ሆነ ምድር ሳልሄድ፣ ጥቂት እጽናና ዘንድ ተወኝ፣ ልቀቀኝም።››*
>
> ኢዮብ 10፡21፣ 22

፴፩

የበዲዎች ጭካኔ

ይህ ምዕራፍ የተጻፈው ከዚህ ቀጥሎ ላሉት ታሪኮች ታሪካዊ ዳራ ሆኖ ያገለግል ዘንድ ነው።

ተኩስ በመክፈት፣ ድንገተኛ ጥቃት ማድረስ፣ መግደል፣ መዝረፍ፣ ማርኮ ባሪያ ማድረግ፤ ከሁሉ በላይ ግን እንስሳትን መስረቅ በአሞ ሸለቆዎች ውስጥ በሚኖሩ አብዛኛዎቹ ጎሳዎች ዘንድ የተለመደ ነገር ነበር። ከዚያ የበቀል ጥቃት ይከተላል፣ ይህ ደግሞ ቀድሞ ከደረሰው ጉዳት በጣም የከፋ ይሆናል። እንዲህም እያለ የቂም እና የዐመፅ ምልልስ ይቀጥላል።

ርኅራኄ በሌለው ጥቃታቸው እንደ ቦዲ ጎሳ የሚፈራ የለም። በራሳቸውና በጠላቶቻቸው ላይ ባላቸው ጭካኔ ይታወቃሉ። በቦዲ ውስጥ መንትያዎች ፈጽሞ የሉም። እናትየዋና ልጆቹ የተረገሙ እንደ ሆኑ ይቆጠራሉ፤ ስለዚህም በአዞዎች እንዲበሉ ወደ አሞ ወንዝ በፍጥነት ይጣላሉ። አካለ ስንኩል ልጅና ልጁን የወለደችው እናትም በሕይወት እንዲኖሩ አይፈቀድም። አንድ በመጠጥ የሰከረ ሰው ሚስቱን በጥቃቅን ስሕተት ተነሣሥቶ ቢደበድባት፣ ማንም ሰው ተው ብሎ አያስቆመውም። ሚስቱ የእርሱ ንብረት እንደ ሆነች ስለምትቈጠር በከብቶቹ ላይ የፈለገውን ነገር የማድረግ መብት እንዳለው ሁሉ፣ በእርሷ ላይም ማድረግ ይችላል። እርሱ ጦረኛ ነው- እርሷን የማግባት መብት እንዲኖረው የሌላ ጎሳ ወንድ ገድሏል።

በዝቅተኛ ስፍራ ላይ በሚገኘው ሸለቆ ውስጥ ያለው መጥፎ የአየር ሁኔታ ሞቃታማና ደረቅ በመሆኑ፣ ብዙ ጊዜ ድርቅና በሽታን በከብቶቹ መካከል እንዲነሣ በማድረግ እነዚህ ጎሳዎች ለምግብነት የሚጠቀሟቸውን ከብቶች ይጨርስባቸዋል። በከብቶቻቸው አንገት ላይ ቀጭን መቃ በመሰካት አንድ ሊትር ያህል ደም በመቅዳት ትኩሱን ወይም ከወተት ጋር በመቀላቀል ይጠጡታል። የረጋ ማንኛውም ደም ለልጆች ምግብነት ይውላል።

ከብቶቻቸውን አያርዱም፣ በድንገተኛ አደጋ ወይም በበሽታ ከሞተ ቆዳው ለሴቶች ልብስ ወይም ለመኝታ ምንጣፍነት ሲውል፣ ከአጥንቱ በስተቀር ሥጋው ጥሬውን ይበላል።

የኦሞ ወንዝ በአነስተኛ ዝናብ ምክንያት መጠኑ ሲቀንስ፣ የቦዲ ጎሳዎች ወንዙን በመሻገር በሰሜን በኩል ያሉትን የኮንታ፣ ከፋ እና ጻራ ጎሳዎችን ይወርራሉ። ወንዙ ሞልቶ ለመሻገር አስቸጋሪ ከሆነ ደግሞ ዲማ፣ ማሎ እና ሙርሲ የተባሉ አጎራባች ጎሳዎችን ይወርራሉ።

በ1960ዎቹ አጋማሽ ላይ ተከስቶ፣ ለረጅም ጊዜ የቆየው ድርቅና ከፍተኛ ራብ በሚልዮን በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ ሞትን አስከትሏል። ይህም የንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ የዘውድ አገዛዝ እንዲያከትምና ከንግሥት ሳባ አንሥቶ ለሁለት መቶ ትውልድ ድረስ ይገዛ የነበረውን ሥረወ መንግሥት ወደ ማብቃት አምጥቷል። ወታደሩም በትረ ሥልጣኑን በእጁ በማስገባት የማርክሲዝም/ሌኒኒዝም የኢ-አማኒያን መንግሥት መሠረተ። አዲሱ አብዮታዊ መንግሥት ሁሉንም ስፍራዎች መቆጣጠር እስኪችል ድረስ ሥርዓት አልበኝነት በመላ ሀገሪቱ ውስጥ ነግሦ ነበር፣ እንዲሁም በኃይል አማካኝነት ብዙ ነገሮችን በቀኑጥጥር ሥር ለማድረግ ተሞክሮ ነበር።

ᚕᚔᚖ

የቦዲ ጎሳዎች መሪ ልጅ ጥቂት የቦዲ ጦረኞችን ይዞ የኦሞ ወንዝን ሲሻገር፣ የኦሞ ወንዝ በሕይወት ዘመኑ እንደዚያ ቀንሶ አይቶ አያውቅም። ውኃ ከጉልበታቸው በታች አልፎ አልፎ ብቻ ይነካቸው ነበር። በቦዲ አካባቢ ያለ ድርቅና ከፍተኛ ራብ በቦዲ ውስጥ የብዙ ሰዎችን ሞት አስከትሏል። እንዲሁም አብዛኞቹን ከብቶቻቸውን በበሽታ ፈጅቶባቸዋል። በሰሜን በኩል ያለው የኮንታ ጎሳ በቀላሉ ሊጠቃ የሚችል ነበር። ጦረኞቹም አንድ ሰው ገድለው ወደ ሃያ የሚሆኑ ከብቶችን ሰርቀው ያለምንም ጉዳት በሰላም ወንዙን ተሻግረው ለመመለስ ችለው ነበር።

ያላስተዋሉት ነገር፣ የኮንታ መሪ እና ሁለቱ ወንድ ልጆቹ በዚያ አቅራቢያ ከሕዝቡ ግብር በመሰብሰብ ላይ ነበሩ። ቦዲዎች እንደ ወረሩ በሰሙ ጊዜ እነርሱና ወታደሮቻቸው እየሮጡ የቦዲ ጦረኞችን እስከ ወንዙ ድረስ ተከትለው መጡ። የቦዲ ጦረኞች የሰረቋቸውን ከብቶች ወንዙን አሻግረው ስለ ነበር ምንም ሥጋት አላደረባቸውም።

የኮንታው መሪ ልጆቹንና ባሪያዎቹን ወንዙን እንዲሻገሩና የቦዲ ጦረኞች

ሳይዘጋጁ እንዲደርሱባቸው ፈቃድ ሰጠ፡፡ በተኵስ ልውውጡም ሁለት የቦዲ ጦረኞች ተገደሉ፣ የቦዲ መሪ ልጅ እግሩ ላይ በጥይት ቁስሎ ተያዘ፡፡ አብዛኞቹ ከብቶች ተመለሱ፡፡ ምሳሌ እንዲሆንና የቦዲ ጎሳዎችንም ለማስጠንቀቅ እንዲሆን የኮንታ መሪ ልጆች ሰይጣናዊ ሥራ ሠሩ- የቦዲ አለቃ ልጅን በትልቅ ዓለት ላይ እግሮቹን ፈልቅቀው አሰሩት፣ የሆድ ዕቃውንም ዘርግፈው ያለ ርኅራኄ ለዝንብ፣ ለጉንዳንና ለጥንብ አንሣ ጥለውት ሄዱ፡፡

እንዲህ ያለው ክፉ ተግባር ፈጣን ብቀላን ያስከትላል፣ ነገር ግን የኮንታ ሰዎች ምን እንደ ተከሰተ አልተነገራቸውም፣ እንዲሁም ሊከሰት ስለሚችለው አደጋም ምንም ማስጠንቀቂያ አልተሰጣቸውም፡፡ የቦዲ መሪ የጎሳውን አባላት ሁሉ በልጁ ለቅሶ ላይ እንዲገኙ ጠራ፡፡ ለክፉ መናፍስት መሥዋዕት እንዲሆኑና ጦረኞች ደማቸውን እንዲጠጡ፣ ጥሬ ሥጋቸውንም እንዲበሉ ብዙ ከብቶች ሰጠ፡፡ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ በጣም ብዙ ሺህ የሚሆኑ ጦረኞችን በመቶዎች ከሚቈጠሩ ሴቶችና ሕፃናት ጋር ወንዙን ተሻግረው እንዲሄዱ ላከ፡፡

በኮንታ ውስጥ ሰላማዊ የሆነ የእሑድ ማለዳ ነበር፡፡ እንደ ተለመደው ፀሐይ በመንደሯ እንደ ወጣች፣ ከወላይታ የመጣው ወንጌላዊ ከአዳዲስ አማኞች ጋር በመገናኘት ይጸልያል፡፡ በድንገትም የመጀመሪያ ዙር የቦዲ ጦረኞች በጣም ብዙ ወንዶች ጠመንጃቸውን እንዳነገቡ ደረሱ፡፡ በወንዝ አቅራቢያ ወደ አለው መንደር እየሮጡ በመሄድ በፊታቸው ያገኙትን ሰው ተኵሰው ይገድሉ ነበር፡፡ ያለማቋረጥ ወደሚቀጥለው መንደር ይሄዳሉ፤ በመንገዳቸውም ላይ ጠብመንጃቸውን እንደገና በጥይት ይሞሉና ያንን ጭካኔአቸውን ይፈጽሙ ነበር፡፡ ሰዎች ፍጹም በሆነ ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ ተሞልተው ወደ የአቅጣጫው ይሮጡ ነበር፡፡ ብዙ ሰዎች የአደን ጦራቸውን ይዘው ለመዋጋት ወደ ቦዲ ጦረኞች በመሮጥ ሞተዋል፡፡ ከጥይትና ከጦር ያመለጡ ሰዎች የሴቶችንና የሕፃናትን አንገት የሚቈርጡ፣ የሚዘርፉና ቤት የሚያቃጥሉ ቆንጨራ የያዙ የቦዲ ሴቶች ያጋጥሟቸዋል፡፡ መንደሮቹ በእሳት ከተያያዙ በኋላ ምንም ሰው በዚያ አይተርፍም፡፡

በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወደ ሰባ የሚደርሱ ሰዎች የተገደሉ ሲሆን፣ በሌላኛው ደግሞ ወደ ሠላሳ አምስት ሰዎች ተገድለዋል፡፡ ተኵሱና ጩኸቱ ሲሰማና በሌላ መንደር ያሉት ሰዎች ወደ ሰማይ የሚወጣውን ጭስና የሚሸሹትን ሰዎች ሲመለከቱ፣ ሰቆቃው መዛመት ጀመረ፡፡ መከላከል ያልቻሉት የኮንታ ሰዎች ወደየ ጫካው በመሸሽ መደበቅ ጀመሩ፡፡ ሴቶች ትንንሽ

ልጆቻቸውን እንዳቀፉ፣ ወንዶች የልጆቻቸውን እጆች እንደ ያዙ ከዚህ ጉድ መደበቅ ወደሚችሉበት ቦታ ሁሉ ሸሹ፡፡ ነገር ግን ሁሉም አላመለጡም፡፡ ምን ያህል ሰው እንደ ሞተ አይታወቅም፡፡ በሺህ የሚቈጠሩ ሰዎች ወደ ሌላ ስፍራ ተሰድደዋል፡፡ ጦረኞቹ የዘረፏቸውን ከብቶች፣ በጎችና ፍየሎች በጠቅላላ ወስደው የአሞን ወንዝ ለማሻገር ብዙ ቀናት ወሰደባቸው፡፡ ሴቶችና ልጆች ዶሮዎችና ብዙ የእህል ዓይነትን እንዲሁም ከሞቱ ሰዎች ላይ የገፈፉትን ልብስ ተሸክመዋል፡፡

ከዚያ ደም የማፍሰስ ጥማት ካለባቸው የተነሣ፣ አንዳንድ የቦዲ ወንዶች ወደ ማሎ ክፍል ሄዱ፡፡ ምንም እንኳ በዚያ የነበሩ ብዙ ክርስቲያኖች ከአደጋው ቢያመልጡም፣ የቦዲ ጦረኞች ብዙ ሰዎችን ገድለው በጣም ብዙ ከብቶችን ዘረፉ፡፡ ከዚያም የማሎ ዋና ከተማን በማጥቃት ብዙ ፖሊሶችን ገደሉ፡፡

ይህ ሁሉ ለመንግሥት ባለ ሥልጣናት በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ እንዲህ እንዲቀጥል መፈቀድ የለበትም፡፡ የቦዲዎች ጭፍጨፋ ማብቃት አለበት፡፡ ተጨማሪ የመንግሥት ኃይል ተጠራ፡፡ አንድ በሞቶ አለቃ የሚመራ ብርጌድ አውቶማቲክ መሣሪያ እንደ ያዘ ወደ ስፍራው ደረሰ፡፡ ቦዲዎችን ተከትሎ ሄደ፡፡ የቦዲ ጦረኞች ወታደሮቹን ለማጥቃት የሚጠቀሙት አንድ የሚያውቁት ዘዴ ብቻ ነበራቸው፡፡ ሁሉም በአንድ መሥመር ይሆኑና ወደፊት መሮጥ ነበር፡፡ ያ በጣም አስከፊ አደጋን አስከተለ፣ በጣም ተጨፈጨፉ፡፡ በጣም ብዙ ሰዎች ተገደሉ፡፡ ከዚያም ወታደሮቹ የቦዲዎችን መሪ በመያዝ ሩቅ ወደ ሆነ እስር ቤት ወሰዱት፤ እስከ አሁን ድረስ በዚያ ይገኛል፡፡

ይህ እንግዲህ የቦዲዎች ጭፍጨፋ ነበር፡፡ ከዚህ ሁኔታ ማገገም ፈጽሞ አልቻሉም፡፡ በቦዲ አካባቢም ተጨማሪ የታጠቁ የፖሊስ ኃይላት ከመገናኛ መሣሪያዎቻቸው ጋር በቦታው ላይ እንዲሠፍሩ ተደረገ፡፡ ይህም የቦዲዎችን የዘረፋ ወረራ እንዲቆም አደረገው፡፡ በአቅራቢያው ካሉት ጠላቶቻቸው፣ ማለትም የሙርሲ ጎሳዎች፣ የነበሯቸው ግጭቶች በቀላሉ ቀጥጥር ሥር ዋሉ፡፡

‹‹ወደ ኪዳንህ ተመልከት፣ የምድር የጨለማ ሰፍራዎች
በጎጥጓን ቤቶች ተሞልተዋልና።››

መዝሙረ ዳዊት 74፡20

32

በላታ

ሁሉንም ነገር ማጣት

በላታ ያን እሑድ ዘግይታ ነበር የደረሰችው፡፡ የሁለት ወንድ ልጆቿን ገላ ማጠብ ስለ ነበረባት ዘግይታለች፡፡ እናቷ በዚያ ሲያልፉ ጎራ ብለው ልጇን በጀርባዋ እንድታዝል ረድተዋታል፡፡ ባሏ ለጸሎት ቀድሟት ወጥቷል፡፡ በላታና እናቷ ከቤት በመውጣት ላይ ሳሉ ተኩስ ተጀመረ፡፡ ከመፍራታቸው የተነሣ ባሉበት ቆመው ቀሩ፤ እየሆነ ያለው ነገር ግራ አጋባቸው፡፡

ከዚያም ገላቸውን የተለያየ ቀለማት የተቀቡ የቦዲ ጦረኞች በመንደሩ ውስጥ ወዲያና ወዲህ እየተሯሯጡ ያገኙትን ሰው ሁሉ ተኩሰው ሲገድሉና ጠመንጃቸውን እያቀባበሉ ወደሚቀጥለው መንደር ሲሮጡ ተመለከቱ፡፡ ከእነርሱ በኋላ በጣም ብዙ ጦር በእጃቸው የያዙ ወንዶች ከጥይት የተረፉትን ሰዎች እየገደሉ በመምጣት ላይ ነበሩ፡፡ በጣም ብዙ ሴቶች ቆንጨራዎቻቸውን እያወዛወዙ፣ ያገኙትን ነገር እየዘረፉና እያቃጠሉ በመምጣት ላይ ነበሩ፡፡ በላታ እንደ ሌሎች ሰዎች ሁሉ እየጮኸች ወደ ጫካው ሮጠች፤ ማሰብ የቻለችው ነገር ማምለጥ ብቻ ነበር፡፡ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ወጥተው በየአቅጣጫው መሮጥ ጀመሩ፡፡ ጥቂቶች ማምለጥ የቻሉ ሲሆን፣ አብዛኞቹ በጥይትና በጦር ተገደሉ፡፡ የቦዲ ወጣቶች እንስሳቱን እየሰበሰቡ ሳለ፣ ከጥይትና ከጦር የተረፉትን ጥቂት ሰዎች የቦዲ ሴቶች በቆንጨራ ከታተፏቸው፡፡

መላ ቤተሰቡ የጦር ውርወራ በበዛበት ሜዳ ውስጥ ይሮጥ ነበር፡፡ የበላታ እናት ከጐኗ ሞቱ፡፡ የአራት ዓመት ሴት ልጇ ቆንጨራ ቆረጣት፡፡ በላታ እንዴት እንደ ሆነ ባታውቅም፣ ጦሩ ሳያገኛት ወድቃ እንደገና እየተነሣች ሮጠች፡፡ ስትሮጥም ልጇ ወደ ላይ እና ታች ይዘልል ነበር፡፡ ከነልጇም ጥቅጥቅ ወዳለው ደን ደረሰች፡፡ ነገር ግን ሁሉም ወንድሞቿና እኅቶቿ ተገድለዋል፡፡ ባለቤቷም ከአደጋው ተርፎ ከጥቂት ቀናት በኋላ ከበላታና ከልጁ ጋር ተገናኘ፡፡ ከሌሎች

ጥቂት ከአደጋው ከተረፉ ሰዎች ጋር በአንድነት ሆነው በጫካው ውስጥ ለሁለት ወራት ያህል ተደበቁ፡፡ ያለ ምግብ ቅጠላ ቅጠል፣ የጫካ ፍራፍሬና የዛፍ ሥራ-ሥር እየበሉ ቆዩ፣ ብዙ ጊዜ ይታመሙ ነበር፡፡ ከቀን ወደ ቀን እየደከሙ ሄዱ፡፡

ዝናቡ እንደገና መዝነብ ጀመረ፣ ወንዞችም እንደገና መሙላት ጀመሩ፡፡ የበላታ ባል ሚስቱንና ልጃቸው ከወንዝ ማዶ ወደ ማሎ ለማሻገር ያለውን ኃይል ሁሉ ተጠቀመ፡፡ በድካም ብዛት ከመውደቃቸው በፊት ማሎ ወደሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ደረሱ፡፡ ከጭፍጨፋው የተረፉትን ሌሎች ሰዎችን ሲቀበሉ እንደ ነበረ፣ ክርስቲያኖች ተቀበሏቸው፡፡ ነገር ግን የበላታ ባል በወባ ተይዞ ነበርና ያገኘው ምግብ ሁሉ ለሚስቱና ለልጁ ይሰጥ ስለ ነበር በምግብ እጥረት ምክንያት ሞተ፡፡ ልጁም በጣም ታምሞ ስለ ነበር ከጥቂት ቀናት በኋላ ሞተ፡፡

በላታ ምግብ ተሰጥቷት መመገብ ጀመረች፡፡ ሁሉንም ቤተሰቦቿን ማለት - እናቷን፣ እኅት ወንድሞቿን፣ ልጆቿንና ባሏን አጥታ ስለ ነበረች ሰዎች ከእርሷ ጋር ሆነው አጽናኗት፡፡ በታላቅ ድንጋጤ ውስጥ ነበረችና ለምንም ነገር ግድ የላትም ነበር፡፡ እርሷም ለመሞት ፈለገች፡፡ እግዚአብሔር እርሷንም ይወስዳት ዘንድ ለመነችው፡፡ ብቸኛ፣ ተስፋ የቈረጠችና መራመድ እንኳ የማትችል ደካማ ሆነች፣ ተስፋዋ ሁሉ ተሟጥጦ ነበር፡፡ ነገር ግን ከብዙ ሳምንታት በኋላ፣ ቀስ በቀስ በክርስቲያን ሴቶች መልካምነትና እንክብካቤ፣ በላታ እየጠነከረች ሄደች፡፡ በቤተ ክርስቲያኑ አቅራቢያ በምትገኝ ትንሽዬ የሣር ቤት ውስጥ ትኖር ነበር፡፡

ከዚያም የቦዲ ጦረኞች ደም ለማፍሰስ ካላቸው ጥማት የተነሣ የማሎን ጥቂት ክፍል ወረሩ፡፡ በላታ ለደኅንነትዋ ስትል አሁንም ወደ ጫካ መሸሽ ነበረባት፡፡ የማሎ ክርስቲያኖች ለበላታ መጠለያ ነገር በማብጀት ምግብ፣ መድኃኒት እና ልብስ ይሰጧት ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ እነርሱ ራሳቸው እየተራቡ ምግብ ይሰጧት ነበር፡፡ ከዚያም ከጥቂላ ወደ ጌታ የመጣው ዳኖ ከዲማ ወደ ማሎ መጣ፡፡ በዲማ ጌሮ በሚባል ስፍራ መኖሪያ ቤት እንደሚሰጣት ሲነግራት፣ ስጦታውን በደስታ ተቀበለች፡፡

ወደ ጌሮ ከወንጌላውያን ዳንኤል እና ወርቁ፣ ተስፋዬና ኤርምያስ ጋር ሆነን መኪና እያሽከረከርኩ ስንሄድ ከዳኖና ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር በመሆን እንጸልይ ነበር፡፡ በላታን ለመርዳት ትንሽ የማቋቋሚያ ነገር ማድረግ ችለን ነበር፡፡ እርሷ ጥጥ በመግዛትና በመፍተል ልብስ መሥራት ትችላለች፡፡

ይህንን በመሸጥ ምግብና ጥቂት ዶሮዎችን መግዛት፣ ከዚያም የዶሮዎችን እንቁላል በመሸጥ ተጨማሪ ዶሮዎችን፣ ከዚያም በጎችን መግዛት ትችላለች።

ባለፈው ጊዜ ወደ ዲማ ሄጄ ነበር፣ በላታ በአካባቢው የሚገኝ አንድ ክርስቲያን አግብታ ሌላ አዲስ ሕይወት ጀምራለች። ውኃ ለመቅዳት እንስራዋን በጀርባዋ ይዛ ወደ ምንጭ ስትሄድ፣ ሁሌ የምትዘምረው አንድ ዝማሬ አላት። በጣም አስደንጋጭና አስፈሪ በሆነ ገጠመኝ ውስጥ በማለፍ በላታ የእግዚአብሔርን ጸጋና ፍቅር አረጋግጣለች። ጌታን በታማኝነት አሁንም ማመስገኗን፣ ማምለኳንና ማገልግሏን ቀጥላለች። እግዚአብሔር ይባርካት!

> *‹‹ሴቶች . . . በምድረ በዳና በተራራ፣ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ። እነዚህም ሁሉ በእምነታቸው ተመስክሮላቸው ሳሉ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አላገኙም።››*
>
> ዕብራውያን ፲፩፡35-39

33

ሳምሶ

ሕይወትን ለማትረፍ ሩጫ

ጠዋት አንድ ሰዓት ገደማ የቡዲ ጦረኞች መንደራቸውን ሲወርሩ ጎፖሎና ሌሎች ወጣት ወንዶች የጸሎት ፕሮግራማቸውን መጨረሳቸው ነበር። ተኩሱ እንደ ተጀመረ፣ ጥይቱ ወደሚተኮስበት ሁሉም እየሮጡ ወጡ፣ ነገር ግን ከእነርሱ መካከል ጥቂቶች ተመቱ። ምንም መሣሪያ ባለመታጠቃቸው፣ ለደኅንነታቸው ሲሉ ወደ ጫካው ሮጡ።

አንድ የቡዲ ጦረኛ ጦሩን እንደ ሰበቀ ጎፖሎን ተከትሎ ይሮጥ ጀመር። ጎፖሎ ሰውዬው እንደ ተከተለው ተመለከተና ፍጥነቱን ጨምሮ፣ አየሩን እየቀዘፈ፣ በጫካው ውስጥ እየወደቀና እየተነሣ ነፍሱን ለማዳን ሮጠ። ነገር ግን የቡዲው ጦረኛ ከእርሱ ይልቅ ፈጣን ስለ ነበር ሊደርስበት ጥቂት ቀረው። ጎፖሎ ተስፋ በመቁረጥ ወደ ጌታ ኢየሱስ ለእርዳታ ተጣራ። ወደ ኋላውም ዘወር ብሎ ሲመለከት የቡዲ ጦረኛ አጠገቡ ደርሷል፣ ጦሩንም ለመወርወር ተዘጋጅቷል።

በድንጋጤ ጎፖሎ ወዴት እንደሚሄድ እንኳ መመልከት አልቻለም። ከዚያም፣ ከፊት ለፊቱ ባለው ጉድጓድ ውስጥ በአፍጢሙ ተደፋ። ከትልቅ ድንጋይ ጋር ተያይዞ ከአንድ ትልቅ መርዛማ እባብ አጠገብ ወደቀ። በድንጋጤ ደርቆ ቀረ! እባቡ ከአሁን አሁን ነደፈኝ ብሎ እየተጠባበቀ ሳለ፣ እባቡ እየተሳበ ከጉድጓዱ ወጣና ከጉድጓዱ አፋፍ ላይ ሆኖ ጦሩን በጎፖሎ ላይ ለመሰካት በማነጣጠር ላይ ወዳለው የቡዲ ጦረኛ እግር አቀና። የቡዲ ጦረኞች ሌሎች ብዙ ነገሮችን አይፈሩም፣ ነገር ግን እባብ በጣም ያስፈራቸዋል! የቡዲ ጦረኛ እባቡን ሲመለከት ወደ ኋላ ዘልሎ፣ ፊቱን አዙሮ ወደ መጣበት እየሮጠ ሄደ።

ጎፖሎ ምንም አላቅማማም። ከጉድጓድ ውስጥ ዘልሎ በመውጣት ወደ ተቃራኒው አቅጣጫ ሮጠ። ያለማቋረጥ ለሰዓታት ስለ ጥበቃውና መልካምነቱ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሮጠ። ወደ አንድ መንደር በደረሰም ጊዜ የአደጋ

ጩኸት እያሰማ፣ የሰዎቹን ቀልብ ሳበ። ቦዲዎች እየመጡ ስለሆነም ሰው ሁሉ ያለውን ነገር እየተወ ነፍሱን ያድን ዘንድ እየጮኸ ጥሪውን ያስተላልፍ ነበር። ከአንድ መንደር ወደ ሌላኛው መንደር ያለማቋረጥ እየሮጠ ይህንን የማስጠንቀቂያ ጩኸቱን ያሰማ ነበር። ያለጥርጥር የእርሱ የማስጠንቀቂያ ጥሪ የብዙዎችን ሕይወት አድኗል።

ጎፖሎ አስፈላጊውን ከለላ ሊያገኝበትና ብዙ ፖሊሶች ወደ አሉበት የዋካ ከተማ እስኪደርስ ድረስ መሮጡን አላቆመም። ከዚያም የቦዲዎችን ጭፍጨፋ ለፖሊስ አስታወቀ። የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮናውያን እርሱን በአስፈላጊው ነገር ለማገዝ በዚያ ነበሩ፣ እንዲሁም ከኮንታ ለመጡ ብዙ ስደተኞች መጠለያ ስፍራ አዘጋጁላቸው። ጎፖሎ ከዚያ አስፈሪ ገጠመኝ ለመላቀቅና እግዚአብሔርን ስላዳነው ማመስገንን ለማቆም ብዙ ጊዜ ፈጅቶበታል።

ጎፖሎ ወደ ኮንታ መንደር እየሄድን በነገረኝ ታሪክ አማካይነት የጠፋውን ንብረትና የደረሰውን እልቂት ለመረዳት ቻልኩ። በስፍራው ላይ ቆመንም አለቀስን። ይህን ያህል ክፋትና፣ ጥላቻ በሰው ልብ ውስጥ እንዴት ሊኖር እንደሚችል መረዳት አስቸጋሪ ነበር። በጉልበቶቻችን ተንበርከክን፣ በሆነ መንገድ እግዚአብሔር ይህንን ሁኔታ ለመልካምና ለእርሱ ክብር ብቻ እንዲያውለው ጸለይን።

እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፣ በእርሱ ጸጋና ምሕረት ያ ጸሎታችን ምላሽ ሲያገኝ በሕይወታችን ተመልክተናል። ባለፈው ዓመት በ2000 ዓ.ም በመቶዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች፣ በኮንታ ውስጥ በኮንፍራንስ ላይ የእግዚአብሔርን ቃል የማካፈል ዕድል አገኘሁ። ወደ ሰባ የሚሆኑ ቤተ ክርስቲያናትን ለመጐብኘትም ዕድሉን አግኝቼ ነበር። ከእነዚህ ቤተ ክርስቲያናት መካከል አንዳንዶቹ ከዚያ አስከፊ ቀን በኋላ የተመሠረቱ ቤተ ክርስቲያናት ነበሩ። የእግዚአብሔርን ፍቅርና ሰላም ለሰው ልጆች ይዘው ከሚሄዱት ሰዎች ጋር እንደገና ኅብረት ማድረግ መቻል ምንኛ አስደሳች ነገር ነው! ጌታ የተመሰገነ ይሁን!

‹‹እግዚአብሔር መልካም ነው፣ በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው
በእርሱ የሚታመኑትንም ያውቃል።››

ናሆም 1:7

34

እንድርያስ

በሁሉም ውስጥ ለኢየሱስ

እንድርያስ እንዲህ ሲል ነገረኝ፣ ‹‹እናቴ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳለችው ሐና ሆና ነበር፡፡ ለአሥራ ሦስት ዓመታት ምንም ልጅ አልነበራትም፤ በዚያን ጊዜ ወላጆቼ ወንጌልን ሰምተው በኢየሱስ አመኑ፡፡ በኢ-አማኒያን ይሰደዱና መንደራቸውንም ለቅቀው እንዲሄዱ ይደረጉ ነበር፡፡ ለብዙ ጸሎታቸው መልስ ሆኜ እኔ ተወለድኩ፡፡ ያን ጊዜ ትልቅ ደስታ ሆነ፣ እናቴም በቤተ ክርስቲያን ምእመናን ፊት ቆማ በእግዚአብሔር ቤት እንዳገለግል ለጌታ አገልግሎት አሳልፋ ሰጠችኝ፡፡›› በመቀጠልም እንዲህ አለ፣ ‹‹ወላጆቼ ማንበብ እንድችል አስተምረውኛል፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ማመንም መርተውኛል፤ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ ሰጥተውኛል፣ ክርስቲያን እንዴት መኖር እንዳለበትም አስተምረውኛል፡፡››

እንድርያስ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የአራተኛ ክፍልን ሲያጠናቅቅ፣ በአንደኛ ክፍል ውስጥ የነበሩትን በመቶዎች የሚቈጠሩ ልጆችን ያስተምር ነበር፣ እንዲሁም የሰንበት ትምህርት ያስተምራቸው ነበር፡፡ ሃዋርድ ብራንት የተባሉ የኤስ ላይ ኤም ሚስዮናዊ ለሰንበት ትምህርት ቤት መምህራን ሥልጠና ሲሰጡ እንድርያስ በዚህ አገልግሎት ጌታን ለማገልገል ራሱን አሳልፎ ሰጠ፡፡

በሉቃስ 14፡26 ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- *‹‹ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የራሱን ሕይወት ሰንኳ ሳይቀር ባይጠላ፣ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።››* እንድርያስ በእግዚአብሔር ቅድስና እንዲሁም በሕይወቱ ውስጥ ስላለው የክርስቶስ ጸጋና ፍቅር በጣም ተደነቀ፡፡ በልቡ ውስጥ ስፍራ ያለው ማንምና

ምንም ሳይሆን፣ ክርስቶስ ብቻ ሆነ። ምንም እንኳ ተቃውሞ፣ ስደትና ብዙ መከራ በእርሱ ላይ ቢመጣም፣ የእግዚአብሔርን ቃል በጣም ይወድዳል፣ ለሌሎችም ለማካፈል ከፍተኛ መነሣሣት ነበረው፣ አሁንም አለው።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከተመረቀ በኋላም፣ እንድርያስ ለሦስት ወራት ከወላይታ ውጭ ሄዶ ወንጌልን ለማዳረስ ፈቃደኛ እንዲሆን ሰዎች ላቀረቡለት ጥሪ ምላሽ ሰጠ። ወደ ኮንታ ለስድስት ቀናት ከተጓዙ ሃያ ሁለት ሰዎች መካከል እርሱ አንዱ ነበር። እርሱ ይዞት የመጣውን የወንጌል መልእክት በመቀበል ምላሽ የሚሰጡ ብዙ ሰዎች ወደሚገኙበት ስፍራ እስኪደርስ ድረስ ተጓዘ። ሁሉም ነገር ለእነርሱ ግራ የሚያጋባና አዲስ ስለ ሆነባቸው፣ እስኪረዱት ድረስ ታሪኩን ደጋግሞ መናገር ነበረበት። ታሪኩም፣ ሰላም፣ ሕይወት እና ነፃነት ሲሆን፣ በሰይጣን ኃይል ለረጅም ዓመታት ከኖሩበት ከጨለማ፣ ከክፋት፣ ከኃጢአትና ከአስጨናቂ ፍርሃት የተለየ ነበር።

እንድርያስ ያረፈበት አካባቢ በኃይለኛ ጠንቋይ ተጽዕኖ ሥር የነበረ ሲሆን፣ ከሰይጣን እና ከመናፍስት እስራት ነፃ ለመውጣት ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ሰዎችን አግኝቷል። በጣም ብዙ ሰዎች አመኑ፣ በኋላ ላይም ተጠመቁ። ከሦስት ወራት አገልግሎት በኋላም አብዛኞቹ ወንጌላውያን ለበለጠ ትምህርት ወደ ወላይታ ተመለሱ፣ እንድርያስና ሌሎች ሁለት ወንጌላውያን ግን አዳዲስ አማኞችን ለማስተማር በስፍራው ቆዩ። ቤተ ክርስቲያን አቋቁመው እንድትጠነክር አደረጓት።

እንድርያስ ወጣቷን ሚስቱን ኤልሳቤጥን ወደ ኮንታ አመጣትና ሴቶችንና ኮረዶችን ሰብስባ መጽሐፍ ቅዱስን ታስተምራቸው ጀመር። አብረውም ቡና እየጠጡና ስለ ኢየሱስ እያወሩ ብዙ ሰዎች የወንጌልን መልእክት ሰምተው አመኑ። ሌሎች ወንጌላውያንም መጡ፣ ወዲያው ወደ አሥራ አምስት የሚጠጉ ወንጌላውያን በኮንታ ውስጥ የወንጌል ትምህርት ጀመሩ። ከጠንቋዩና ከአካባቢው አስተዳዳሪ በጣም ብዙ ተቃውሞዎች ይደርሱበት ነበር። የኮንታ አካባቢ አስተዳዳር እንድርያስ መስበኩን ካላቆመ እንደሚገድለው አስፈራርቶታል። ለማስፈራራትም፣ የሰውዬው የታጠቁ ሰዎች እንድርያስን ገድለን እንቀብርሃለን ወዳሉት ቦታ ወስደውት ነበር፣ ነገር ግን የአስተዳዳሪው ሚስት ጣልቃ በመግባት እንድርያስን ልትታደገው ችላለች።

ከዚያም፣ ከቦዲ ጦረኞች መካከል ጥቂቶች የኦሞን ወንዝ ተሻግረው

መጥተው የመሪውን አንድ ባሪያ በመግደል ጥቂት ከብቶች ዘርፈው ሄዱ፡፡ የአካባቢውም መሪ ለዚህ ነገር ተጠያቂዎቹ ክርስቲያኖች ናቸው በማለት የክርስቲያኖችን መኖሪያ ቤት ማቃጠል ጀመረ፡፡ እንድርያስና ኤልሳቤጥ እግዚአብሔር እንዲሸሹ ሲያስጠነቅቃቸው የእግዚአብሔርን ጥበቃ ተረድተው ነበር፡፡ ለመቆየትና ክርስቲያኖችን ለመርዳት የልብ ሰላምና ፍላጎት ነበራቸው፡፡

ከአንድ ወር በኋላም የቦዲው ጭፍጨፋ ተካሄደ፣ በዚህም በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሞቱ፣ ይህ ቍጥር ጥቂት ክርስቲያኖችንም ያካትታል፤ በጣም ብዙዎቹ ግን በሚገርም ሁኔታ አመለጡ፡፡ እንድርያስና ነፍሰ ጡር ሚስቱ ወደ አቅራቢያው ገደል በመሮጥ በጫካው ውስጥ ተሸሸጉ፡፡ የቦዲ ጦረኞች እየተከሱና በጦሮቻቸውና በቆንጨራዎቻቸው ሰዎችን እየገደሉ፣ እንድርያስና ባለቤቱ በተደበቁበት ስፍራ አጠገብ እየሮጡ ሲያልፉ እነርሱ እየጸለዩ ነበር፡፡

የቦዲ ጦረኞች የዘረፏቸውን ከብቶችና ቍሳቍሶች ይዘው ከተመለሱ በኋላ፣ እንድርያስ ጥቂት ከእልቂቱ የተረፉ ሰዎችን በጫካው ውስጥ አገኘ፡፡ ምንም ዓይነት ምግብ አልነበራቸውም፣ ነገር ግን በጫካው ውስጥ ለደኅንነታቸው ሲሉ ተሸሽገው ያሳለፏቸውን ጊዜያት ሁሉ ሥራ ሥርና ቅጠላ ቅጠሎችን ሲመገቡ ቆዩ፡፡ በእርግጥ፣ በዚህ አሰቃቂ ጭፍጨፋ ጊዜ ውስጥ ከወላይታ ከመጡ ወንጌላውያን መካከል አንዱም አልሞተም፣ ነገር ግን ሁሉም የነበሩአቸውን ንብረት ሁሉ አጥተዋል፡፡

የኮንታ መሪና ሁለቱ ልጆቹ ከቦዲዎች ጋር ሲዋጉ ተገደሉ፣ ነገር ግን ሚስቱና ትንንሽ ልጆቹ ከእልቂቱ አምልጠዋል፡፡ በኋላ ላይም እርሷ ወደ ክርስቶስ መጥታ እግዚአብሔርን ማመስገን ጀመረች፣ ዛሬ አብዛኞቹ ቤተሰቦቿም ጌታ ኢየሱስን በማመስገን ላይ ናቸው፡፡ በ2000 ዓ.ም ለመጐብኘት ወደዚያ ሄጄ ከአንዳንዶቹ ጋር ጌታን አመስግኛለሁ፡፡ በኮንታ ውስጥ ክፉትን ወደ በጎ ነገር የቀየረው እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፡፡

እንድርያስና ኤልሳቤጥ በኋላ ላይ ወደ ወላይታ ተጠሩ፡፡ እንድርያስ መጋቢ ሆኖ በሚያገለግልበት ከተማ ውስጥ በምትገኝ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምእመናን ቍጥር ከአንድ ሺህ በላይ አድጓል፡፡ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በሚገኘው ስፍራ በተከናወነው የስብከት አገልግሎት አማካይነት እግዚአብሔር ሌሎች አዳዲስ ቤተ ክርስቲያናት እንዲጀመሩ አድርጓል፡፡

ለጌታ አገልግሎት የተሰጠው የሐና ልጅ ትንሹ ሳሙኤል በአገልግሎቱ መጨረሻ ላይ እንዲህ ብሎ ነበር፣ *‹‹ደግሞ መልካሙንና ቅኑን መንገድ አስተምራችኋለሁ እንጂ ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ። ብቻ እግዚአብሔርን ፍሩ፣ ያደረገላችሁንም ታላቅ ነገር ዐይታችኋልና በፍጹም ልባችሁ በእውነት አምልኩት።››*

እንድርያስ እንዲህ ብሎ ነገረኝ፣ ‹‹እግዚአብሔር ደኅና እንድሆን ጠበቀኝ እንዲሁም በቃሉ ውስጥ ያለውን የተስፋ ቃሉን ጠበቀ፡፡ እኔም አማኞች በስደትና በመከራ ቀን በጌታ ኢየሱስ ላይ ተጣበቁ ብዬ አስተማርኩ፡፡ በኮንታ ውስጥ የሆኑት ነገሮች ምንም ላደርጋቸው አልችልም፡፡ የእግዚአብሔር መንገድ ከእኛ እውቀት ውጭ ነው፡፡ በልዩ ስብሰባ ላይ የእግዚአብሔርን ቃል ለማካፈል ወደዚያ በሄድኩ ጊዜ ሰባ ቤተ ክርስቲያናት በዚያ ተመልክቻለሁ፡፡ ከአሰቃቂው እልቂት የተረፉና በኋላ ላይ ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ማለትም ወደ ክርስቶስ የመጡ በመቶዎች ከሚቈጠሩ ሰዎች ጋር ተገናኝቻለሁ፡፡››

35

ሃብታሙ

የወንድሜ ጠባቂ

ኣንድ አጭር፣ ሰውነቱ ደልደል ያለ፣ የአሥር ዓመት ልጅ ፊቴ ቆሞ እንዲህ አለ፣ ‹‹እኔ ከአንተ ጋር እሄዳለሁ፡፡ ከአንተ ጋር ወደ ቦዲዎች እሄዳለሁ፡፡››

ኮንታ ባሮዳ ውስጥ ነበርኩ፣ ዋካ ወደሚገኘው የኤስ ኣይ ኤም የሚስዮናውያን ጣቢያ ለመመለስ በቅሎዬን ለረጅም ጉዞ በማዘጋጀት ላይ ነበርኩ፡፡ እኔ እና ቪዳ ብዙ ጊዜ በኤምኤኤፍ አውሮፕላን በረራ እናደርግበት ከነበረ ቦታ ላይ ሆኜ በሁሉም አቅጣጫ ቦዲዎች ያጠፏቸውን እና ጭፍጨፋ ያደረጉባቸውን መንደሮች ማየት ችያለሁ፡፡ የተቃጠሉ ቤቶች፣ ባዶ ማሳዎች መታየት፣ እንስሳትና ሰዎች ግን በአካባቢው አለመታየት፣ በሰማይ ላይ ክብ ሠርተው የሚበሩ ጥንብ አንሣዎች እና በሁሉም አቅጣጫዎች እስከ ብዙ ኪሎ ሜትሮች ድረስ ያለው የቦዲዎች ጥቃት፣ ማለትም በኡሞ ወንዝ ዙሪያ ያደረጉት ወረራ ምን ያህል ከባድ እንደ ነበር ምስክሮች ናቸው፡፡

ሥ

የቦዲ ጦረኞች ሁሉንም እንስሳት እየነዱ፤ ሴቶቹን እና ሕፃናቱን እንዲሁም ጥራጥሬንና የሚችቹን ልብሶችን ተሸክመው፣ ወንዙን ተሻግረው ወደ ድንበራቸው ሲሄዱ በመቶዎች የሚቆጠሩ የበሰበሱ ሬሳን እና አመድ የሆኑ ቤቶችን ትተው ነበር የሚሄዱት፡፡ አስከሬኖች እዚህ እና እዚያ በሰፊ መሬት ላይና በተለያዩ መንደሮች ውስጥም ከመንደሮቹ በተለያዩ መኖሪያ ቤቶች ውስጥም ተበትነዋል፡፡ አንዳንዶች ሰዎች ጦረኞቹ ከገደሏቸው ሰዎች ሬሳ ላይ ልብስ በመግፈፍ ለብሰዋል፡፡ አራት ትንንሽ ልጆችን፣ ሦስት ሴቶችንና አንድ ወንድ ልጅ በምርኮኝነት ወስደዋል፡፡ ትንሹ የተወሰደው ወንድ ልጅ ስሙ አካሉ

ሲሆን፣ የአምስት ወይም የስድስት ዓመት ልጅ ነበር። አካሉ የሀብታሙ ወንድም ነበር። ጦረኞቹ እነዚህን ልጆች የወሰዷቸው ምናልባት ባሪያ ሊያደርጓቸው ወይም ለመሥዋዕትነት ሊሆን ይችላል። እነዚህ ሕፃናት እስከ ዘላለሙ ጠፍተዋል።

በዚያ ጸጥታ በሰፈነበት የእሑድ ጠዋት፣ የማለዳ ፀሐይ እንደ ወጣች፣ ሀብታሙ ወደ ጸሎት ፕሮግራም ለመሄድ በተነሣው አባቱ አማካይነት ከእንቅልፉ ነቃ። ሀብታሙ ከብቶቹን ፈትቶ ከበረት አስወጣቸው። ታናሽ እኅቱ አስቴር፣ እናትየው በዚያ ቀን እንዲመገቡት የሰጠቻቸውን የተቆላ በቆሎ በአንገት ልብሷ ጫፍ ቋጠረችና ከሀብታሙ ጋር በመሆን ከብቶቹን ሣር ለማስጋጥ ከመንደሩ ወጥታ ሄደች።

ከምንጭ ከብቶቹ ውኃ ከጠጡ በኋላ፣ በሰፊው የግጦሽ መሬት ላይ ሣር ፍለጋ መበታተን ጀመሩ። በመንደሩ ውስጥ ተኩስ ሲጀመር ሀብታሙና እኅቱ ውኃው አካባቢ ነበሩ። ደነገጡ፣ በጣምም ፈሩ። ምን እየሆነ እንዳለ ግራ ገባቸው። ከፍ ወዳለ ስፍራ ላይ ወጥተው ለመመልከት ሞከሩ። በሚሰሙት የሰቆቃ ጩኸትና ጫጫታ በጣም ተደናገጡ፣ ሰዎች በየአቅጣጫው ሲሮጡና በጥይት ተመትተው ወይም ተወግተው ሲወድቁ ተመለከቱ።

የቡዲ ጦረኞች ወደ እነርሱ አቅጣጫ እየሮጡ ሲመጡ አዩ። እጅግ በጣም የፈራው ሀብታሙ ምን ማድረግ እንዳለበት አላወቀም። አካባቢውን ቃኘ። ከምንጩም አጠገብ እጅብ ብሎ የበቀለ ቍጥቋጦ አየ። ምናልባት እዚያ ሥር መደበቅ ይችል እንደ ሆነ አሰበ። የሚሮጡ እግሮች ድምፅ እየተቃረበ በሄደ ቍጥር፣ ሀብታሙ የትንሽዋን እኅቱን እጅ አጥብቆ ይዞ እየንተተ በጫካው ውስጥ ተደበቀ። ብዙዎች ጦረኞች ሮጠው አለፉ፣ ነገር ግን ጥቂት ወጣቶች ግን በአካባቢው ያሉትን እንስሳት ከመሰብሰባቸው በፊት ውኃ ለመጠጣት ምንጩ ጋ ሲደርሱ ቆሙ።

ሀብታሙ እኅቱ ከፍራቻ የተነሣ ወይም ከብቶቻቸው በመወሰዳቸው የተነሣ በንዴት እንዳትጮህ አፏን በእጁ ግጥም አድርጎ ያዛት። ሀብታሙ እና እኅቱ ለመንቀሳቀስ ፈርተው ለብዙ ሰዓታት በጫካው ውስጥ ተደበቁ፣ ቀኑንም ሙሉ በዚያው አሳለፉ። በመጨረሻም፣ ፀሐይ ስትጠልቅ፣ ከምንጩ ውኃ ለመጠጣት ቀስ ብለው ወጡ።

ወደ መንደሩ ቀስ እያሉ ተጠጉ፡፡ ምንም የተረፈ ቤት አልነበረም፡፡ ባዩት የሰዎች ሬሳና እልቂት ደነገጡ፡፡ ሀብታሙ እኅቱን ወደ መሸሸጊያ ስፍራቸው እየመራ ወሰዳት፡፡ ምንም ቃል አልተነፈሱም፡፡ ልጆቹ ከደረሰባቸው ድንጋጤ የተነሣ መተኛት አልቻሉም፣ ምን ማድረግ እንዳለባቸውም አላወቁም፡፡ ከምንጩ ውኃ ብቻ እየጠጡ ለሁለት ቀንና ሌሊት ተደብቀው ቆዩ፡፡

ለብዙ ቀናት የቦዲ ሰዎች በዚያ መንገድ ያልፉ ነበር፡፡ ወንዶቹ የዘረፏቸውን ከብቶች እየነዱ፣ ሕፃናቱ ዶሮዎችና በጎንቦ ማር ሲሸከሙ፣ ሴቶች ደግሞ በጭንቅላታቸው እህሎችን ተሸክመው፡፡ ሀብታሙ የጅብ፣ የአንበሳና የነብር ድምፅ መስማት ሲጀምር፣ እነዚህ እንስሳት በየቦታው የወደቀውን ሬሳ የሚመገቡ ስለ ሆነ፣ ይህ ቦታ ለእነርሱ አደገኛ መሆኑን ተረዳ፡፡ ሀብታሙ እኅቱን ወደ ተራራው እየመራ ወሰዳት፡፡ በኋላ ላይም እንደ እነርሱ ከእልቂቱ የተረፉ ሌሎች ሰዎችን አገኙ፤ ከእነርሱም ጋር ቅጠላ ቅጠል፣ ሥራ ሥርና ፍራ ፍሬ ይመገቡ ጀመር፡፡

የቦዲ ጦረኞች ከሄዱ ከሳምንት በኋላ፣ አንድ የፖሊስ መኪና በአቅራቢያው ከሚገኝ ከተማ መጣች፡፡ የኤም ኤፍ ኤፍ አውሮፕላን ብዙ ምግብና መድኃኒት ይዛ ወደ አካባቢው ደረሰች፡፡ በጣም ጥቂት ከእልቂቱ የተረፉ ሰዎች ወደ አካባቢው ተመለሱ፡፡ ሀብታሙና እኅቱ ከእነርሱ ጋር ሄዱ፡፡ ዝናብም መዝነብ ጀመረ፤ ይህም መሬት ቆፍሮ ጥቂት በቆሎ መዝራት አስቻለ፡፡ በስኳር ድንችና ከጫካ በሚገኝ ማር አማካይነት ከአደጋው የተረፉት ጥቂት ሰዎች እንደገና ሕይወታቸውን መገንባት ጀመሩ፡፡ ሀብታሙና እኅቱ ሣርና እንጨት በማጨድና በመቀኑረጥ ለራሳቸው ቤት ሠሩ፡፡

ᎏᎏ

ከጥቂት ወራት በኋላ፣ ከእረፍት ተመልሼ እያዘገምኩ ወደ ኮንታ ቦሮዳ መጣሁ፣ ምክንያቱም የደርግ መንግሥት የኤምኤኤፍ አውሮፕላን እንዳይበር አግዶ ነበር፡፡ አንዳንድ ስደተኞች ከተሰደዱበት ስፍራ እየተመለሱ መኖሪያ ቤታቸውን በመገንባት ላይ ይገኛሉ፡፡ የሀብታሙና የአስቴር ዘመዶች መጥተው ከእነርሱ ጋር መኖር ጀመሩ፡፡ ሣር ቤት ሠሩ፣ እንዲሁም በቆሎ፣ ስኳር ድንችና ማሽላ ለመዝራት ተጨማሪ መሬት ቆፈሩ፡፡

በቦረዳ ለጥቂት ቀናት ከቆየሁ በኋላ፣ በፈረስ ብዙ ሰዓታትን ለመጓዝ ወደ ዋካ ለመሄድ ተነሣሁ፡፡ ከዚያም ሀብታሙ ተነሣና ፊት ለፊቴ ቆሞ ከእኔ ጋር ወደ

ቦዲዎች እንደሚሄድ ነገረኝ፡፡ ገዳይ ወደ ሆኑት ጎሳዎች በመሄድ እግዚአብሔር ሰዎችን ከኃጢአት ለማዳን ያለውን ዕቅድ፣ ስለ ኃጢአት ይቅርታና ዕርቅ፣ የልብ ሰላም እና ፍጹም አዲስ ሕይወት ለመናገር ማቀዴን ሰምቷል፡፡

ከወረራው በኋላ፣ ቦዲዎች ትንሹ ወንድሙን አካሎን ይዘው የኦሞ ወንዝን እንደ ተሻገሩ ሰምቷል፡፡ ወንድሙ ከቦዲዎች ጋር በሆነ ስፍራ መሆኑን ሰምቶ፣ ሀብታሙ ወንድሙን ለመፈለግ ቁርጦ ተነሥቷል፡፡

‹‹ሀብታሙ፣ እኔ ይገፍህ ልሄድ አልችልም፡፡ ወደ ዋካ፣ ከዚያም ወደ ዋና ከተማዋ አዲስ አበባ፣ ከዚያ በጎፋ በኩል አድርጌ ወደ ዲማ መሄድ አለብኝ፡፡ ወደ እነዚህ ቦታዎች ለመሄድ ደግሞ ለሳምንት ያህል ተጉዤ፣ ሰዎች በማይኖሩበት ጫካ ውስጥ ከእኔ ጋር ተጉዞ ወደ ቦዲዎች ድንበር ለመሻገር ፈቃደኛ የሆነ ሰው ማግኘት ያስፈልገኛል፡፡ በሰላም ይቀበሉን አይቀበሉን ምንም የምናውቀው ነገር የለም፡፡ በጭራሽ፣ በጣም አደገኛ ስለሆነ፣ ከእኛ ጋር መሄድ አትችልም፣›› አልኩት፡፡

ሀብታሙ እግሮቼን የሙጥኝ ይዞ እንዲህ ሲል ለመነኝ፣ ‹‹ጌታዬ እባክህን፣ ውሰደኝ፡፡ ሄጄ ወንድሜን መፈለግ አለብኝ፡፡ እኔ ላይ ምንም አደጋ ቢደርስ ግድ የለኝም፣ አካሎ ወንድሜ ነው፡፡ ሄጄ እርሱን መፈለግ አለብኝ፡፡ ወላጆቻችን ተገድለዋል፣ እርሱ ግን በሕይወት አለ፡፡ እባክህን ከአንተ ጋር ውሰደኝ›› አለኝ፡፡

የሀብታሙን እጆች በሁለት እጆቼ ይገፍ ከእግሬ ላይ አላቀቅኩ፡፡ በጉልበቶቼ ተንበርክኬ ያዘነውን ፊቱንና ቡናማ ዐይኖቹን እየተመለከትኩ ከእኔ ጋር ይገፍው እንደማልሄድ ደግሜ ነገርኩት፡፡ ነገር ግን ለሀብታሙ ወንድሙን እንደምፈልገውና ካገኘሁትም እንደምዋጀው፣ ይገፍውም እንደምመጣ ቃል ገባሁለት፡፡ ሀብታሙ ያልኩትን ተቀብሎ ምንም ተጨማሪ ነገር አላለም፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሆንና በመንገዳችን ላይ የእግዚአብሔር ጥበቃ እንዲበዛልን ተንበርክከን ስንጸልይ፣ ከእኛ ጋር ተንበርክኮ ጸለየ፡፡

ከቦዲዎች ጋር ግንኙነት ለማድረግ ከወንጌላዊ ተካ እና ከናና እንዲሁም ከብዙ ክርስቲያን ሠራተኞች ጋር ሆነን ባደረግናቸው በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንታት ጉዞዎች በምርኮ የተወሰዱ ልጆች ወይም የተዘረፉ ከብቶችን አላየንም፡፡ ከኮንታ

የመጡ በደም የተጨማለቁ ልብሶችን ግን አይተናል።

በኋላ ላይ ወንጌላዊ ተካን እና ናናን ጨምሮ፣ ከአምስት ወንጌላውያን ጋር በቦዲዎች መሃከል ለዘጠኝ ወራት ለመኖር በተመለስንባቸው ጊዜያት፣ ከኮንታ የተወሰደ አካሎ ስለሚባል ልጅ ምንም ወሬ አልነበረም። ስለ ልጁ ስንጠይቅ ቦዲዎች ጠብ መፈለግና ማስፈራራት ሲጀምሩ፣ ተካ ስለ ልጁ በቀጥታ መጠየቅ እንደሌለብኝ አስጠነቀቀኝ። ስለ ልጁ ምንም ነገር እንድናውቅ በእርግጥ አይፈልጉም። ልጁን ምን አድርገውት ይሆን ብዬ? ራሴን ጠየቅኩኝ።

ዛሬም ድረስ ያ ትንሽ ልጅ ወንድሙን ለመፈለግ ሲለማመጠኝ በፊቱ ላይ ይታይ የነበረውን ፍቅርና ውሳኔ አስታውሳለሁ። ሀብታሙ በትውስታዬ ውስጥ አሁንም አለ። የጠፉ ሰዎችን ለመፈለግ እንደዚያ ያለ ሽክም ቢኖረኝ ምን አለ!

> *‹‹የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና አለው።››*
>
> ሉቃስ 19፡10

> *‹‹በፍጹምም ልባቸው ምለዋልና፣ በፍጹምም ሕሊናቸው ፈልገውታልና፣ እርሱም ተገኝቶላቸዋልና ይሁዳ ሁሉ በመሐላው ደስ አላቸው እግዚአብሔርም በዙሪያቸው ዕረፍት ሰጣቸው።››*
>
> 2ኛ ዜና 15፡15

36

ክንታ ዘሬ ሳይሆ

(2001 ዓ.ም)

እግዚአብሔር እንዲሆን ያደረገው ነገር

ከሦላሳ ዓመታት በኋላ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ባለፈው ዓመት ወደ ኮንታ፣ ቦሮዳ በመመለሴ ትልቅ ደስታ ተሰምቶኛል፣ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ብዙ ምስጋና ለማቅረብ ምክንያት ሆኖልኛል። ጥሩ የውኃ ማስኬጃ ቦዮች ያሉት፣ በድንጋይ በደንብ የተሠራው አዲሱ መንገድ በመኪና የምናደርገውን ጉዞ ፈጣን አድርጎታል። ስፍራው እንደገና በብዙ ሕዝብ ተጨናንቋል፣ የሕዝብ ብዛት የጨመረው በኮንታ ሰዎች ብቻ ሳይሆን፣ መንግሥት ለም ወደ ሆነው ተራራማው አካባቢ እና ወደ ኮንታ ሸለቆዎች በሺህ የሚቈጠሩ አዳዲስ ሰፋሪዎችን ለግብርና አመች ካልሆኑ ቦታዎች አምጥቶ ስላሰፈራቸው ነው። በመንገዶቹ አቅራቢያና በሠፈራ ጣቢያዎች አካባቢ ከተሞች ተከትመዋል። ነጋዴዎች ትንንሽ ሱቆችን ከፍተው በከባድ መኪናዎች ቀሳቁሶችን ያመጣሉ። የወፍጮ ቤቶች መከፈት ሴቶችን በድንጋይ ወፍጮ እህል ከመፍጨት አድኗቸዋል።

አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ባላቸው ሕፃናት ተሞልተዋል። በአካባቢው ያለው የፖሊስ ጣቢያ በመገናኛ ሬዲዮ አማካይነት በየጊዜው ከሌሎች የፖሊስ ጣቢያዎች ጋር ቶሎ ቶሎ መረጃ ይለዋወጣል። ስለዚህም ብዙ ሕዝብ ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴ ሲያደረግ ለመቈጣጠር ተችሎአል። የአዲሱ መንገድ መገንባት በከባድ መኪናዎችና በሚኒባሶች ሰዎች ከቦታ ቦታ በቀላሉ እንዲዘዋወሩ አድርጓል። የስልክ መሥመር መዘርጋት የመገናኛ መንገድን በጣም ቀላል አድርጎታል፣ እንዲሁም የሞባይል ስልክ መያዝ በከተሞች ብቻ ሳይሆን፣ በጣም ሩቅ በሚባሉ ስፍራዎችም ሳይቀር አዲስ የሆነ የማንነት መለኪያ ሆኗል። ምክንያቱም ሞባይል የባለሀብቶች የመገናኛ መሣሪያ በመሆኑና በተራራዎቹ ጫፍ ላይ ጥሪ ማስተላለፊያ ጣቢያዎች በመተከላቸው

ምክንያት ነው።።

ነገር ግን በኮንታ ውስጥ የታየው ትልቁ ለውጥ በአሁኑ ጊዜ ሰባ የወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናት መኖራቸው ነው፣ ብዙዎቹም በቆርቆሮ የተሠራ ጣሪያ ሲኖራቸው፣ ሁልጊዜ በየቀኑ ጌታን ለማምለክ የሚሰበሰቡ በመቶዎች የሚቈጠሩ ጥሩ ምእመናን አሏቸው።። ምንም እንኳ ቅድመ-ማስጠንቀቂያ፣ ሳንሰጥ የመጣን ቢሆንም፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች በፍጥነት ለስብሰባ መጡ።። ለእግዚአብሔር ሕዝብ መሰጠትና ለእግዚአብሔር ቃል ትምህርት የሚሰጡት ምላሽ መገኘት ብዙ ደስታንና ምስጋናን ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ያመጣል።።

ብዙ ሰዎች መጋቢና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እንዲሆኑ ሥልጠና የሚወስዱበት ሦስት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በአካባቢው ሲኖር፣ ከዚህ ትምህርት ቤት የሚወጡ ሰዎች ደግሞ ሌሎችን የሰንበት ትምህርት ቤት መምህራንና በወጣቶች ጉዳይ ላይ እንዲሠሩ ሥልጠና ይሰጣሉ።። በኮንታ ያለው እያንዳንዱ አካባቢ ወንጌልን እንዲሰብኩና ወንጌልን እስካሁን ወደ አልሰሙ ሰዎች ይዘው ይሄዱ ዘንድ ከወንጌላውያን ሥልጠናን ይወስዳሉ።። በተለያዩ ጎሳዎችና የተለያዩ ቋንቋዎች ባላቸው ሕዝቦች መካከል እስከ መጨረሻ የሚጸና ሰላምና በቀላሉ ከቦታ ቦታ ለመጓጓዝ አመቺ ሁኔታ መኖሩን የኮንታ ክርስቲያኖች የክርስቶስን ወንጌል ለማሰራጨት ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ስጦታ እንደ ሆነ አድርገው ይመለከቱታል።። በኮንታ ሕዝብ ላይ ጌታ ስላሳየው ጸጋና መልካምነት ከእኛ ጋር አብራችሁ ለማመስገን ተነሡ።።

‹‹. . . ታርደሃልና፣ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ››

‹‹በታላቅም ድምፅ፡- ‘የታረደው በግ ኃይልና ባለ ጠግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል’ አሉ።።››

‹‹በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ፡- ‘በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፣ ለበጉም ይሁን’ ሲሉ ሰማሁ።።››

ራእይ 5፡9፣ 12፣ 13

37

ጨቋኙ ዝሬ ሳጅ

2001 ዓ.ም

ያልተጠናቀቀ ሥራ

በኦሞ ሸለቆዎች ውስጥ ካሉ ጎሳዎች መካከል በክርስቶስ ወንጌል ለመድረስ የቦዲ ጎሳ የመጨረሻ አስቸጋሪ የሆነ ሕዝብ ለመሆኑ በጣም ብዙ አሳማኝ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል አንዱ በቦዲ ድንበሮች አካባቢ ለረጅም ጊዜ ከ40 ዲግሪ ሴንቲግሬድ እስከ 50 ዲግሪ ሴንቲግሬድ የሚደርሰው የሙቀት መጠን ነው፡፡ የመንገድና የመገናኛ መንገድ፣ የትምህርት ቤትና የሕክምና ተቋማት እንዲሁም እህልና አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለመግዛት ገበያ አለመኖር እና ሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች ናቸው፡፡ እንደ ኮሌራ፣ ቢጫ ወባ፣ ታይፎይድ እና የማጅራት ገትር ወረርሽኞች በአካባቢው ላይ ቶሎ ቶሎ የሚነሡ በመሆናቸውና ሁልጊዜም ወባ፣ የዐይን በሽታ እና የሳንባ ነቀርሳ በስፋት መገኘታቸው ነው፡፡

ተጨማሪው ምክንያት ደግሞ፣ በአካባቢው ያሉ ሰዎች ለወተትና ደም ሲሉ ለሚያረቧቸው ከብቶች በአካባቢው ዝናብ አለመዝነቡ ለከብቶቹ ሣር ስለሚጠፋና የውኃ ጉድጓዶች ስለሚደርቁ፣ በዝንብ ወረርሽኝና በፄሴ ተናካሽ ዝንቦች አማካይነት ከብቶቻቸው ስለሚጐዱ ነው፡፡ ቦዲዎች በአካባቢው ባሉ ጎሳዎች ዘንድ በክሕደት፣ በጭካኔና በወረራ በመታወቃቸው ምክንያት፣ በሚያደርጉት ሰይጣናዊ ድርጊት ለእነርሱ ወንጌል ለማድረስ አስቸጋሪ ተጽዕኖ ፈጥሮአል፡፡

በኮንታ ውስጥ በቦዲዎች ከተደረገው ጭፍጨፋ በኋላ፣ በጎ ፈቃደኞች የሆኑትን የክርስቲያን ቡድንን እየመራሁ፣ ከዲማ ተነሥተን ሰዎች በማይኖሩበት አካባቢ አድርገን ለአጭር ጊዜ የቦዲ ድንበርን ተመልከተን ተመለስን፡፡ ይህ እንግዲህ ከቦዲ ጎሳ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገ ግንኙነት ነበር፡፡

ወንጌላውያን ናና፣ ተካና ካሳ የጀመሩት ግንኙነት በራሳቸው ላይ አደጋ የነበረው ቢሆንም፣ ግንኙነቱን ግን ቀጥለውበት ነበር። ከዚያም ተመልሼ ከእነርሱ እና ከሌሎች ወንጌላውያን ጋር በመሆን ትንሽ ከተጓዝን በኋላ ከቦዲ ጎሳ መካከል፣ ጊዩ ከሚባል ዘር ጋር ለዘጠኝ ወራት ኖርኩኝ። ከዚያን ጊዜ በኋላ፣ ምንም የውጭ ሀገር ዜጋ የሆነ ሚስዮናዊ በቦዲዎች መሃከል ኖሮ አያውቅም። በዚህ ጊዜ ነበር አንድ የቦዲ ሰው ተካን የገደለው።

የዘጠኝ ወራት ቆይታችን በኮምዩኒስቱ መንግሥት ምክንያት አበቃና የአሥራ አምስት ዓመታት የዝምታ ጊዜ ሆነ፤ ምክንያቱም፣ ማንም ወንጌላዊ በዚያ አካባቢ ምንም ነገር መሥራት አይፈቀድለትም ነበርና ነው። ከዚያ በኋላ ግን አንዳንዶች ወንጌላውያን፣ በወንጌላዊ ኤርምያስ መሪነት ወደዚያ ስፍራ ተመለሱ። ወንጌላዊ ኤርምያስ ለሚቀጥሉት አሥራ ሰባት ዓመታት ምንም የፖሊስ ጣቢያ በሌለበት ሐና በሚባል ትልቅ መንደር ውስጥ በትጋት ሲሠራ ለረጅም ጊዜ ቆይቷል።

ሐና በአሁኑ ጊዜ፣ የመገናኛ ሬዲዮ ያለው ፖሊስ ጣቢያ ያላት፣ ትምህርት ቤቶች እና የሕክምና መስጫ ክሊኒኮች የተከፈቱባት፣ ሳምንታዊ ገበያ የተጀመረባት፣ ትንንሽ ሱቆች፣ የውኃ ጉድጓድ፣ የእህል ወፍጮ ያላት፣ ስልክ እና የበጋ መንገድ የገባባት፣ የግንባታ ቀሳቀሶችና ሌሎች ዕቃዎች መግባት የሚችሉባት ትልቅ ከተማ ሆኗ አድጋለች።

መንግሥት ከኮንሶ ጎሳ በሺህ የሚቈጠሩ ሰዎችን አምጥቶ በስድስት ጣቢያዎች ለግብርና ተስማሚ በሆነ ስፍራ ላይ አስፍሮአል። ሁሉም የሠፈራ ጣቢያዎች አስፈላጊ ነገሮች ተሟልተውላቸው፣ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ክሊኒክ፣ የእህል ወፍጮ፣ የውኃ ጉድጓድ እና የፖሊስ ጣቢያ አሏቸው። አንድ የቦዲ ከብቶች ጠባቂ እረኛ እንደ ነገረን፣ ይህ ስፍራ ለከብቶቸቻቸው የግጦሽ ስፍራ ነበር፣ አሁንም ቢሆን ጥቂት ቦታ ቀርቶላቸዋል፣ ነገር ግን የኮንሶ ታታሪ ገበሬዎች ጥሩ እህል ማምረታቸውን ሲመለከቱ፣ በጣም ብዙ ቦዲዎች እህል ማምረት ጀምረዋል።

በሐና ያለችው ቤተ ክርስቲያን የተጀመረችው በኤርምያስ አማካይነት ሲሆን፤ ይህችን ቤተ ክርስቲያን ሌሎች ወንጌላውያን ከዚህ ተነሥተው ወደ ሌላ ስፍራ ሄደው ለማገልገል እንደ ማዕከላዊ ስፍራ አድርገው ይጠቀሙባታል። ከአሞ ወንዝ ማዶ ካሉት፣ ከመኤን ጎሳ የመጡት ወጣት ወንጌላውያን፣ ቦዲዎች

የሚናገሩትን ቋንቋ ስለሚናገሩ፣ ወንጌል ለቦዲዎች በማካፈሉ ሥራ ላይ ተሳታፊ ሆነዋል። ቤተ ክርስቲያን፣ ትምህርታቸውን ለመከታተል ከሩቅ ስፍራ ለመጡ ተማሪዎች ማደሪያ አዘጋጅታለች። ከተለያዩ ጎሳዎች የመጡ ወጣቶች አብረው በመኖራቸው፣ በመጫወታቸው፣ በመማራቸው እና በመመገባቸው ምክንያት፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የነበረው የተሳሳተ ግንዛቤና ጥላቻ ሊሰበር ችሏል። በተመሳሳይ ጊዜም፣ ወጣቶች የክርስቶስን ወንጌል የእነርሱን ቋንቋ ከሚናገር ወንጌላውያን መስማት ችለዋል።

በቅርብ ጊዜም ስድስት የቦዲ አማኞች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው ከተቀበሉ በኋላ ተጠምቀዋል፣ እንዲሁም በአዲሱ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ውስጥ የመጀመሪያው ክርስቲያናዊ ጋብቻ ተፈጽሟል። እስካሁን ድረስ የቦዲዎች ምላሽ በጣም ጥቂት ነው። ብዙዎች ደኅንነትን ያገኙ ዘንድና የአካባቢው ተወላጆች ወደ መሪነት ስፍራ ያድጉ ዘንድ መጸለያቸንን እንቀጥላለን።

እግዚአብሔር የቦዲዎችን ታሪክ የመጨረሻ ምዕራፍ ገና አላጠናቀቀም!

> *‹‹የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና። እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት ሊድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? ‘መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው!’ ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?››*
>
> ሮሜ 10፡13-15

> *‹‹በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን- ‘መከሩስ ብዙ ነው፣ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት’ አላቸው።››*
>
> ማቴዎስ 9፡37-38

፴፰

ማክ

ትክክለኛ ቃል

በኮንታ ውስጥ አሰቃቂ ጭፍጨፋ ከተካሄደ በኋላ፣ ከቦዲ ነፍስ ገዳዮች ጋር ተገናኝተን ስለ ኢየሱስ መናገር እንችል ዘንድ፣ እግዚአብሔር መንገዱን እንዲከፍትልን በዓለማችን ላይ ላሉ ሰዎች እንዲጸልዩልን መልእክት አስተላለፍን። ሰዎች በማይኖሩበት ምድር በኩል አድርጌ፣ ምንም ዓይነት መሣሪያ ሳልታጠቅ፣ ወደ ቦዲ ድንበር ለመሄድ መነሣቴን ተካ ሲሰማ ከእኔ ጋር ለመሄድ ፈቃደኛ ከሆኑ ሰዎች መካከል የመጀመሪያው ነበር። ከዚያ አንድ ቀን፣ ጌታን ሳይቀበል በፊት ተካ በየዓመቱ በጣም ብዙ የታጠቁ ሰዎችን ይዞ በመምጣት ከቦዲዎች ግብር የሚሰበስበው የዲማዎች አለቃ ዕቃ ተሸካሚ ነበር። ተካ የቦዲዎችን የእግር መንገድ፣ ከከብቶቻቸው ጋር የሚኖሩባቸውን አካባቢዎችንና አስቸጋሪ የሆነው ቋንቋቸውን ተምሯል። ወንጌላዊ ናና፣ ተካ ምትክ የሌለው ሀብታችን እንደ ሆነ አስተያየቱን ሰጥቷል፤ ምክንያቱም፣ ከዲማ ከመጡት ሁለቱ፣ ከካሳና ከደስታ ይልቅ የሀገሬውን ቋንቋ በደንብ የሚችለው ተካ ስለሆነ ነው። ካሳና ደስታ ለቦዲ ሰዎች በገቢያ ስፍራ በዲማ ውስጥ፣ እህል ይሸጡ ስለ ነበር፣ የሚያውቁት የመገበያያ ቋንቋን ብቻ ነበር። ካሳና ደስታ ሁለቱም በፊታችን ባሉት ጥቂት ወራት ውስጥ ብዙ ነገር በመማር ታማኝ ወንጌላውያን ይሆናሉ።

አምስቱ ወንጌላውያንና እኔ ለዘጠኝ ወራት በቦዲ ጎሳዎች መካከል ጊዩ በሚትባል መንደር ውስጥ ኖርን። ለመኖሪያም ትንሽ የሣር ጎጆ ሠራን። የእኛ ሣር ቤቶች ከቦዲዎች ጎጆ ትንሽ ከፍ ይላል። ለሕዝቡም ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስንናገር ተካ ይተረጉምልናል። ሕዝቡ የክርስቶስ የሕይወት ታሪክን፣ ተአምራቱንና ሕመምተኞችን መፈወሱን፣ እንዲሁም በምሳሌ ያስተማራቸው ትምህርቶችን ሁሉ ወደዱት። ተካ ታሪኩን እየተረጐመ በእንቅስቃሴ ያሳያቸው ስለ ነበር፣ የቦዲ ሰዎች በጥሞና ያደምጡ ነበር። የቦዲ ልጆችም ሁል ቀን ጠዋት

በማለዳ ይመጡ ነበር፤ እኛም እነርሱን የአማርኛ ፊደልን ማስተማር ጀመርን፡፡ አማርኛ እነርሱ የሚያውቁት ቋንቋ አይደለም፣ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ያለው በዚህ ቋንቋ ብቻ ስለ ሆነ ነበር፡፡

በየዕለቱ ማታ ማታ በጋራ የጥሞና ጊዜያችን ላይ በአንድነት እየጸለይን ሳለ፣ ምንም እንኳ ቦዲዎች ታሪኩን ቢወድዱትም፣ አንዳንዶቹን መንፈሳዊ ሐሳቦች መረዳት እንዳልቻሉ ደረስንበት፡፡ ወንጌላውያን ‹‹መታረቅ›› ወይም ‹‹ይቅርታ›› ወይም ‹‹ስርየት›› ለሚለው ቃል ተተኪ የቦዲ ቃል ማግኘት አልቻሉም ነበር፡፡

አንድ የቦዲ ሰው ከሌላ ጎሳ ከመጣ ሰው ጋር ጓደኝነት ፈጥሮ፣ ይህንን ለማድረግ አሥር ዓመታት የሚፈጅ ቢሆንም እንኳ ማለት ነው፤ ምግቡን ተመግቦ፣ ሁሉንም ነገር ተጋርቶ፣ በጓደኛው ቤት ለማደር መሣሪያ ሳይዝ ሄዶና በዚያ አድሮ (በእነርሱ ባህል ጠዋት በማለዳ ለአደን ወጥተው ሊሆን ይችላል)፣ ነገር ግን በድንገት ተነሥቶ ጓደኛውን ከገደለው ጀግና ተብሎ፣ ምስጋና የተገባው ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ከጎሳቸው ውጭ ከሆነ ሰው ጋር ጓደኝነትን መፍጠር ለአንድ ዓላማ ብቻ ነበር- ለመከዳትና እርሱን ለመግደል፡፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ ውስጥ ይሁዳ ኢየሱስን የከዳበትን ታሪክ ማውራት እንደሌለብን ተረዳን፣ ምክንያቱም ቦዲዎች በታሪኩ ውስጥ ይሁዳ ጀግና እንደ ሆነ ስለሚያስቡ ነው!

ይቅር ማለት የሚለው ሐሳብ ለቦዲዎች እንግዳ ነገር ነበር-የሰደባቸውን፣ አካላዊ ጉዳት ያደረሰባቸውን ወይም በተሳሳተ መንገድ የተረዳቸውን ፈጽሞ ይቅር አይሉም፡፡ ቂም በቀል ግዴታ ነበር፡፡ ተካ ‹‹አትጥላ››፣ ‹‹አትበቀል››፣ ‹‹ምላሽ አትስጥ›› ወይም ‹‹አትግደል›› በማለት አሉታዊ ቃላትን ይጠቀማል፡፡ እኛ ‹‹ይቅር በሉ›› የሚለውን ቃል እንጠቀማለን፡፡ ይህ ቃል ‹‹በደሉን እንደገና አታስቡ›› የሚል ትርጓሜ ከሚኖረው ይልቅ፣ ለቦዲዎች የሚኖረው ትርጓሜ ‹‹አሁን ሳይሆን በኋላ ላይ እበቀላለሁ›› የሚል ነበር፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለእነርሱ ስናካፍል ትኩረት የምንሰጠው ኃጢአትንና ሰይጣንን በመተውና ኃጢአታቸውን በመናዘዙ፣ በማመን እንዲሁም ኢየሱስ የሚሰጠውን አዲስ ሕይወት ስጦታ በመቀበሉ ላይ ነበር፡፡ ይህ ሕይወት ደግሞ ነፃና ዘላለማዊ መሆኑን በመንገር ላይ ነበር፡፡

ተካ በቀላሉ ከቦዲ ሰዎች ጋር ጓደኝነት ፈጠረ፡፡ የሺርም ዘር አለቃ የሆነው ኬንሺማ መኖሪያ ቤት ከእኛ ብዙ አይርቅም፤ ብዙ ጊዜ ወደ እኛ መጥቶ ከተካና

ከናና ጋር ለረጅም ጊዜ ያወራል። ተካ አጎራባች ወደ ሆኑ መንደሮች ስለ ኢየሱስ ታሪክ ለመናገር ሲሄድ፣ ብዙ ጊዜ ከአለቃው ልጅ ከዳኩባ ጋር ብዙ ቀናትን እየተገናኙ ያወጋሉ። ዳኩባ እንደ ሌሎች የቦዲ ወንዶች ሁሉ በጣም ትንሽ ሥራን ይሠራል፤ በባህላቸው ሥራ መሥራት የሴቶች ኃላፊነት ነበር። ነገር ግን ዳኩባ፣ ተካ ሁሉንም ነገር ለመሥራት ያለውን ጥንካሬና ፈቃደኝነት ያደንቅ ነበር። ለኤምኤኤፍ አውሮፕላን ማረፊያ የሚሆን 1000 ሜትር ርዝመት ያለው ስፍራን ለማጽዳት ስንነሣ፣ ዳኩባ የቦዲ ሴቶችንና ረዳቶችን በመሰብሰብ ረድቶናል። ሣሩንና ጫካውን መንጥረው ድንጋዮቹን በማንሣት ረድተውናል፣ እንዲሁም ጉድጓዶቹን በአፈር ሞልተዋል። ዳኩባ ሴቶቹ ሲሠሩ እየተዘዋወረ ይቈጣጠራቸው ነበር።

ከሌላ ስፍራ ከመጣ እንግዳ ሰው ጋር ጓደኝነት መፍጠር፣ ዕርቅን፣ ይቅርታን እና ልጅነት የሚለውን ሐሳብ ለቦዲ ሰዎች ለማብራራት የሚጠቅም ነገር መስሎ ለተካ ታየው። ነገር ግን ሁላችንም ይህንን የተካን ሐሳብ አልተቀበልነውም፤ ምክንያቱም፣ በቦዲዎች አእምሮ ክሕደትና መግደልን በዚህ ውስጥ ስለሚያካትት ነበር። ሌላ ከዚህ የተሻለ ቃል ሊኖር ይገባል፣ ነገር ግን መፈለግ አለብን። በአሞ ወንዝ ሸለቆ ውስጥ እንዳሉት ሌሎች ጎሳዎች ሁሉ ቦዲዎች ጠንካራ ቤተሰባዊ ትስስር አላቸው። አንድ ወንድ በጦር ሜዳ ወይም በበሽታ ከሞተ፣ ቤተሰቦቹ፣ ሚስቱና ልጆቹ የወንድሙ ቤተሰብ አባል ይሆናሉ፤ እርሱም የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ የማሟላት ግዴታ አለበት።

በጭንቅላት ወባና ታይፎይድ ክፉኛ ተይዤ ከጉዩ ለአንድ ሳምንት ርቄ በሄድኩ ጊዜ፣ ተካ በቦዲ ክልል ውስጥ፣ በሰሜን በኩል ለሚገኙት የጉራ ዘር ወንጌልን ለመናገር ሄደ። ለብዙ ወራት ተካ ለጉራ ዘሮች ከባድ ሸክም ነበረውና ብዙ ጊዜ እነርሱ ወደ ክርስቶስ ይመጡ ዘንድ ይጸልይ ነበር። እኔ እና እርሱ አብረን ለመሄድ አስበን ነበር፣ ነገር ግን ተካ እኔ ከመመለሴ በፊት ብቻውን ሄደ። በመመለሻው ጊዜ ሳይመለስ ሲቀር ፍለጋውን ጀመርን። የዚያ ዘር አለቃ ኬንሺማ እና ልጁ ዳኩባ ሄደዋል። (‹‹ከብቶች ለመጠበቅ›› ሄደዋል ተባለ።) ነገር ግን ወንጌላውያኑ ተካን በሚፈልጉበት ወቅት ሌላ ሰው ከእነርሱ ጋር እንዲሆን ተደረገ። ወዲያውም ተካ እንደ ተገደለ ሰሙ!

ወንጌላዊ ጀማሪ የተካን ቦታ ለመተካት እንደገና ተመልሶ መጣ። የተካን አሟሟት ሙሉ መረጃ ብልሃት በተሞላበት መንገድ ፈልፍሎ ያገኘው እርሱ ነበር። ለልጁ ጠመንጃ በመስጠት አድፍጦ እንዲጠበቅ ዕቅድ ያወጣው

ኬንሺማ ነበር፣ ነገር ግን ተካን ተኩሶ የገደለውና አካሉን የበለተው የተካ ልዩ ‹‹ጓደኛ›› የሆነው ዳኩባ ነበር፡፡ ለሳምንት ያል ዳኩባ ከአካባቢው ተሠወረ፡፡ ምንም እንኳ እኛ የተካ ገዳይ እርሱ መሆኑን ብናውቅም፣ እርሱ ግን ከእኛ ነገሩን ሠወረው፡፡ የፈራበትም ምክንያት እኛ የወንድማችንን ገዳይ የምንበቀል መስሎት ነበር፡፡

ከወራት በኋላም የኮምዩኒስቱ መንግሥት ሁሉንም የውጭ ሀገር ሚስዮናውያን ከደቡብ ኢትዮጵያ እንዲወጡ ሲያስገድድ፣ እኔም ጊዩን ለቅቄ መሄድ ግድ ሆነብኝ፡፡ በኤምኤፍ የመጨረሻው አውሮፕላን ከጉዩ ለቅቄ መውጣት አለብኝ፤ ብዙ የጉዩ ሰዎች ሊሰናበቱኝ ተሰበሰቡ፡፡ ምክንያቱም ሁለተኛ ተመልሼ እንደማልመጣ አውቀዋልና፡፡ ምንም እንኳ ነገሩ አስቸጋሪና አደገኛ ቢሆንም፣ በዚያ እንዲቆዩ ወንጌላውያኑን ለብዙ ቀናት አበረታታኋቸው፡፡ ወንጌላውያን ናና፣ ጀማሪ፣ ካሳና ደስታ በዚያ ለመቆየት ፈቃደኞች ሆኑ፣ ነገር ግን እነርሱም ወዲያው እንዲወጡ ተደረገ፡፡

የኤምኤፍ አውሮፕላን ምድር ላይ ሲያርፍ፣ እኔ ከእነዚያ ጐበዝ ወንጌላውያን ጋር የመጨረሻውን ጸሎት እየጸለይኩኝ ነበር፡፡ እየመሸ በመሆኑ፣ ፓይለቱ በጣም ቸኩሏል፣ በሚስዮን ጣቢያው በጣም ሳይመሽ መድረስ አለበት፡፡ የቡዲ ጦረኞች በኮንታ ውስጥ በጣም አሰቃቂ ጭፍጨፋ ያደረጉ ሰዎች ነበሩ፤ እየዞርኩኝ በመጨበጥ ወንጌላውያኑ የሚነግሯቸውን መልእክት ያደምጡ ዘንድ ጠየቅኳቸው፡፡ በመጨረሻም ወደ አለቃው ኬንሺማ ደረስኩኝ፡፡ እጁን ጨበጥኩት፣ ጀርባውንም በእጄ መታ መታ በማድረግ ‹‹በኢየሱስ እመን›› አልኩት፡፡

በድንገት የተካን ገዳይ ዳኩባን ከሕዝቡ መጨረሻ አካባቢ በሌላ ሰው ግማሽ ፊቱን ደብቆ ቆሞ ተመለከትኩት፡፡ በሰዎች መካከል እየተሸለኮለኩ ሄጄ ፊት ለፊት አገኘሁት፡፡ ፈርቶ ለመሄድ ፊቱን አዞረ፣ ነገር ግን እጁን ይገፍ፣ ከሰዎች ራቅ አድርጌ ከአውሮፕላኑ በስተ ጀርባ ወደ ነበረው ቦታ ወሰድኩት፡፡ የአውሮፕላኑ አብራሪውንም ለትንሽ ደቂቃዎች ይጠበቅኝ ዘንድ ጮኽኩበት፡፡ በሁካታ ተሞልቶ የነበረው ሕዝብ በአንድ ጊዜ ጸጥ አለ፡፡ በዳኩባ ትከሻ ላይ እጆቼን ሳደርግ ሕዝቡ በጠቅላላ አፍጥጦ ይመለከተኝና ሲያቃስቱ ይሰማኝ ነበር፡፡ እንደ ቡዲዎች እንዳደርግ ነበር የሚጠብቁት፤ ይኸውም የወንድሜን የተካን ደም መበቀል፡፡ ዳኩባ እጆቼ ትከሻው ላይ እንዳሉ ጐልበት ከዳው፡፡ አንገቱን እንዳቀረቀረና በፍርሃት እየተንቀጠቀጠ ዝም ብሎ ቆሟል፣ መንቀሳቀስ

አልቻለም። ጩቤዬን መዝዤ ደረቱ ላይ እስክሰካ ድረስ ነበር የሚጠብቀው፤ ቦዲዎች በበቀል ጊዜ የሚያደርጉት እንደዚያ ነበር። በዚያ ቦታ የሚሞት መሰለው።

ይልቁንም፣ ለዳኩባ እንዲህ አልኩት፣ ‹‹ወንድሜ ተካን እንደ ገደልከው አውቃለሁ፣ ነገር ግን እኔ አልጠላህም። የወንድሜ ተካንም ደም አልበቀልም። አልገድልህም።›› ዳኩባ አንገቱን ቀና አድርጎ ዐይኑን አፍጥጦ ተመለከተኝ።

በቅጽበትም ወደ አእምሮዬ አንድ ቃል መጣ። እግዚአብሔር መናገር የሚገባኝን ትክክለኛ ቃል ሰጠኝ። ለዳኩባ እንዲህ አልኩት፣ ‹‹እኔ እወድሃለሁ። ወንድሜ አድርጌሃለሁ።›› ዳኩባን በሁለት እጆቼ አቀፍኩትና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙና ጌታው ይቀበል ዘንድ ጠየቅኩት።

የአውሮፕላኑ አብራሪ ለመሄድ በጣም ቸኩሏል። ‹‹አሁን መሄድ አለብኝ፣›› በማለት ተናገረ! የአውሮፕላኑን ሞተር ማሞቅ ጀመረ። ናና፣ ጄማሪ እና ካሳን ጠራኋቸውና ዳኩባን አስረከብኳቸው። ከሚጮኸው የአውሮፕላን ድምፅ በላይ ድምፄን ከፍ አድርጌ እንዲህ ስል ተናገርኩኝ፣ ‹‹ዳኩባ አሁን ወንድሜ ነው። የክርስቶስን ወንጌል አስተምሩት፣ እንዲያምንም እርዱት›› አልኳቸው። የተቀመጥኩበት ወንበር ቀበቶ ሳይታሰር የአውሮፕላን ማኩብኩቢያውን ሜዳ ግማሽ ያህል ተጓዝን።

አውሮፕላኑ በአሞ ወንዝ አጠገብ በመብረር ወደ ሰሜን አቅንቶ ወደ ተራሮቹ በመውጣት ላይ ሳለ፣ ወንጌላውያኑ ከዳኩባ እና ከአባቱ ኬንሺማ ጋር አብረው ቆመው ይመለከቱኝ ነበር። በማንኛውም የፍርድ ቤት ሕግ ሁለቱም የወንጌላዊ ተካ ገዳዮች በተፈረደባቸው ነበር። ነገር ግን ዳኩባን ወንድሜ አደረግኩት፣ እዚህ ላይም ልንደርስበት የቻልነው ‹‹ከይቅርታ›› ጋር ተቀራራቢ በሆነ ቃል ነበር።

‹‹እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላቸንን ይቅር በለን፤››

ማቴዎስ 6፡12

‹‹እናንተ ግን ይቅር ባትሉ በሰማያት ያለው አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።››

ማርቆስ ፲፡26

ቅጣይ

በጥቂት ወራት ውስጥ ሁሉም ወንጌላውያን ከቦዲ አካባቢ ተጠራርገው እንዲወጡ ተደረገ፡፡ እነርሱ ጊዩን ለቅቀው ከመውጣታቸው በፊት፣ ዳኩባና ኬንሺማ ኃጢአታቸውን እንደ ተናዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመኑ ደብዳቤ ጽፈው ነገሩኝ፡፡

በቀጣዩ አሥራ አምስት ዓመታት ከቦዲ ሰዎች ጋር በጣም ትንሽ ግንኙነት ነበረ-በጣም ጥቂት ሴቶች አልፎ አልፎ ዲማ ወደሚገኘው ገበያ ይመጣሉ፡፡ በእነዚያ ዓመታትም ሦስት በጣም ከባድ ወረርሽኞች በአሞ ወንዝ ሸለቆ ውስጥ ተከስተው ነበር- በመጀመሪያ ቢጫ ወባ፣ ከዚያ ኮሌራ እና በመጨረሻ ማጅራት ገትር፡፡ እነዚህ ሦስቱ ወረርሽኞች እያንዳንዳቸው በመቶ፣ እንዲያውም በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ገድለዋል፡፡

ጊዩን እንደገና የመጐብኘት ዕድል ሳገኝ፣ ወንጌላውያን ጀማሪና ካሳ ወደዚያ ተመልሰው በማገልገል ላይ ይገኙ ነበር፡፡ የጎሳ መሪ የነበረው ኬንሺማ ከነቤተሰቡ መሞታቸውን ነገሩኝ፡፡ ከዚያ ቤተሰብ ውስጥ አንድም ሰው ከወረርሽኙ አለመትረፉን- ዘሩ በጠቅላላ መጥፋቱን ሰማሁ፡፡

ተካ ለጉራ ጎጎ ከልቡ ይጸልይ የነበረው ጸሎት አሁንም እየተመለሰ ይገኛል፡፡ ከዚህኛው የቦዲ ጎሳ ውስጥ ያሉ ብዙ ሰዎች ከሌሎች የቦዲ ጎሳዎች ይልቅ በክርስቶስ እያመኑ ይገኛሉ፡፡ እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር ስለሚል ምስጋና ይገባዋል!

፴፱

የክርስቶስ መልእክተኞች

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሎ ጽፏል፣ ‹‹እኛ የክርስቶስ አምባሳደሮች ነን›› (1ኛ ቆሮንቶስ 5፡20)፡፡ አምባሳደር የሚለው ቃል በሦስት የኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ የአማርኛ ትርጉሞች ውስጥ ሦስት የተለያዩ ቃላትን በመጠቀም ተተርጉሟል፡፡ አምባሳደር የሚለው ቃል *‹‹ባለ ሙሉ ሥልጣን፣ እንደ ራሴ፣ እና መልእክተኛ››* ተብሎአል፡፡

ባለ ሙሉ ሥልጣን ማለት ‹‹ከአለቃው ወይም ከባለቤቱ ሙሉ ሥልጣን›› የተሰጠው ማለት ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይና በምድር ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ እኛም ወደ ዓለም ሁሉ ሄደን ሰዎችን ለእርሱ ደቀ መዛሙርት የማድረግ ሥልጣን አለን፡፡ የተሰቀለውን፣ የተነሣውን እና በአብ ቀኝ ሆኖ የሚገዛውን የምንሰብከው በእርሱ ሙሉ ሥልጣን ነው፡፡

እንደራሴ ‹‹እንደ እኔ›› ማለት ነው፡፡ የክርስቶስ ሕዝቦች የእርሱ የግል ተወካዮቹ ናቸው፡፡ በምናደርጋቸው ማናቸውም ነገሮችና ምላሽ በምንሰጥባቸው ነገሮች ሁሉ፣ በምንናገረው ነገርና ከሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት እንደ እርሱ መሆን አለብን፡፡ ሕይወታችን በፍቅር፣ በጸጋ፣ በርኅራኄና ለአብ ፈቃድ በመታዘዝ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት ማንጸባረቅ አለበት፡፡

መልእክተኛ ‹‹የተላከ›› ማለት ነው፡፡ የክርስቶስን ፍቅርና የኃጢአት ይቅርታን፣ የመዋጀት፣ የእርቅና የዘላለማዊ ሕይወት መልእክትን እንዲያደርስ ተመርጦ የተላከ ማለት ነው፡፡ ከዚህ የሚበልጥ፣ በጣም ሊነገር የሚገባውና ጠቃሚ መልእክት የለም፡፡ ጌታ ኢየሱስ፣ እርሱ መሄድ ወደሚፈልገበት ቦታ ልኮናል- ሩቅም ይሁን ቅርብ ማለት ነው፡፡

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ሰዎች ታሪኮች የክርስቶስ ልዩ መልእክተኞች ተብለው ይጠራሉ - እነዚህ ሰዎች እንደ ማሄ፣ ተካ፣ ኤርምያስ፣ አቤል፣ ኢካሶ፣

ብርሃኑ፣ ዳንኤል እና ሌሎችም በጣም ብዙ ሰዎች ከሚስቶቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመሆን ወንጌልን በጨለማ ላሉ ነሳዎች ይዘው ሄደዋል። ይዘውት የሚሄዱት መልእክት በጣም ውድና ጠቃሚ በመሆኑ፣ ምንም መከራና ተቃውሞ ቢደርስባቸውም፣ መልእክቱን ለማድረስ ሁልጊዜ ይሄዳሉ። ይህንን የሚያደርጉት አንዳንድ ጊዜ ሕይወታቸውን እስከ ማሳጣት ድረስ መሥዋዕትነት የሚያስከፍላቸው ቢሆንም ማለት ነው። አሁንም ቢሆን ተራሮችን ወጥተው፣ ሸለቆዎችን ወርደው እና ሜዳዎችን አቋርጠው የእግዚአብሔርን የፍቅርና የጸጋ መልእክትን ለማድረስ በመሮጥ ላይ ስላሉት መልእክተኞች በምናደርገው ጸሎት ተሳተፉ።

እንደ አንድ ትንሽ የክርስቶስ መልእክተኛ ከጳውሎስ ጋር ሆኜ፣ ‹‹ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ›› ብዬ እለምናችኋለሁ፣ እማጸናችኋለሁ።››

> *‹‹በዚያን ዘመን ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር፣ ከረጅምና*
> *ከለሰለሳ ሕዝብ፣ ከመጀመሪያው አስደንጋጭ ከሆነ ወገን፣*
> *ከሚሰፍርና ከሚረግጥ፣ ወንዞችም ምድራቸውን*
> *ከሚከፍሉት ሕዝብ ዘንድ እጅ መንሻ የሠራዊት ጌታ*
> *የእግዚአብሔር ሰም ወደሚገኝበት ስፍራ ወደ ጽዮን ተራራ*
> *ይቀርባል።››*
>
> ኢሳይያስ 18፡7

የክርስቶስ መልእክተኞች ወንጌልን ይዘው በመሄድ በአሞ ወንዞዝ ዙሪያ የሚኖሩ የተዋጁ ሕዝቦች የአምልኮ፣ የምስጋና እና የመታዘዝ መሥዋዕትን ማምጣት እንዲችሉ በማድረጋቸው እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።

ከዚህ ቀደም በዲክ ማከሌላን የተዘጋጀ መጽሐፍ፡-

ኢትዮጵያውያን የወንጌል አርበኞች፡-

በአሞ ወንዝ ሸለቆ ውስጥ የሚያገለግሉ የወንጌል ጀግኖች